# ማርያሽ

ከሲሳይ ንጉሱ

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ግርዶሽ

ከሲሳይ ንጉሡ

1981 ዓ.ም

# ማስታወሻነቷ

ለእናቴ ለወይዘሮ ቀፀላ ተክሉ

NIGUSS DIGITAL LIBRARY

ሰዓቷን ደጋግማ ተመለከተች። ከምሽቱ ስድስት ሰዓት ከሩብ ሆኗል። ከውጭ የሚንቀሳቀስ የመኪና ድምፅ ጠፍቷል። ቤቱም ፀጥ - ረጭ ብሏል። ሁለቱ ልጆቿ ዳንኤልና ሰብለ ከተኙ ቆይተዋል። ሠራተኛዋ እልፍነሽ እንቅልፍ ሲያንጎላጀጃት ቆይታ ስድስት ሰዓት ላይ ተስፋ ቆርጣ ተኛች። ፅጌረዳ ብቻ እንዳፈጠጠች ተቀምጣለች። ስድስት ሰዓት ከሩብ! ወንዳፍራሽ አልመጣም።

ዛሬስ ጭራሹን ሊያድር ነው እንዴ? ስትል ለራስዋ ተነፈሰች። - አይደረግም! አለች እንደገና ራስዋን ማመን አቅቷት። ነገር ግን ሆኗል፤ ተደርጓል።

የንዴት ሳቅ ስቃ ከመቀመጫዋ ተነሳችና ወደ በሩ ሄደች። ልቧ ተስፋ አልቆርጥም ስላላት በሩን ከፍታ ጆሮዋን ወደ ውጭ ጣለች። የሰውም የመኪናም ድምፅ የለም።

እህህህ! ጭራሹን አዳር? ይቺ ናት ጨዋታ!

በሩን ቆላልፋ ወደ መኝታ ክፍሏ ሄደች። ነገር ግን መተኛት አልቻለችም። ቅናት ከወዲያ ወዲህ ያወራጫት ጀመር። ወንዳፍራሽ ከሌላ ሴት ጋር ማምሸትና መቅበጥ ከጀመረ ቆይቷል። ሲያድር ግን የመጀመሪያ ጊዜው ነው። የትዕግሥቷ ውጤት እንዲህ መሆኑ ፅጌረዳን አብከነከናት።

ዘጠኝ ዓመት ሙሉ ቤቷን ለማሳመር ትዳሯን ለማጣፈጥ ያደረገችው ጥረት ሁሉ ከንቱ ሆኖ ታያት። አልጋዋ ላይ ቁጭ እንዳለች ብዙ ተከዘች። ነገሩን ከጅምሩ አሁን እስካለበት ደረጃ አውጠነጠነች።

ከተጋቡ ጀምሮ ለስምንት ዓመታት ያህል በሰላም የኖሩት። ፅጌረዳ ለባሏ ብቻ ሳይሆን ለመንደረተኛውና ለመስሪያ ቤት ባልደረቦቿ ጭምር ትሁት፣ አስተዋይ፣ ገርና አሳቢ ነች። እንዲያውም የመስሪያ ቤቷ ሰዎች «ቅድስት ፅጌረዳ» እያሉ የሚጠሯት። ለትዳራቸው መሻሻልም ሆነ በዕቅድ ለመኖር ፅጌረዳ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለበት አሁንም ቢሆን ወንዳፍራሽ አይክድም። እሱም ራሱ ለትዳሩ ታታሪ ነበር። የዛሬ ዘጠኝ ወር ገደማ ነው አዲስ ፀባይ ማሳየት የጀመረው። እያመሸ ሲገባ እየጠጣ ሲገባም ቤቱን ችላ ማለት ሲጀምር ፅጌረዳ ነገሩ ስለ ከነከናት

«ምነው ወንዴ - ለምን በጊዜ አትገባም? መጠጡ ደግሞ የምን አዲስ ፀባይ ነው?» እያለች ማባበል ጀመረች።

ወንዳፍራሽም ወደ ውች ፍቅር ቢከጃጅለውም የሚስቱን ፍቅር ውለታ በቀላሉ ሊረግጠው አልቻለም። ለተወሰነ ጊዜ የአክብሮት መልስ ነበር የሚሰጣት። አንዳንዴ ሞቅ ሲለው ግን የውስጥ ምሬቱን ይተነፍሳል።

«ምነው ፅግሽ ...... ወንድ ልጅ እኮ ነኝ። ገና በአስራሁለት ሰዓት ቤት ውስጥ ሰፍሬ ምን አደርጋለሁ?.... አንቺስ ቢጊሆን ከጊዜ ብዛት አፉ ወተት ወተት የሚሸት ባል ሳያስጠላሽ ይቀራል....... ባይሆን አንዳንዴ ጂን፣ ጂን፣ ይሸተትሽ እንጂ......»

ይህን የመሰለውን አነጋገር ከአንዳንድ ድርጊቶቹ ጋር ተደምሮ ፅጌረዳን ጭንቀት ውስጥ ይከታት። እንዲያም ቢሆን ግን ጭንቀቷ በአልኮል ራሱን ከመጉዳቱና ብር ከማባከኑ፣ እንዲሁም ትዳሩን ቸል ከማለቱ ላይ እንጂ ሌላ ሴት ወድዷል የሚል ጥርጣሬ አልነበራትም። የዋህ ልቧ ከወንድአፍራሽ ጋር ጥንት የጀመሩትን ፍቅር የዕድሜ ልክ ቆይታ ሰጥቶት ነበር።

ጀሮ ለባለቤቱ ባዕድ የሚሆነው ለተወሰነ ጊዜ ነው። ወንዳፍራሽ ሌላ ሴት መውደዱን ፅጌረዳ ከተለያዩ ምንጮች ሰማች በየዋህነቷ የሚያዝኑላትም፣ በትዳሯ የሚቀኑባትም፣ ሁሉም በየበኩላቸው ወሬውን ቱስ አሏት። ቅናት ከውስጧ እያንሠራራ መንፈሷን መረበሽ ቢጀምርም እንደምንም ዋጥ አድርጋ ወንዳፍራሽን ወደ እሷ ፍቅር ለመመለስ ሞከረች። ውስጥ ውስጡን እየተቃጠለች ላይ ላዩን የትዳሩ ምሰሶ እንዳይላላ አቅሟ በፈቀደው መጠን ሁሉ ጣረች። ወንዳፍራሽ ግን ወደ ውጭ ያወጣውን ልብ በቀላሉ ወደ ቤት ሊመልሰው አልቻለም። በቀላሉ ማምለጥ የማይችለው ፍቅር ላይ ነበር የወደቀው። እና የምንጊዜም ልቡ ወደ ውጭ ሆነ። ጎረ ቤቶቹ ለፅጌረዳ እያዘኑ ስትገባና ስትወጣ ከንፈራቸውን ሲመጥጡላት ትሰማ ጀመር። የመንደሩ ወሬ ትዕግሥቷን አሳልቆ ቅናቷን እያጎላው መጣ። «ይህችን የመሰለች ሴት መልክና ፀባይ አሟልቶ ሰጥቷታል.....ጥላው አትሄድም እንዴ! ምን እስኪያደርጋት ነው የምትጠብቀው?..... ልጆቹም እንደሆነ በእድላቸው ያድጋሉ.....» የማይል ጎረቤት አልነበረም።

ቅናቷ ከፍ እያለ መጣ ጣውንቷን ሴት የማወቅ ጉጉት አደረባት። አንድ ሰሞን በተከታታይ ሌሊት እየተነሳች የወንዳፍራሽን ቅዠት ማዳመጥ ጀመረች። በውድቅት ጨለማ አልጋውን እየዞረች፣ ከራስጌው እየተንበረከከች፣ ጆሮዋን ወደ ወንዳፍራሽ አፍ እያስጠጋች ቅዠቱን ለመስማት ሞከረች። አብዛኛውን ጊዜ የሚያደርገው ልፍለፋ ተራ መንተባተብ በመሆኑ ትርጉም ያላቸው ቃላት ልታገኝ አልቻለችም። የኋላ ሁላ የጣውንቷን ስምና ቄመና አንድ የመስሪያ ቤት ጓደኛዋ ስራዬ ብላ ተከታትላው አጥንታ ነገረቻት። ሮዛ የምትባል ብስል ቀይ ረዥም ኮረዳ መሆኗን አወቀች። ሮዛን በዓይኗ አይታት ባታውቅም ከጓደኛዋ ባገኘችው መረጃ መሠረት ምስሏ ከአዕምሮዋ ውስጥ ተቀረፀ። ብስል ቀይ ረዥም ሴት ባየች ቁጥር ከውስጥም ደሟ እየፈላ የጥላቻ ዓይን ማሳየት ጀመረች።

ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ወንዳፍራሽ የውጭ ጉዳዩን ቀን ወይም አመሻሽ ላይ ይፈፅማል እንጂ ከቤቱ ውጭ አድሮ አያውቅም። ውጭ ማደር ለሚስቶች ከፍተኛ በትር መሆኑን ህሊናው አላጣውም ነበር። ዛሬ ግን.....

እና ዛሬ ውጭ ማደሩ ነው ማለት ነው? አለች ፅጌረዳ ከሀሳብ ጉዞዋ ስትመለስ በረዥሙ ተንፍሳ፣ እኔው ነኝ ያበቃሁት፤ ትዕግሥቴ ነው ይህንን ያሳየኝ፤.....ገና ውጭ ማምሸት የጀመረ ዕለት ፊት ባላሳየው ኖሮ እንዲህ አይንቀኝም ነበር......

የቅናት እንባ ደርሶ ልውረድ ልውረድ እያለ ዓይኖቿን ቆጠቆጠው። ጥርሷን ነክሳ ወአጥ አደረገችው። ስድስት ሰዓት ተኩል ሆኗል። በዚህ ሰዓት ወንዳፍራሽ ከሮዛ ጋር ምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ገመተች። ጣውንቷን አቅፎ ተኝቶ ሲያለከልክ በሀሳብዋ ታያት። ብስል ቀይ፣ ረዥም ሴት ወንዳፍራሽ ደረት ላይ ፊቷን ደፍታ ፍቅር ስትቀበል..... ወንዳፍራሽ ከዘጠኝ ዓመት በፊት በአዲስ ፍቅር ስሜት ለፅጌረዳ ይተነፍስ የነበረውን የፍቅር ቃላት ለሮዛ ሲያዘንብላት፣ በውን በጆሮዋ የምትሰማው መሰላ። ሰውነቷ ተንቀጠቀጠ። ....ለመሆኑ በዚህ ሰዓት እኔ ትዝ እለው ይሆንን ወይስ ጭራሹን ረስቶኛል? ስትል ራሷን ጠየቀችው።

ቅናት ለውጊያው ቀንዱን አሹሎ፣ ጥፍሩን ስሎ፣ ዓይኖቹን አፍጥጦ ከተፍ አለ። የሚፋለመው ጠላት አጠገቡ ባይኖርም በባዶ ቤት ለመወራጨት ፅጌረዳን ጎትቶ አስነሳት። ለፍልሚያ እንደሚዘጋጅ ሰው የሹራቧን ክናድ ሰብስባ በቀጥታ ሳሎኑ

ኮመዲኖ ላይወደ ተቀመጠው ፎቶ ግራፍ ሄደች። ወንዳፍራሽ አሳድጎ ያሳጠበውን ምስል ነበር። ከበፊቱ ላይ አንስታ ጥርሷን ነክሳ አፈጠጠችበት። ፈገግ ብሎ የተነሳው ፎቶ ግራፍ በንዴት የሚያፌዝ የሚስቅ፣ ይመስል ነበር። ከስዕል ጋር ሳይሆን ከሰው ጋር እንደምትተናነቅ ዓይነት ፎቶውን ጥብቅ አድርጋ ይዛ ተፋችበት።

ቤቴ፣ ትዳሬ፣ ልጆቼ ብሎ መድከም እንዲህ ያስንቃል? የዋህነት እንዲህ ያዋርዳል?.....እኔ የምባልግበት መልክ አጥቼ ነው? ውበት አጥቼ ነው?.......እኮ የንቀትህ ምንጭ ምንድን ነው? በርጥም ናቅከኝ፣ አዋረድከኝ? ባዶ ቤት ጥለኸኝ አደርክ - ይኸው ነው የድካሜና የፍቅሬ ምላሽ??.....

አስተያየቷ ከፎቶግራፉ መልስ የምትጠብቅ ዓይነት አስመሰላት። የወንዳፍራሽ ምስል ግን ያው ፈገግ እንዳለ ነበር።

ባለ በሌለ ኃይሏ ፎቶ ግራፉን ቁልቁል ወረወረችው። እንጨቱና ምስሉ ተአመሙ ሲቀሩ መስታወቱ ግን ክሽክሽ ብሎ ተሰባበእር። በተጣመመ ፍሬምና በተጨማደደ ወረቀት ላይ አሁንም ፈገግ ያለ ምስል ይታያል።

የፎቶ ግራፍ መስታወት ሲሰበር የተፈጠረው ድምፅ የመጀመሪያ ልጃቸውን፣ ዳንኤልን፣ ከሞቀ እንቅልፉ አባነነው። አባቱ ሞቅ ብሎ ወይም ሰክሮ አምሽቶ ሲገባ በእጁ አንድ ነገር እንደሚይዝ ያውቃል። ብስኩት ወይም ፍራፍሬ ወይም ተመሣሳይ ነገር እየያዘ መግባት አስለምዷል። ዳንኤልና ሰብለም ይቺን ለምደው አንዳንዴ እንቅልፍ እያንጎላጀጃቸው ሶፋው ላይ ተቀምጠው ይጠብቁታል። አሁንም ዳንኤል ከእንቅልፉ እንደነቃ የሰማው ድምጽ የበር መከፈት መስሎት የአባቱን እጅ ለማየት ከመኝታው ወርዶ ወደ ሳሎን ሄደ።

አባቱ የለም። ፎቶ ግራፉ መሬት ላይ ተከስክሶ፣ እናቱ እንዳፈጠጠች ቆማለች። ዳንኤል ደነገጠ።

«ምነው ፅግዬ?..... ድመቷ ፎቶግራፉን ሰበረችው እንዴ?» አላት የሱም ፊት ቅጭም ብሎ።

አባታቸው «ፅግዬ» ሲል እየሰሙ ስላደጉ ሁለቱም ልጆቿ «እማማ» በማለት ፋንታ «ፅግዬ» ነው የሚሏት። አባታቸውንም እናታቸው በምትጠራው ዓይነት

«ወንዴ» ይሉታል። ልጆቻቸውን ጓደኞቻቸው አድርገው የማሳደግ ዝንባሌ ስለ ነበራቸው ወላጆቻቸውም ለቁልምጫ አጠራሩ አበረታተዋቸዋል።

«ዳኒ!.....» አለችና ፅጌረዳ መናገር የፈለገችውን ሳትጀምር እንባ በሁለት ዓይኖቿ ግጥም አለ።

«ምን ሆንሽ?....ወንዴ እስካሁን አልመጣም እንዴ?» ሲል በማባበል ዓይነት ጠየቃት።

«አባትህማ ዛሬ ከሮዛ ጋር አድሮአል። በዚህ ሰዓት ሮዛን አቅፎ ተኝቷል!.....» አለችው እንባዋን መጥጣ ጥርሷን እያንቀጫቀጨች።

»ሮዛ ማን ናት?»

»አዲሱ ሚስቱ ናታ.... ለእናንተ አዲስ ናት ሊያመጣላችሁ ነው»

«ለምን?.... አንቺ ምን አደረግሺው?»

«የዚህን መልስ የሚያውቀው አባትህ ብቻ ነው፣ ዳኒ ለኔም ያልተመለሰልኝ ጥያቄ ነው... ተናቅኩ፣ ተዋረድኩ....የንቀቱ ምንጭ አልገባኝም።»

የእናቱን ፊት አይቶ የዳኒን ልብ እንባ ቋጠረ። የሚሠራውንና የሚናገረውን ሲያስተውሉት የስምንት ዓመት ልጅ አይመስልም። ዘመኑም ሊሆን ይችላል፤ የአስተዳደግ ሁኔታውም ሊሆን ይችላል፤ የአካባቢው በአስተሳሰብ መምጠቅ ውጤትም ሊሆን ይችላል - ዳኔ ከእድሜው በላይ ነው የሚያስበው።

«እኔና ሰብለ እሺ አንለውም። እናታችን አንቺ እንሽ።» አላት ጉሮሮውን ሳግ እየተናነቀው።

የዳኒ ዓይኖች ቀልተው ስትመለከት እናትየዋ ወደ እስዋነትዋ ተመለሰች። ተጫጭኖአት የቆየውን የቅናት አውሬ ሸሽቶ የእናትነት ፍቅር ተተካ። እንዲህ ዓይነቱን መራራ ነገር ለልጅዋ ማሳወቋ ፀፀታት።

«በቃ ዝም በል ዳኒ...... ቀ - ል - ዴ - ን እኮ ነው።.....» አለችው ድምጿ እየተርበተበተ።

ቀልዴን ያለመሆኑን ግን ዳኒ አላጣውም። ዘጠኝ ወር ታግላ ያቆየችው ትዕግሥት ፈንድቷል፣ ፈጣኑ የዳኒ ጭንቅላትም ነገሩን ቀርጿል። የፈሰሰ ውሃ አይታፈስም፤ የምላስ ወለምታ በቅቤ አይታሽም፤ ከምላስ ያመለጠ ቃል መልሶ አይዋጥም፤ ጭንቅላት ውጥ የተቀረፀም ነገር በቀላሉ አይፋቅም።....

ዳኒ ፊቱን ክስም አድርጎ ወደ መኝታ ቤቱ ሲመለስ «ሮዛ» የሚለው ስም በአፍራሽ ስሜት አእምሮው ውስጥ እያቃጨለበት ነበር - ሮዛ! - ሮዛ!..... በዚህ ስም የምትጠራ ሴት ዓይቶ አያውቅም። በልጅነት አእምሮው ነገሩን እያላመጠ መኝታው ውስጥ ገባ። ሰብለ ድብን ያለ ዕንቅልፍ ላይ ነበረች።

«ወንዳፍራሽ.....ወንዴ!.... ተነስ! ሰዓት ረፍዷል።....»

ወንዳፍራሽ እንኳንስ ጠጥቶ አድሮ ወትሮውንም የጠዋት እንቅልፍ ነገር አይሆንለትም። አሁንም ሮዛ ስትቀሰቅሰው በቀላሉ ሊሰማት አልቻለም። ቢቸግራት ብርድ ልብሱን ከላዩ ላይ ገፈፈችው።

እንደምንም ነቅቶ የእጅ ሰዓቱን ተመለከተ። ለሁለት ሰዓት አስር ጉዳይ ሆኖአል።

«ኡህ!....ሰዓቱ ሄዶአልና አባክሽ!» አለና ዓይኖቹን በጣቶቹ አሻሸ።

«እንቅልፋም!.....» አለችው ሮዛ አልጋው ጠርዝ ላይ ተቀምጣ፤ የውስጥ ሱሪዋን እያጠለቀች።

የግዱን ከመኝታው ውስጥ ወጥጦ ልብሱን ይለብስ ጀመር። ማታ የጠጣው አልኮል ሰውነቱን አድክሞታል። እጆቹ ሱሪውን ሽቅብ መሳብ አቅቷቸው ሲታገሉ አይታ ሮዛ ሳቀች። ጫማ ለማሰር ጎንበስ ማለቱ ደግሞ ከአቅም በላይ ሆነ። - መላ ሰውነቱ ድቅቅ ብሎአል።

«እንዲያ ተዝለፈለፍክ እኮ - ደካማ»

«...አንቺው ነሻ ያደከምሺኝ»

«እንኳን!....» አለችና ሮዛ እንደ ሕጻን ልጅ ከንፈሯን ጣል አደረገች።

«ግድየለሽም፤ ቀዝቃዛ ሻወር ልውሰድ መሰለኝ።»

«ይረፍድብሐላ.... እዚሁ ሁለት ሰዓት ሊሞላ እኮ ነው።»

«ቢረፍድም...... ቀኑን ሙሉ ተደብሬ ከምውል ይሻለኛል» አለና ያጠለቀውን ሱሪና ሸሚዝ አውልቆ ወደ መታጠቢያው ክፍል ገባ።

ሮዛ ለባብሳ ጨርሳ ከቦርሳዋ ውስጥ ትንሽ መስታወትና ጌጣጌጦቿን አወጣች። ባትኳኳልም ቆንጆ ናት። ብስል ቀይ ፊቷ በጣት ቢነኩት ትርሙክ ብሎ የሚጎደጉድ ፖም ይመስላል። ከጥቁር ይልቅ ወደ ሰማያዊ የሚወስደው የዓይኖቿን ቀለም ቀርበው ሲመለከቱትክልስ መሆኗ ያስታውቃል። ወንድ አያቷ የግሪክ ክልስ ነበሩ። ደማቸው አንድ ቤት አልፎ እሷም ላይ ይንፀባረቃል። ረዘም ያለው ሰልካካ አፍንጫዋን ወንዶች በጉጉት፣ ሴቶች ደግሞ በቅናት ዓይን ይመለከቱታል። የውበት መገለጫዋ አፍንጫዋ ይመስላል። የጥርስ ነገር ባዶ ነው። ትንሽም የፊት ጥርሶቿ ይሻላሉ እንጂ መንጋጋዋ በጣፋጭ ምግብ ተበላሽቶ አልቆአል። ጣፋጭ ነገሮች አሁንም ትወዳለች። ልብሶቿና ጫማዎቿ ሁሉ ለረዥም ቁመናዋ የሚስማሙ ዓይነት ናቸው። ለስላሳ ፀጉር ቢኖራትም ማስረዘም አትወድም። ፊቷን አጉልቶ የሚያሳይ ዓይነት የራሷ የሆነ አበጣጠር አላት።

«እፎይ.....አቀዘቀዘኝ እኮ.....» እያለ ወንዳፍራሽ በፎጣ ሰውነቱን እያደራረቀ ከመታጠቢያው ክፍል ወጣ።

«በዚህ ላይ ደግሞ የቲማቲም ጭማቂ ብታገኝ ፈፅሞ ትታደስ ነበር።.....» አለችው ሮዛም የወንዳፍራሽን ደንደን ያለ ሰውነት ከታች እስከ ላይ እየቃኘች።

ኮስማና ወንድ አትወድም። ጡንቻው ፈርጠምጠም ያለ፤ ጨምደድ አድርጎ የሚይዝ ደንደ ያለ ሰውነት ያለው ወንድ ስታይ ግን ልቧ ይጠፋል። ከዚህ በተጨማሪ ደረቱ ላይ ትንሽ ፀጉር ያለው ወንድ ከሆነ አለቀላት። ብሥል ቀይ ፊቷን ከወንድ የደረት ፀጉር ላይ ማለት ደስ ይላታል። ወንዳፍራሽ በስፖርት ያዳበረው ጡንቻ ባይኖርውም ሰውነቱ በተፈጥሮ ደንደን ያለ ነው። በሀገራችን የውበት ማነጻጸሪያ ዓይን ሲታይ ቆንጆ ለመባል የሚበቃ ዓይነት አይደለም - መልኩ። ነገር ግን የደስ ደስ አለው።

«ደግሞ ሌሊት ትቃዥ ነበር እኮ!.... ይታወቅሃል?» ስትል አፋጠጠችው።

«ኧረ እንዲያውም!.....»

«ሚስትህ ናፍቃህ ነው መሰለኝ እንዲሁ ስትቃዥ ነው ያደርከው።»

ወንዳፍራሽም ዝብ ብሎ ልብሱን መለባበሱን ቀጠለ። አዝማሚያዋ የጦርነት ክብሪት ለመጫር ስለመሰለው መልስ አልሰጣትም።

«....እንግዲህ ምን ይውጣት ይሆን? ይኸው ውጭ አደርክላት.... ራሷን አትሰቅል!» አለችው እንደገና ለመልስ በመጓጓት ትክ ብላ እያየችው።

ወንዳፍራሽን ውጭ በማሳደሯ ልቧ በኩራት ተሰምቶታል። አንድ ድል አድርጋ ወስዳዋለች። ቀን ወይም አመሻሽ ላይ ይወጣሉ እንጂ አብረው ውጭ አድረው አያውቁም። ትላንት ማታ ግን መጠጡም፣ ፍቅሩም አሸነፋት። ውጭ በማደሩ የወንዳፍራሽ ሚስት ምንኛ እንደምትቃጠል ስለምታውቅ ነው ሮዛ አንጀቷ ቅቤ የጠጣው።

«ለባብሺ ጨርሼአለሁ፣ መሄድ እንችላለን» አለ ወንዳፍራሽ ሌላውን ነገር ሁሉ ሆነ ብሎ ቸል በማለት።

ተያይዘው ወጥተው መኪናውን ቀዳቆመበት ጥግ አመሩ። የሮዛ ዓይኖች የጥያቄ ምልክት ሰርተው እንዳተኮሩበት ምንም ሳይመልስላት መኪናው ውስጥ ገብተው ተንቀሳቀሱ።

«ይሄኔ ቢሮህ ደውላ ይሆናል።.....» አለችው ትንሽ መንገድ እንደ ተጓዙ።

«ማን?» አላት ወንዳፍራሽም ተዘናግቶ።

«ሚስትህ ናታ»

«አዎ.... ይሆናል.....»

ይህን ርዕስ ማሳጠር ወይም መዝጋት ፈለገ። ርዞአ ግን አልለቀቀችውም። ማወቅ የምትፈልገው ነገር አለ። ሚስትና ሁለት ልጆች እንዳሉት ቀድሞውንም አልደበቃትም። በተዋወቁ ሁለት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ነግሮአታል። ትዳሩንም

እንደ ትዳሩ ዳሩ እሷንም እንደሷነቷ ሊያስተናግድ ተስማምተው ቆዩ። ሮዛም እሱን እንዳገኘችው ለፍቅሩ እንጂ ለትዳሩ ስላልከጀለችው ሙሉ ሰው መሆኑ አላሸሻትም ነበር። ሁለቱም በቀላሉ ሊያቋርጡት እንደሚችሉ ዓይነት ግንኙነት አድርገው ሲያስቡ ቆዩ። ፍቅር ግን በውስጣቸው መሠረቱን እየጣለ ነበር።...በፊት እንደምታስበው መውደዷ ብቻ ሊበቃት አልቻለም። ወንዳፍራሽ ከእሷና ከሚስቱ ማንን አብልጦ እንደሚወድ የማወቅ ጉጉት አደረባት። ያፈቀሩትን ወንድ የግል አድርጎ የመያዝ አዝማሚያ በውስጧ አንሰራራ። የፍቅር ደረጃዋ ጡንቻ አውጥቶ ራሱን ማስከበር ፈለገ ማለት ነው። አሁንም የነገር ፍለጋዋ አዝማሚያ ይኸው መሆኑን ወንዳፍራሽ አላጣውም። ነገር ግን ራሱም ተምታቶበታል።

«ምን ይዘጋኃል?» አለችው ድንገት።

አቀማመጧን የመኪናውን በር በግማሽ ጀርባዋ ተደግፋ እሱን ፊት ለፊት ለማየት እንዲመቻት ዓይነት ነበር። ሀሳቡን ሁሉ ከፊቱ ላይ ለማንበብ የተዘጋጀች ትመስላለች።

ወንዳፍራሽም ድንገት ብልጭ አለበት።

«ምን እንድልሽ ነው የምትፈልጊው ሮዛ?» አላት፤ የመኪናውን መሪ ተከትለው ፊት ለፊት ያተኮሩ ዓይኖቹን ሳይነቅል።

« - እ.....እንዴት ......ምን» የምትለው ነገር ድንግር ግር አላት።

«እወድሻለሁ። እንደምወድሽ ደጋግሜ ነግሬሻለሁ። ስለምወድሽ ነው ሚስቴን ቤት ውስጥ አስቀምጬ ከአንቺ ጋር የምባልገው.......»

«አሃ! ከኔ ጋር የምትባልገው?! አባላጊህ ነኝ እ?.....ነኝ!......ነኝ!.....»

«ቆይ እንጂ ሮዛ፤ አስጨርሺኝ እንጂ! ለማለት የፈለግሁትን አዳምጪኝ! መባለግ ማለቴ.....»

«በል ብቻ ቀጥል!... ማለት የፈለግከውን ብለሐል።»

«ስሚኝ ሮዛ፤....አንቺ በኔ ቦታ ብትሆኝም ምን ታደርጊ ነበር?!»

መልስ አልሰጠችውም። ለአፍታ ያህል አይኑን ከመስታወቱ ላይ ነቅሎ በጎን ተመለከታት። ትክ ብላ እያየችው ነበር። ትክ ብለው የሚያዩት አይኖቿ በዳመና ሊሸፈኑ ተቃርበዋል።...... ውኃ አርግዘዋል። እና ደግሞ ቀይ ፊቷ ከመጠን በላይ የበሰለ ቲማቲም መስሏል።

«ሚስትህን ፍታ፣ ልጆችህን በትን ነው የምትይኝ?! ንገሪኝ እስቲ ሮዛ!»

«እንጃልህ!....እሱ የራስህ ጉዳይ ነው።»

አንዳች ነገር ጉሮሮዋ ላይ ተናነቃት። የጉሮሮዋን ትግል እቆጣጠራለሁ ስትል ዓይኖቿ ሁለት ዘለላ እንባ አንጠባጠቡ። መሐረብ ልታወጣ ቦርሳዋን ስትከፍት ወንዳፍራሽ ተመለከታት።

በአንድ እጁ መሪውን እየተቆጣጠረ በቀኝ እጁ እጇን ይዞ ሊያባብላት ሞከረ። እጁና መንጭቃ አስጥላው በመሐረቧ ዓይኖቿንና አፍንጫዋን ደባበሰቻቸው። ሹፌርነቱ ለማባበል ስላልተመቸው ወንዳፍራሽ ልቡ እያእልቀሰ ዝም ብሎ ፊት ፊቱን ይሾፍር ጀመር።

በባልቻ ሆስፒታል ጀርባ ውስጥ ለውስጥ ገብቶ ቤቷ በር ላይ ካወረዳት በኋላ ከአፏ አንድ ነገር በመጠብቅ ዐይነት በመኪናው መስኮት አንጋጦ ተመለከታት። የሰላምታ ቃል እንኳ ሳትተነፍስ በሩን በኃይል ዘግታ ሄደች።

«ሮዚና....»

ዘወር ብላ ልታየውም አልፈለገችም። እሱም ደግሞ ከመኪናው ወርዶ ለማባበል ጊዜ አልነበረውም። ነዳጅ መስጫውን ረግጦ መኪናዋን ካስጮሀት በኋላ የንዴት አነዳድ እየነዳ ፈትለክ አለ።

ምን አድርግ ነው የምትለኝ? ሲል አሰበ። በአንድ በኩል ውጭ ማደሩ ከውስጥ መንፈሱን እየረበሸው ነበር። ለፅጌረዳ ምን እንደሚላት ጨንቆታል። በሌላ በኩል ደግሞ ከሮዛ ጋር ያለው ግንኙነት እየጠበቀ መምጣቱ ህይወቱን መላቅጥ እያሳጣው ነው። ማኩረፍ ወይም ማልቀስ ከጀመረች ሰንበት ብላለች። አኩርፋ ትለየዋለች፣ ነገር ግን አንድ ሰዓት ሳትቆይ ትደውልለታለች። ፍቅር ነው

የሚያኮርፋትም፣ የሚያስለቅሳትም። ወንዳፍራሽም ልብ የዚያኑ ያህል ውስጥ ውስጡን እያለቀሰ ነበር። ሮዛ ፊት ፅጌረዳን አናንቆ ወይም አጣልልቶ አውርቶ አያውቅም። እንዲያውም የሚስቱን የዋህነትና ታታሪነት ነው የሚነግራት። ይሄ ደግሞ እያደር በሮዛ ልብ ውስጥ ቅናትን ፈጠረ። ፅጌረዳን እንዲጠላት፤ እንዲያጥላላት ፈለገች።

እዳ እኮ ነው!.....

እዳ መሆኑን እያወቅክ ለምን ገባህበት?......

መጠምዘዣ መንገድ ላይ ሲደርስ የመኪናውን መሪ ብቻ ሳይሆን የራሱንም ሕሊናም በሚጠበዝዝ ዓይነት መዘውሩን ፈጥኖ አዞረው። መኪናዋ ዞራ ዋናውን መንገድ ስትይዝ ህሊናውም ወደ ቀጥታው መሥመር ተመልሶ ጥያቄውን ቀጠለ።

በአንድ ጊዜ ሁለት ሴቶች እኩል ማፍቀር ይቻላላ ወይ?!......

ፍዝዝ ቅዝዝ ብላ የፅሕፈት መኪናውን ታንቀጫቅጫለች አይኗና ጣቶቿ የጽሕፈት መኪናውን ሥራ ስለተካኑት ጠንቅቀው ቢሠሩም፤ ዓዕምሮዋ ከእነሱ ጋር አልነበረም። እንደ ልማዷ በኃሳቧ ርቃ ሄዳለች። የቅናት ዕንባ እየታገላት ዓይኖቿ አጠገብ ደርሶ ይመለሳል። - ጥርሶቿን ነክሳ ትውጠዋለች። እና፤ ቁጭቷን እንደ ተወጣች ዓይነት፤ የጽሕፈት መኪናውን ቁልፎች ጫን ብላ ትመታቸዋለች።

ግማሽ ሰዓት ያህል እንደ ሰራች፤ ለሦስተኛ ጊዜ ስልኩ ተደወለ። ሁለቱ ትሪዎች የአለቃዋ ስለ ነበሩ አስተላልፋዋለች። ይኸኛው ግን የራስዋ ጥሪ መሆኑን የተናጋሪውን ድምፅ የመጀመሪያ ፊደል ስትሰማ አወቀችው።

«ሀሎ......ጽጌረዳ እንደምን አደርሽ?»

የገዛ ባሏ ውጭ አድሮ እንደ ባዕድ «......እንደምን አደርሽ?» ሲላት፣ መስል መስጠቱ ጉሮሮዋ ላይ ተናነቃት። ተዋት እንቅልፍ ይዞት ስለ ረፈደ ቤቱ ሳይደርስ በዚያው ነበር - ወደ ቢሮው የሄደው። ይህንንም እንደ ተጨማሪ ንቀት በመቁጠር ተብከነከነች እንዳለፉት ወራት የሆዷን በሆዷ ይዛ፣ ቅናቷን ደብቃ በትዕግሥት

ልታነጋግረው አትችልም። ያ ሂደት ጡዘቱ ላይ ደርሶ ወድቋል። እና ምን ትበለው?..... ለሰላምታው ምላሽ ዕልኋን የምትገልጽበት ቃላት እንዳጣች ሁሉ ቴሌፎኑን ጆሮው ላይ ዘጋችበት። - ከቃላት ይልቅ እንዲህ ዐይነቱ ድርጊት መጠነኛ እፎይታ ሳይሰጥ አይቀርም!......

ወንዳፍራሽ እንደገና ደወለ። የቢሮ ስልክ ስለሆነ መቀበል አለባት። የስኩን እጀታ እንደተጠየፈች አይነት ፈቷን አጨማዳ በዝግታ አነሳችው።

«ሀሎ..... ምነው እባክሽ?! ምን ችግር ገጥሞኝ እንዳደርኩ መጠየቁ አይቀልም እንዴ?......»

«ምነው ቸኮልክ?... ዛሬንም አድረህ ነገ ጠዋት ብትደውል ይሻል ነበር እኮ......»

«አንድዬኤ .......ገና ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ተኩል መሰለኝ።»

«ገባኝ፤ ዛሬንም ውለህ አድረህ፣ ነገ ወደ ማታ ቤትህን ብቅ ብለህ ብታየው ትችል ነበር። ፍቅር በአንድ ሌሊት አያልቅም ብዬ እኮ ነው!.......ያውም አዲስ ፍቅር!.....»

«እሱስ ልክ ነህ?...... ለመሆኑ ሮዛ ደህና ናት!»

«የ- የማነች ሮዛ?!»

ፅጌረዳ የፌዝ ሳቅ ስቃ በቴሌፎን ልታሰማው ፈለገች። ነገር ግን በሳቅ ፈንታ ሳግ መጥቶ ጉሮሮዋ ላይ ግጥም አለ። የብሶትና የፌዝ ንግግሩንም ልትቀጥልበት አልቻለችም። ሲያደጉ ማየትና ማድረግ የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ቁጭታቸውን በፌዝ ሳቅ፣ በአሽሙር ንግግር ወይም ወንዱ ፊት ቀሚሳቸውን እየነሰነሱ በማክላላት የሚወጡ ሴቶች አይታለች። አድራጎቱን ጠልታው እንጂ ቀላል ነበር የሚመስላት። ያልነበሩትን በአንዴ መሆን እንጂ ቀላል ነበር የሚመስላት። ያለነበሩትን በአንዴ መሆን እንደማይቻል አሁን ገባት። የዋህና ግልጽ ተፈጥሮዋ ከእንዲህ ዓኡመቲ ፣ አጅጅነራዎ ንችፌያ ሸሽቶ ወይም ተገልሎ ስለኖረ በአንድ ምሽት ያሰበችውን መሆን አቃታት። በአግድሞሽ ጥያቄና መልስ በስልክ መነቻቸፋን ስላልቻለች እንደገና የስልኩን እጀታ ቀፎው ላይ ወርውራ፣ ፊቷን እጆቿ ውስጥ ቀብራ የፅሕፈት መኪናው

ላይ ተደፋች። በእጆቿ ተሸፍነው የተጨፈኑት አይኖቿ ዓለምን አጨልመው ተመለከቱ። የዘጠኝ ዓመት ጥረት መና ሆኖ ሲቀር..... ምሰሶ ሲወድቅ.... ድንጋዩ ሲናድ..... ፍሞ የኖረው ፍቅር ከስሞ ዓመድ ሲሆ......ዳኒና ሰብልዬ በእንጀራ እናት ወይም በእንጀራ አባት እጅ ሲያድጉ.....ፊታቸውን ክፍል ብሎት ሲያምጹ ከቤት ወጥተው በየመንገዱ እየተንከራተቱ ሲለምኑ ታያት። እናም ደግሞ ለሷ የጨለመው ዓለም ለሮዛ ብርሃኑን ሲፈነጥቅ የጨፈነችው ዓይኗ አሳያት።

«ፅጌረዳ...... ፅጌ......»

የትውሲት ድምፅ ፅጌረዳን ከሀሳቧ አባንኗት በዝግታ ራስዋን ከፅሕፈት መኪናው ላይ ቀና አደረገች። ትሲሲት የስራ ጓደኛዋ ናት። አለቆቻቸው ቢለያዩም በቢሮ ጥበት ምክንያት ሁለቱ ሴቶች አንድ ክፍል ይጋራሉ። ሁለቱም ፀሐፊዎች ናቸው። ፅጌረዳ በቅናት ተመስጣ የቆየችባቸው ደቂቃዎች ትውሲት አጠገቧ መኖሯን አስረስተዋት ነበር። በስልክ ስታወራም ትዝ አላለቻትም። አሁን ወደ ራስዋ ስትመለስ ከፊል ሐፍረት ሰለ ተጫጫናት ስሙና በጠራቻት ጊዜ ቶሎ ብላ ፊትዋን አላዞረችም።

ትውሲትም ብትሆን ለነገሩ እንግዳ አይደለችም። የቢሮ ጓደኛዋ እንደመሆኗ መጠን ብዙውን ነገር አውርተውታል። እንዲያውም የሮዛን ስምና ቁመና ተከታትላ የነገረቻት ትውሲት ናት። ያም ቢሆን ግን የስብዕና ጉዳይ ስለ ሆነ ፅጌረዳ ባሳየችው ድርጊት ትንሽ አፈር አለች።

«ምንድን ነው?.... ባለቤትሽ ነው እንዴ የደወለው?.... ውጭ አድሮ ነው?.....» እያለች ትውሲት በጥያቄ አፋጠጠቻት።

ፅጌረዳ ያሳየችውን ሁኔታ መልሳ የማውጠው፤ ጉዳዩንም የማትደብቀው ስለሆነባት በአዎንታ ራሷን ነቀነቀች።

«አዳር?!......አዳር?! አዳር?!»

ትውሲት ልቧን ባይፈነቅላትም ነገር ማግነን ትወዳለች። ለፅጌረዳ ማዘኗ እንኳ አሌ አይባልም። ድንጋይም አይን ቢኖረው ለፅጌረዳ ያለቅሳል። በወንዳፍራሽ ውጭ ማደር ይህን ያህል መደነቋ ግን ከአንገት በላይ ነበር። ከዚያ ይበልጥ የሚያስደንቁ ብዙ ነገሮች አይታለች፤ እሷም ሰርታለች።

«....አዎ አደረ። ምን ታደርጊያዋለሽ?» አለች ጽጌረዳ ሳታስብው ከንፈሯን እየነከሰች።

«አንቺ ፊት እያሳየሽው እኮ ነው፤ ፅጌ»

«ምን ላድርግ ትያለሽ፤ ትውሲት። እኔማ ከቀን ወደ ቀን ይታረማል ብዬ ነበር።....የትዕግሥቴን ውጤት አየሁት።»

«አይ ፅጌ!.... የዋህነትሽ ነው እንጂ..... ወንዶች እኮ ይበልጥ የሚጨማለቁት ስትታገሻቸው ነው። እነሱን በትዕግሥት እገራለሁ ማለት ዘበት ነው። የባሰውን ይንቁሻል። ለንቀታቸው ምላሽ ካልሰጠሻቸው አሻንጉሊት አድርገው ይጫወቱብሻል። »

ንግግሯን አቋርጣ ከንፈሯን እየመጠጠች ፅጌረዳ በጥያቄ አይነት ትክ ብላ ተመለከተቻት። ፅጌረዳ በሐዘኔታ ራሷን ከመነቅነቅ ሌላ ምንም አልተናገረም።

«.......ምነው አንቺ ይህን ያህል... መልክ አላጣሽ፤ ፀባይ አላጣሽ፣.... እመቤቴ እያለ የሚያኖርሽ ወንድ ሞልቷል።.......ገና በልጅነትሽ ለምን ትቃጠያለሽ?!........»

«ሁለቱ ልጆች አሉን እኮ.....ያ ነው ችግሩ» አለች አይኖቿን ቦዘዝ እንዳደረገች።

«እሱም እንዳንቺ ለልጆቹ ቢያስብ ቀድሞውንም አይቀብጥም ነበር። ያንቺ ብቻ ማሰብ ምን ዋጋ አለው?!»......

ፅጌረዳ ነገሩን ዕይሰማች ታላመጠው ጀመር። አይኖቿን ቡዝዝ እንዳደረገች አሰበችበት። - እውነት እኔስ ቤቴ ውስጥ ቁጭ ብዬ በቅናት ከምቃጠል ለምን ከሌላ ወንድ ጋር አልወጣም? የሚል ሐሳብ ብልጭ አለባት። በዓያቸው የቋመጣቱ ወይም ቀርበው እንደዋዛ የከጀሏት ወንዶች ለአፍታ ያህል በሀሳብዋ ውስጥ ድቅን አሉባት። ነገር ግን ይሄም ልምድ ይጠይቃል። እሷነቷን በአንዴ ለውጣ ማቅረብ እንደማትችል ተሰማት። ፍቅር ሳይኖር ለእልህ ብቻ ከሌላ ወንድ የመውጣቱ ሀሳብ መልሶ ዘገነናት።

ባል መፍታት ወይም ወንድ መቀያየር ለትውሲት ቀላል ጉዳይ ነው። በዚህ ረገድ ከፅጌረዳ ጋር ፈፅሞ ስለማይግባቡ ወሬውንም አያነሱትም ነበር። በቢሮ ጓደኝነታቸው ሌሎች ነገሮችን ይጫወታሉ እንጂ ስለ ወንድና ሴት ግንኙነት

አይነጋገሩም። አንዳንዴ ትውሲት አፍ አምልጧት ስትጀምር ፅጌረዳ ነገሩን ታጥፈዋለች፤ ወይም ግንባሯን አጨማዳ ፈቃደኛ ያለመሆኗን ታሳያለች። አሁን ግን በራሷ ችግር ስለገባችባት ከዚህ ርዕስ ሊያመልጡ አልቻሉም። በችግር ወይም በፀብ ወቅት የማንም ስሜት ቢሆን ተባባሪ ወይም አዳማጭ ጓደኛ ይፈልጋል። «የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው» የሚል አባባልም አለ። የትውሲት ወንዳፍራሽን አድኖ ከሴት ጋር መያዝና ለፅጌረዳ ማዘን ቅርበታቸውን አጠናክሮ ለዚህ ዐይነቱ ጨዋታ አደረሳቸው። ትውሲት በፅጌረዳ ትዳር ውስጥ ገብታ ለመናገር ሙሉ ድፍረት አገኘች።

«......የምትተባበሪኝ ከሆነ» በማለት ፅጌረዳ የፀጥታውን ዓየር ሰበረችው «የምትተባበሪኝ ከሆነ አንድ ቀን ሮዛ ያልሻትን ሴት ባያት ደስ ይለኝ ነበር።»

ሮዛ የሚለውን ስም ስትጠራ እንዳቅለሸለሻት አይነት ፊቷን ጭምድድ አደረገችው። ሀሳቧን አስባ የጥፋቱን ደረጃ ከወንዳፍራሽ ይልቅ በሮዛ ላይ ከፍ ካደረገች በኋላ ነው ልታያት የፈለገችው። ካየቻትም በኋላ ምን እንደምታደርግ ግን አላወቀችውም።

«እኔምን ቸገረኝ። - ደስ ይለኛል። ኧረ እንዲያውም እሱው ይዟት ሲዝናና እጅ ከፍንጅ መያዝ ትችያለሽ። በተለይ ዓርብ ማታ «ስርቆት አዳራሽ» አይጠፉም። ......»

«የት አካባቢ ነው እሱ»

«ንፋስ ስልክ መስመር ነዋ «ስርቆት አዳራሽን» አታውቂውም?!....እኔ አሳይሻለሁ።»

«እሺ በቃ፤ አንድ አርብ ማታ አብረን እንሄዳለን።»

ወንዳፍራሽ ከቀኑ አስር ሰዓት ከቢሮው ወጥጦ ወደ ቤቱ ሲያመራ መሪ የያዘበት እጁ ሁሉ እየተንቀጠቀጠ ነበር። የፅጌረዳን ዓይን ማየት ፍርቶአል። ምንም ማስተባበያ ሊያሸንፉት እንደ ማይችል ልቡ አውቋል። ለወትሮው ቢሆን ከሥራ ሲወጣ በፅጌረዳ መስሪያ ቤት በኩል ሄዶ በመኪናው ነበር የሚያመጣት። ዛሬ

ምናልባት ገና ስታየው መስሪያ ቤቷ በር ላይ ጦርነት እንዳታነሳ ፈርቶ ቀድሞ ወደ ቤት መጣ።

ቤቱ ደርሶ የመኪና ጥሩንባውን ድምፅ ሲያሰማ ሠራተኛዋ እልፍነሽ ወጥታ በሩን ከፈተችለት። ትንሿ ልጅ ሰብለ ድክ፤ ድክ እያለች ከበረንዳው ላይ ወርዳ «ወንቴ......ወ-ን-ቴ!» እያለች ቀረበችው። ከመኪናው ወርዶ አቅሮ ሳማትና እያጫወታት ወደ ቤት ውስጥ ይዞአት ገባ። ዳኒ ገና ከትምህርት ቤት አልመጣም። ፅጌረዳም አልገባችም። ሠራተኛዋ ወደ ኩሽና ተመልሳ ሄዳለች። - በቱ ወና ሆነበት። እንደ ባለቤት ሳይሆን እንደ እንግዳ ጭር ያሉትን ክፍሎች እየተዘዋወረ ጎበኘ። ዕቃዎቹን ሁሉ አስተያየቱ፤ አንድ ቀን ሳይሆን ብዙ ወራት ውጭ እንደ ከረመ ዓይነት ነበር። በሥራ ምክንያት አንድ ወይም ሁለት ጊዜ ወደ ክፍለ ሃገር ሄዶ ከርሟል። ያኔ ወደ ቤቱ ሲመለስ እንዲህ እንደ አሁኑ ዓይነት የእንግድነት ስሜት አልተሰማውም። አሁን መንፈሱን ባዶ ያደረገው እንግዳ ድርጊቱ ነው። ማንኛውም ነገር የስሜት ነፀብራቅ መሆኑን ገመተ።

«ትግዬስ?.....የታለች?» አለችው ሰበል ደረቱን ጥብቅ ብላ።

«......ትመጣለች፤ መንገድ ላይ ነች።» አለና ግንባርዋ ላይ ሳም አድርጓት ወደ መኝታ ክፍሉ ይዞአት ገባ። ጫማውን ሳያወልቅ አልጋው ላይ ተጋድሞ መጠባበቅ ጀመረ።

ጽጌረዳ መጥታ ጦርነቱ እስኪፈንዳ ድረስ መንፈሱ ከፉኛ ተጨነቀ። ወንዳወዳዊ ትምክህቱ ድርጊቱን እንደ ቀላል ጉዳይ ቆጥሮ ሊያፅናናው ቢሞክርም፤ ህሊናው ሊያርፍ አልቻለም። - ሴትየዋ ፅጌረዳ ናት! በሥራዋም ቦታ «ቅድስት» የተባለች ሴት ናት። ከእሱ እኩ ወገቧን አሥራ እጎጆአቸውን ምሰሶ ያቆመች ሴት ናት።

ሦስት ነገሮች በልቡ ረገመ። - የትላንቱን ምሽት፣ ያሳሳተውን መጠጥና የሮዛን ፍቅር። እስከ ምሽቱ አምስት ሰዓት ድረስ «ቤቴ እሄዳለሁ» እያለ ሲፎክር ማምሸቱ ትዝ ይለዋል። ከዚያ በኋላ ነው ሮዛ መጠጡን በላይ በላዩ እየቀዳች፤ የፍቅር መልክት በሚያስተላልፉ ለስላሳ ጣቶቿ አንገቱን እያሻሸች፤ ራሱን ስቶ እንዲያድር ያደረገችው። እሷ ኢላማዋን እስክትመታ ድረስ አጠጣጧን ትቆጣጠር ነበር። መኝታ ተከራይተው

ወንዳፍራሽ ከጎኗ መተኛቱን ካረጋገጠች በኋላ በድል አድራጊነት ስሜት ስትጠጣ አመሸች። መጠጡን ከቡና ቤቱ አዝዛ መኝታዋ ድረስ እያስመጣች!

ወንዳፍራሽ የሰው ድምፅ ስለሰማ የአዳሩን ሀሳብ ትቶ ጆሮውን ወደ ግቢው ጣለ። የዳንኤል ድምፅ ነበር። የአባቱን እምኪና አይቶ እየቦረቀ ወደ ሳሎን ገባና ደብተሩን አስቀመጠ።

«ዳኒ.....» አለው አባቱ ከመኝታ ክፍሉ፣ በአረማመዱ ለይቶት።

ዳኒ ቦርቆ እንደገባ ወንዳፍራሽን ሰላም ሊለው አልቻለም። የአባቱን ፊት ሲያይ ድንገት የማታው የእናቱ ሁኔታ ትዝ አለው። በአንድ አፍታ ፊቱን አጨፍግጎ ለሰላምታ ያህል እጁን ብቻ ዘረጋለት።

«ና እንጂ ሳመኝ ዳኒ!» አለና እጁን ጎትቶ አስጠጋው።

ሲስመው ፈገግ አላለም። ዝም ብሎ እንዳኮረፈ ጉንጩን ሰጠው።

«ምን ሆነሃል ዳኒ?»

«ፅግዬን ለምን ታስለቅሳታለህ?.....»

ወንዳፍራሽ ራሱን እንደተመታ ያህል ክው አለ። ዳኒ ጉዳዩ ጠልቆ አውቆ ፊቱን እስከማጨማደድ ይደርሳል ብሎ አልገመተም ነበር።

«መቼ ነው ያስለቀስኳት?.....»

«ትላንትና ማታ ነዋ!.....አንተ ሌላ ሚስት ስላገባህ እሷ አለቀሰች። ፎቶግራፍህንም ስብርብር አደረገችው።

ሳሎን ውስጥ በገባ ጊዜ ዓይኑን ቅር ያለው ነገር ምን እንደሆነ ገባውና ለማረጋገጥ ተነስቶ ሄደ። ባፌቱ ላይ ተቀምጦ የኖረው ፎቶግራፍ የለም።

ወደ ኩሽና ሄዶ እልፍነሽን ጠየቃት። እልፍነሽ ማታ በጊዜ ስለተኛች ፎቶግራፉ ማን እንደሰበረው አላየችም። ነገር ግን ጠዋት ቤት ስታፀዳ የተሰባበረውን መስታወት ፍሬም በምትጠርግበት ጊዜ፤ የወንዳፍራሽን ውጭ ማደር አያይዛ፣ ፎቶውን ማን ሊሰብረው እንደሚችል መገመት አላቃታትም። ስንጥቅ ወይም

መካከለኛ ስብር ሳይሆን ሆነ ተብሎ በሰው እጅ የተከናወነ ጥፋት መሆኑን ከእንክትክቶቹ መረዳት ይቻል ነበር።

«.......እኔ እንጃ ማን እንደ ሰበረው። ድመቷ ነች መሰለኝ ጠዋት ቤት ስጠርግ ጣውላው ላይ ተንኮታኩቶ አገኘሁት። መስታወቱ ነው እንጂ የተሰበረው የወረቀት ስዕሉ አለ።» አለችው እልፍነሽ ግማሽ ፍርሀት በተጫጫነው አነጋገር።

«የወረቀቱ ስዕል......የተረፈው የታለ?» አላት፤ ቆጣ ብሎ።

ቁም ሣጥኑ አናት ላይ አስቀምጣው ነበር። ወደ መኝታ ክፍላቸው ሄዳ ከሰቀለችበት አወርዳ ሰጠችው። ወረቀቱ ላይ የሠፈረው ምስሉ ተሰነጣጥሮ ተጨማዶ ሌላ ፍጡር መስሏል።

ፈገግታው ብቻ ከላዩ ላይ አልጠፋም።

«አየሽው አይደል?......አለው ዳኒ ኮስተር ብሎ ከኋላ ከኋላው እየተከልተል።

ወንዳፍራሽ የፎቶውን መሰበር ሲመለከት የተለያየ ሀሳብ ውስጥ ገባ። «በቃኸኝ፣ ፍቅራችን አክትሟል!» ማለቷ ይሆን?..... ትዳሩን ለማፍረስ ቆርጣ ይሆን?..... ወይስ ደግሞ በአንድ ቤት ውጥ የደባልነት ኑሮ ለመኖር ራሷን አዘጋጅታው ይሆን?!.....

«እኛ እንደሆንን ሌላ እናት አንፈልግም። እናታችን ፅግዬ ናት።...... አይደል ሰብሊ?!»

ሰብለ ነገሩ ሳይገባት ወንድሟን ለመደገፍ ያህል ብቻ ራስዋን በአዎንታ ነቀነቀች። የሦስት ዓመት ታናሹ ናት።

«እናትህ አትመናት። ዝም ብላ ነው የምታወራው። እኔ ሌላ ሚስት የለኝም.....ትሰማኛለህ ዳኒ»

«ውሸትህን ነው። ፅግዬ ነገራኛለች። ሮዛ የምትባል አዲስ ሚስት ልታገባ አይደል?!......»

ሌላ ዱላ! የሮዛ ስም ሲጠራ የወንዳፍራሽ ድንጋጤ ጨመረ። ልጆቹን የሚላቸው ነገር ጠፍቶት ዝም ብሎ ዓይን ዓይናቸውን ይመለከት ጀመር። አጠገቡ እያሉ የራቁት መሠለው። የሕሊና ዱላ ስለቆጠቆጠው እንደ አባት ኮስተር ብሎ ሊገስጻቸው አልደፈረም። ቢሞክርም የዳኒ አዝማሚያ የሚበገር እንደማይሆን ገመተ። - ልጆቼን ስታሳምፅብኝ ከርማለች ማለት ነው፤ አለና ፅጌረዳን በልቡ ረገመ።

አስራ አንድ ሰዓት ተኩል አካባቢ ፅጌረዳ መጣች። ወንዳፍራሽ ድምጿንና ኮቴዋን ስለሰማ ከአሁን አሁን ወደ መኝታ ክፍል ትገባለች ብሎ በጠንቀቅ ይጠባበቅ ነበር። ፅጌረዳ ግን እሱን ላለማየት ሳሎን ተቀምጣ ቀረች። ዳንኤልና ሰብለ እየሮጡ ሄደ ተጠመጠሙባት። ሁለቱን ልጆቿን በቀኝና በግራ ጎኗ አስቀምጣ የቆጥ የባጡን እያወራችላቸው ቆየች። ሰብለ የአባቷን መምጣት ስታወራ እናቷ ሆነ ብላ አርዕስት ታስቀይራታለች። ዳኒ እንገሩ ስለ ገባው ዝም አለ።

የወንዳፍራሽ ልብ ከበሮ እየደለቀ ነበር። አኩርፋ ሳሎን መቀመጧ ገባው። ኩርፊያዋ የፍቅር ወይም የቅናት በመሆኑ እሱ ሄዶ ይቅርታ ሊጠይቃት ፈለገ። ነገር ግን ወንድነቱ ታገለው። - ስንቱ በየዳሮ በየጊዜው፣ የሚፈጽመውን ስህተት እኔ በህይወቱ አንዴ ፈፀምኩና ወንጀሉ ምንድነው? የራሷ ጉዳይ! ለማለት ሲከጅል ለዘጠኝ ዓመታት ያሳየችው ፍቅርና ታማኝነት ከፊቱ መጥቶ ድቅን አለበት።

ቀበቶውን ሸቅብ ሰብስቦ ተነሣና ወደ ሚስቱ ሳይሆን ወደ ፍርድ ቤት እንደሚቀርብ ዓይነት ግንባሩን ኮምተር አድርጎ ህሊናውን አዘጋጀ። እግሮቹን እየጎተተ ከመኝታ ክፍሉ ወደ ሳሎን ሲገባ ፅጌረዳ ቀና ብላም አላየችው። በንቀት ዓይን ፊቷን አስጨማዳ የሰብለን ፀጉር እያሻሸች ነበር። - ድርጊቱን ሁላ በጆሮዋ እየተከታተለች።

«እንደምን አመሸሽ፤ ጽጌረዳ......»

እንደወትሮው «ፅግዬ» ማለቱ የፌዝ ይመስላታል ብሎ ፈራ። ፍርሐቱ ራሱን ለሚስቱ ባዕድ እንደሚያደርግ ጋበዘው።

«ደህና....» አለች ፅጌረዳ፤ ኮስተር ብላ እንዳጎነበሰች የልጇን ፀጉር እያሻሸች።

ፊቷን በጥያቄ መልክ ትክ ብሎ ተመለከታት። አመለካከቱ ለመናን ያዘለ ይቅርታን የሚጠይቅ ዐይነት ነበር። - ፈጽሞ ቀና አላለችለትም። አምርራለች።

የትላንት አዳሩን ማስተባበል እንደማያዋጣው አወቀ። የሆዷን ችላ ውሸትንም ውነቱንም ስትቀበል የቆየችበት ትዕግሥቷ ማለቱ ፊቷ ላይ ይነበባል። ነገሩን አፍረጥርጦ አውጥቶ ይቅርታ ከመጠየቅ ሌላ አማራጭ እንደሌለው ገመተ።

ከፊት ለፊቷ ትይዩ ሶፋ መርጦ ተቀመጠ።

«ዳኒና ሰብለ ሂዱ፤ ከእልፍነሽ ኩሽና ተጫወቱ» አላቸ በአባትነት ድምፀት።

«አይሔዱም!» ባላ ፅጌረዳ፤ የባሰውኑ ግንባሯን ጭምድድ አድርጋ፤ ሁለቱንም ልጆች ወደ ጭኗ አስጠጋቻቸው።

«ተይ እንጂ ፅጌረዳ፤ በልጆቹ አዕምሮ ውስጥ መጥፎ ነገር አትቅረጭባቸው። ......»

መልስ አልሰጠችውም። ከአንጀትም ይሁን ከአንገቷ፣ ንቀት በማሳየት በዝምታ ዕልኋን እየተወጣች ነበር። ልጆቹም ለእናታቸው ወገናዊነት እንደማሳየት አይነት፣ ጭኖቿን ደገፍ ብለው ፊታቸውን አጨፈገጉት።

«......ብንነጋገርበት አይሻልም ፅጌረዳ?!»

«የንግግሩማ ዘመን አለቀ እኮ! አሁን ከቃላት በላይ ተግባር ተናገረ። ከቤትህ ውጭ አደርክ! የእኔ ትዕግሥት የአንተ ንቀት ለዚህ አበቃን!.....አለቀ.....»

«ብዙ ወራት ታግሰሽ መቆየትሽን አውቃለሁ። ለምን በአንድ ጊዜ ቱግ ትያለሽ?! እንደማመጥ። ነገሩን ግልስጽ አድርጌ ልንገርሽ።»

ዕልህ ቢተናነቃትም ቅሉ የሚለውን የመስማት ጉጉት ስላደረባት ወደ ሌላ እያየች ጆሮዋን አስልታ ሰጠችው።

«.......አዎ፤ ግምትሽም ሆነ ጥርጣሬሽ ልክ ነበር።» መናገር የፈለገውን መቀጠል ፈራ። እንደምንም ራሱን ታግሎ ቀጠለ። «......ከአንዲት ሮዛ ከምትባ ሴት ጋር ስወጣ ቆይቻለሁ። ይሄ ግን ወድጄ ወይም አንቺን ለመጉዳት አስቤ ያደረግኩት ጉዳይ አይደለም። አንቺም ሆነ ልጆቼን አሁንም እወዳለሁ።.......»

ፅጌረዳ ከንፈሯን በንቀት ስታጣምም ተመልክቶ ወንዳፍራሽ ንግግሩን አቋረጠ።

«ቀጥል እንጂ!.....» አለችው በብሽቀት ድምፅ።

ቀስ ብሎ ገጿን አጠና። የሮዛ ስም ከተጠራ ጊዜ ጀምሮ ቀስ በቀስ ልውውጥ እያለ መሔድ ጀመሮአል። ቅንአት ቀንዱን አሹሎ፤ ጥርሱን ስሎ እያስገመገመ ከተፍ አለ። ዓይኖቿ እንደ ከዋክብት ተወርውረው የወንዳፍራሽን ፊት ጠቅ/ አደረጉት።

ያበጠው ይፈንዳ፤ ብሎ ወንዳፍራሽ ንግግሩን ቀጠለ።

«ከሮዛ ጋር የተገናኘነው በአንድ ባልታሰበ አጋጣሚ ነው። ግንኙነታችን ይቀጥላል የሚል ግምት አልነበረንም። በአንዳች እሳታዊ ስሜት ተገፋፍተን አብረን መውጣት ጀመርን።......»

ፅጌረዳ ሳይታወቃት ጥርሶቿን አንቀጫቀጨች።

«ትዳር እንዳለኝ፣ ሚስትና ልጆች እንዳሉኝ ለሮዛ አልደበኳትም። ......ግን እንዴት እንደሆነ እንጃ፤ በዚህ ሁሉ ችግር መሐል ከሮዛ ጋር ተላመድን።.......»

የሮዛ ስም ተደጋግሞ መጠራቱን ፅጌረዳ አልወደደችውም።

«አስሬ ሮዛ ሮዛ አትበልብኝ። እሷው ጋ ሂድና ክንድህን አንተርሰህ አቆላምጣት።።»

«ሎዛ ማን ናት?» አለች ሰብለ፣ ጣልቃ ገብታ እየተኮላተፈች። ሮዛ ለእናትና አባቷ ፀብ መነሻ መሆኗን በደመነፍስ ያወቀት ትመስል፣አለች።

«....አዲሱ ሚስቱ ናታ!.....አዲስ እናት ሊያመታላችሁ እኮ ነው፣ ሰብልዬ።።»

ወንዳፍራሽ ግልፍ አለው።

«ነግሬሻለሁ ፅጌረዳ! ይሔ የእኔና የአንቺ ጉዳይ ነው። የልጆቹን ጭንቅላት አትመርዥ!.......»

«ልጆቹ በእንጀራ እናት ልታሳድጋቸው ማቀድህን መች አጡት!?..... ጅል አትሁን።........»

የዳኒ ዓይኖች አርግዘው የቆዩትን እንባ ቁልቁል ለቀቁት። የእናቱን ትከሻ ተደግፎ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ። ሰብልዬም ነገሩ ሳይገባት ዳኒን ተከትላ አለቀሰች።

ወንዳፍራሽ ሚስቱ ላይ አፈጠተ። በገዛ ቤቱ ውስጥ የልጆቹና የሚስቱን የተባበረ ዓመፅ ማየቱ አበሸቀው። ወንድንነቱ ጡንቻዎቹ እየወጣጠረው ከተቀመጠበት ተነሳ። በህይወቱ ለጀመሪያ ጊዜ ሴት ልጅ በእጁ መምታት ፈለገ። ልታዳምጠው ያልፈለገችውን ከልጆቹ ያጣላችውን ፅጌረዳን በክርኑ ሊደቁሳት በጥፊ ሊያላጋት ፈልጎ በዚያ ደንዳና ሰውነቱ አኮበኮበ።

እናትየዋም አርፋ አልተቀመጠችም። የዘመናት ሩህሩህነትና ታጋሽነት በአንድ ምሽት ከላይዋ ላይ በርሮ እንደጠፋ ሁሉ፤ ልጆቿን ገፈታትራ ባልዋን ልትጋተረው ተነሳች።

«ም - ምን ልትሆን ነው የተንሳኸው!» አለችው። በለስላሳ ጠይም ግንባሯ ላይ ደምስሮቿ አፍጥጠው ሌላ ሴት አስመስሏት። የወንዳፍራሽ ግዙፍ ቁመናና ደንዳና ሰውነት አላስፈራትም። ትልቅ ሰውነቱ ትንሽ ሆኖ ታያት።፡ - በጥሮቿ ብትቧጭረው በደም የሚጥለቀለቅ፤ በጥርሷ ብትግተው የሚቦጫጨቅ ጫማዋን ብትወረውርበት ፍንክትክቱ የሚወጣ ትንሽ ፍጥረት ሆኖ ታያት።

ወንዳፍራሽ እንኳንስ እጁን ሊሰነዝር ጭራሹን ፍዝዝ ብሎ ቀረ። ጉልብቷ ሳይሆን ሁኔታዋ አስፈራው። ዘጠኝ ዓመት ሙሉ አብረው ሲኖሩ ዓይቷት አያውቅ፤ የተደበቀች የቤት ውስጥ ነብር ሆና ታየችው። በመማታት ፈንታ እንደ አዲስ ፍጡር ትክ ብሎ ይመለከታት ጀመር። - እውነት ቅናት እንዲህ ያደርጋል እንዴ? በአንዴ ሰውን ይለውጣል እንዴ? እያለ አሰበ።.....

እልፍነሽ የልጆቹን ለቅሶ ሰምታ ከኩሽና ስትወጣ ባልና ሚስት ተፋጠው ቆመው ተመለከተች። ነገሩ ስለጋባት ተንደርድራ ሄዳ ወንዳፍራሽ እግር ላይ ወደቀች።

«ኧረ ተነሺ.... ምን መሆንሽ ነው አንቺ ደግሞ?!» አለና አስነሳት።

እልፍነሽ ግልግል መግባቷ ነበር። ነገር ግን ከወንዳፍራሽ ይልቅ ጽጌረዳን ማብረድ እንደሚገባት አላወቀችም።

«ተነሽ!.....ማን ገላጋይ አደረገሽ?!...... ደሞ እግሩ ላይ ተድቂያለሽ?!......» ስት ጮኸችባት።

«እሺ እትዬ....ይታገሱ እባክዎ!......የዛሬን ይለፏቸው በቃ!»

ከጦር ሜዳው ገለል ማለቱ ሳይሻል አይቀርም ብላ ወንዳፍራሽ ወደበረንዳው ወጥቶ ቆመ። የፅጌረዳ ድምፅ ግን በረንዳ ድረስ ተከትሎ ይሰማ ነበር። -

«ስሚኝ እልፍነሽ=፤ - ያንን የእንግዳ ታጣፊ አልጋ አውጪና ልጆቹ መኝታ ቤት ዘርጊልኝ። አዎ!.....አነጣጥፊልኝ ከልጆቹ ጋር ነው የምተኛው።»

በበረንዳው መስኮት በኩል ወደ ውስጥ ተመለከታት። ወገቧን ይዛ እየተውረገረገች ነው።

ዘነላት፡፡- እውነት ይህን ያህል በድያታለሁ? ሲል አሰበ።

«አሁን ጎረቤት ሰምቶ ጉድ ጉድ ቢል ምን ያደርጋል። ፅጌረዳ?! ለምን እንደማመጥም?! አሁን ለአንዳፍታ የነፈግሺኝ ትዕግሥት ለብዙ ወራት ከታገሽው አይበልጥም ነበር እኮ!......»

«እንኳን ጎረቤትና ገና አገር ይሰማዋል።.....የጎረቤቱ ነው የሚደንቅህ?!.....»

«ማንም ቢሰማ ደንታ የለኝም። ማንም በእኔ ሕይወት አያገባውም። አሁንም የምለምንሽ ለአንቺ ፍቅርና ክብር እንጂ ሌላውን ሰው ፈርቼ አይደለም። የበደልኩት አንቺን ነው። እይምፈራውም አንቺን ብቻ ነው።.....»

«ስለምትፈራኝ ስለምታከብረኝማ ነው ውጭ ያደርከው?.......አይደለም እንዴ?!»

«.....አጥፍቼአለሁ አልኩ እኮ! ጥፋቴን ለማረም ትንሽ ጊዜ ብትጠብቂኝ ምን አለበት?!.....»

እሱን ዘግታው ከሠራተኛዋ ጋር መነጋገሯን ቀጠለች።

«......በይ እንጂ እልፍነሽ፤ ቶሎ አንጥፊልኝ። ልጆቹ መኝታ ክፍል ለብቻዬ አንጥፊልኝ.....»

ከመጠን ያለፈ ታጋሽነት መጥፎ መሆኑ ገባው። ፅጌረዳን እንዲህ ያብከነከናት ባንዴ ፀባይዋን የለወጠው ታግሳ በመቆየቷ መሆኑ አወቀ። በየጊዜው ብትተነፍሰ ወይም ትንሽ ትንሽ ብትጨቃጨቅ ኖሮ እንዲህ በአንዴ ነብር አትሆንም ነበር፤ ሲል አሰበ። ሰላማዊ ቤት ውስጥ የፈነዳ ፈንጂ መርዙ ቶሎ አይጠፋም።

እና አሁን ምን መደረግ አለእብት?!....

«ዳኒ! ና እንጂ እንጫወት?!»

ዘነበች ድምጽዋን ከፍ አድርጋ ከርቀት ብትጠራውም ዳኒ ከቆመበት ቦታ ነቅንቅ አላለም። የትምህርት ቤቱ የዕረፍት ደውል ተደውሎ ተማሪዎቹ በሙሉ እየተሯሯጡ ወደ ጨዋታ ሜዳ ሄደዋል። ከፊሉ የኳስ ሜዳውን ከፊሉ «ሰኞ ማክሰኞ» መጫወቻቸውን ከፊሉ የገመድ መዝለያውን ቦታ እየተሻሙ ይዘዋል ዘነበችም በበኩሏ ተሽቀዳድማ «የሰኞ ማክሰኞ» መጫወቻ ካሰመረች በኋል ነበር ዳኒን የጠራችው።

ለጥሪዋ ምላሽ ባለመስጠቱ መጫወት ያለ መፈለጉ ገባትና የያዘችውን ቦታ ለሌሎች አስረክባ ዳኔ ወደ ቆመበት አመራች። የመማሪያ ክፍሉን በር ተደግፎ ሁለት እጆቹን ኪሱ ጨምሮ፤ ልክ እንደ አዋቂ የግቢውን እንቅስቃሴ በርቀት ይመለከት ነበር።

«ምነው?.....ዛሬ መጫወት አልፈለክም እንዴ?» አለችው። ዘኒ አጠገቡ ደርሳ ዓይን ዓይኑን እያየች።

«እባክሽ ዛሬ ጨዋታ አላማረኝም።» አላት ፊቱን ከፍት እንዳደረገ።

«ደሞ ፊትህ ያዘነ ይመስላል። ለምንድን ነው?»

«የፅግዬና የወንዴ መጣላት አሳዝኖኛል። ወንዴ አዲስ ሚስት ሊያመጣ እንዳሰበ ፅግዬ ነግራኛለች። እኔና ሰብለ ደግሞ ሌላ እናት አንፈልግም። ፅግዬ ጥሩ እናት ነች።»

የዳኒን ስሜት ተከትሎ የዘኒም ልብ ወዲያው አዘነ። የምትወደው የትምህርት ቤት ጓደኛዋ ከመሆኑም በላይ በዕድሜም ቢሆን በሁለት ዓመት ያህል ልዩነት እሷ ስለምትበልጠው ልትንከባከበው ትሞክራለች። ትውውቃቸው በቤተሰብ ደረጃ የተሳሰረ ስለሆነ የዕለት ተዕለት ቅርበታቸ ከጓደኝነትም በላይ ወደ ዝምድና ያደላል። ወንዳፍራሽ ለኤርምያስ የቅርብ ጓደኛው ነው። ኤርምያስ ማለት ደግሞ ዘነበችን የሚያሳድጋት አጎቷ ነው። በዚህ ቅርበት ሳቢያ ዘነበች በእላፉ ገደም እነ ዳኒ ቤት እየሄደች ስትጫወት፣ ዳኒና ሰብለም ኤርምያስ ቤት ይሄዳሉ። ሁለቱ አንድ ትምህርት ቤት መማራቸው ደግሞ ፈፅሞ የማይለያዩ ጓደኛ አደረጋቸው።

«.......ግን አባትና እናትህን ምን አጣላቸው?» አለችው በሚያተዛዝን ድምፀት።

«ወንዴ አዲስ ሚስት ማግባት ስለፈለገ ፅግዬ ተናደደች። ትልቁን ፎቶ ግራፉን አውርዳ ሰበረችበትና አለቀሰች።»

«ጋሽ ወንዳፍራሽ ሌላ ሚስት የሚያገባው ለምንድን ነው?»

«እኔ እንጃ! ፅግዬ እንደነገረችኝ ከሆነ እሷም ራሷ ምክንያቱን አታውቅም። ነገር ግን ወንዴ ንቋታል።ር ሮዛ የምትባለውን አዲስ ሚስት ነው የሚፈልገው።»

«ስሟ ሮዛ መሆኑን በምን አወቅህ?»

«ፅግዬ ነገረችኝ። መጥፎ ሴትዮ ናት። ስሟ ሲጠራም አትወአትም። ወንዴ ፅግዬን እንዲያስለቅሳት ያደረገችው እሷ ናት። ደሞም ፅግዬና ወንዴ ሊደባደቡ ነበር። እኔና ሰብለ ስናለቅስ ጊዜ ተዉት።»

ዘኒ አንዳች ሐሳብ እንደገባት ሁሉ ለጥቂት ሴኮንዶች ውብ ዓይኖቿን ዳኒ ላይ አንከባለለቻቸው። የጓደኛዋ ልጥቅ ስሜት በማግኔታዊ ኃይሉ እሷንም ነካካት። እናም የእናቷን ምክር አስታወሳት።

«ወንዶች ሁልጊዜም ሴቶችን ማናደድ፣ ማስለቀስ፣ ማሰቃየት፣ እንደሚወዱ እማዬ ነግራኛለች።» አለችው የተጣበቀ ከንፈሯን አላቅቃ።

«ለምንድን ነው?....» አላት ዳኒም በወላጆቹ ላይ ያየው ችግር የዘኒን ንግግር እንዲያምን አድርጎት።

«ወንዶች ጨካኞች ስለሆኑ ነዋ!.... ይህንንም እማዬ ነግራኛለች።»

ዳኒ በደመ ነፍስ የራሱም ወንድነት ተሰምቶት፣ በዘኒ ንግግር እንደተነካ ሁሉ፣ ስሜቱ ሲለዋወጥ በገፅታው ላይ ታየ። የሚሰማውንና የሚያየውን በአዕምሮው ውስጥ ፈጥኖ የሚቀርፀው ትንሹ ቆት፤ ዘኒ በየዋህነት የምትዘባርቀውን ሁሉ እየመዘገበ ነበር።

ዘኒ በዕድሜና በትምህርት ክፍል ብትበልጠውም ቅሉ በብልጠት ዳኒ ላይ አትደርስም። እሱ በተፈጥሮ ንቁ ብልህና ፈጣን ነው። እንደታናሿ እያየችው ልትንከባከበው ስትሞክር በሆዱ ይስቅባታል። እጁን ይዛ የመኪና መንገድ ልታሻግረው ስትል በትምክህት እጁን መንጭቆ ያስለቅቃታል። ታናሽነቱን አምኖ መቀበል አይፈልግም። የዋህዋ ዘኒ ማኩረፍ አታውቅም መቆጣት አታውቅ፣ መናደድ፣ አታውቅ....... እንዲያው ብቻ ነገሮቹን ሁሉ በዝርጉ የምታይ ልጅ ናት። የዋህነቷ ከልጅት ውበትዋ ጋር ተደምሮ ዓይን የምትስብ ትንሽዬ ፅጌረዳ አድርጓታል። አንዳንድ አስተማሪዎች ‹ትንሿ ርግብ› በሚል ስያሜ ይጠሯታል።

ይሁን እንጂ እናትዋ በልጅነት አዕምሮዋ የቀረፀችባት ነገር አብሮአት አድጓል። ዘኒ አባትዋን አታውቅም። የጎረቤት ልጆች ስለ አባቶቻቸው ሲያወሩ ሰምታ፤ እሷም እናቷን ስለ አባቷ በምትጠይቅበት ጊዜ፤ ወይዘሮ ፀሐይ የምትነግራት ስለ ወንዶች መጥፎነት ጨካኝነትና በሴቶች ላይ ስላላቸው ያልተቃና አመለካከት ነበር። ዘኒ ጭራሹንም ከአባት መፈጠሯን እንዳታውቅ በራሷ ስም ነው የምታስጠራት - ዘነበች ፀሐይ።

ክብረንጽሕናዋን ገስሶ ከተሻሚዎቹ መሐል መንጥቆ ወስዶ የወጣትነት ወበቷን አርግፎ ዘነበችን አሳቅፎአት በከዳት ባሏ ሳቢያ ፀሐይ ሁሉንም ወንዶች ትጠላለች። ባልነቱም ቢሆን ከስድስት ወር አላለፈም ነበር። አዲስ አበባ የሦስት ልጆቹን እናት አስቀምጦ ለሁለት ዓመት የሥራ ግዳጅ ወደ ባህር ዳር በሄደችበት ጊዜ በፀሐይ ድንገተኛ ፍቅር ታውሮ ባለ ትዳር መሆኑን ደብቆ አከታልቦ አገባት። ቤተሰቦቿም ችግረኞች ስለ ነበሩ ለአቅመ ሔዋን የደረሰች ልጃቸው ሌላ ችግር ሳታስከትልባቸው አግብታ ከአጠገባቸው እንድትሔድ ይፈልጉ ነበር። «ከባልም ባል» አዲስ አበባ ወንድ በማግኘቷ ደስ አላቸው። ፀሐይም በአፍላ ፍቅር ስለታወረች ሰለሰውየው የጀርባ ታሪክ ለማጠያየቅ ፋታ አላገኘችም። አጅሬ የተመደበበትን

የግዳጅ ጊዜ ሲጨርስ ሰበብ አስባብ ፈልጎ ከፀሐይ ጋር ተጣልቶ አፍላ ፍቅሯን እንኳን አያስጨርስ ወደ አዲስ አበባ ተመልሶ የሦስት ልጆቹ እናት ቤት ተከተተ። ፀሐይ ተከትላው ሄዶ አድራሻውን አጠያይቃ ደረሰችበት። ማዘጋጃ ቤት የሚያቅለት ሕጋዊ ሚስትና ልጆች እንዳሉት ተናግሮ እሷን ከዳት። ቅርበቱ ቀርቶ በርቀትና በሚስጥር ሊረዳት እንኳ ፈቃደኛ ያለመሆኑን በግልጽ ነገራት። በህግ ፊት ልትሞግተው ሞክራ አቅም አታች። ሰውየው የገጡን ጊዜያዊ ጋብቻ ያከናወነው በጣም ዘዴ በተሞላበት ሁኔታ ስለነበር ለምስክርነትም ሆነ ለፍርድ የሚያበቃ በጽሁፍ የሰፈረ ነገር ጠፋ። ፀሐይ አከ እንትፍ ብላ ጥላቻዋን አሳይታ፣ ነገሩን ከመተው ሌላ ምርጫ አልነበራትም። - አንጀቷ እያረረ ተወችው።

ያን ጊዜ ዘነበችን የአራት ወር እርጉዝ ነበረች። ወደ ቤተሰቦቿ ተመልሳ ጥገኛ መሆን አልፈገችም። አዲስ አበባ ውስጥ ወድንሟ ኤርሚያስ ዘለቀ መኖሩን ብታውቅም በዚያ በሽንፈት ሰዓት ልትጠጋው አልፈለገችም። ከአንድ እናት ባለመወለዳቸውና በአንድ ላይ ባለማደጋቸው ቅርበቱና ፍቅሩ አልነበራቸውም። በወሬ ካልሆነ በስተቀር በዓይነ - ሥጋ የተያዩበት ዘመንም ርቋል። መልከ - መልካምነቷ ለቡና ቤት ሙያ ጋበዛት። እርግዝናዋ እስኪያስታውቅ ድረስ ከአንድ ቡና ቤት ውጽጥ ሰራች። ሆድዋ ዘነበችን አርጎዝ ወደ ፊት ሲገፋ አዕምሮዋም በበኩሉ ለወደፊቱ እንደሚጠቅማት የተረዳችው የቡና ቤት ባለቤትም ፀሐይን እንደዘመድ አዋልዳ አረሰቻት። አዲሷ ህጻን ዘነበች ፀሐይ አባት - አልባ ሆና ወደዚህ ዓለም መጣች።

ከመቆየት ጋር ሕይወት የራሷን መፍጨርጨሪያ መንገድ ቀየሰች። የፀሐይ ውበት ብዙዎቹን ወንዶች ሳበ። እሷ ግን በውስጧ ከፉዎችና የማይረቡ ፍጥረቶች አድርጋ በመውሰድ፤ ላይ ላዩን ብቻ እያጫወተች ገንዘባቸውን መጋጥ ጀመረች። ዕድል አንዱን የከተማ ቱጃር አምጥቶ በወበቷ አከነፈው። አንድ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ከእግሯ በታች ዋለ። እናም በስሟ ቡና ቤት ከፍቶላት ነጻነቷን አወጀላት። እንደ ሩቅ ውሽማ ብቅ ጥልቅ እያለ፤ እንደ አሽከር እየታዘዘ እስካሁን አብረው ናቸው። ሁለት የጭነት መኪናዎች ስላሉት ፍቅሩን በገንዘቡ ይገልጻል። ይህም ሰው ቢሆን ባለትዳርና የብዙ ማቴዎች አባት ነው።

ከዚህ ሁሉ ትርዒት በኋላ ነበር ኤርምያስና እህቱ በወሬ ወሬ ተፈላልገው የተገናኙት። በታላቅነቱ ገስፆ የጀመረችውን ሙያ አስትቶ ከእሱ ጋር እንድትኖር ለማድረግ ቢሞክር አልተሳካለትም። በአጭር ጊዜ ውስጥ ስለተደራጀች ወደ ኋላ ተመልሳ የወንድም ጥገኛ ሆና እጆችዋንና እግሮቿን ሰብስባ የምትቀመጥ ሴት አልሆነችም።ኤርምያስም ቢሆን በትምክህትና በአጉል ጉራ የተወጣጠረ ሰው ስላልነበረ ምርጫዋን ፈቀደላት። ህይወት ራሱና ላለመጣል ከምትቀይሳቸው አቅጣጫዎች በአንዱ ውስጥ ማለፍ የግድ ነው። ትንሿ ዘኒ ግን ቡና ቤት ውስጥ ተኮትኩታ እንድታድግ አልፈገም። በግድም ሆነ በውና ከእናቷ እጅ ቀምቶ እያስተማረ ያሳድጋት ጀመር። በቤቱ ውስጥ የየዋህዋ ርግብ ትንፋሽ መግባሩ ለእሱም ቢሆን ወንደላጤነቱን ሳያስረሳው አልቀረም። ሚስት የማግባት ፍላጎት ስለሌለው ብቸኛ ነው። ሆኖም የልጅ ፍቅር ስላለው የእህቱን ልጅ አቅፎ ሲያጫውት ይውላል።

ዘኒ ከአጠገቧ ብትርቅም የእናቷ ፍቅር አልተለያትም። መጫወቻ ወይም ልብስ ወይም ጣፋጭ ነገር ገዛት እየወሰደችላት ትጠይቃታለች። አሁን አሁን እያደገች ስትመጣ፣ ዘኒ ራሷ በአለፉ ገደም እናቷ ቡና ቤት ድረስ እየሄደች ትጠይቃታለች። እናትዋም ልጅዋን ባገኘች ቁጥር ፍቅሯን ሙሉ በሙሉ ወደእሷ ያስቀረች እየመሰላት ስለ ወንዶች መጥፎነት መስበክ ልማድ አድርጋዋለች። የአባቱና ከኃዲነት፣ በአጠቃላይም የወንዶችን ጉረኝነት ስራዬ ብላ ጭንና ጭኗ መሐል አስገብታ ፀጉሯን እያሻሸችላት ትነግራታለች። ተፅዕኖውም የዋዛ አልሆነም። ቀስ - በቀስ በዘኒ አዕምሮ ውስጥ እየተቀረፀ ሄዷል።

«ዳኒ......አንተም ስታድግ እንደ ሌሎቹ ወንዶች ጨካኝ ትሆናለህ?»

ዘኒ ለጥቂት ሴኮንዶች ያህል የእናቷን ምክር ስታሰላስል ቆይታ ከውስጥ የመነጨ ጥያቄዋን ወደ ዳንኤል ሰነዘረች።

ዳኒ አሁንም የተቋጠረ ግንባሩን አልፈታም። ሀሳቡ እዚያው ቤተሰቦቹ ፀብ ላይ እንዳተኮረ ነው። ዘኒን በማዳመጥ ፋንታ እሱ የሚነግራትን ሲያሰላስል ነው የቆየው።

«አሁን እኮ ፅግዬና ወንዴ አብረው አይተኙም።» አላት እንደ ገና ትክዝ ብሎ።

«ታዲያስ?.....ለየብቻቸው?»

«አዎ! ወንዴ አዲስ ሚስት እንደሚያመጣ ካወቀች ጀምሮ ፅግዬ እኛ መኝታ ክፍል ውስጥ አልጋ ዘርግታ ለብቻዋ ነው የምትተኛው፡፡»

«አየህ፣ ጥፋተኛው እኮ ጋሽ ወንዳፍራሽ ነው፡፡ እሱ ሌላ ሚስት ባይፈልግ ኖሮ እትዬ ፅጌ ብቻቸውን አትተኛም ነበር፡፡» አለችው ዘኒ የማፅናናት ቅላፄ ባዘለ ድምፅ፡፡

«አዎ ልክ ነሽ፤ ወንዴ ነው ፅግዬን ያናደዳት፡፡» አለና ሳይስበው ጥርሱን ነከሰ፡፡

«......በቃ አሁን ና፤ ወደ ክፍል እንግባ፡፡ እረፍትም እያለቀ ነው፡፡»

ተማሪዎች ወደ የክፍላቸው እየተሯሯጡ ሴመለሱ ዘኒም በማፅናናት ዓይነት የዳኒን ክንድ ደገፍ አድርጋ ወደ ክፍሉ ወሰደችው፡፡

ኤርምያስ ከአራት ወራት በፊት የጀመራትን የሴት ሥዕል እየኳኳለ አቃቂር ሲያወጣላት ድንገት የክፍሉ በር ተንኳኳ....

«ኤርሚ!.....ክፈት፡፡ ምሳ ሰዓት ደርሷል፡፡»

ዘኒ መሆኗን ወዲያው አወቀ፡፡ - ከመቼው!? አለ ራሱ ለራሱ፣ የሰዓቱ አከናነፍ አስገርሞት፡፡ ጠዋት ዘኒ ወደ ትምህርት ቤት ስትሔድ ነበር እሱም ወደ ሥዕል ክፍል የገባው፡፡ በህብረ ......ቀለማት ውህደት እየተመራመረ፤ በምናቡ የፈጠራትን ሴት ማስያዝ የሚፈልግወን ውስጣዊና ውጫዊ መልክ ሲያወጣና ሲያወርድ አራት ሰዓት ሙሉ ቆየ፡፡ ለራሱ ግን ሠላሳ ደቂቃ እንኳ የቆየ አልመሰለው፡፡

በሩን ሲከፍትላት ዘኒ አንዳች ነገር ልትነግረው እንደቸኮለች ዓይነት ወደ ሥዕል ክፍሉ እየገባች ዓይኖቿን ሽቅብ ስታቁለጨልጭ ሽፋሽፍቶቿም ይረገብገቡ ጀመር፡፡ ይሁንና ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ሌላ ምናብ ውስጥ የቆየው የኤርምያስ አዕምሮ የዘነበችን ስሜት ፈጥኖ ማጤን አልቻለም፡፡ እንደ ወትሮው ጉንጭዋን ሳም አድርጎ ትከሻዋ ላይ ያንጠለጠለችዋን የደብተር መያዣ ባለማንገቻ ቦርሳ እያወረደላ፤ «ተማሪ ዘኒ ፤ እንኳን ደህና መጣሽ ዛሬ ጥሩ ምሳ ሳይዘጋጅልን አይቀርም፡፡.......» አለና የቆጥ የባጡን ቀበጣጠረላት፡፡

የዋህዋ ርግብ ከውጭ አስባ የመጣችውን ሳትናገር የሴትየዋ ስዕል ዓይኖቿን ስለሳበው፤ ሐሳቧ ወደ ስዕሉ ዘለለ፡፡

«ኤርሚ......ይቺን ሴትዮ መቼ ነው ልብስ የምታለብሳት?» አለችው በተወጠረው የስዕል ሸራ ላይ እርቃኗን የተጋለለችውን የሴት ምስል አትኩራ እየተመለከተች፡፡ ዘኔ የሴትየዋ ስዕል ከተጀመረ ጀምሮ፤ አራት ወር ሙሉ፤ ስታያት ያው እርቃኗን እንደተሳለች ነው፡፡ ቆንጆ ልብስ ለብሳና አምራ የምታይበት ጊዜ ናፍቋታል፡፡ የኤርምያስ ጭንቀት ደግሞ የሴትዮዋን ባህሪይ ከውስጥ ለመቅረፅ እንጂ የውጪያዊውን ጌጧና ልብሷ ብዙም አላሳሰበውም፤ አላስቸኮለውም፡፡ ሐፍረተ - ሥጋዋን ለመሸፈን ያህል ብቻ ትንሽ ጨርቅ መሳይ ነገር ጭኗ ላይ ጣል አድርጎበታል፡፡

«ልብስ ከመልበሷ በፊት መስተካከል የሚገባው ውስጣዊ ባህሪይ አለ፡፡ ባህሪዋ በደንብ ተስተካክሎ ሳይቀረፅ ቀሚስ ከለበሰች ነገር ተበላሸ ማለት ነው፡፡ የማስባት አዲስነቷ ቀርቶ ለብዙ ዘመናት በጌጥ እየተሸቀረቀሩና የቀሚሳቸውን እየነሰነሱ እንዳለፉት ሴቶች ትሆንብኛለች፡፡ አየሽ ዘኒ ልብስ ከሐሩርና ከቁር እምከላከያ መሆኑ ቀርቶ ውስጣዊ ማንነታችንን መደበቂያ (መሸፈኛያ) እየሆነ ነው፡፡ ውስጣዊ ማንነታችን ከመጀመሪያው በደንብ ቢቀረፅ ግን ኋላ ሽፋን አያስፈልገውም ነበር፡፡»

የኤርምያስ ንግግር ጥልቀት ለዚኒ ሊገባት አልቻለም፡፡ እሱም ገብቶበት የቆየውን ተመስጦ እንዲነጋገር ገፋፋው እንጂ ይህች ትንሽ ፍጥረት ፍልስፍናው ይገባታል ብሎ አልነበረም፡፡

«በቃ....ልብስ ሳትለብስ ብዙ ትቆያለች ማለት ነው?» አለችው፤ ትኩር ብላ ዓይን ዓይኑን ስታየው ከቆየች በኋላ፤ በተደናገረ ስሜት፡፡

«አዎ ትቆያለች፡፡ ልብስ የመጨረሻው ደረጃ ነው፡፡ በዚያ ላይ ደግሞ ሁልጊዜ ቤት ውስጥ ስለሆነች አይበርዳትም፡፡ አታስቢ፡፡» አለና ቀላለደ፡፡

«.....ግን ቆንጆ የምትሆነው ልብስ ብትለብስ ነበር፡፡» አለችና ዘኒ ወደ ሳሎን ለመሄድ ከፊት ከፊት ቀድማ ወጣች፡፡ ኤርምያስም ሐሳቡ ወደ ስዕሉ ላይ ቀርቶ በድን እግሩን እየጎተተ ተከተላት፡፡

ሠራተኛዋ ከሳሎኑ ጠረጴዛ ላይ ምሳ አቅርባ እየጠበቀቻቸው ነበር።

ሁለቱም ተሰየሙ።

ዘኒ ረሀቧን ለማስታገስ ጎረስ ጎረስ ካደረገች በኋላ፤ ከትምህርት ቤት ይዛው የመጣችውን ሀሳብ እንደገና ትዝ አላት።

«ኤርሚ የዳኒ እናት እና አባት እንደ ተጣሉ ሰምተሃል?» አለችው ምግቡን አቋርጣ።

«አልሰማሁም። ተጣሉ እንዴ?» አላት ብዙም ባልተጨነቀ አነጋገር በባልና ሚስት መሐል ሊከሰት የሚችል ጊዜያዊ ግጭት አድርጎ ነው የወሰደው።

«ተጣሉ እኮ። ዛሬ ጠዋት ዳኒ ነገረኝ። ጋሽ ወንዳፍራሽ እትዬ ፅጌረዳን ፈትቶ ሮዛ የምትባል አዲስ ሚስት ማግባት ይፈጋል።.......»

ኤርምያስ ይሄኔ ደንገጥ አለ። ሮዛ የሚለውን ስም ሲሰማ አንዳች ነገር ስሜቱን ጠቅ አደረገው። ወንዳፍራሽ ከሮዛ ጋር የተዋወቁ ሰሞን የግንኙነታቸው ሁኔታ ጨንቆት ጉዳዩን ለኤርምያስ አጫውቶት ነበር። ኤርምያስ ስለ ፍቅር ስለ ጋብቻና፣ ስለ ወሲብ የራሱ የሆነ አመለካከት አለው።.... ይሁንና ኅብረተባችን በነዚህ ሦስት ጥምር ነገሮች ላይ ያለውን አቋም ስለሚያውቅ የወንዳፍራሽን አድራጎ አልደገፈለትም። ፅጌረዳን ሁኔታው ምን ያህል እንደሚያበሳጫት ገምቶ ድርጊቱን አወገዘበት። ከዚያ በኋላ ወንዳፍራሽ ነገሩን ሁሉ ደብቆት በሚስጥር ያከናውን ስለ ነበር የግንኙነታችውን ዕድገትም ሆነ መቀጨት መከታተል አልቻለም። አሁን ከዘኒ የሮዛን ስም መስማቱ ግን በጉዳዩ ላይ እንደገና እንዲነቃ አደረገው። ፀቡም ከረር ያለ እንደሚሆን ገመተ።

«አንቺ.......እንዴት አወቅሽ ዘንዬ?»

«ዳኒ ነገረኝ እያልኩህ!»

«ዳኒስ እንዴት አወቀ?»

«እንዴዬ....ልጃቸው አይደለም እንዴ?! እንዲያውም ተጣልተው ሲደባደቡ ሲሉ ዳኒና ሰብሊ ሲያለቅሱ ጊዜ ነው የተውት። እኔም እኮ እናቴና አባቴ ሲጣሉ ተወልጆጂ ቢሆን ኖሮ ማወቅ አያቅተኝም ነበር።

«ወቸ ጉድ!.....አለ ኤርምያስ፤ ዓይኑን ዘኒ ላይ ተክሎ፤ በሀሳቡ ርቆ እየሄደ።

ብቻ ጋብቻዎች በገንዘብና በጭንቀት የተሞሉ መሆናቸውን ያውቃል። የዩኒቨርሲቲ ተማሪ በነበረበት ጊዜ፣ የስነ ልቡና ኮርስ ሲከታተል ባደረገው አካባቢያዊ ጥናት፤ ብዙ ሴቶች ውስጥ ገብቶ የሚስቶችን እሮሮና የባሎችን ብሶ አዳምጧል። ይሁን እንጂ፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ፤ የፅጌረዳና የወንዳፍራሽ ትዳር ሙሉ ፍቅርና መተሳሰብ ሲታይበት የቆየ በመሆኑ፤ ድንገተኛ ለውጡ አስደነገጠው። ስሜቱ የኋሊት ተጉዞ ወንዳፍራሽና ፅጌረዳ ፍርቅ ሲጀምሩ የነበራቸው ሁኔታ ብልጭ ድርግም እያለ በሀሳቡ ታየው። ለወንዳፍራሽ በነበረው የቅርብ ጓደኝነት ሳቢያ ፍቅሩን «ሀ» በልው ጀምረው ለጋብቻ እስከበቁ ድረስ ከጎናቸው ነበር። ለሠርጋቸውም ቢሆን ኤርምያስ የወንዳፍራሽ አንደኛ ሚዜ ሆኖ ነበር። ያኔ በወንዳፍራሽና በፅጌረዳ መሐል ንፋስ የማይገባበት ቅልጥ ያለ ፍቅር አይቷል። ‹ያ ሁሉ አለፈና አሁን ለፀብ ደረሱ?› እያለ በሀሳቡ ካወጣ ካወረደ በኋላ በረጅሙ ተነፈሰ።

«......ብሉ እንጂ ምነው?» አለች ሠራተኛዋ ከጓዳ ወጣ - ኤርምያስ እጁን ሰብስቦ መቀመጡን ካጤነች በኋል።

«በላሁ፤ በቃኝ።..... ዘኒ ብይ እንጂ። አለ አፉን በእጁ እየጠራረገ።

«በቃኝ፤ ጠገብኩ።» አለች ዘኒም በበኩሏ።

ከልጆች ጋር ተሻምታ ለመብላት ባለመታደሏ የዘኒ አበላል እንደ ልጅነቷ አይደለም። ወስፋቷ ትንሽ ስትቀምስ ይዘጋል። ከኤርምያስ ጋር ገበታ የቀረበ ሰው ምን ጊዜም ቢሆን ጥሩ ወስፋትም አይኖረውም። እሱ ለኮፍ ለኮፍ አድርጎ ሲተው የሌላውንም የመብላት ፍላጎት ይዘጋል። አዲስ የቤት ሠራተኞች በገቡ ቁጥር ያቀረቡለት ምግብ ያልጣፈጠላቸው እየመሰላቸው መሸማቀቃቸው አይቀርም። እየቆዩ ሲሄዱ ይለምዱታል። ተፈጥሮው መሆኑ ይገባቸዋል ይተውታል። የኪነ ጥበብ ፍቅር ነው ሆዱን የዘጋው። በስዕል ለመግለጽ የሚያስበውን አንጥሮ ማውጣት

ሲያቅተው ይናደዳል፣ ይበሳጫል። ሲሳካለትና ሀሳቡን አንጥሮ ማውጥት በስዕሉ ሲገልፅ ደግሞ ከመጠን ያለፈ ይረካል። ንዴቱም ሆነ ርካታው፤ ወስፋቱን የሚገዙ ነገሮች ናቸው። ንዴቱ አያስረበውም፤ ርካታው ደግሞ ሳይበላ ያጠግበዋል። - ለመሄድ ያህል ብቻ ይቀምሳል።

«እትዬ ፅጌረዳና ጋሼ ወንዳፍራሽ ከተጣሉ ጀምሮ አብረው እንደማይተኙም ዳኒ ነገረኝ።» አለችው ዘኒ፤ ገበታው ተነስቶ እጃቸውን ከተጣጠቡ በኋላ ወንበሩ ላይ ተስተካክላ እየተቀመጠች።

«....ለየብቻቸው ይተኙ ጀመር?»

«አዎ እትዬ ፅጌረዳ እነ ዳኒ ክፍል ነው የምትተኛው።»

ኤርምያስ የፀቡን ጥንካሬ ገምቶ አስቸኳይ መፍትሔ ለመፈልግ ልቡ ተነሳሳ። ወንዳፍራሽን ወይም ፅጌረዳን ፈልጎ ነገሩን በደንብ ለመረዳት ቸኮለ። ነገሩ እነ ዳኒ ዘኒ አዕምሮ ድረስ መድረሱ በአንድ በኩል ሲያናድደው፣ በሌላ በኩል ደግሞ ባልና ሚስቱ ቀድሞ ለልጆቻቸው ምን ያህል ጥንቁቅ እንደ ነበሩ ሰልሚያውቅ፣ አሁን ልጆቹ ጆሮ ያደረሱት ችግሩ ከአቅማቸው በላይ ቢሆን ነው የሚል ግምት ወሰደ።

«ኤርሚ.....ግን ለምንድ ነው ወንዶች ሁልጊዜ በሴቶች ላይ እንደዚህ ጨካኝ የሚሆኑት?»

የዘኒ ድንገተኛ ጥያቄ ኤርሚያስን ሌላ ድንጋጤ ውስጥ ከተተው። እንዲህ አይነቱን አስተሳሰብ በዝኒ አዕምሮ ውስጥ የቀረፀችው እናቷ መሆኗን ያውቃል። ብዙ ጊዜ ሊያስተባብላት ቢሞክርም፤ የልጅነት አዕምሮዋ የቀረፀውን ነገር በቀላሉ መቅረፍ አልተቻለም። በዚህ ጉዳይ ኤርሚያስ በሽቆ ብዙ ጊዜ ከዘኒ እናት ጋር ተጣልቷል። አሁንም እንደገና ብልጭ አለበት።

«ለካ እኔ የምመክርሽን አትሰሚኝም፤ ዘኒ?!» አላት በመከፋት ዓይነት ራሱን እየነቀነቀ፡

«ሁል ጊዜም እስማሃለሁ እኮ....... ኤርሚ»

«ታዲያ ለምን ትረሺዋለሽ? እናትሽ ወንዶችን የምታጥላላው በራሷ ላይ በደረሰባት ምክንያት ነው እንጂ ወንዶች በተፈጥሮ ጨካኝ ያለ መሆናቸውን ስንት ቀን ነግሬሽ የለ?!»

«አሁንስ እትዬ ፅጌረዳን ያናደዳት ጋሼ ወንዳፍራሽ ጨካኝ ቢሆን አይደል?»

«ይሄም ደግሞ ሌላ አጋጣሚ ነው እኒ በደፈናው የወንዶችን ጭካኔ የሚያሳይ አይደለም። አንቺ ሳትሰሚ ቀርተሽ ነው እንጂ ወንዶችን ያሳበዱና ለሚት የዳረጉ ጨካኝ ሴቶችም ሞልተዋል።.....»

ዘኒ ግራ በተጋባት ስሜት ዝም አለች።

«....እና አየሽ በደፈናው ወንድ መጥፎ ነው ሴት ጥሩ ነች፤ ወይም ደግሞ ሴት መጥፎ ነች ወንድ ጥሩ ነው፤ የሚባል ነገር የለም። ሁሉም እንከን አያጣም። ፍጹም አስተዋይና ልበ ሙሉ ሴት «ሔዋን 1999) ብቻ ናት» አላት ከአዋቂ ጋር እንዲያውራ ሁሉ በተመስጦ።

«ሔዋን 1999 ማን ናት?»

«ያቺ የጀመርኳት ስዕል ናታ። እስከዛሬ ስሟን አላወቅሽም ነበር እኔ?»

«አሃ! ያቺ ሴትዮ?......ታዲያ ሰርተህ ሳትጨርሳት ነው እንዴ ስም የተጠሃት። ገና መቼ ልብስ አለበስካት?!»

«ስሟን ተመርኩዤ ነው እንጂ የምሥራት! ስሟ ነው ወደ ባሕሪዋ የሚመራኝ.......» አላት አሁንም በተመስጦ።

«.......ግን ምን ማለት ነው?.......እንደዚህ ዓይነት ስም ሰምቼ አላውቅም።»

«ሔዋን 1999....አዎ አዲስ ዓይነት ስም ነው። ምክንያቱም ሴትየዋ አዲስ ዓይነት ሴት ናት።»

«እንዴት አዲስ?»

«በዘመናችን ከምናያቸው ሴቶች የተለየች ማለት ነዋ!»

«አሃ!......» አለች ዘኒ አሁንም ግርታ በተሞላበት መንፈስ «እሺ ቆይ፤ ሔዋን የሴትየዋ ስም ይሁን «1999» ደግሞ የአባቷ ስም ሊሆን ነው?»

«አይደለም ዘኒ፤ አየሽ ሔዋን የሴትየዋ ስም ሲሆ 1999 ደግሞ የምትፈጠርበት አመተ ምህረት ነው።»

ዘኒ ግርታው በዝቶባት ፍዝዝ ብላ ዓይን ዓይኑን ታየው ጀመር። ኤርሚያስ ከተመስጦው ወጣ ብሎ ወደ ማኅበራዊ እሱነቱ ሲመለስ በሃሰቡ - ይህችን ሕጻን አሁን ምን አድርጊ ብዬ ነው የማደርቃት? አለና ፀጉሯን አሽት አሽት አድርጎ «ዘኒ፤ የትምህርት ቤት ሰዓት እስኪደርስ ድረስ አልጋሽ ላይ ትንሽ ዓረፍ ብትይ ይሻላ።» አላት።

«አይ፤ ከጌጤ ጋር እጫወታለሁ።» ብላው ሠራተኛዋ ወዳለችበት ጉዳ ገባች።

ኤርሚያስ ሰዓቱን ተመለከተ። ሰባት ሰዓት ተኩል ሆኖ ነበር። ለወትሮው ቢሆን ቡና ጠጥቶ ወይም ትንሽ አረፍ ብሎ ወደ ሥዕል ክፍሉ ይመልስ ነበር። አሁን ግን የወንዳፍራሽና የፅጌረዳ አዕምሮው ውስጥ ስለ ገባ ሀሳቡ ተረጋግቶ ወደ ስዕሉ ሊመለስለት አልቻለም። ጫካ የመሰለ ጺሙን በጣቶቹ እየቆፈረ ምን ማድረግ እንደሚችል ማሰላሰል ጀመረ። ምን ጊዜም ሀሳብ ሲገባው ጺሙን መቆፈር ይቀናዋል። እና ትናንሽ ውብ ዓይኖቹ ደግሞ ቅርብ የሚያዩ መስለው በጣም ርቀው ይሄዳሉ። ሰልካካ ቀይ፣ ፊቱን የዋጠውን ጺሙን መላጨት አይወድም። - ግርማ ሞገሱ ከላዩ ላይ የሚገፈፍ ይመስለዋል። ለአለባበሱ ብዙም ደንታ የለውም - ለንጽህናው ግን ይጨነቃል። የሚለብሳቸው ሰፋፊ ልብሶች ረጅም ቀጭን ቁመናው ላይ ተሰቀሉ እንጂ፣ የተጠለቁ አይመስሉም። ከሰውነቱ ውስጥ ጎልቶ የሚታየው ፊቱን የከበበው ጺሙ ብቻ ነው።

ትንሽ ሲያስብ ከቆየ በኋላ ወደ ወንዳፍራሽ ቢሮ ለመደወል ወደ ስልኩ ተጠግቶ እጀታውን አነሳ።.....

ንቦች በፅጌረዳ ዙሪአይ አንዣበቡ።

መቼም ወሬ አይደበቅም። በተለይ የወንድና የሴት ጉዳይ የራሱ የሆነ ፈጣን ማስተላለፊያ መንገድ ያለው ነው የሚመስለው። ፅጌረዳ ከባሏ ጋር ተጋጭታ በቅናት መንገብገቧ ከአብዛኞቹ የመስሪያ ቤት ባልደረቦቿ ጆሮ ደርሶ ነበር። ወሬውን ለማራባት እንኳ ትውሲት ብቻ ትበቃለች። የፅጌረዳ ገጽታ መለዋወጥ ደግሞ የብዙዎቹን ዓይን ስቦ ነበር። አንዳንዴ በሀሳብ ትመሰጥና የምታውቃቸውን ሰዎች ስላምታ ሳትሰጣቸው ታልፋለች፤ ወይም ደግሞ ፊቷን እንዳጨፈገገች አንገቷን ሰበር አርጋ ትሄዳለች። የራሷ የሆነ ፈገግታ ከገፅዋ ላይ ከጠፋ ቆይቷል። «ወይዘሮ ፅጌረዳ ሰሞኑን ምን ሆናለች?» የማይል ሰው አልነበረም።

ቀድሞ በልባቸው የከጀሏት በዓይናቸው ቀሚሷን የገለቧት በህልማቸው የተዳሯት ሁሉ፤ አሁን አጥር ለመዝለል መልካም አጋጣሚ እንዳገኙ አድርገው ገመቱ። እናም ፅጌረዳን ለማጥመድ መረባቸውን ዘረጉ።

«አቶ ክብረት.....» ስትል ጀመረች ትውሲት፤ «ሁልጊዜ ስለ አንቺ ይጠይቁኛል። ባገኙኝ ቁጥር ከአፋቸው ጠፍተሽ አታውቂም።»

የአቶ ክብረት ስም ሲነሣ ፅጌረዳ ደንገጥ አለች። የመስሪያ ቤቱ የአንድ መምሪያ ሓላፊ መሆናቸውን ታውቃለች። በዕድሜም በአገልግሎት ዘመንም ትልቅ ሰው ናቸው። በተረፈ ስለግል ሕይወታቸው ብዙ የምታውቀው ነገር የለም። የተዘበራረቀ ወሬ ይወራባቸዋል።.......የተጨበጠ ወይም ከእሳቸው አፍ የተሰማ ምንም ነገር ግን የለም።

«አቶ ክብረትን....... አወቅሻቸው?» አለቻት ትውሲት፤ እንደገና የፅጌረዳን ዝምታ ለመስበር።

«አዎ፤ አወቅኳቸው።......»

«የሚገርምሽ ነገር ስለ አንቺ ሲያነሱ ፍዝዝ፣ ቅዝዝ፣ በልው ነው የሚያወሩት። ‹ያቺን የመሠለች ሴት ወይዘሮ የሚያስቀይም ወንድ ባለጌ ነው› ይሉኛል፤ ያንቺን ነገር ባነሱልኝ ቁጥር።»

አቶ ክብረት መረባቸውን በትውሲት በኩል እንደዘረጉባት ፅጌረዳ ጠረጠረች። የሚያገኛቸው የቅርብ ሥራ ወይ የአካባቢ ቅርበት ስላልነበራቸው

አጥብቆ ጥያቄአቸውን እንደተራ ሐዘኔታ። ልትወስደው አልቻለችም። አዝማሚያው አዲስ ነገር አልሆነባትም። የያዘ ይዟቸው ነው እንጂ ጥንቱንም ቢሆን ፈላጊዎቿ ብዙ ናቸው። አንዳንዶቹ ሰሞኑን የቆየ ምኞታቸውን ገሀድ ሲያወጥቱ ታያለች። ሁኔታው በመጠኑም ቢሆን ቤቷ ውስጥ አንገቷን ያነቃትን የቅናት ሲባጎ ሳያያላት አልቀረም።

«ምን ታረጊዋለች!» አለች ፅጌረዳ መልስ መስጠት ስላለባት ብቻ።

የፅጌረዳ መልስ ጨዋታውን ለማራዘም ባለመመቸቱ ትውሲት አሁንም አሁንም ሻይዋን ፉት እያለች ስታሰብ ቆየች። ፅጌረዳም በዝምታ ትጠጣ ጀመር። የመስሪያ ቤቱን ሰው ወሬና ዓይን ስለጠላች በእረፍት ሰዓት ሻይ ቤት በመሄድ ፋንታ ቢሮዋ እያስመጣች መጠጣት ከጀመረች ጥቂት ቀናት ሆነዋታል። በተለይ ባሏ ወንዳፍራሽ ውጭ ባደረ ማግስት ፣ መስሪያ ቤቱ ሻይ ቤት ውስጥ ሳታስበው ያሳየችው ድርጊት እያደረገ ያሳፍራት ጀመር። ወደ ኋላ መለስ ብላ ስታስበው አሁንም ይሸመቅቃታል።

ሠራተኛውን አቀራርባ የምታጨዋወተውና የምታቀላልደው ይህች የጠዋት የእረፍት ጊዜ ናት። ወንደላጤው ሴተላጠውም ባለትዳሩ ብድን ለይቶ ይተባበራል። ቀልዱ ሁሉ ወዝ አለው። ሌላው ቀርቶ የአቀማመጥ እንኳ ልዩነት ይፈጠራል። ወንደላጤውና ሴተላጤው በአንድ ወገን ለብቻ፤ ባለትዳሩና ባለትዳሯ በሌላ ወገን ይቀመጡና ፊት ለፊት ተፋጥጠው የቀልድ ርቅት መልቀቅ ነው።

ፅጌረዳ የዘወትር ምድቧ ከባለትዳሮቹ ነበር። ወንዳፍራሽ ውጭ አድሮ ጠዋቱስ ስልክ በደወለላት ዕለት ከትውሲት ጋር ወደ ሻይ ቤት ሲሄዱ አባላት ቀደም ብለው መቀመጫቸውን ይዘው አገኟቸው። ይሄን ትውሲት ከሴተላጢዎቹ ጎን ሄደውና ተቀመጠች። ፅጌረዳ ግን የወትሮው የባለትዳር ቦታዋን ጥላ፣ በአንድ ዳር በኩል ለብቻዋ ተቀመጠች።

«አንዳንዴ ምነው? የምን ማፈንገጥ ነው ፅግሽ?! በይ እዚያው ከባለትዳሮቹ ጋር ተቀመጭ።» አላት ከወንደላጤዎቹ አንዱ - ዘገየ ወርቃለማሁ። ተጫዋችና ቀልደኛ በመሆኑ በግቢው ውስጥ «ዘጌ» በሚባል የቁልምጫ ስም ነው የሚታወቀው። ሸርም ከፈለገ የዚያኑ ያህል ሸረኛ ነው።

«ቦታዬ እዚህ ለብቻዬ ይመስለኛል።......ዘጌ» አለችው ፅጌረዳ ኮስተር ብላ።

«እንዴት?......አፈነገጥሽ እንዴ።»

ዘጌ እንደ ልማዱ ሊቀልድ አፉን አሞጠሞጠ። ፅጌረዳ ግን በአንዳፍታ ሰውነቷ ሁሉ ልውጥውጥ አለ። አዕምሮዋ ውስጥ በባሏ ምክንያት የተፈጠረው ቁስል በቅፅፈት አመርቅዞ ናላዋን አዞረው።

«......አዎ! ቦታዬ እዚህ ነው።» አለቻቸው የተቀመጠችበትን ወንበር በሌባ ጣቷ እየቆረቆረች «......እንኔ ከሁላችሁም በኩል አይደለሁም። - ጋለሞታ ነኝ!...... የጋለሞታ መቀመጫ ደግሞ ለብቻው ነው።»

ሁሉም ተደናገጡ። ቀደም ብለው የወሬውን ጭምጭምታ የሰሙት ጉዳዩ ገባቸው። ሌሎቹም ቢሆኑ ስትናገር ኩምትርትር ያለ ገጽታዋንና ሁኔታዋን አይተው ቁስሏን ለመናገር አልተቸገሩም ለብዙ ጊዜ የሚያውቋት «ቅድስት ፅጌረዳ» ሳትሆን፤ እንግዳ ሰይጣን ነበር የመሰለቻቸው። የተናገረችውን ተናግራ ሻይ እንኳን ሳትጠጣ እየከነፈች ወደ ቢሮዋ ተመለሰች። የሻይ ቡድኑም ያን ዕለት በደንብ ስያጫወት እንደተደናገጠ ተበተነ ፡ ከዚያ በኋላ የፅጌረዳ ጉዳይ በየቢሮው መንሾካሾኪያ አርዕስት ሆነ።

ፅጌረዳ ብስጭቱ በረድ ብሎላት ወደ ራስዋ ስትመለስ ሻይ ቤቱ ውስጥ ያሳየችው ድርጊትና የተናገረቻቸው ቃላት ዘገነኗት። ነገር ግን «የፈሰሰ ውሃ አይታፈስም።» ከዚያ ወዲህ ሻይ ቤት መሄዱን እርምብላ ተወች።

ትውሲት የሻይ ቤቱ ጨዋታ እንዲያመጣት ባትፈልግም፤ ፅጌረዳን ብቻዋን ላለመጣላት አንዳንዴ አብራት ቢሮ ትጠጣለች። አሁን የጀመረችውን ዓይንነት ዓርዕስት የምታነሳባትም እንዲህ ዓይነቱን የቢሮ ውስጥ የሻይ ሰዓት ጠብቃ ነው።

«ደሞ'ኮ.....» አለች ትውሲት፤ ሻይዋን አጠናቅቃ ጠጥታ ብርጭቆውን ጠረጴዛ ላይ እያስቀመጠች፤ «አቶ ክብረት ያቹን ስም ሲያነሱልኝ እያቆላመጡ ነው። «እኔማ ቀደም ብላችሁ ቅርበት ያላችሁ መስሎኝም ነበር።»

ፅጌረዳ በአሉታ ራስዋን ነቀነቀች።

«......ነገሩን ማለቴ ነው እንጂ። እና ስለ አንቺ ሲያወሩልኝ እንዲያው ሁኔታቸውን ሳየው የራሳቸው ትዝታ ውስጥ የሚገቡ ነው የሚመስለኝ።......»

ፅጌረዳ በጥያቄ መልክ ቅንድቧን ሸበሸበች።

«.......በውነት እልሻለሁ፤ ፅግዬ።....እንዲያውም ትክዝ ይላሉ የወሬ ወሬ ስሰማ በጣም የሚወዷት ቆንጆ ሚስት ነበረቻቸው ይባላል። ወዳጅ መሳይ ጠላት መሐላቸው ገብቶ አጣላቸው። በጣም የሚዋደዱ ሰዎች ደግሞ ሲጣሉ ፀባቸው ይከርራል። አንዴ ከተጣሉ በኋላ እርቅ ቢባል ሁለቱም አሻፈረኝ አሉ። እና ጎጆአቸው እንደ ቀልድ ፈርሶ ቀረ። ሚስትየዋ የዛሬ ሁለት ዓመት እንደ ልጃገረድ በቬሎ አዲስ ባል አገባች። ያገባችውን ሰውዬ ብታይው ይገርምሻል። - ጭርጭር ያለ ሽማግሌ እኮ ነው። ሆኖም ገንዘብ አለው አሉ።.....»

«ልጆቻቸውስ?.....» ስትል ፅጌረዳ አቋረጠቻት፣ ነገሩ እሷንም እንደሚመለከት ዓይነት ትኩር ብላ።

«የማ?.....» አለች ትውሲት ፈጠራው ተደናግሮባት።

«የአቶ ክብረትና የሚስታቸው?»

«እ?!.....ደግነቱ ልጆች አልወለዱም ነበር።»

ፅጌረዳ ሌላም ጥያቄ ነበራት። ሳታስበው የአቶ ክብረት ታሪክ ሰባት። በመጠኑም ቢሆን ከእሷ ታሪክ ጋር ተመሳሳይነት እንደሚኖረው አድርጋ ገምታ ይሆናል። ስለ ሚስታቸው ሌላ ባል ማግባት ሰማች። አቶ ክብረትስ ሌላ ሚስት አግብተዋል ወይስ ብቻቸውን ነው የሚኖሩት? - ይህን መጠየቅ ፈልጋ ትውሲት የምትሰጠውን ትርጉም በመፍራት መልሳ ዋጠችው። ትውሲትም ይህን ጉዳይ በልብ መስቀያነት ያዘችው።

«......‹ነገሩ ነው እንጂ ጨቤ ሰው አይጎዳም› ይላል የሀገራችን ሰው ሲተርት። ትውሲት ጨዋታዋን አያይዛ ቀጠለች፣ «ባልና ሚስቱ መፋታታቸው ጥሩ አልነበረም ለማለት ያህል ነው እንጂ አሁንም ቢሆን አቶ ክብረት ቆንጆ ኑሮ ነው የሚኖሩት። ጥሩ ቤት፣ ጥሩ መኪና፣ አላቸው። ገንዘብም ቢሆን ከአብዮቱ በፊት ያጠራቀሙት

ብዙ ብር አላቸው ይባላል። የፊታቸው ቀለም የጠራ፣ ቁመናቸው ያማረ በመሆኑ አሁንም ቢሆን የሚፈልጓትን ሴት አያጡም። ሽበታቸው ራሱ የውበት ግርማ ሞገስ አለው።......»

ትውሲት ንግግሯን አቋርጣ የፅጌረዳን ሁኔታ ማጥናት ጀመረች። የውስጥ ስሜቷን ከፊትዋ ላይ ማንበብ የምትችል ይመስል ትክ ብላ ተመለከተቻት።

«ይገርማል!......» አለችና ፅጌረዳ በረዥሙ ተነፈሰች፡፡-----ያስገረማት የአቶ ክብረት ታሪክ ይሁን የትውሲት አቀራረብ ግልፅ አልነበረም።

«ምኑ?» ስትል ትውሲት አፋጠጠቻት።

«ሁሉ ነገር ነዋ!»....... ጽጌረዳም ነገሩን ድፍን አደረገችባት።

ትውሲት ተልዕኮዋን እንዴት አድርጋ ከግቡ እንደምታደርስ በሀሳብዋ ታውጠነጥን ጀመር። በአንድ ጊዜ ስለ አቶ ክብረት የሰጠችው ቅጥ ያጣ መግለጫ ለትዝብ የሚያበቃት መሆኑን አላጣችውም።

ነገር ግን ይዛ የተነሳችው ዓላማ ከትዝብት በላይ በመሆኑ አላፈረችበትም። ዋናው ነገር አቶ ክብረት እንደሚፈልጓት ፅጌረዳ እንዲገባት ነው። ይህን በጉራማይልኛም ይሁን በግልፅ አማርኛ ተናግራለች። አሁን የቀራት ፅጌረዳን ፈቃደኛ አድርጋ ለአቶ ክብረት ማቅረብ ነው። ይሄ ቢሳካላት!.....

«ያንንም ነገር እኮ ረሳነው.....» አለች ከሀሳብዋ መለስ ስትል።

«የቱን ነገር?» - ጽጌረዳ ጠየቀች።

«አንድ ምሽት እዚያ «ስርቆት አዳራሽ» እንሄዳለን ብለን አልነበር?!»

«አ! አይቀርም እንሄዳለን። ይሄን ሰሞን እሱም ሊያዘናጋኝ አስቦ፤ በጊዜ ቤቱ ስለሚገባ እኛ ብንሄድም ዋጋ አይኖረውም ብዬ ነው።»

ፅጌረዳ የባሏን የወንዳፍራሽን ስም መጥራት አሰጠልቷት «እሱ» ማለቷ ለትውሲት ትልቅ መረጃ ነበር። ባልና ሚስት ስማቸውን ትተው አንተ አንቺ ወይም

እሱ እሷ የሚባባሉት ምን ደረጃ ላይ ሲደርሱ እንደሆነ ጠንቅቃ ታውቃለች። - መረጃዋን ልብዋ ውስጥ ጽፋ ቅራኒ ማጠናከሪያ ቢጤ ለገሰቻት -

«....ሲያስመስል ነው እባክሽ። ትውሲት ምን አለች በይኝ!......ወንድ ልጅ አንዴ ልቡ ወደ ውጪ ከሄደ ወደ ቤቱ ይመለሳል ማለት ዘበት ነው።

ፅጌረዳ ማጠናከሪያውን በይሆናል ተቀብላ ዝም አለች። ትውሲትም የዓላማዋን መንገድ የምታሰላስልበትን ስልት በሀሳብዋ መንደፏን ቀጠለች።

ወንደላጤው ዘጌ፤ ትውሲትን ለብቻዋ አግኝቶ ለማነጋገር ብዙ ጊዜ አልወሰደበትም። አቶ ክብረት ቢሮ ብቅ ጥልቅ ስትል አይቷት የጠረጠረውን ጉዳይ ጠርጥሯል። እና በልቡ «ተቀደምኩ» ብሎ በሽቋል። ፅጌረዳ ላይ በርቀት መረባቸውን ከጣሉ መሐል ዘጌም አንዱ ነው። ምንም ቀልጣፋ ቢሆን ፅጌረዳን ለማውጣት መድፈረ አልቻለም። - አጠገቧ ሲደርስ ሁሉ ነገሩ ወደ ቀልድ ይለወጥበታል። እሷም እንደ ቀድሞ ግንኙነታቸው በቀልዱ ትዝናናለች። ስለዚህ ያለው አማራጭ ትውሲትን መሰላል ማድረግ መሆኑን ካሰበበት ሰንብቷል። እንዲሁ ዳር ዳር ሲል፤ መሰላሏ በሌላ ሰው ተያዘችበት።....

«ምነው እባክሽ?!.....» አላት ትውሲትን ቢሮው ውስጥ ለብቻዋ ቆልፎባት።

«ምነው?.....» አለችው ትውሲትም መልሳ - ሳትደናገጥ

«.....ስትፈለጊ መጥፋትሽሽ ነዋ!!»

«ሂድ፤ ጉረኛ......በቀን አስር ጊዜ አይደል እንዴ ግቢ ውስጥ የምንገናኘው።»

«እንደሱ ሳይሆን.....እንደዚህ ለብቻሽ አግኝቼ ላነጋግርሽ የምፈልገው ጉዳይ ነበረኝ።»

«ኡ - ሁ - ሁ!......» ይሄው አጠገብህ ነኝ እንግዲህ.....ንገረኛ»

ጉዳዩ አልገባትም። የገዘየን ንግግር መእንሻ ስትሰማ እሷኑ ለድሪያ የፈለጋት መስሏት፤ እያከላላች ከመቀመጫዋ ተነስታ እንደልሟ ቀሚሷን ነሰነሰችበት።

ወንድ ሲጠይቃት ልቧ ይኩራራል። ለሴትነቷ ትልቅ ግምት ትሰጠዋለች። በአለባበስም በአነጋገርም፤ በሰውነትም ቅርጽ አጠባበቅም መሥሪያ ቤቱ ውስጥ ጎላ ብላ ስለምትታይ ብዙ ወንዶች የከጅሏታል። ብዙዎችም በስርቆሽ አውጥተዋታል። ጊዜው ይርዘም እንጂ ዘገየም አንዴ ደርሳዋለች። - ትዲያ ግቢው ውስጥ አይሰሩ ስራ ሲሰራ ወንዱ ሁሉ የሚያነጣጥረው ወደ ዳሌዋ አካባቢ ነው እንጂ፤ ለቁም ነገር የሚያስባት የለ። አሁን አሁን «ሙጭጭ አለብኝ» የምትለው ሰው የመሥሪያ በቱ ኦዲተር ደጀኔ ነው። እውነትም ደጀኔ ወድዷታል። መስሪያ ቤቱ ውስጥ በዓይነ - ቁራኛ ነው የሚጠብቃት። ከዚያ ውጭ እግዜር ይወቀው! አጠገቡ ታክብረዋለች። ዘወር ብላ ከጓደኞቿ ጋር ስትልጠው ግን ለጉድ ነው። «አንድ ቀን ‹ትስማወርቄን ቢቀምስ ዘላለሙን እኔው ላይ ጥብቅ ብሎ ቀረ እኮ!» እያለች ታፌዝበታለች። - «ትስማወርቅ» የምትለው ዘወትር ከአፏ የማይተፋ ቅፅል አላት። አረማመዷ እንኳ ሳይቀር «ደሞ ለሰው!» የምትለው ዓይነት አላት። -

«እኮ ቁጭ በይ፤ የተጠራሽበትን ጉዳይ ሳልነግርሽ ለምን ትነሻለሽ?!» አላት ዘጌ፣ መላ ሁኔታዋና በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ የሚወራባትን ታሪክ ሀሳቡ ውስጥ ብልጭ ድርግም ሲልበት ቆይት።

«እኮ ንገረኝ፤..... ቸኩላለኋ፤ ከስራ ላይ ተነስቼ እኮ ነው የመጣሁት።»

«ጉረኛ፤ መቼም ጉራሽ አይቻልም። በሞቴ ቁጭ በይ።.....» አለና ቀላልዶ አስቀምጦአት ቀጠለ። «ምነው በናትሽ፤ ቢሮአችሁ ስመላለስ እንኳ አይገባሽም እንዴ?......»

«ምኑ?.... በናትህ?»

እንደገና አክላለች። ዘገየም በሳቅ እያለሳለሳት ጨዋታውን ቀጠለ -

«ጽጌረዳን.....»

አሁን የተፈለገችበት ጉዳይ ገባት። ደሟ በአንዳፍታ ቅዝቅዝ አለ። ሴትነቷን ተመርኩዞ ሊኩራራ የተነሳው ስሜቷ ተኮላሸ። ወገቧን ይዛ ልትውረገረግባቸው የነበሩትን ክንዶቿን ደረቷ ላይ አጣምራ፤ ጥርሶቿን ከድና ግንባሯን አጨማዳ ዘጌ የሚናገረውን ታዳምጥ ጀመር።

«.......የምናገረው ነገር እንደማያስደንቅ ተስፋ አለኝ። ፅጌረዳን የፈጠራት አምላክ ራሱ ሳይመኛት አይቀርም። ባሏ መቼም እሷን ያስቀየማት ታውሮ መሆን አለበት እንጂ በጤናው አይመስለኝም። ወይም ደግሞ ‹በእጅ ያለ ወርቅ እንደ መዳብ ይቆጠራል› እንደሚሉት ሆኖበት ይሆናል። ‹...» የትውሲትን ፊት ፈካ ለማድረግ ንግግሩን መሐል ቀልድ ቢጤ ቀልቀል አደረገበት፤ «.....የባልና ሚስቱ መጣላት ለወንደላጤ ሲሳይ ነው። እና.....»

«እና.....ምን?» - ኮስተር እንዳለች።

«ያው.....በአንቺ በኩል ይቀላል..........»

«እኔ ‹ሚገርመኝ›.......ስንት ሰው ነው ፅጌረዳ የሚጠይቀኝ?! ትውስቲ አቃጣሪ መሰለቻችሁ እንዴ?!»

ትውሲትን በደንብ ስለሚያውቃት ዘጌ በአነጋገሯ አልተደናገጠም።.....ለዘብ ያለ ፈገፍታ እያሳየ ጉዳዩን ቀጠለ።

«.......እንደዚያ ማለቴ ሳይሆን.....እኔና አንቺ ወንድምና እህት ነን።.....በተለይ ከደጀኔ ጋር መውጣት ከጀመርሽ በኋላ..... አይደለም እንዴ?!»

«ታዲያ ደሞ ምን መሆን አምሮህ ነበር?» አለችው ትንሽ ፈካ ብላ።

ዘጌ የደጀኔን ስም ያነሳው ሆነ ብሎ ነው። - የማስፈራሪያ ዱላ መሰንዘሩ መሆኑን ትውሲትም አላጣችውም። ሚስጥር ለሚስጥር ይተዋወቃሉ። ለዚህ ነው ትንሽ ፈካ ያለችው።.....

«......እና፤ ፅጌረዳ ከእኔ ይልቅ ለአንቺ ትቀርብሻለች። ባንቺ በኩል መንገዱ ቢጠረግልኝ ያምራል።»

«እኔ የሚገርመኝ....» አለችው ትውሲት፤ እንደ ተገረመ ሰው አገጯን በእጇ ደግፋ፣ «ወንዶች ስትባሉ የማትረቡ ፍጥረቶች መሆናችሁ ነው። ፅጌረዳ ከባሏ ስትጣላ በማዘን ፋንታ ልታወጧት ትሽቀዳደማላችሁ። ትንሽ እንኳ ይሉኝታ የላችሁም። አበስኩ ገበርኩ እቴ!.....»

«ማውጣቱም እኮ ሐዘኔታ ነው። መቼም እስካልቀረበች ድረስ ከባሏ ተጣልታ እንዲሁ አትኖር......»

«አንዴዬ......ተጣሉ እንጂ ከቤት አልወጣችም እኮ!.......»

«ያው ነው እባክሽ። መኝታ ሁሉ ለያይተው ነው የሚተኙት።

«አቤት አቤት?! - ይሄን ደሞ በምን አወቅክ?»

ሁለቱም ጆሮዎቿ ሰልተው ቆሙ። ፅጌረዳና ወንዳፍራሽ በመኝታ እስከ መለያየት መድረሳቸው ለትውሲት አዲስ ዜና ነበር። የማታውቀውን መረጃ ከዘጌ በማግኘቷ ደስ አላት። በጣም የምትፈልገው መረጃ ነበር። አጥር ለሚዘሉት መሰላል ከመሆኗ በፊት የግቢውን መረጃዎችን አጠናቃ መሰብሰብ እንዳለባት ታውቃለች።

በዘይገ ቅልጥፍናም ተገረመች። መስሪያ ቤትም ውጭም ከብዙ ሰው ስለ ሚተዋወቅና ስለ ሚግባባ ማንኛውም ወሬ አያመልጠውም። ስራው ንብረት ክፍል ውስጥ ቢሆንም አንዳንዶቹ «የመሥሪያ ቤታችን የውጭ ግንኙነት ክፍል ሐላፊ ነው» እያሉ ይቀልዱበታል። የማይገባበት የሚስጥር ቀዳዳ የለም። አብዛኛውን ወሬ የሚያቀብሉት ከተለያየ መሥሪያ ቤት የሚያወጣቸው ሴት ፀሐፊዎች ናቸው ይባላል። በዚህ ሙያ ስለሚበልጣት ትውሲት ትቅናበታለች። እሷ ራሷ ወሬ የተባለ ነገር አያመልጣትም። የእያንዳንዱን ሠራተኛ የግል ሕይወትና የቤተሰብ ይዞታ ሳይቀር ተናገሪ ብትባ የሚያቅታት አትመስልም። ዘገየ ግን አንድ ደረጃ ቀድሟት አገኘችው። ......

«.....እውነት የምርህን ነው?......በመኝታ እስከ መለያየት ደርሰዋል?!....»

«እየነገርኩሽ!.....»

«ለአንተ ማ ነገረህ?»

«እኔ ደሞ ከፈለግኩ ምን ወሬ ያመልጠኛል! በሆነ ዘዴ ደረስኩበታ!.... እመኚኝ፤ እውነቴን ነው።»

ወሬውን እንዴትና ከየት እንዳገኘው አልነገራትም። አድናቆቷ ከፍ እንዲል ወይም ልቧ እንዲሰቀል ደበቃት። ሚስጥሩን ያገኘው ግን ከትክክለኛ ምንች ነበር።

እልፍነሽ የተባለች የፅጌረዳ ሠራተኛ እነዘገየ ሰፈር ዘመዷ ስላለች አልፎ - አልፎ እየሄደች ትጠይቃታለች። ዘገየ ይህንን ስለሚያውቅ፤ መረጃውን ለማግኘት የተጠቀመባት የእልፍነሽ ዘመድ የሆነችውን ጎረቤቱን ነበር።

«ጉደኛ ነህ!....» ብላ ትውሲት ተነፈሰች።

«ይሔ ሁሉ ጥረት ፅጌረዳን ለማግኘት ነው። ይገባሻል?!....»

«እሱ የራስህ ጉዳይ ነው።....ቅልጥፍና ካለህ ራስህ ሞክር።»

«በአንቺ በኩል አይሆንም ማለት ነው?»

«ዘገየ ሙት፤ እኔ እንዲህ ዓይነት ነገር ውስጥ መግባት ደስ አይለኝም። ፅጌረዳንም እንደምታውቃት በዚህ ጉዳይ ኮስታራ ናት።..... ብሞክርም እንጣላለን እንጂ እሺ አትለኝም።» አለችና ከተቀመጠችበት ተነሥታ ወደ በሩ አመራች።

እሱን ተዪው፤ አለ ዘጌ በልቡ። ትውሲትን ያውቃታላ!.....ሆኖም አንድ ነገር ቁጭ ብሎ ታየው። እምቢታዋን የምን ምልክት እንደሆነ አወቀ። - ቀደም ብሎ እንደነጠረው ሁሉ፤ አቶ ክብረት ቀድመውታል ማለት ነው። ትውሲት ያለወትሮዋ አቶ ክብረት ቢሮ መግባት መውጣት ያዘችበት ምክንያት ገባው። አቶ ክብረትን በእንዲህ ዓይነቱ ጉዳይ በደንብ ስለሚያውቃቸው ነው ቀድሞውንም ጥርጣሬ የገባው። ውጪያዊ ፀባያቸውን እያሳመቱ ውስጥ ውስጡን የሚሰሩትን ያውቃል። እሳቸውን የሚጠላበት ምክያትም አለው።

እናም በመቀደሙ በሸቀ። ለፅጌረዳ ክፏ ቋምጦላት ነበር። ራሱ ዘጌ ትልቁ በሽታው ይህ ነው። የከጀላትን ሴት ካልቀመሰ ያቅበጠብጠዋል። ቆንጆ ሴት ሲያይ የማያምንበትን ታቦት ይሳልለታል። አስራ ሁለት ዓመት ሙሉ በሥራ ላይ ውሎ እስካሁን የባንክ ደብተሩ ላይ ሀያ ብር እንኳ የለም። - ቀሚስ ሲከተል ጨርሶታል። ሁሉን መቅመስ ይፈልጋል። አንድ ጊዜ መንገድ ላይ ተዋውቋት «እባክሽ ልቅመስሽ?» ያላት ሴት የሰጠች መልስ እስከ አሁን ትዝ ይለዋል። «......ወጥ መሰልኩህ እንዴ የምትቀምሰኝ?! የማነው እባካችሁ!» ብላ ጥላው ሄዳለች።

አሁን የፅጌረዳን ነገር በግሉ ራሱ ቢሞክርም ዋጋ የለውም፡፡ ምክንያቱም ትውሲት ጉዳዩን ለአቶ ክብረት ከያዘችላቸው አጠገቧ እስካለች ድረስ፣ ሌላውን ሁሉ እንደምትዘጋ ያውቃል፡፡ አቶ ክብረትን ለማገልገል የፈለገችበትም ምክንያት አላጣውም፡፡.......

«ስሚ አንጂ ትውሲት....» አላት በሩን ከፍታ ለመውጣት ቁልፉን ስታዞር፡፡

«አቤት?.......» አለችው በሰለቸ ድምፅ፡፡

«እምቢ ማለትሽ ነው?»

«አፉ!.....ዘገየ ደሞ.....»

«.......ያለበለዚያ ለደጀኔ ነው የምነግርልሽ!» አላት እንደ ቀልድ አድርጎ፡፡

«ኧረ ባክህ!?......» - እንደገና ልትውረገረግ ቁልፉን ጥላ በሁለት እጆቿ ወገቧን ያዘችና የጎድን ቆማ ዳሌዋን ታሳየው ጀመር፡፡ «ደጀኔ ውሽማዬ እንጂ ጌታዬ መሰለህ እንዴ?! ንገረዋ!......አሁኑኑ፤ አንካሳ ዶሮ ሳትቀድምህ!.......»

የውስጥ ቁስሏ አስቀድሞ አስጮኋት እንጂ፤ ለደጀኔ የሚነግርባት ምን እንደሆነ አላወቀችም ነበር፡፡ ቆይታ ድነው ይህን ያሰበችው....

«ደሞስ ምኑ ነው የምትነግርው?»

«አቶ ክብረት ቢሮ የሚያመላልስሽ ጉዳይ ምን እንደሆነ ነዋ!.......»

«ንገረው ንገረው፡፡ እኔን በእሳቸው ማንም አይጠረጥረኝም፡፡»

«እንደሱ ማለቴ አይደለም....»

«ታዲያስ?.......»

በማስፈራራት ዓይነት ግንባራኡን አኮማትራ አይኗን አፈጠጠችበት፡፡ ዘጌም መናገር የፈለገውን አፉ ውስጥ ሲያድበሰብሰው ትንሽ ቆየ፡፡ ትውሲት ወጥታ ለመሔድ በሩን ከፈተች፡፡

«ስሚ እንጂ»

«እህ?!» አለችው ግማሽ ሰውነቷን ከበሩ አሰወጥታ።

«.....የሽማግሌ አጥር ለመዝለል መሰላል ከምትሆኝ እኛ ወጣቶቹ እንሻልሽም?»

«ምን?! ምንድነው የምታወራው?»

«መቸኤም አይኔ እያየ እዚህ መሥሪያ ቤት ውስጥ ሴት አቃጥረሽ ዕድገት አታገኚ!»

«ቡዳ!» አለችና በሩ አስጩሃ ዘግታበት ሄደች።.... ቡዳ ነው፤ ቡዳ፤

«ኤርሚ!......ኤ......ልሚ!......ኤ......ርሚ!.....»

ዳኒና ሰብለ እየተንደረደሩ ኤርሚያስ ላይ ተጠመጠሙበት። ቤታቸው ከመታ ሰነብት ብሎ ነበር። የዛሬዋን ቅዳሜ ከቀትር በኋላ ግን ሲናፍቃት ነው የከረመው። ፅጌርዳን ከቤት እንዳያጣት ምሳው ከጉሮሮው ላይ ሳይወርድ እየከነፈ መጣ።

«ምነው ጠፋህ?» አለው ዳኒ ኤርሚያስን ግራ እጅ በሁለት እጆቹ ይዞ እየጎተተው።

«ምነው ተፋህ?» አለች ሰብለውም የዳኒን ድምፅ ተከትላ፤ መራመድ እስኪያቅተው ድረስ የኤርሚያስን ቀኝ እጅ ጨብጣ ሽብቅ እንዲያነሳት እየተንጠራራች።

«ስራ በዝቶብኝ ነው።» አላቸው ኤርሚያስ ሁለቱንም እንደ አያያዛቸው ለማስደሰት እየታገለ።

«ኬክ አላመትህም?» - ሰብለ አፋጠጠችው።

ለወትሮው ባዶ እጁን አይመጣም ነበር። ዛሬ ግን ስለ ልጆቹ ኬክ ለማሰብ ጊዜ አልነበረውም። የአዋቂዎቹ ጉዳይ ነው እጅጉን ያሳሰበው። - ከሁለት ቀን በፊት ዘነ የነገረችውን ዜና በመንተራስ ወንዳፍራሽ ጋ ስልክ ደውሎ ያገኘው መልስ ይበጡን ግራ አጋብቶታል። ሰላምታ እንኳ ሳይሰጠው ነበር ወደ አርዕስተ - ነገሩ የገባው።

- ሀሎ ወንዳፍራሽ ነህ?

- አዎ፤ ኤርምያስ ነኝ...ማን ልበል?

- ኤርምያ ነኝ። ስማ እንጂ፤ ምንድን ነው የምሰማው
እባክህ? ከፅጌረዳ ጋር.....

- አዎ ፅጌረዳ ሰሞኑን ቤት ውስጥ ጦርነት ከፍታለች።

- ከፍተኛ ችግር ላይ ነን። መደማመጥ አልቻልንም።

- እኔ እኮ ያቋረጥክ መስሎኝ ነበር።

- ምን?

- ከሮዛ ጋር የጀመርከነው ግንኙነት።

- የለም፤ ሊቋረጥ አልቻለም። ችግር አለ። ይልቅ ለፅጌረዳ በሚገባት ቋንቋ ብትነግራት ጥሩ ነው። እኔ ትዳሬን አልጠላሁም ሆኖም ከሮዛ ጋር ያለኝን ግንኙነት በአንድ ጊዜ ርግፍ አድርጌ መተው አልችልም።....ችግር አለ ብዬሀለሁ። እና ትንሽ እንድትታገሰኝ እፈልጋልሁ።

ኤርሚያስ ጉዳዩን ከባለቤቱ አፍ እንደሰማ ለምን ደብቆ ቆየ ብሎ አልተናደደበትም። መጀመሪያውንም ሁኔታውን ስላወገዘበት ይሉኝታ ይዞት እንደቆየ ያውቃል። ያም ሆነ ይህ የቅርብ ጓደኛው እንደመሆኑ መጠን አሁን የችግሩ ተካፋይ እምሆኑ አልቀረም። ወንዳፍራሽ ሮዛን መተው አለመቻሉን ከራሱ አፍ መስማቱ የችግሩን ጉልህነት አሳየው። ተንደርድሮ የሚገባበት ጉዳይ አልሆነም። ሁለት ቀን ነገሩን ሲያወጣና ሲያወርድ ከርሞ በመጨረሻ በዕረፍት ቀን ቅዳሜ ፅጌረዳን ለማነጋገር ወሰነ።....

ሰብለን ታቅሮ፣ ዳኒን ደግሞ በእጁ እየጎተተ ከሳሎኑ የውጭ በር አጠገብ ሲደርስ ፅጌረዳ ከውስጥ ብቅ አለች። ኤርሚያስን ስታየው በአንድ ጊዜ ሁለት የተዘበራረቀ ስሜት ተሰማት። - የወንዳፍራሽ የቅርብ ጓደኛ በመሆኑ ልቧ ጠላው፤ የጥፋቱ ተባባሪ አድርጋ ወሰደችው። በሌላ በኩል ደግሞ ለወንዳፍራሽ ብቻ ሳይሆን

ለረዥም ጊዜያት ለእሷም ለልጆቿም ጓደኛ ሆኖ መቆየቱን ስታስታውስ አንጀቷ ሊጨክንላት አልቻለም።

«.....ደህና ነህ ኤርሚያስ?......ምነው ጠፋህ?»

ጉሮሮዋ ላያ የሚታገላት ነገር አለ። ድምፅዋም ሆነ መስተንግዶዋ የወትሮዋ ፅጌረዳ አይደለም። ዘወትር የፈካ አበባ የሚመስለው ፊቷ አሁን ዳመና አዝሎ የግዷን ፈገፍታ ልትረጭበት ትታገላለች። - ወንዳፍራሽን የቅርብ ጓደኛ ስታይ የባሰ ቂሟ አገረሸ። ብሶት ብሶት አላት።

ኤርሚያስም ቆቅ ነው። - ነገሩ ገባው። ልቡ እየደማ ወደ ሶፋው ሄዶ ተቀመጠ። ዳኒና ሰብለ አልለቀቁትም። ጨዋታ ስላ ስለመዳቸው እንደልማዳቸው ይተሻሹታል። ሀሳቡ ከእነሱ ርቆ በድን እጁ ብቻ ከልጆቹ ጋር ይጫወታል።

እልፍነሽ ብቅ ብላ ሰላምታ ሰጥታው ወደ ጉዳ ተመለሰች።

«....ምሳ እናቅርብልህ ኤርሚያስ?»

«የለ፣ አሁን ከምሳ ላይ ተነስቼ ነው የመጣሁት። አንድ ነገር እኮ ሰምቼ.....»

የመጣበትን አርዕስት ለመጀመር ዳር ዳር አለ። ፅጌረዳም አርዕስቱን እንደምትፈልገው ከፊቷ ላይ ማንበብ የቻለ መሰለው።

«ፅግሽ......መቼም የቅርብ ጓደኛው በመሆኔ አታምኚኝም ይሆናል። ፅጌ ሙች እልሻለሁ፤ ከትላንት ወዲያ ነው ከቤታችሁ ውስጥ እንዲህ ዓይነት ችግር መፈጠሩን የሰማሁት።

ኤርሚያስ አይዋሽም። እንዲያውም ለእምነቱና ለፍላጎቱ ግትር መሆኑን ፅጌረዳም ታውቃለች። ነገር ግን ራስን የሚፈትን ነገር ሲመጣ ልቧ ጠረጠረ። የሚነግራትን ነገር ባለ ማመን ወይም በመጠራጠር «እሱን ተወው» እንደማለት ዓይነት አገጯን በመዳፏ ደግፋ አንገቷን ዘንበል አደረገች።

ኤርሚያስ ዝም ብሎ ንግግሩን ቀጠለ -

«......ነገሩን ስሰማ ደነገጥኩ። በእናንተ ትዳርና ቤት ውስጥ ፈጽሞ ይከሰታል ብዬ ያልገመትኩት ነገር ነበር። የፍቅራችሁን ልክ ስለማውቀው አሁን የተፈፀመውን እውነት ስሰማ ጨከኘ ወይም አምኘ መዋጥ አቃተኝ። በየሌላው ቤት ከዚህ የከፋ ችግር አለ። ልጆቻቸውን ቤት ውስጥ ቆልፈው፤ ባል ለብቻው በአንድ በኩል፤ ሚስት ለብቻዋ በሌላ በኩል የሚወሰልቱበትን ትዳር አውቃለሁ። ያ ሁሉ አላስደነቀኝም። - ፍቅራቸው መሠረት እንዳልነበረው አውቃለሁ። የናንተ ግን የትዳር ዓርዓያ ነበር።»

ፅጌረዳ የማደንዘዣውን መርፌ እንዳልተሰማት ዓይነት ፊቷን ጨምደድ አደረገች።

«እውነቴን ነው የምልሽ ፅጌረዳ። እና አሁን እኔ ልነገርሽ የምፈልገው በጊዜያዊ የስሜት እሳት ተገፋፍታችሁ የሞቀ ጎጆአችሁን እንዳታፈርሱ ነው። በዚህ ረገድ እኔ መሐላችሁ ለመግባት እገደዳለሁ። - አዎ! የሞራል ግዴ አለብኝ። ዝም ብዬ ማየት አልችልም። ከወንዳፍራሽ ጋር እስካሁን በስልክ ብቻ ነው የተነጋገርነው። በውን አግኝቼ በደንብ አነጋግረዋለሁ። በስልክ እንደነገረኝ ከሆነ የሮዛን......»

የፅጌረዳ ፊት ልውጥውጥ ብሎ ኮሶ የጠጣች አስመሰላት። ብስል ቀይ፣ ረዥም ሴት ከፊቷ መጥታ ድቅን አለችባት። ዳኒም የሮዛን ስም ሲሰማ ፊቱን ክፍት ብሎት፤ መተሻሸቱን አቁሞ ሁለት እጆቹን ሰብስቦ ሶፋው ላይ ቁጭ አለ። ሰብለውም ዳኒ እንዳደረገው አደረገች። የቤተሰቡ በአንዳፍታ መለዋወጥ ኤርሚያስን አስገረመው። ነገሩ ከርሮ ምን ደረጃ ላይ እንደ ደረሰ ገባው።

«.....አዎ፤ ከሮዛ ጋር የጀመረውን ግንኙነት በአንዴ መቁረጥ እንደሚያስቸግረው ነግሮኛል። አንድ ችግር ሳይኖር አልቀረም። ችግሩን አውቀን መፍትሔ እስክንፈልግለት ድረስ አንቺ እንድትታገሺው።......»

«ትዕግሥት?!.........» አለች፤ ድንገት የፌዝ ሳቅ እየሳቀች «ትዕግሥት እኮ ነው ለዚህ ያበቃኝ፤ ኤርሚያስ ችግር አለ አልከኝ?!......ችግር መኖሩንማ እኔስ መች አጣሁት። ችግር?!.....»

«ችግሩ ምን እንደሆነ ገና አልታወቀም፤

«እንዴዬ.....ከአንተ የተሰወረ ችግር ነው እንዴ?»

ጥያቄ ሳይሆን የአሽሙር ንግግር ነእብር። ‹ጓደኛው ስለሆንክ እንኳን ይህን ሌላ ታውቃለህ ማለቷ ነው። የፌዝ ሳቅ፣ የአሽሙር ንግግር ቀስ በቀስ እየለመደች መምጣቷን ኤርሚያስ በጥቅቲ ደቂቃዎች ውስጥ ታዘበ። - ያቺ ቅድስት ሴት እየተለወጠች ነው። የዱሮዋ' ፅጌረዳ መዓዛዋ እየጠፋ ነው! - እና ለዚሁ ሁሉ ተጠያቂው ማን ነው? የዋህዋ ሴት ወደ ጥፋት ጎዳና በመምጣቷ ኤርሚያስ ከልቡ አዘነላት።

ጥንት የሚያውቀውን ውበቷን አሁንም እንደገና በቁጣዋና በንዴቷ ውስጥ እንደ አዲስ ሰው ማጥናት ጀመረ። የሚያባብሉ ዓይኖቿ የዕልህ እና የቅናት ዕንባ በማልቀስ ብዛት ቢቀሉም ውበታቸው አልጠፋም። የቸኮላት ቀለም የያዘው ጠይም ፊቷ አንዳች አፍዝ አደንግዝ አለው። ከራስ ፀጉርዋ እስከ እግር ጥፍርዋ የተስተካከለው ቁመናዋ የአላፊ አግዳሚውን ምራቅ እንዳስዋጠ ይኖራል። ጡቶቿ በጡት መያዣ ተወዳድረው ሲታዩ ሁለት ልጆች ያጠባች አትመስልም። ለመናገር ጥርሶቿን ገለጥ ስታደርግ በጉጉት የአድማጯን ለሐጭ ታዝረከርካለች፤ የተመልካቿን ዓይን ታፈዝዛለች። ሰሞኑን ፀጉርዋ ላይ በግድየለሽነት ዓይነት ሻሽ ሸብ ማድረግ ብትጀምርም፤ ውበትዋን ጨርሶ አልዋጠውም። ሻሹን አውልቃ ዓይኖቿን ጠራርጋ ብትኳኳል፤ በአንዳፍታ ቦግ ሊል የሚችል ውበት በድብቅ ይታያል። በዚህ ላይ ደግሞ ወርቅ የሆነ ፀባይ ተጎናጽፋለች።

ይህች መሳይ ውብ ጥሎ የወንዳፍራሽን ልብ ወደ ውጭ ያሸፈተው ጉዳይ ምን ይሆን? ሲል አሰበ - ኤርሚያስ። - አንዳንዴ እኮ እኛ ወንዶች እውሮች ነን!..... ነው ወይንስ እኛ የውጭ ሰዎች የማናውቀው ወንዳፍራሽ ብቻ የሚያውቀው የውስጥ ችግር ይኖር ይሆን? አንድ ነገር ብልጭ አለለት። - ለብዙ ትዳር መፈናቀል ምክንያት የሆነ! የማይነገር! ድብቅ!..... አዎ! የግብረ ሥጋ ግንኙነት ጉዳይ ነው። ብዙ ትዳር ውስጥ ለፀብ ምክንያት ሆኖ ሳለ ነገር ግን ውጭያዊ ሽፋን ይደረገለታል። የዱሮ ሰዎች እንኳ «ኮከባችን አልገጠመም።» የሚሉት ገላጭ ቋንቋ ነበራቸው። አሁን ግን የፀቡ ምንጭ ይሸፈንና በሀሳብ አለመስማማት፤ በኢኮኖሚ ችግር ወይም በመሳሰሉት ይደበስበሳል። ትዳር ውስጥ እንደ ምግብ ዝግጅት ሁሉ፤ እንደ ጎጆ ቅየሳ ሁሉ፤ እንደ ሌላው የኑሮ ስንክሳር ሁሉ የወሲብም ጉዳይ በባልና በሚስት መሐል ግልፅ ውይይት

ቢደረግበት የችግሩ ምንጭ ተጠንቶ ይደርቃል። አዎ! አለመጣጣምን ያሚያስከትለው አለመወያየቱ ነው። መወያየት ቅራኔን ጨፍልቆ መጣጣምን ይፈጥራል።

«.....ለምን ብዙ ትጨነቃለህ ኤርሚያስ?...... አይዞህ ንገረኝ.......ችግሩ እኔ መች አጣሁትና ነው?!....... ዲቃላ ወልዳለት ወይም አርግዛለት ይሆናል!......» በማለት ፅጌረዳ ከሐሳቡ አባነነችው።

ኤርሚያስ ደነገጠ። ያላሰበው ነገር ነበር።......እውነት ሮዛ አርግዛበት ይሆን እንዴ? አለ በሐሳቡ። ሆኖም ሀሳቡን ለማሰብ ፅጌረዳ ጊዜ አልሰጠችውም።

«........ይሔንኑ ነበር የምጠብቀ።..... ዲቃላ እስኪያመጣልኝ ድረስ!......»

«ዲቃላ» የሚለውን ቃል ስትጠራ ሰውነቷን እንዳንቀጠቀጣት አይነት ተንዘፈዘፈች።.....እውነት ከሆነማ ከወንዳፍራሽ ጋር አንድ ቀንም አብረን አንውላትም፤ ስትል አሰበች። የግምቷን ትክክለኛነት የሚነግራት የወንዳፍራሽን ሌላ ቅሌት የሚነግራት ሰው ስትፈልግ በሀሳቧ ትውሲት ብቅ አለችላት።.....አዎ፤ ትውሲት ጉድጓድ ምሳ ገብታ ሚስጥሩን ልታወጣላት ትችላለች። ሰኞ ደርሶ መስሪያ ቤቷ የምትሄድበት ጊዜ ራቀባት!

«አሁን እኮ ያንቺም ግምት ነው እንጂ፤ ገና በውል የታወቀ ነገር የለም፤ ፅጌረዳ።» አላት ኤርሚያስ አለሳልሶ።

አሁንም እንደቅድሙ «......እሱን ተወው» በሚል ዓይነት፤ አነጋገሩን ናቅ አድርጋ ከተቀመጠችበት ተነሳችና ወደ ጓዳ ሄደች። በብስጭት ተኮማትራ የተቀመጠች ሰውነቷን ለማፍታታት ካልሆነ በስተቀር ወደ ጓዳ የሄደችበት ምክንያት ለራሷም ግልጽ አልሆነላትም።

በጓደኝነቱ ሳቢያ እሱንም ሙሉ በሙሉ ወንዳፋራሽ ሚስጥር ውስጥ እንደጨመረችው ገባው። አልፈረደባትም። ማንኛውም የተጎዳ ሰው ሊጠረጥር የሚችለውን ጥርጣሬ ነው። ከአሁን ቀደም ግን በቅርብ ጓደኝነት ደረጃ ከማንም ይበልጥ እሱን እንደምትወደውና እንደምታከብረው ያውቃል።

አዎ፤ ፅጌረዳ ሰው አክባሪ ነበረች፤ በማለት ተመልሶ ወደ ኃሳቡ ገባ። - ነገር ግን ፀባይና መልክ ብቻ ዋጋ የላቸውም። ዋናው ቁም ነገር ያለው ከአዕምሮ ጥንካሬ ላይ ነው። ችግርን የመቋቋም ብሶትን የመመከት፣ ይሕይወትን እንዳመጣጧ የመቀበል ጥንካሬ ያስፈልጋል። አብዛኞቹ የሐገራችን ሴቶች ይህ ጥንካሬ ይጎድላቸዋል። ተወልውለውና ተኳኩለው ከቀረቡ ለባላቸው በቂ ይመስላቸዋል። ሁለቱ ከወለዱ በኋላ መኳኳሉንም አቁመው ራሳቸውን ለእርጅና የሚሰጡ አለሉ። - ይህ እንዲህ በአዕምሮ ያለ መጠንከር ውጤት ነው። አንዳንድ ሴቶች የሚያገቡት ባላቸውን ለግንባር ራሳቸውን ለደጀንነት እያጩ ነው። ይህ አስተሳሰብ ደግሞ ምን ጊዜም ወንዱን ትምክህተኛ እንደሆነ ያቆየዋል። የለም!......ትዳርን ከማኅበራዊ ሕይወት ጋር የሚያገናኘው ሰንሰለት የሚጠብቀው ባልና ሚስት ተረዳድተው ሲአይስሩት ብቻ ነው። ባል ብቻውን የሆነው እንደሆነ ከአንድ በኩል ሲያጠብቅ፤ ከሌላ በኩል ይላላበታል። ትዳር የጋራ ነው። ለባለትዳሮች ደግሞ ማኅበራዊ ህይወትም የጋራ ነው።.....

ልጆች የመንከባከቡና የቤት ውስጥ ጉዳዮችን ማከናወኑ፤ ለሴቷ ብቻ የተተወ እንደሆነ የወንድ ልብ ወደ ውጭ ሲወሰልት ይቻላል። የልጆቹ ፍቅር ወደ እናታቸው ሊያደላ ይችላል። አንዳንዱ ወንድ የቤት ማስተዳደሪያ ገንዘብ ከሰተ በቃ! ትዳሩን ቀጥ አድርጎ የያዘ ይመስለዋል። ነገር ግን በቤት ውስት ፍቅሩም ሐላፊነቱም እኩል መሆን አለበት። የቤት ውስጥና የውጭ የሥራ ክፍፍል ቢኖርም፤ ሐላፊነት የጋራ ነው። ጾታዊ ፍቅር እየሰከነ ሲሄድ፤ ቤተሰባዊ ፍቅርን የሚገነባው ይህ የጋራ ሐላፊነትና መተሳሰብ ነው። ትዳር ወደ ውች የሚቅበዘበዙ ዓይኖችን ማገድ፣ መንፈስን መማረክን ልብን ማረጋጋት አለበት። በአፍላ ዘመን የሚታየውን ዓይነት ቅፅበታዊ ጣፋጭ ፍቅር በትዳር ውስጥ መጠበቅ ጅልነት ነው። ያንን ዓይነት ፍቅር ሰመመን ከመሆኑም ሌላ የሚያጣፍጠውም ዕውርነት ነው። የትዳርን ፍቅር የሚያጣፍጠው ግን ዓይናማነትና የጋራ ኃላፊነት መሆኑ መዘንጋት የለበትም።

«ኤርሚ......ፅግዬን ለምን ታናድዷታላችሁ?» አለው ዳኒ፣ ሲያስብ ቆይቶ፤ እናትየው ከሳሎን ከሄደች በኋላ።

የዳኒ ጥያቄ ጥያቄዋ እንደሆነና መልስ እንደምትጠብቅ ሁሉ፤ ሰብለም የኤርሚያስን ዓይን - ዓይን ትመለከት ጀመር።

«መቼ አናደድኳት?! ዳኒ? እንዳትናደድ እያበባልኳት እኮ ነው።» አለው በጥያቄው ተደናግጦ የሁለቱንም ሕፃናት ጭንቅላት እያሻሸ።

«ወንዴ ለምንድን ነው ሮዛን የሚያገባው? እኛ እንደሆነ ከፅግዬ ሌላ እናት አንፈልግም።»

«ሌላ እናት አንፈልግም።» አለች ሰብለም ተደርባ።

«ማነው እንዲህ ብሎ የነገራችሁ?» አለ ኤርሚያስ፤ ይበልጥ ተደናግጦ፤ «ውሸት ነው። ሌላ ሚስት ሌላ ባል የሚባል ነገር የእልም።»

ድንገተኛ ሐዘን መላ ሰውነቱን ወረረው። ኤርሚያስ እዚህ ቤት ውስጥ ለብዙ ዓመታት ቤተኛ ነው። ወንዳፍራሽና ፅጌረዳ ጓደኞቹ ናቸው። ዳኒና ሰብለ ጓደኞቹ ናቸው። «ጋሼ» እንኳ አይሉትም። ወላጆቻችው እንደሚጠሩት «ኤርሚ» ነው የሚሉት። በጣም ይወዱታል። ልጆቹ ከወላጆቻቸው ጋር እንደ ጓደኛ ሆነው በፍቅር ማደጋቸው ስለሚያውቅ አሁን ቤቱ ውስጥ የተፈጠረው ችግር አሳዘነው። ለአባትም ለእናትም እኩል የነበረው የልጆቹ ፍቅር ወደ አንድ ጎን እያደላ ሲሄድ ታየው። ችግሩ ከአዋቂዎቹ ይልቅ ልጆቹ አዕምሮ ውስጥ ጥሎ ያሚያልፈውን ጠባሳ ለመገመት አልተቸገረም።

እሱ አርዕስቱን ረስቶ ልጆቹንም ያስረሳ ለመምሰል ሰብለን በግድ ጭኑ ላይ አውጥቶ እየኮረኮረ ያስቃት ጀመር። የዳኒ ፊት ግን የጥያቄ ምልክት አዝሎ ነበር።

«ለመሆኑ አባባ ይህንን ነገር ስምተዋል እንዴ?......»

ፅጌረዳ ከጓዳ ተመልሳ ስትመጣ ኤርሚያስ ጠየቃት። ምንም ሳትፈይድ ነበር ከጓዳ ወደ ሳሎን የተመለሰችው።

«እስካሁን አልሰማም በቅርቡ ይሰማል።»

«በተቻለ መጠን እንዳይሰሙ አድርጊ እባክሽ። ሰምተውም የሚጨምሩት ነገር የለም።......ብስጭት ነው የሚተርፋቸው።.....»

«ይሰማል እንጂ.......ተደብቆ አይቀር።» አለች የራሷ ባል ሆነ ድምፅ።

አባቷ አቶ ኃይሉ ይህን ጉድ ቢሰሙ እንዴት እንደሚሆኑ ለመገመት ሞከረች። ግንባሮቻቸው ላይ የተጋደሙት ደምሥሮች ሲግተረተሩ ጉሮሮአቸው ላየልህ ሲተናነቃቸው መሬቱን በበትራቸው እየቆረቆሩ ጥርሳቸውን ሲያንቀጫቅጩ ሚስታቸው ላይ አፍትጠው «....ምንድነው የምሰማው?» ሲሉ በሀሳብዋ ታያት። በተደናገጡ ወይም በተቆጡ ቁጥር «.....ምንድነው የምንሰማው?!» ማለት ይቀናቸዋል። የሰሙትን አያምኑም። ሚስታቸው እንደገና አባብለው መንገር አለባቸው።

ፅጌረዳ የህይወታቸውም የአይናቸውም ተስፋ ናት። አራት ልጆች ወልደው ሦስቱ ከምንም ጉዳይ አልዋሉላቸውም። የመጀመሪያ ልጃቸው ወንድ ነበር - ፈረንሳይ ሀገር ለትምህርት ሄዶ በዚያው ቀልጦ ቀረ። በይህወት መኖሩን እንኳ ደብዳቤ ጽፎ አያውቅም። ሦስተኛ ልጃቸው መልከ መልካም ልጃገረድ ነበረች። የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪ ሳለች ካልተወቀ ወንድ አርግዛ በሀገር ባህል መድኃኒት ለማስወረደ ስትሞክር ሕይወቷን አጣቻ። ለቤተስቡ በሙሉ መሪር ሀዘን ሆነ። የመጨረሻ ልጃቸው ደግሞ ትምህርቱንም ትቶ ፋሽን ተከታታይ ሆኖ ቀርቷል። ከተማ ውስጥ የገባ የልብስ ፋሽን አያመልጠውም። ፀጉሩን ለማለስለስና ለማበጠር የሚፈጅበት ጊዜ ሲያዩ አባትየው አንጀታቸው ያርራል። «ፓንክ» «ጀንትራቮልታ» ወይም «ማይክል ጃክሰን» ዓይነት አበጣጠር ዕድሜው የደረሰበት ፋሽን ሆኗል። የመጨረሻ ልጅ በመሆኑ በእናትየው በኩል ቅምጥል ነው። - ለጥፋቱ ሁሉ ሽፋን ይሰጣሉ። እሱ ለጠየቃቸው ነገር ሁሉ መቀነታቸውን ይፈታሉ። አባትየው ጡረታ ሲወጡ የከፈቷት ልኳንዳ ባትኖር ኖሮ እስካሁን ቤተሰቡን አራቁቶ ለድህነት ዳርጎት ነበር።

እንግዲህ ከዚህ ሁሉ መሐል የተዋጣላቸው ሁለተኛ ልጃቸው ፅጌረዳ ናት። እስካሁን ድረስ በእሷ ኮርተው ቆይተዋል። የልጅ ልጆቻቸውን ስመዋል።.... እና አሁን በአናቱ፤ የአንዲት የሚወዷት ልጃቸውን ጥቃት ቢሰሙ እንዴት ይብከነከኑ?!....ምን መሬት ይበቃቸው ይሆን?.....

ፅጌረዳም ይህንኑ አውቃ እስካሁን አልነገረቻቸውም። በግሏም ሆነ እንዲሁ ቤት ውስጥ በቅናት ከመብከንከን በስተቀር የወሰነችው ነገር የለም። አንዳንዴ ቅናቱ

ሲያይልባት ቤቱን ጥላ መብረር መብረር ያሰኛታል። ነገር ግን ለትዳሯ ያጠፋችውን ጊዜና ጉልበት ስታስብ «....ለማናባቱ ብዬ» የሚል ስሜት ይገታታል። በሌላም በኩል የልጆቿ የዳኒ እና የሰብለ ነገር ያሳስባታል። ያለ አባት ወይም ያለ እናት የማደጉ ሁኔታ ሲታያት እንዲሁ በቅናት እየተርገበገበች ከወንዳፍራሽ ጋር መርኖሩን ትመርጣለች። «......ግን እስከመቼ? የሚለው ጥያቄ ደግሞ ጣልቃ እየገባ ጭንቅላትዋን ይበጠብጠዋል።

«ለማንኛውም ትንሽ ታገሽ፣ ፅግሽ.....እኔን የወንዳፍራሽ ጓደኛ ብቻ አድርገሽ አትውሰጂኝ። እኔ ውጭ ብሆንም የቤተሰቡ አባል ነኝ፣ ልጆቻችሁ ልጆቼ ናቸው። እናንተ ወንድሞቼና እህቶቼ ናችሁ።» አላት ኤርሚያስ ለመሄድ ተነስቶ።

«እሱን ተወው......አሁን ይህን ያህል ጊዜ የሚሰራውን ስራ ሳይነግርህ ወይም ሳታውቅ ቀርተህ ነው?!»

ጥያቄዋን ሕሊናው ቆንጠጥ አደረገው። - ከሮዛ ጋር የተደረገውን ግንኙነት ዕድገቱንም ባይሆን ጅማሬውን መስማቱን ቢነግራት ጥርጣሬዋን ያጎላዋል በሚል ግምት ይህንን ደበቃት።

«.....ግደለይም ፅግሽ......መልሰሽ እንደ ጥንቱ የምታምኚኝ ጊዜ ይመጣ ይሆናል። ብሎአት ወጣ።

ልጆቹ በመኪናው መዘዋወር ሰለለመዱ በጥያቄ መልክ በርቀት ተከተሉት። አሮጌ ቮልስዋገኑን ከአጥር ውጭ እንዳቆማት ተመልከተው ነበር።

«.....ኑ ከኔ ጋር አይስክሬም እገዛላችኋለሁ።»

ዳኒና ሰብለ ፈቃድ በመጠየቅ አይነት ወደ እናታቸው ተመለከቱ። - ኤርሚያስ ነገሩ ገባው።

«ፅግሽ....እነ ዳኒን ዘወር ዘወር አድርጌ አመጣቸዋለሁ።» አላትና ከእሷ መልስ ሳይጠብቅ ሁለቱንም ልጆች ይዞ ወጣ።

ፅጌረዳ በረንዳ ላይ ቆማ ሞተሩ ሲነሳ ሰማች። ኤርሚያስ ሳያስበው እሾህ ጥሎባት ሄደ። ብቻዋን በእሾሁ ትጠቀጥቅ ጀመር ......

«......ችግር» ያለው ነገር ምን ይሆን? ዲቃላ መሆን አለበት። ዲቃላ! ሆ ሆ ሆ ሆ ሆይ ከሮዛ ተወልዶልኝ ይሆናል!........

ሰኞና ትውሲት ራቁባት።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሊከሰት የሚችለውን ጦርነት እያሰበ ልቡ ከበሮ መደለቁን ጀመረ። የልቡን ድቤ ላለማዳመጥ የመኪናውን ጥሩንባ ደጋሞ አስጮኸው - ቢ - ኢ- ኢ- ኢ- ኢ- ጿ!..... የቀጠሮው ሰዓት ደርሷል። ጦርነትና ፍቅር ጥሩን ባውን ሲሰሙ ይመጣሉ። ማን ቀድሞ ማንኛው እንደሚከተል ግን ማወቅ አይችልም። - ፍቅሩ ቀድሞ ጦርነቱ እንዲዘገይለት፤ ወንዳፍራሽ የህሊና ጸሎት ቢጤ አደረገ።

የግቢያቸውን በር ከፍታ ብቅ አለች - ሮዛ። ነጻ አስተዳደግ ስላላት ከቤተሰቦቿ ተደብቃ አትወጣም። ማንም ወንድ ቢሆን ከቢቷ ወስዶ ቤቷ ይመልሳታል እንጂ ሆቴል ውስጥ አትቀጣጠርም። ዛሬ ቅዳሜ ከቀትር በኋላ፤ ወንዳፍራሽ ጋር በስልክ ቀጥሮ ስለያዙ ለባብሳ እየጠበቀችው ነበር። በስልክ ውስጥ እንደዚያ የተነጫነጨችበት በዓይነ ሥጋ ስታገኘው ምን እንደምትሆን ማሰቡ ነገር ሲይስፈራው የቆየው።

ዝንጥ ብላለች። ከመቼውም በበለጠ ለብሳና ተኳኩላ ነው የወጣችው። - ወገቧን ጠበቅ አድርጎ ይዞ ቁልቁ እየሰፋ የሚሄድ ነጭ ባለኪስ ቀሚስ፤ ......ደረቱ ላይ በወርቃማ ቀለም አበባ የተነደፈበት ቀይ ሹራብ.......ከጫማዋ ቀለም ጋር የሚሄድ ኃምራዊ የእጅ ቦርሳ......እና ደግሞ ይህንኑ ቀለም የሚከተል ረዥም የጆሮ ጌጥ እና የአንገት ሐብል አድርጋለች። ....ትጥቋ ወንዳፍራሽን አስፈራው። የተፈጥሮ ቁንጅና ስላላት እንዲህ ተጨንቃ ተጠባ ስትለብስ አይቶ አያውቅም። በቀላሉ ነበር የምታጌጠው። እና ይሄ ሁሉ ትጥቅ ከጀርባው ያዘለው እሳት ይኖራል ብሎ ፈራ።

«ሮዚና» ብሎ ሰላምታ የመኪናውን መስታወት ዝቅ ሲያደርግ ሮዛ፣ እርምጃዋን እንደምትቆጥር አይነት መሬት፣ መሬት እያየች አልፋው ሄዳ የመኪናውን የቀኝ በር ከፍታ ገባችና ቁጭ አለጭ። የአረማመዷም ሆነ የአቀማመጥ ስልት ማኩረፏን ያሳይ ነበር።

ጦርነቱ ሊቀድም ነው መሰል፤ አለ ወንዴ በልቡ። መኪናዋ በሽቶ መዓዛ ታወደች።

«አትስሚኝም እንዴ?.....ሮዚና» አላት ዝም ብላው ስትቀመጥ ዓይን ዓይኗን እያየ።

የራሷ ሳይሆን የሰው ንብረት እንደምትሰጥ ዓይነት ጉንጮቿን በግድየለሽነት ስሜት ወረወረችለት።.....የከንፈር ቀለም ሰለተቀባች ለከንፈር መሳሳም አልቻሉም።

ጉንጭ - ለጉንጭ ከተናካኩ በኋላ ያለ አንዳች ንግግር ተራርቀ ተቀመጡ። ወንዳፍራሽ በይቅርታ አስተያየት ሲመለከታት ሮዛ ምንም ነገር ሳትፈልግ - እሱን ለመዝጋት ብቻ - ቦርሳዋን ከፍታ መጎርጎር ቀጠለች።

እስዋን ትክ ብሎ ሲመለከት፤ በእሷ ውስጥ እሱነቱ ታየው። ራሱን ትንሽ ጣል ስላደረገ ሹፌሯ እንጂ ውሽማዋ አይመስልም። ለመቆነጃጀት ሁኔታዎች አላመቹትም። የጽጌረዳን ግልምጫ ፈርቶ ከሥራ እንደወጣ፣ ቤቱ ሳይደርስ፣ በቀጥታ ወደ ቀጠሮው ነው የመጣ። ከምላጭ ተራርቆ እቆየው ፂሙ ይኮሰኩስ ጀምሯል። ሐሳቡ ውስጥ በገባ ቊጥር በጣቶቹ የሚቆፍረው ጸጉር እንደ ተመሰቃቀለ ነው። ቤቱ ስላደረሰ ልብሱንምን አልቀየረውም። ውሃ ሰማያዊ የደንብ ልብስ ደንደ ለበሰ ነበር።

ይህን ሁሉ ግን ሮዛ ከጉዳይም አልጣፈችውም። ዛሬ፤ የሚያውቀውን ወበቷን ይበጥል ልታየው እንጂ ልታየው አልመጣችም። በዚህ ውበቷ ላይ ኩራት ማከሉ አስፈላጊ መስሎ ስለ ታያት ፊቷን ፈካ ላለማድረግ የቆረጠች ትመስላለች። በዚያ ላይ ደግሞ ከወስጥ ብሶቱ አለ።

«እንሂድ እንጂ!.....» አለችው ቁጣ ባዘለ ድምፅ፤ ዓይኗን ከቦርሳዋ ላይ ሳትነቅል።

በአለቃው እንደታዘዘ ዓይነት ፈጥኖ መኪናውን አስነሳ። መድረሻቸውን ሁለቱም ያውቁታል። መንገድ ላይ ምንም ሳይነጋገሩ የመሄዱን ቀዝቃዛ ጦርነት ግን ወንዳፍራሽ አልወደደውም።...ጸጥታውን መስበሪያ ዘዴ ያገኘ ይመስል፤ የመኪናዋን የውስጥ ኪስ ከፍቶ፤ አንድ የዘፈን ክር ለይቶ አውጥቶ፤ ማጫወቻው ውስጥ ጨመረው።

ወንዳፍራሽን ለማብሸቅ ብላ ዘፈኑን አቋርጣ እሱ የጨመርወን ክር አወጣችና ከቦርሳዋ ውስጥ አንድ የእንግሊዝኛ ክር አውጥታ ማዘፈን ጀመረች። ምንጊዜም አንድ ወይም ሁለት ክሮች ከቦርሳዋ ውስጥ አይጠፉም። ወንዳፍራሽ በልቡ - ይህች እንኳ የፍቅ ነች፣ እያለ በፍጥነት መሾፈሩን ቀጠለ። ግማሽ አይኑና እጁ መኪና መንዳሩ ላይ ስላተኮረ በዘፈን ምርጫ ከእሷ ጋር መሟገት ወይም መታገል አልቻለም።

«......ሳምንት ሙሉ?!.....ሳምንት ሙሉ?!.....»አለች ሮዛ በሙዚቃው ጣልቃ ገብታ፤ ራሷን እየነቀነቀች።

ጥይት ከአንድ በኩል ብቻ ቢተኮስ ጦርነት አይሆንም። ለአንዱ ጥይት ምላሽ መስጠት ሲጀመር ነው ጦርነት የሚሆነው። - ወንዳፍራሽ ጦርነቱን ፈርቶ ጭጭ! ይልቁንም እሷ አከታትላ እንዳትተኩስ በንፋስ ስልክ መንገድ መኪናውን በኃይል እያበረረ በማስደንገጥ አዘናጋት።

«ስርቆት አዳራሽ» ሲደርሱ ዘበኛው ሞቅ ያለ ሰላምታ ሰጥቶ አስገባቸው። መኝታውን ሰለሚያዘወትሩን በደንበነት ያውቃቸዋል። እጃቸውንም ደጋግመው ቀምሷል።

በጓሮ በኩል መኪናዋን ሸጉጠው አቁመው ተላላኪውን ለመጥራት ጥሩንባውን አስጮኹት።

ይህን ለመሰለው ደፈጣ ውጊያ «ስርቆት አዳራሽን» የመሰለ ምቹ ቦታ አይገኝም። ግቢው ከፊቱ ትልቅ የምግብ አዳራሽ ይዞ ከጀርባው በሚከራዩ መኝታ ክፍሎች ተከብቧል። አዳራሹ ማታ ማታ ምግብ ይበላበታል፤ ውስኪ ይጠጣበታል፤ የክራርና የማሲንቆ ዘፈን ይንቆረቆርበታል። ከዚያ በኋላ ፍቅር የሰመረላቸው ጥንዶች በጓሮ ተያይዘው ወደ መኝታ ክፍሎች መንጎድ ነው። በመኝታ ክፍሎቹና በምግብ አዳራሹ መሐል በሐረግ ተከብቦ ሰፊ ዋሻ የመሰለ የመኪና ማቆሚያ አለ። አዳራሹ ወይም ግቢው በውል የሚታወቅበት የተለጠፈ ስም አልነበረውም። በስውር የሚደረገውን የተሟላ መስተንግዶ በመታዘብ ተጠቃሚው ሰው «ስርቆት አዳራሽ» ብሎ ሰየመው። በብዙ ደንበኞች ዘንድ ይህ ስም እየተለመደ መጣ።

«አቤት?......» አለ፤ አንድ አሳልፊ በመኪናው መስኮት በኩል ቀርቦ።

«......ደህና፤ ደህና።......ምነው ጠፋችሁ?»

«እስኪ......የተለመደውን ቶሎ በል። እና ደግሞ.....» ካለ በኋላ ወንዳፍራሽ ወደ ሮዛ ፊቱን አዞሮ «ምግብ ይምጣልን?» ሲል ጠየቃት።

ሮዛ ግንባሯን እንዳኮሳተረች በአሉታ ራሷን ነቀነቀች።

«እሺ እንግዲያው....ሁለት ደብል ዊስኪ አስከትልልን።» አለው።

ጥንድ ህዋ መጥቶ በጓሮ በኩል መኪናውን ለሚያቆም ደንበኛ ብዙ ዝርዝር ጥያቄ አያስፈልግም። ተላላኪው ሮጥ ብሎ ቁልፍ አምጥቶ አንድ ክፍል ከፍቶ አስገባቸው።

ወንዳፍራሽ አልጋው ላይ ዘፍ ሲል፤ ሮዛ ግን የእጅ ቦርሳዋን ድጋፍ ላይ አንጠልጥላ ወንበሩ ላይ ቁጭ አለች። - የአርቅ ኩርፊያዋ ወንዳፍራሽን አላናደደውም። ይብሱ ወብቷ በኩራት በመታጀቡ የፍቅር ጥማት ለቀቀበት።

«......ግማሽ ሰዓት ያህል አኮረፍሺኝ እኮ ሮዚና። አሁን ይብቃሽ......አጥፍቼ ከሆነ እክሳለሁ።» አለና እጇን ጎተቶ አስነሳት።

«እጄን ልቀቀኝ፤ እባክህ። ዱሮም ወንዶች ይሄው ናችሁ።» አለችና፤ አልጋው ላይ ከጎኑ ተቀመተች።

የተቀባችው ሽቶ ልቡን ሰንጥቆ ገብቶ ሰውነቱን - ወጣጠረው።

«ምን አጠፋሁ?....ሮዚና?»

«ሳምንት ሙሉ ዘግተሽኝ ከመረከረምህ ሌላ ምን ትፈልጋለህ?»

«አልተመቸኝም ነበር የሥራ ውጥረት ነበረብኝ.....»

«አሃ! መሥሪያ ቤትህን ማታም ማገልገል ጀምረሃል!......ሕጻን ልጅ አደረግከኝ እንዴ ወንዴ?!»

«ቤቱም ውስጥም ችግር እንደ ተፈጠረ ነገሬሽ ነበር።.....ሰላም የለም።»

የምላስ ወለምታ በቅቤ አይታሽም። ሲሸሽ የቆየውን ጦርነት የሚከፍት ሐረግ ሳያስበው ሰነዘረ። ሮዛም ታጥቃበት የመጣችውን የጦርነት ስሜቷን ለማርካት ተነሳች።

«.....እኮ የችግሩን ምክንያት እኔ ነኝ?......አይደል?! ሰላም ያጣኸው በእኔ ምክንያት ነው!.....ፍቅር እንደጀመርን ምን ትለኝ ታስታውሳለህ?! አታስታውሰውም። አሁን ፍቅርህን ጨርሰኃላ!.....»

«እንደሱ ሳይሆን.....»

«ነው እንጂ!.....ሳምንት ሙሉ.....ሌላው ቢቀር ስልክ መደወል ማንን ገደለ?!....»

የመኘታ ቤታቸውን በር ሲንኳኳ ንግግራቸውን አቋረጠች። አሳላፊው (ተላላኪው) የጠርሙስ ውስኪ ከብርጭቆዎች ጋር በትሪ ይዞ ገብቶ ለሁለቱም ደብል ቀዳላቸው። ወንዳፍራሽ ተላላኪውን ሲያይ፣ ቤቱ ከመቃጠሉ በፊት የእሳት አደጋ መከላከያ እንደደረሰለት ያህል ደስ አለው።

አሳላፊው ስራውን ጨርሶ ሲወጣ ወንዳፍራሽ ተከትሎ በሩን ቆለፈው። .....ምንጊዜም ከሮዛ ጋር ሆኖ በር ሲቆልፍ በደሙ ንዝረት ከፍ ይላል። ልቡ ድው! ድው! ማለት ይጀምራል።

«ቺርስ.....ለፍቅር!» አላት የውኪው ብርጭቆውን ከፍ አድርጎ። ሮዛ ግንባሯን ሳፍፈታ ብርጭቆዋን አጋጨች።

«....እኔ የሚገርመኝ ማፍቀሬ ሐጢያት መሆኑ ነው። ከፍቅር ሌላ ከአንተ የፈለግኩት ነገር አልነበረም። ጌጣጌጥ ግዛልኝ ብዬ አላስቸገርኩህም......ትዳር እንዳለህ እያወቅኩ ነው የወደድኩህ። ለፀባይ ተገዛሁ። ለፍቅርህ ተንበርከኩ። አዎ! ፍቅር ብታሳየኝ ፍቅር ሰጠሁህ እና ይሄ ነው ያስናቀኝ?....»

በእጁ የጨበጠችውን ውስኪ ሳታሰብው ጭልጥ አደርገችው። ወንዳፍራሽም በአነጋገሯ ተመስጦ እሷ እንዳደረገችው ሁሉ ውስኪውን ጅው አድርጎ ጠጣና ብርጭቆውን ጠረጴዛው ላይ ወረወረው።

አነጋገሯ ልቡን ነክቶት ነበር። ሮዛ እንዳለችውም ከፍቅር ሌላ ከእሱ የምትፈልገው ነገር የለም። የምታጌጠው በወላጆቿ ሐብት ነው። የመኪና ዕቃዎች መለዋወጫ የሚሸጡበት ትልቅ ድርጅት አላቸው። ቤት ውስጥ ለአቅመ ሔዋን የደረሰች ሴት እሷ ብቻ በመሆኗ ፍላጎቷን ሁሉ አሟልተው በእንክብካቤ ነው የያዟት። ከዚያም ውጭ እሷም የወንድ ኪስ የማሟጠጥ ዝሙታዊ ጸባይ የለባትም። - ችግሯ ፍቅር ነው፤ የፍቅር ሰው ነች፤ ፍቅር ያጠቃታል። ለፍቅር እንጂ ለጥቅም አትረታም።

ወንዳፍራሽንም ለወሳኔ ያስቸገረችውና በሁለት ሴት መሐል የሚያዋልለው ይኸው ፀባይዋ ነው። ከጥቅም ውጭ የሆነው ፍቅሯ አንጀቱ ውስጥ ገብቷል። - ይወዳታል። ጓዙን ጠቅሎ ከእሷ ጋር እንዳይሆን ሁለት ልጆቹና ሚስት አሉት። ሮዛን እርግፍ አድርጎ እንዳይተው ደግሞ በፍቅሯ ወጥመድ ውስጥ ገብቷል። አንድ ቀን ተኮራርፈው ቢውሉ በሁለተኛው ቀን ይደዋወላሉ። - ሁለቱም አያስችላቸውም። ሳምንት ሙሉ ሲዘጋጉ ይሄ የመጀመሪያ ጊዜያቸው ነው።

«አንድ ነገር ልብሽ ውስጥ እንድትፅፊልኝ እፈልጋለሁ፤ ሮዚና ንቀት የሚባል ነገር በአዕምሮዬ ውስጥ የለም። ፍቅርሽን አከብረዋለሁ። እንደምትወጂኝ እወድሻለሁ። የሰሞኑ መራራቃችን በቤቱ ውስጥ የተፈጠረው ችግር ነፀብራቅ ነው እንጂ የንቀት ወይም የሌላ ጉዳይ አይደለም።......»

«በቤት ውስጥ የሚከሰተውን ችግር ከፈራህ ቀድሞውንስ ከእኔ ጋር መውጣት ለምን ጀመርክ?!.....»

ወንዳፍራሽ ቶሎ አልመለሳላትም። ያላሰበው ጥያቄ ስለሆነ አስደነገጠው። ትንሽ አሰብ አደረገና፤ «....ሲጀመርማ አይታወቅም። ትዳሬንም ያንቺንም ፍቅር እንደ የአመጣጡ አስተናግደዋለሁ የሚል ግምት ነበረኝ። እያደር ችግር ተፈጠረ። ሚስቴ በሕይወቷ ለመጀመሪያ ጊዜ ቁጡና ብስጩ ሆነች። አንቺም በለኢላ ወገን ሆድ ይብስ ጀመር። ለዚህ ሁሉ ምክንያቱ እኔ መሆኔ ተሰማኝ። በአንድ ጊዜ ሁለት ሴት እኩል ማፍቀር ይቻላል ወይ? የሚል ጥያቄ ጭንቅላቴ ላይ ያቃጭል ጀመር።.......» ሲል ሮዛ ከአፉ ላይ አቋረጠችው።

«.....እና አንዱን ፍቅር መተው እንዳለብህ ወሰንክ። ያ ነው ሳምንት ሙሉ ያጠፋህ!.......አይደለም እንዴ?!»

«አይደለም ሮዜና። ለምን ችግሬ አይገባሽም? የውስጥ ስሜቴን ስገልፅልሽ ለምን አትረጂኝም?!......»

ሮዛ አላዳመጠችውም። የፍቅር እልህ እንደያዛት ሁሉ ጉሮሮዋ ላይ የሚተናነቃትን ነገር አሁንም እየዋጠች በሀሳብ ጭው ከአጠገቡ መራቅ ጀመረች። የአሁኑ መነቻቸፍ የጥንቱን የፍቅር አጀማመራቸውን ሁኔታ እያስታወሳት ነበር።

«መጀመሪያ ስንገናኝ የተናገርኳቸው፤ የልቤ ለፍቅር እንድሰጥ የገፋፉኝ ሐረጎች ትዝ ይሉኃል?» አለችው ዓይኖቿን በግማሽ ትሽታ ቡዝዝ እንዳደረገች።

ወንዳፍራሽ አሁን ለፍቅር እንጂ ለትዝታ ጊዜ አልነበረውም። ሆኖም ቡዝዝ ያሉ አይኖቿን ሲከተል እሱም ከትዝታው ፈረስ ላይ መጫኑ አልቀረም። -

ከዘጠኝ ወር በፊት ነበር። ማክሰኞ ከቀትር በኋላ ሠራተኞች ከሥራ በሚወጡበት ሰዓት ኃይለኛ ዝናብ ይዘንባል። ሮዛ በዚያን ሰዓት፤ ቤት ውስት የጦፈ ጦርነት ላይ ነበረች። ዓለማየሁ ግርማ መልከ መልካምነቱ ከገንዘ ጋር ተደምሮ ትዕቢት ቢጤ ያሳደረበት በከተማው አለሁ አለሁ ባይ ቢሆንም ሮዛ ወድዳው ቆይታለች። «ከአንድ ሴት ጋር ከሦስት ሳምንት በላይ አልቆይም» የሚል ንቀታዊ ፈሊጥ ነበረው። ከሮዛ ጋር ግን ሰባት ወር ያህል ወጡ። ወደደችው ለፍቅር የተፈጠረ ሰውነቷ ዓለማየሁን ከነትዕቢቱ ወደደው። ዓለማየሁ እንደ ልማዱ የተወሰነ ጊዜ የፍቅር ኮንትራቱን ጨርሶ ገለል ማለት ሲጀምር ሮዛ የባሰውኑ ትከንፍለት ጀመር። ናቅ እያደረጋት በሄደ ቁጥር ዕልህ የተቀላቀለበት ፍቅር እየወሰደ እሱ ጉያ ስር ያሳድራት ጀመር። ያለ ዕቅድ ከዓለማየሁ ጋር መውጣትና ማደር ማዘውተሯ ያልታሰበ ችግር ፈጠረ። ችግሩን በሆዷ ስታውጠነጥነው ቆይታ በመጨረሻም በዚያ በዝናብ ዕለት ለአለማየሁ አስተዛዝና አማከረችው። -

«ዓሌ፤ ዛሬ የመጣሁት አንድ ነገር ልነግርህ ነው»

»ምን?»

«....ሳይታሰብ የሆነ ነገር ነው።»

«እኮ ምን?»

ልቡን ያለሰለሰች መስሏት አስቀድማ በአይኖቿ አባበለችው። ዓለማየሁ ለእንዲህ ዓይነቱ ጉዳይ እንግዳ ባለመሆኑ የምትነግረውን አስቀድሞ አውቋል።

« ኦ - አረገዝኩ።» አለችው ፊደላቱን በፍርኃት እየቆጠረች።

«አስወጪዋ!» - ድንጋጤም ሆነ ሐዘኔታ ፊቱ ላይ አልታየም። ድምፁ ንቀት አዘል ነበር።

«ምን አልክ?» አለችው ጆሮዋን ማመን አቅቷት።

«አስወጪው!» ጮክ ብሎ ደገመላት።

«ዓይንህ ይውጣ!» ብላ እሷም አፈጠጠችበት። ንቀቱ አንገበገባት። ርህራሄቢስ መሆኑ አብከነከናት። ማስወጣት አዲስ ነገር ሆኖባት ሳይሆን የቃላት አመራርጥና አወራሩ ነበር ያብከነከናት። ግድ የለሽ ሆና ለግድየለሽነቱ ምላሽ መስጠት አልቻለችም። በጥፍሮቿ ብትቧጭረው በጫማዋ ብትቀጠቅጠው በጥርሷ ብትዘለዝለው በወደደች ነበር። የስድብ መዓት ስታወርድበት ከምንም ሳይቆጥራት ዝም ብሎ መፅሔት ማገላበት ቀጠለ።

ሮዛ ከዚያች ደቂቃ በኋል እዚያ ቤት ውስጥ መቆየት አልፈለገችም። ዕልህ ተናንቆአት እየተሳደበች በዚያ በዝናብ ከቤቱ ወጣች። የትዕቢቱ ብዛት ዝናቡ እስኪያባራላት እንኳ እንድትቆይ አልጠየቃትም። - በዝታም አባረራት።

ከዓለማየሁ በፊት የምትወደው አንድ ጓደኛ ነበራት። ድንገተኛ ሞት ነጠቃት። - እና እዚህ ትዕቢተኛ ላይ ጣላት። የዓለማየሁ ንቀትና ትዕቢት ሮዛ ወንዶችን ሁሉ እንድትጠላና እንድትበቀል ጋበዛት። ዝናቡ በላይዋ ላይ ሲወርድ ታክሲ እየጠበቀች የምታስበው ከዚያ ሰዓት ጀምሮ በወንዶች ለመቀለድ ለማላገጥ ለመጫወት ነበር። በወንዶች ስሜት ለመጫወት በቂ መልክና ቁመና እንዳላት ታውቃለች።......ይህን በመሰለው ውስጥ ስለሰመጠች ላይዋ ላይዋ ላይ የሚወርደው ዝናብ ምንም አልተሰማት።

አንድ ብጫ ፊያት 124 እየከነፍፈች ስትመጣ ሮዛ በድፍረት እጇን አውለብልባ አስቆመቻት። እንኳንስ ሴት ወንድም ቢሆን እዚያ ዝናብ ላይ ቆይሞ

እያየ የሚያልፍ ልብ ጨካኝ ነው። ከሥራ ወጥቶ ወደ ቤቱ የሚበርረው ባለ መኪና አቁሞ በሩን ከፈተላት። ያ ሰው ወንዳፍራሽ በቀለ ነበር።

ሮዛ «አመሰግናለሁ።» እንኳ ሳትል መኪናው ውስጥ ገብታ ተቀመጠች። ወንዳፍራሽን ርዳታ ከምንም ባለመቁጠር ወንዶችን ለመበቀል የመጀመሪያ ኢላማዋ እንደሆነ አድርጋ ገመተችው። ወንዳፍራሽ ሁኔታዋ ገርሞት መኪናዋን ካስነሳ በኋላ ሁሉ ሰረቅ እያደረገ ያያት ጀመር። - ሹፌሩን ያስቆመ አለቃ እንኳ ፊቱን ፈገግ ያደርጋል። ሮዛ ወይ ፍንክች!.....ሹፌሩን ያስቆመ አለቃ እንኳ ፊቱን ፈገግ ያደርጋል። ሮዛ ወይ ፍንክች!.... ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት እንባ በማዝነብ የቀሉ ዓይኖቿን አይቶ አንድ ችግር እንደደረሰባት ተረዳ።

«......ምነው ዝናብ እንዲህ እስኪመታሽ ድረስ?.....ማለቴ፤ ምን ችግር ገጥሞሽ ነው?» አላት በሐዘኔታ ድምፅ።

«እሱ የግል ጉዳዬ ነው። ሰልትህታንህ አመሰግናለሁ።» አለችው ግንባሯን እንዳጨማደደች።

ወንዳፍራሽ በመልሷ አልተናደደም። ይልቁንም እሷ እጅግ የተጎዳችበት ነገር መኖሩን ገምቶ በልቡ አዘነላት። በስርቆሽም ቢሆን ቁንጅናዋን ተመለከተ። በእንባዋ ቅሪት የዳመነው ፊቷ የረጠበ አበባ አስመስሏታል። ወንዴ በሰብዓዊ ርህራሄው ውጽጥ ተባዕታዊ ስሜት ሲያንሰራራ ተሰማው። ሐዘኔታው መውድድ የተቀላቀለበት አንድ አስቸጋሪ ስሜት ድንገት ሰውነቱን ወረረው። እንደ ምንም አዋርቶ ችግሯን መካፈል ፈለገ። ነገር ግን ሮዛ ለአፍራሽ መልስ ታጥቆ በመነሳቷ ሁኔታዋ ለውይይት አልጋበዘውም።

መንገድ እየመራችው ቤቷ በር አጠገብ ካደረሳት በኋላ በብጫቂ ወረቀት የቢሮውን ስልክ ቁጥር ፅፎ ሰጥትና፤ «ፈቅድሽ ከሆነ ደውይልኝ። በችግር ላይ መወያየት መጥፎ አይደለም። ሕይወት ረዥምና ባለብዙ አቅጣቻ ነው። በአንድ መንገድ ተመልክተሽው ተስፋ አትቁረጪ። ወጣት ነሽ ቆንጆ ነሽ፤ - ብሩህ ተስፋ ሊታይሽ ይገባል።» አላት።

መልስ ሳትሰጠው መኪናውን ወርዳ ወደ ግቢዋ ገባች።

ለሦስት ቀናት ያህል አልደወለችለትም፥ አላገኘችውም። ከመኪናው ስትወርድ የወረወራቸው የማስተዛዘኛ ውብ ቃላቶች በየደቂቃው አዕምሮዋ ውስጥ ቢያቃጭልም በመጥፎ ሰዓት ስላገኘችው ልቧን ሰጥታ ልትጠጋው አልፈለገችም። በሌላ በኩል ደግሞ እንድትደውልለት የሚገፋፋት ነገር ነበር። ከዓለማየሁ ለመለያየት ስልቆረጠች፤ እሱን የሚያስረሳት ወይም ለብስጭቷ ሽፋን የሚሆናት አንድ የምትቀልድበት ወንድ አስፈለጋት። ባዶ ቤት ውስጥ ትራስ አቅፋ እያለቀሰች መዋሏ፤ ወይም የአፍላ ፍቅር ትዝታን የሚቀሰቅስ ዘፈን እያዳመጠች ማላዘኗ ሰለቻት።

ከአራት ቀናት በኋላ ግልፍ ብሎአት ለወንዳፍራሽ ደወለችለት። አሁንም ተገናኝተው በጥሩ ስሜትና በሩህሩህነት አስተናገዳት። ቅዳሜ ማታ በመኪናው እንዲያዞራት ጠየቀችው። በጥያቄዋ መሠረት በቦሌ መንገድ የሚገኙ መዝናኛዎች አንድ ሳይቀሩ አንሽረሸራት። - ፍላሚንጎ ችቦ ‹ቶከ አፍ ዘ ታውን› እና ፒኮክ ካፌቴሪያ በር ላይ እየወሰደች ስትገትረው ወንዳፍራሽ ሚስጥሩ አልገባውም። ሮዛ ግን የመዝናናት ሳይሆን የበቀል ዓላማ በልቧ ቋጥራ የምታንከራትተው። ዓለማየሁ በነዚህ መዝናኛዎች አካቢቢ ስለማይጠፋ ወንዳፍራሽን የተጠቀመችበት እንደ ማስቀኛ መሣሪያ ነበር። ዓለማየሁን የመሠለ የከተማው አለሌ ግን እንኳንስ ቀንቶ ሊከተላት ይባስ ብሎ ሶስት ሴቶች እየጫነ ያሳያት ጀመር። - ተማርራ ተወችው።

አጋጣሚው እያደር ከወንዳፍራሽ ጋር አስተሳሰራት። ከቀን ወደ ቀን አኳኋኑን ስታየው የበቀል ኢላማዋ ማድረግ ሕሊናዋን ከበዳት። ትህትናውና የዋህነቱ እንዲሁም ሐዘኔታ የተሞላበት መስተንግዶው ልቡና አራራው። ብቀላም ቢሆን የተፈጥሮ ጭካኔን ይጠይቃል። ሮዛን ዓይነት ለፍቅር የተፈጠረ ሰው በአንዴ ራሱን መለወጥ አይችልም።

ወንዶችን ልትበቀልበት ያሰበችው ሰው በአጭር ቀናት ውስጥ ትወደው ጀመር። ወንዳፍራሽም መጀመሪያ ቀን ሲያገኛት የገጠማት ችግር ምን እንደሆነ ለማወቅ ጉጉ ነበር። አንድ ቀን የዓለማየሁን ትዕቢትና በዚያ በዝናብ ከቤቱ ያስወጣትን ሁኔታ ስቅስቅ ብላ እያለቀሰች ነገረችው። በማስወረድና በመውለድ መሐል እየዋዠቀች በፍርሃት እየተጨነቀች ፅንሱ ማሕፀኗ ውስት መቆየቱን ሲሰማ ወንዳፍራሽ ይበልጥ አዘነ። - ሁለት ወር ሊሞላው ምንም ያህል አልቀረው ነበር።

ወላጆቿ የሷን ልጅ ተንከባክበው ማሳደግ ባያቅታቸውም አባት የሌለው ልጅ መውለድ እንደማትፈግል ግልፅ አድርጋ ነገረችው።

«......ችግርሽ ችግሬ ነው። እኔ የሁለት ልጆች አባትና ባለ ትዳር ነኝ። ነገር ግን ይህ ሁኔታ አንቺን ከመርዳት አያግደኝም። ብዙ ሳይዘገይና ለህይወትሽ ሳያሰጋ ማስወረድ የምትችይበትን መንገድ እንፈልጋለን።» አላት ከልብ በመነጨ ስሜት።

አነጋገሩ አንጀቷን በላው። ያስረገዛት በትዕቢት «አስውርጂው!» ያላትን አስታውሳ፣ ለብቀላ ኢላማ ያስበችው ወንድ ከሚያደርግው እንክብካቤ ጋር በማነጻጸር ወንዳፍራሽን ወደደችው። በዚያ ጊዜ የተናገራቸው ሐረጎች ናቸው የፍቅ መሠረት ሆነው እስካሁን አዕምሮዋ ውስጥ የቆዩት።

ሐኪሞች አማክሮላት ሆስፒታል ውስት በሰላም ፅንሷን አስወረደች። እስከዚያ ጊዜ ድረስ ወንዳፍራሽና ሮዛ ግብረ ሥጋ ግንኙነት አልፈጸሙም ነበር። የኋላ ኋላ ግን ግንኙነታቸው ሲጠነክር ተከታዩ ጥያቄ አስከተለ። ወደ «ስርቆሽ አዳራሽ» ማረፊያ ጎራ ማለት ጀመሩ። በስርቆሽ የጀመሩት ድርጊት እስካሁን ካሉበት ደረጃ ያደርስናል ብለው አልገመቱም ነበር። እንዲያውም የወንዳፍራሽ ባለ ትዳር መሆን ከሮዛ ጋር የጀመሩትን የፍቅር ገደብ ያበጅለታል የሚል ዕምነት ነበራቸው። - ነገር ግን እንዳሰቡት ወይም እንደ ጀመሩት አልሆነም። ፍቅር የራሱ በሆነ ረቂቅ ጥበብ የማይነቀል ውስብስብ ስሩን ተከለ። ወንዳፍራሽ ከትዳሩ ጋር እየተጋጨበት ግንኙእንቱን ማቋረጥ ሲያስብ ሮዛ «.......ራሴን እሰቅላለሁ» እያለች ታስፈራራው ጀመር። ለማስፈራራት ያህል ብቻ ሳይሆን በእርግጥም ፍቅሩ አውሮአት ነበር። እሱም በሀሳብ ከመዋለል በስተቀር ቆረጥ አድርጎ መተው አልቻለም። እንዲሁ እንዲሁ ሲሉ ይሄው ዘጠኝ ወር አለፋቸው። - ግንኙነታቸው ወንዳፍራሽ ቤት ውስጥ ገብቶ ምሶሶውን ይነቀንቅ ጀመር።

«......ያለፈውን እንርሳው አባክሽ። ፍቅር አጠገባችን አስቀምጠን ለምን በትዝታ ጊዜያችንን እናጠፋለን?!.....» አላት ወንዳፍራሽ ስሜቷን ወደአሁን ለመመለስ በሚጥር አነጋገር።

ነገር ግን ሮዛ ጠልቃ ከገባችበት የትዝታ ባህር በቀላሉ ልትወጣለት አልቻለችም። - አስተያየቷ ይናገራል።

«....ከሚስቴ ጋር ተኳርፈን መኝጣ ከለየን ሰንበት ብለናል እኮ!» አለና እሷን ጉተት አድርጎ አጵጠግቶ ጉንጯ ላይ ሳማት።

ይሂኔ ነቃች። ሰውነቷ ሁሉ ጆሮ ሆነ። - እውነት ከፅጌረዳ ጋር በመኝታ አለያይቼው ከሆነማ መታደል ነው፤ አለች በልቧ። አልጋ ከለያዩ ምን ያደርጉ አብረው ይኖራሉ?....የኔ የግሌ የሚሆንበት ጊዜ ሩቅ አይደለም ማለት ነው።.....

«እውነትህን ነው አንዴ?»

«ሙች እውነቴን ነው።»

«በቃ....ብቻችህን ነው የምትተኛው?»

«ሮዛ ሙች ስልሽ!....ከሳምንት በላይ ሆኖናል።»

ሮዛ ከንፈር ቀለሟን ወደ ውስጥ መምጠጥ ጀመረች። ከንፈሯን እየመጠጠች ሽፋሽፍቶቿን የምታርገበግበው በምን ሰዓት እንደሆነ ወንዳፍራሽ ያውቃል። ቀለሟን መጥጣ ጨርሳ ከንፈሯን መንከስ ስትጀምር የእሱም የደም ስሮች ስሜቷን ተከትለው ማባበጥ ይጀምራሉ።

ደገመና ሳምት።

ፂሙ ስለኮሰኮሳት ለጥቂት ሴኮንዶች ቀና ብላ አስተዋለችውና፣ «የኮሌጅ ተማሪዎች ዊዝድሮዋል ለመጠየቅ ሲሄዱ እንዴት እንደሚያደርጉ ታውቃለህ?» አለችው።

«እንዴት ነው?» አላት በግማሽ ስሜት።

«ከራሳቸውን ጣል አድርጎ፤ ህመምተኛ ወይም በህይወት ተስፋ የቆረጡ መስለው ነው የሚቀርቡት።»

«ለምን?»

«ለምን እንደሆነ መች አጣኸው! ‹ዊዝድሮዋሉ› እንዲ ፈቀድላቸው ነዋ!»

ተኩሱ ወደ እሱ መሆኑ ገባው። ጦርነቱ እንደገና እንዳይጀመር ፈርቶ፤ አንገቷን ጭምቅ አድርጎ አቅፎ፤ ፊቷን ደረቱ ላይ አሸው።

ቀና ስትል ቆዩ ፊቷ ይብስ ቀልቶ የበሰለ ቲማቲም መስሏል። እና ሽፋሽፍቶቿ የመርገብገብ ስልታቸውን ጨምረዋል። የወንዳፍራሽም ልብ የስሜት ከበሮውን ሲደልቅ ቤት የሚነቀንቅ ይመስል ነበር።

ጫማና ልብስ የማውለቁ ረዥም ሥራ ቢያስጠላቸውም አልቀረላቸውም። የጫማ ማሰሪያው ቶሎ አልፈታ ብሎ ወንዳፍራሽ ስላናደደው በጥሶ ጣለው። ሮዛ ከቤትዋ ስትወጣ በጥንቃቄ የለበሰችውን ልብስና ያጠለቀችውን ጌጣጌጥ አሁን እንደዋዛ ከላይዋ ላይ ገሽላልጣ ጣለችው።

አንሶላ ውስጥ ለመግባት ፋታ አላገኙም።.....

«......ምን ዓይነቱ የዋህ ሰው ናቸው በናትሽ?!..... አድራጎታቸው ሁሉ ይገርማል እኮ።»

ትውሲት ሰኞ ጠዋት ወደ ቢሮዋ ስትገባ ይሕን መሳይ የንግግር መክፈቻ አስቀድማ ነበር። በእጇ የተጠቀለለ ነገር ይዛለች። ግማሽ ሰዓት ያህል አሳልፋ ወደ ቢሮ ስትገባ፤ ፅጌረዳ ልትጠይቃት ያሰበችውን ከባድ ጉዳይ ስላላት፤ ውጭ ውጭውን ስታይ ነበር የቆየቻት።

«ማን?.......ምን?» አለቻት ፅጌረዳ ድንግርግር ብሎአት።

«እንደምን አደርሽ ፅግዬ፤ የኔ ነገር! ከሰላምታ በፊት ወደዝርዝር ጉዳይ ገባሁ። ....ገርሞኝ እኮ ነው።» አለችና የያዘችውን ዕቃው ወደ ግራ እጇ ዞራ ፅጌረዳን ጨበጠቻት።

«ምንድን ነው» አለች ፅጌረዳ እንደገና።

«የአቶ ክብረት ነገር ነዋ! በእሳቸው ቢሮ በኩል ነበር የመጣሁት። የየዋህነታቸው ብዛት ስጦታ ውሰጅጂልኝ ብለው ላኩኝ።»

«ለማን?.....»

«ለአንቺ ነዋ! የሚገርምሽ ደግሞ፤ ቀላል ሥጦታ መሰለሽ እንዴ?!.....አርቲፊሻልም ቢሆን ውድ ዕቃ'ኮ ነው።» አለቻትና መጠቅለያውን ፈትታ የተላከላትን የእጅ አምባር አሳየቻት።

እኚህ ሰውዬ አልለቀቁኝም ማለት ነው! አለች ፅጌረዳ በልቧ። በትውሲት በኩል በየዕለቱ ሰላምታ ሳይደርሳት ቀርቶ አያውቅም። ግቢ ውስጥ በርቀት እንኳ ሲያይዋት ፈገግ በልው ሰላምታ ያልፋሉ። በስርቆት ቁመናዋን እየቃኙ ምራቃቸውን ይውጣሉ። ፅጌረዳ ሌላው ቢቀር የባሏን ዕልህ ለመወጣት ያህል ከአቶ ክብረት ጋር መውጣት ብታስብም ይሉኝታ ጨምድዶ ይዞአታል። የዕድሚያቸው ጠና ከማለቱ ሌላ የመሥሪያ ቤቷ ባልደረባ በመሆናቸው ድርጊቱ አሳፋሪ ሆኖ እየተሰማት በማመንታት ቆየች። ከባል ሌላ ወንድ የማውጣቱ አዲስ ሀሳብም ከህሳብነቱ አልፎ፤ በተግባር የመዋሉን ነገር ከወዲሁ ስታስበው ይዘገንናታል።

ትውሲት ግን በመሐል ቤት ትንፋሽ አጣች። በየቀኑ ተስፋ ተሸከማላቸው ስለምትሄድ አቶ ክብረት እሱና ባዩ ቁጥር ፅጌረዳን እንዳገኙ ያህል ይደስታሉ። እሷ ስለ ፅጌረዳ መሳላል ስትሆናቸው እሳቸው ደግሞ ለእሷ የሥራ ዕድገት መሰላል እንደሚሆኗት ቃል ገብተውላታል። የጐልቱ ስውር ውል ማንም አያውቅም። ትውሲት ተልዕኮዋን አሟልታ ውሉ ከተፈጸመላት በአንድ ጊዜ የመቶ ሃያ ብር ዕድገት ታገኛለች። አቶ ክብረት ይህን ማስደረግ እንደሚችሉም ታውቃለች። አቶ ክብረት ለቦታው እንዳጯት ታውቃለች። በተዘዋዋሪ መንገድ ለቦታው እንዳጯት ነግረዋታል። አሁን ቶሎ አልወጣ ብላ እንቅፋት የሆነችባት ፅጌረዳ ናት።.....

ፅጌረዳ የተላከላትን አምባር በመቀበልና ባለ መቀበል ሀሳብ ውስጥ ገብታ ስትዋልል ቆየች። አምባሩን መቀበሉ ለማንኛውም ጉዳይ እጅ የመስጠት ያህል ሆኖ ተሰማት። እምቢ ማለቱ ደግሞ ከትውሲት ጋር የሚያቃርናት መስሎ ታያት። - ብቸኛ የመረጃ ምንጯ በመሆኗ በአሁኑ ሰዓት ከትውሲት ጋር መጋጨቱን አልፈለገችም።

እያመነታች አምባሩን ተቀብላ አገላብጣ ተመለከተች። አርቲፊሻል ጌጥ ነው። ከብርና ማዕረግ የለውም።.....

«እንግዲህ ምስጋናዬ በአንቺው በኩል ይድረስልኝ። ጌጡም ለጊዜው አንቺው ጋር ይቀመጥልኝ።.....» አለችና አምባሩን ለመመለስ እጇን ዘረጋች።

«እንዴዬ!......እጅሽ ላይ አድርጊው እንጂ!» አለቻት ትውሲትም፤ ኮስተር ብላ።

«አሁን አላደርገውም። ሌላ ጊዜ ከአበሻ ቀሚስ ጋር ይሻላል።» ብላ ነገሩን አሳጠረችው።

የሰጠቻት መልስ ለማስገደድ ስላልተመቻት፤ ትውሲት አምባሩን ተቀብላ ኮመዲናዋ ውስጥ ከጨመረችው በኋላ በረዥሙ ተንፍሳ ተቀመጠች። ከቅዳሜ የዞረ ያልተጠናቀቀ ሥራ ጠረጴዛዋ ላይ ተከምሮ ስታይ ደበራት። ሰሞኑን የዕድገት ቦታዋን በማለም ላይ ስለሆነች ታይፕ መቀጥቀጡ ሰልችቷታል። - እጅ - እጅ ብሎአታል።

«አንድ ነገር ልጠይቅሽ አስቤ ነበር እኮ፤ ትውሲትዬ.....»

ፅጌረዳ ሁለት ቀንና ሁለት ሌሊት ሲያሳስባት የቆየውን ጉዳይ ለመተንፈስ ዳር - ዳር ማለት ጀመረች። ትውሲትም ጆሮዋን አቆመች።

«ምን?.....ፅግዬ።»

«....ሌላም ነገር ሲወራበት ሰማሁ። ግልፅም ባይሆን በተዘዋዋሪ ጆሮዬ ውስጥ ሽው አለ።»

«ማን ነው?»

«እሱ ነዋ!» አለች ፅጌረዳ አሁንም ይወንዳፍራሽን ስም መጥራት አስጠልቷት። ስለማን ማውራት እንደፈለገች የተጨማደደው ፊቷን ይገልፅ ነበር።

«ደሞ ምን ሰማሽ?!... አይ ወንዶች! መቼም ጉዳያቸው አያልቅ።» - ትውሲትም፤ የጨዋታው ርዕስ ወንዳፍራሽ መሆኑን ስታውቅ፤ ስሜቷ ናረ።

«ለዚያች ለሮዛ ሳይወልድላት ወይም ሳያስረግዛት አይቀርም።.....»

«......ልጅ?!......ዲቃላ?!....»ስትል ትውስት ማጋነኗን ቀጠለች።

«ነገሩን እርግጠኛ አይደለሁም። እንዳልኩሽ በቀጣ አልሰማሁትም። .....ምናልባት አንቺም የሰማሽው ነገር ኖሮ ደብቀሺኝ እንደሆነ.....»

«ፅግዬ ሙች፤ ስለዚህ ጉዳይ የሰማሁት ነገር አልነበረም። ይልቅ አሁን ፍንጭ ከሰጠሽኝ ስራዬ ብዬ አጠያይቃለሁ።»

ግድ የለሽም! በኔ ጣይው። እውነት ይህን ያህል ድፍረት ፈፅሞብሽ ከሆነማ ጉድ ነው። ይህችን ሚስጥር ካላገኘኋት ደግሞ እኔ ትውስቲ አይደለሁም!.......ቆይ እስቲ.....» አለችና፤ ቅንድቧን ሰብሰብ አድርጋ እንዳየች ነገር እንደምታስብ ዓይነት ጣራ ጣራውን ስታይ ከቆየች በኋላ፤ «አዎ የገቡበት ጉድጓድ ገብቼ ይህችን ሚስጥር አገኛታለሁ። ትክክለኛ መረጃ ሊሰጡኝ የሚችሉ ሰዎች ይኖራሉ።» አለቻት።

«.......እንዲያው ትልቅ ውለታ እንደሰራሽልኝ ነው የምቆጥረው።» አለች ፅጌረም፣ ጉጉቷ ገጿ ላይ እየተነበበ።

«ጥፋተኛው እኮ አንቺው ነሽ ፅግዬ። ባልሽ ይህን ያህል በደል እንዲፈፅም የሚገፋፋው ያንቺ ትዕግሥትና የዋህነት ነው። ወንዶች እሹሩሩ ሲሏቸው አይወዱም። በቂ ሥራና ደመወዝ አለሽ፣ ራስሺን ማስተዳደር ትችያለሽ። ቆንጆ መልክ አለሽ - ከፈልግሽው ሰው ጋር መውጣት ትችያለሽ። አቶ ባል ግን ትዕግሥት ስታሳይው ይህን ሁሉ ማድረግ ያቃተሽ ይመስለዋል። ይንቅሻል። ቁንጅናሽ ሁሉ አይታየውም። ከሌላ ወንድ ጋር መውጣት ስትጀምሪ ነው እንደገና ዓይኑን ገልጦ ቁንጅናሽን የሚያየው። አትሞኝ ፅግዬ። - ወንድን በወንድ ነው። እንኳን አንቺን የመሰለች ሴት ቀርቶ ስንቷ ጎማዳ ተዓምር ትሰራለች።»

«አሁን ያወራነው ጉዳይ እውነት ከሆነ መቼ....»

«እሱን ግድ የለሽም። እኔ አጣራዋለሁ ብዬሻለሁ። አንቺም የኝህን የሰውዬ ነገር አንድ በያቸው። ስለ እውነት፤ እኔ አሳዘኑኝ።»

ሳይሰጡ ማግኘት የለም። የምትፈልገውን መረጃ ለማግኘት ስትል ለምትፈልግበት ጉዳይ ራሷን ማቅረብ እንዳለባት ፅጌረዳ ገባት። ሆኖም ሀሳቡ አልዋጥልሽ ስላላት ከውነታው ለመራው ያህ ዓይኖቿን ለአፍታ ጨፈነቻቸው።

ደጀኔ እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ ቤቱ ውስጥ ሲጠብቃት፤ ትውስቲ ሀገር ሰላም ነው ብላ እንደወትሮዋ በፈገግታ እየተውረገረች ገባች። ምን ጊዜም ደጀኔ ቤት ስትመጣ በር ሳታንኳኳ ዘይ ማለት ይቀናታል። «ለምን በር አታንኳኪም?» ብሎ

ሲጠይቃት «እጅ ከፍንጅ በድንገት ልይዝህ ነዋ!» ትለዋለች። - ፍቅረኞች የሚያደርጉትን ለማስመሰል ካልሆነ በቀር፤ ደጀኔ ከእሷ ሌላ ሴት እንደማይሄድ ታውቃለች።

ዛሬ ግን ለዚህ ሁሉ ቀልድ አልተመቻትም። ቤቱ ውስጥ ከገባች በኋላ ስትጨብጠው ሁሉ ደጀኔ ፊቱን ጭፍግግ እንዳደረገ ነበር።

«ምን ትኮሳተርብኛለህ?......በደንብ ሰላም አትለኝም እንዴ?» አለችው፤ እሷም ግብሯን አኮሳትራ።

«እስቲ መጀመሪያ ቁጭ በይ!.....»

የቁጣው መንሥኤ ምን እንደሆነ ለመጠርጠር ብዙ ጊዜ አልወሰደባትም። ቀን ቢሮዋ ስልክ ደውሎ ከሥራ መልስ ቤቱ ድረስ እንድትመጣ ሲነግራት ድምጹ ሻክሮ እንደ ነበር አስታወሰች። እናም ቁጣው ከመሥሪያ ቤታቸው ጋር የተያያዘ ጉዳይ እንዳዘለ ገባት። - ዘገየ ድንገት ከህሳቧ ውስጥ ብልጭ አለባት።

ምንም ሆነ ምን፤ የደጀኔ ቁጣ ኮስተር ብሎ መጋፈጡ ጥፋቷን የሚሸፍንላት መስሎ ታያት። መቅለስለስ ወይም የልመና ገፅታ ማሳየት አንዳንዴ የዕውነትን መንገድ በርግዶ መድፈት መሆኑን ታውቃለች። - ለቁጣው እሷ ከእሱ ብሳ ቁጭ አለች -

«ኧረ አልቀመጥም!.....ምን ‹ቦጣኝ!.....ሰተት ብዬ ቤትህ ድረስ ስለመጣሁ ነው እንዴ ተኮሳትረህ የጠበቅከኝ?!.....ተመልሼ እሄድልሃለሁ!»

«አርፈሽ ቁጭ በይ ብዬሻለሁ። ኋላ ጉድ እንዳይፈላ!»

«እሺ ምን አድርጊ ነው የምትለኝ?»

የእጅ ቦርዋዋን ጠረጴዛው ላይ አስቀምጣ በግማሽ ጎኗ አንዱ ወንበር ላይ ተቀመጠች።

«እኔ እዚያ መሥሪያ ቤት ውስጥ ማንንም እንደማልፈራ ታውቂያለሽ ወይስ አታውቂም?!»

«አንድዬ!....ምንድ'ን ነው የምታወራው ደጀኔ?»

«አቶ ክብረት ቢሮ የሚያመላልስሽ ጉዳይ ምንድን ነው?!......»

የአቶ ክብረትን ስም ሲተራ ምናባዊ ጣውንቱ ከአጠገቡ የቆሙ ይመስል የደም ስሮቹ ተግተርትረው ጥርሶቹን አንቀጫቀጨ።

«መቸ ነው የተመላለስኩት?»

«ብዙ ጊዜ ነዋ! መጀመሪያ ወሬውን ከሰዎች ሰማሁ። በኋላ ለማረጋገጥ እኔው ራሴ በስውር ተከታትዬ ደረስኩበት። ከነምልክቱ ከአቶ ክብረት ቢሮ የሆነ ዕቃ በእጅሽ ይዘሽ ስትወጪ በአይኔ ተመለከቼሻለሁ።»

«ታዲያ ሰው አንድ መሥሪያ ቤት ሆኖ በሥራ ጉዳይ አይገናኝም እንዴ?!» አለችው፤ ግንባሯን ሳትፈታ።

«አለቃሽ ሌላ ሰው!....እሳቸው ጋ ምን ታደርጊያለሽ?!» ካለ በኋላ በድንገት ግልፍ ብሎት አንቱታውንም ተወውና «እሱ ሰውዬ ደሞ ቅሌታም ሸማግሌ መሆኑን ከብዙ ምንጮች ሰምቻለሁ። እኔ ደጀኔ ደግሞ እዚያ ግቢ ውስጥ አንዳቸውንም አልፈራም።» አላት እልሁ እንደ ሕፃን ልጅ እንነዘት አድርጎት።

«አበስኩ ገብርኩ እቴ! እነኢ እንደው የዕድሌ ነገር ይገርመኛል። ያገኘኝ ወንድ ሁሉ ለምን እንደሚቀናብኝ አይገባኝም። እስካሁን በቅናት ጦፎ የማይከታተለኝ አንድም ወንድ አላጋመኝም። አሁን እኔን በአቶ ክብረት ትጠረጥረኛለህ?! እንዲህ ሌባና ፖሊስ መሆን አያዋጣም፤ ደጀኔ። ይልቅስ በፍቅር ተማምነን ብንቆይ ይሻላል። ካለበለዚያ እኔ ሁለተኛ በራፍህ ላይ አልደርስም።.......አሁንም ቅሌታሟ እኔው ነኝ። በቀጠርከኝ ቁጥር ቤትህ ድረስ ሰተት ብዬ እመጣልሃለሁ። አንተ ምን ታደርግ?!......»

ድንገት ምርር እንዳላት ዓይነት ከተቀመጠችበት ብድግ ብላ፣ ቀሚሷን እየነሰነሰች ከቤቱ ለመውጣት ቦርሳዋን ስታነሳ፤ ደጀኔ የሰነዘረው ካልቾ ዳሌዋ ላይ አረፈ።

«ውይ! ምነው ደጄ?›.....»

ያነሳችው ቦርሳ ተመልሶ ወደቀ። የተመታችበን ቦታ ቀሚሷን ገለጥ አድርጋ እያሻሸች መነፋነፍ ቀጠለች -

«....ምን አረግኩህ እብናትህ?!....ትማስ ወርቄን እግዜር እኮ ነው ያወጣኝ!....»

«ቁጭ በይ ብዬሻለሁ!....ዛሬ እውነቱን ሳትናገሪ ከዚህ ቤት አትወጪም።»

«የምን ዕውነት?!......»

«ከአቶ ክብረት ጋር መውጣትሽን?» እያለ በማስፈራራት ተጠጋት። የቅናት ስሜቱ ከፍ እያለ መሄዱ ከመላ አድራጎቱ ይነበብ ነበር። ዓይኑን አፍጥጦባት ጥርሶቹን እያንቀጫቀጨ ተናካሽ አውሬ መስሏል።

ትውሲት የተጠረጠረችበትን ነገር ባትፈፅምም ማስቀናቱ የደስደስ ሰጣት። የደጀኔ ሰውነት በቅናት ተወጣጥሮ ስታይ መንፈሷ ርካታ አገኘ።

«....የምነግርህን አታምነኝም ማለት ነው?!.....ነግሬሃለሁ ደጀኔ ጫፌን እንዳትነካኝ.....ነግሬሃለሁ!.....ነግሬሃለሁ.....»

ልትሸሸው ልቻለችም፤ ወይም አልፈልገችም። በቃሪያ ጥፊ ሲያቃጥላት ለአንዳፍታ ጭውው! አለባት። ከዚያ በኋላ ጥፊው የፍቅር ስሜቷን እንደቀሰቀሰው ዓይነት ሁለት እጁቿን ዘርግታ ደጀኔ አንገት ላይ ጥምጥም አለች።

«.....ሚስጥሩ እነግርሃለሁ፤ በቃ።»

አንገቱና ጉንጩን እየሳመች፤ ደረቱ ላይ ፊቷን እያሸች በሽቶዋ በዓዛ እየገፈተረች ወደ አልጋው ስትወስደው፤ የደጀኔ ስሜት እሳታዊ አቅጣጫውን ለወጠ።

«እሺ፤ በይ ንገሪኝ።» አላት ወኔውን ባሚጠጠ ድምፅ

«ሳመኝና?.....»

ሁኔታዋ አስገረመው። የፍቅር ስሜቷ ከዱላ ጋር የተቆራኘበት ምክንያት ምን እንደሆነ ለማወቅ አልቻለም። አዲስ ሳይሆን ደጋግሞ የሞከረው ነገር ነበር። ፀባይዋ ሲቅበጠበጥ ስታኮርፍ ወይም ስትሽኮረመም ከዱላ በስተቀር መድኃኒት የላትም። - አባብላለሁ ማለት ኩርፊያውን ማባባስ ነው። እጁ የሚሳሳና እንደ ፍቅረኛ ዓመታት ለኮፍ የሚያደርግ ወዳጅም አትወድም። እጁን ጠምዘዝ አድርጎ ጠቀም ያለ ዱላ የሚሰነዝር ግን አንጀቷ ይደርሳል።

የዱላ ሱስ አለባት እንጂ? እያለ ደጀኔ በሀሳብ ብዙ ዋተተ። ሳትነግረው ቀርታ ነው እንጂ፤ የአፍሪቃን ዱላ ምንነት የተማረችው ከሴት አያቷ ነው። የሚያፈቅራት ወንድ እጅ ባረፈባት ቁጥር፤ ሴት አያቷ ጥጥ መሳይ ፀጉራቸውን አጎፍረው ሀሳብዋ ውስጥ ብቅ ይላሉ። እናም ደግሞ ንግግራቸው አዕምሮዋ ውስጥ ያቃጭላል። -

ሁልት ባሎች ነበሩኝ ነፍሳቸውን ይማርና። የመጀመሪያው ባሌ እንኮኮ ተሸከሙኝ እንኳ ብላቸው አንገታቸውን የማያዞሩ መሬት ነበሩ። እጃቸውን ሊዘነዝሩብኝ ቀርቶ ግንባራቸውን አከፍትውብኝ እንኳ አያውቁም። ታዲያ ወንድሜ እንጂ ባሌ አይመስሉኝም ነበር። በጾታ ፍቅር ብዙም አልወደድኳቸውም። አፈሩን ገላባ ያድርግላቸውና፤ እሳቸው ሲሞቱ ሁለተኛ ባሌን አገባሁ። - አቤት ኃይለኝነት! አቤት ቅናት! ማንም ጋ የለም እኮ! ሁለተኛው ባሌን?! እንዲያው ጭኔ ስር ይገቡና ልቤ እስኪጣፋ በቁንጥጫ ልምዝግ ያረጉኛል በሉ ሲላቸው ቀጭን ልምጭ ይቀጥፉና ላዩ ላይ ይጨርሱታል። አንድ ቀን የወጥ ማማሰያዬን ከእጄ ቀምተው ጀርባዬ ላይ ሲያሳርፉት ለሁለት ክፍል! ያለው ነገር እስካሁን አይረሳኝም። ደሞ ደብድበውኝ ማልቀሴን ካላረጋገጡ በስተቀር አይለቁኝም ማልቀሲን ያረጋግጣሉ። ታዲያ ለጊዜው አለቅሳለሁ እንጂ ሁለተኛ ባሌን ባጣም ነበር የምወዳቸው። - ዱላቸው የፍቅር ምልክት ነበራ! እሳቸውም በጣም እንደሚወዱኝ የማወቀው አንጀታቸው እርር ብሎ ሲሰድቡኝ ነው። ሣይመቱኝ ሰንበት ያሉ እንደሆነ ማኩረፍ ዕቃ መሰባበር እጀምራለሁ። ልባቸው ወደ ውጭ ያለመሸፈቱን የማረጋግጠው በዱላቸው ነበር።

ትውሲት የሴት አያቷን ፀባይ በቀጥታ ነው የወረሰችው። አራት ዓመት እስኪሞላት ድረስ እሳቸው ጋ ስትቀመጥ ጠዋትና ማታ ወሬያቸው ይኸው ነበር። በልጅነት አዕምሮዋ የተቀረፀው ነገር ቀስ በቀስ አብሮአት አደገና እሷውም ዱላውን የፍቅር መመዘኛ ታደርገው ጀመር። -

ከተመታች በኋላ ካሳ ትጠይቃለች። አንድ ቀሚስ ወይም አንድ ሹራብ ወይም ጫማ ያስፈልጋታል። ፍቅረኛዋ ገንዘብ የለኝም ያለ እለት ቢያንስ ቢያንስ የጥፍር ቀለም ይገዛል። - ደጀኔም ለዚህ ወደ ኋላ አይልም። የምትፈልገውን ገዝቶ ያለብሳታል። ኪሱ ውስጥ እስካለ ድረስ ትውሲት ጠይቃው እምቢ ያለበትም ቀን

ለየም። እሱ የሚጠላው መንቀዥቀዧን ብቻ ነው። እንድታስቀናው አይፈልግም። የሚወዳት ስለምታስቀናው መሆኑን አላወቀም።

ትውሲት ደግሞ ደጀኔን የምትወደው በቸርነቱ ብቻ አይደለም። ሌላ ሴት ዞር ብሎ ስለማያይ የእሷ መሆኑን ብቻ ታውቃለች። የእርሷን ቀሚስ የሚከተል በሙቶ የሚቆጠር ወንድ ከኋላዋ እንዳለ አድርጋ ታወራለታለች። የደጀኔን ሱሪ የምትከተል ግን አንድም ሴት ከኋላው እንደሌለች ታውቃለች። - እሱም ለሌላ ሴት ፊት አይሰጥም፤ ግንባሩን ቋጥሮ አይፈታም፤ አለባበሱም አይማርከም። ይሄ ሁሉ ትውሲትን ያኮራታል። ደጀኔ በእሷ መሆኑ ብቻ ማምለኩ ያስደታታል።

«.....ነገሩ ምን መሰለህ» አለችው፤ በሀሳቧ አውጥታ አውርዳ፤ የደጀኔ ሚስጥሩን ካላወቀ እንደማይለቃት ካረጋገጠች በኋላ፤ «......አቶ ክብረት ከኔ ጋር ምንም ጉዳይ የላቸውም። ነገር ግን በእኔ በኩል የሚፈልጓት ሴት አለች።»

«ማነች እሷ?»

«ቢሮ አብራኝ ያለች ።.....ጽጊረዳ።»

«ውሸትሽን ነው።»

«ደጀኔ ሙት!» ብላ እጁን መትታ ማለች።

ያበላትንና ያጠጣትን እጅ መትታ በመማሏ ደጀኔ አመናት። እናም መጠነኛ እፎይታ አገኘ። በቅናት የተወጥጠረው ሰውነቱ ቀስ በቀስ እየተፍታታ ሄደ። ፅጌረዳ በመልክ ያውቃታል እንጂ ስለማንነቷም ሆነ ስለ ምንነቷ የሚያውቀው ነገር የለም። ከባሏ መጣላቷን ግን ትውሲት ራሷ በቅርብ ነግራዋለች። ተፈጥሮው ሆኖ ስለ ሌላ ሰው ብዙ ማወቅ አይፈልግም። ከትውሲት ጋር አንዳንዴ የሚያጣላቸው ይሄው ነው። እሷ ሰለ ሁሉም ሰው ማወቅ ሁሉንም ማውራት ትፈልጋለች። እሱ ጆሮውን አይሰጣትም። አሁንም የፅጌረዳን ምንነት ሳይጠይቃት የራሱ መንፈስ እፎይታ ማግኘቱ ብቻ አስደስቶት ዝም አለ።

ትንሽ ቆይታ ነገር ማገናዘብ ሲጀምር ግን የአድራጐቷ ፀያፍነት ታየው። -

«......ታዲያ አንዲ ምን አገባሽ?»

«እኔማ ምን አገባኝ ሰውዬው ሲጨነቁ ሳይ ጊዜ......ደሞም፤ በተዘዋዋሪም ቢሆን አለቃዬ ስለሚሆኑ......ልተባበራቸው ብዬ ነው እንጂ......»

«እሳቸው ሰውዬ ግን ቅሌታም ሸማግሌ ናቸው አሉ። እስቲ በዚህ ዕድሜያቸው አርፈው ተከብረው አይቀመጡም?!......» በማእልት በትውሲት ሳቢያ ከዘገየ ያገኘውን መረጃ ሳያስበው አወጣ።

«ዝም በል እባክህ.....ስማቸውን ሲያጠፉት ነው እንጂ ሰውዬው ንጹህ ናቸው። አዳሜ የራሱን ጉድ ጉያው ውስጥ እየደበቀ ሰው መቦጨቅ ይወዳል። አለችው፤ በተቆርቋሪነት ስሜት።

«ለማንኛው......አንቺ ከማህላቸው ብትርቂ ጥሩ ነው።»

አነጋገሩ ልመና የተቀላቀለበት ነበር። ባልፈፀመችው ተግባር በመጠርጠሩ የበደላት መስሎ ታየው። አሁን ዋናው ምኞቱ ዘገየን አግኝቶ የነገረውን ማስተባበል ነበር። ዘገየ ስራዬ ብሎ ደጀኔን በድንጋጤ ላብ ያስመጣውን ያህል፤ አሁን ደግሞ በተራው ዘገየን ፈልጎ አግኝቶ እየሳቀ ነገሩን ለማስተባበል ቸኮለ።.....ዘገየ አውቆ የፈጠረው ሸር መሆኑን አልጠረጠረም።

«.......ባትልም እኔ መሐላቸው አልገባም። እንዳይጠሉኝ በርቀት እተባበራቸዋለሁ።.....አንተ ግን አሁን እፎይ አልክ አይደል?! አጉል ጥርጣሬ ዋጋ እንደሌለው አወቅክ!» አለችና በተራዋ ግራ ጉንጩን በለስላሳ ጣቶቿ ጥፊ ነካ አድርጋው ከአጠገቡ ተነሳች።

ዳሌዋን ግራ ቀኝ እያስደነሰች ወደ ፊት ስትራመድ ደጀኔ የደረቀ ምራቁን አሁንም፤ አሁንም፤ እየዋጠ በአንክሮ ተመለከታት።.....በቀጥታ ወደ ትልቁ የፊት መስታወት ነበር የሄደችው።

በመስታወቱ ውስጥ ፊቷን ስትመለከት የደጀኔ ጥፊ ያረፈበት ቦታ በከፊል ሰንበር አውጥቶ አየች።

«አንተ ደጀኔ፤ ፊቴን አበላሸተኸዋል እኮ!»

«ምን ሆነ!»

«አይታይም እንዴ?....» ብላ ፊቷን አዙራ በርቀት አሳየችው።

ቀርቦ ሊያይላት ወይም ሊያሻሽላት ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደ እስዋ ሄደ።

ትውሲት የፊቷን ሰንበር ስታይ አንዳች ሌላ ነገር ትዝ አላትና ግራ እጇን ሰረቅ አድርጋ ተመለከተች። አንድ ኢንች ያህል ቀጭን ጠባሳ ተጋድሟል። ከጠባሳው ታሪክ ጋር እንድ ወንድ ሀሳብዋ ውስጥ ብልጭ ብሎ ድርግም አለ።.....ምን ዓይነት ዕድል ነው? ቀናተኛ ወንድ ብቻ ነው የሚያጋጥመኝ፤ አለች በልቧ

አሁን ፊቷ ላይ የተጋደመው ሰንበር ግን እምብዛም አያሳፍራትም። እንዲያውም በማግስቱ ለመስሪያ ቤቷ ሰዎች እያሳየች ማከላላቱ «ፍቅረኛዬ ከንፈሬን ነክሶ አሳበጠኝ» የማለት ያህል ያስደታታል።

«......እውነትም ጎድቼሻለሁ ለካ?» አላት ደጀኔ ጉንጯን በእጆቹ እያሻሸ።

«እንዴዬ?! ገድለህኛለ እንጂ!.......ግን እንዴት እጅህ እንዲህ ጨከነልህ?»

«ተናድጄ ነዋ!....በቃ ካሳ እከፍላለሁ።»

«ቀላል ካሳ አልቀበልም።»

«ግድየለሽም......ብቻ ደመወዝ እስኪወጣ ታገሺ።»

የጥፊው ሰንበር ተረሳት። ደጀኔ አቅፋው እንደቆመች፤ ከውጭ የመጣ አዲስ ፋሽን የሴት ጫማ ያየችበት ሱቅ በሀሳብዋ መዳሰስ ጀመረች።

ስማኝ ዘገየ ነገሮችን ሳታጣራ አታውራ። ትውሲት ከአቶ ክብረት ጋር ከቶም አልወጣችም። አቶ ክብረት የሚፈልጉት በትውሲት በኩል ፅጌረዳን ማግኘት ነው። ይህንን እኔ ራሴ ከትውሲት አፍ አረጋግጫለሁ። ገባህ?!.....

የደጀኔ አነጋገርና ሁኔታ እያስታወሰ ዘገየ በኃሳብ ተመስጦ ቆየ። ትውስት ከአቶ ክብረት ጋር እንደምትወጣ አድርጎ ሲነግረው በንዴት ጭራ አውጥቶ የበረረው ደጀኔ፣ አሁን ብስጭቱ ረግቦለት ሐቁን ከትውሲት አፍ ሰምቶ፤ ደረቱን ነፍቶ ወደ ዘገየ አስተጋባ። ዘገየ ቀድሞውንም ይህን አጥቶት ሳይሆን የትውሲትንና የአቶ ክብረትን ግንኙነት ቆርጦ አላማቸውን ለማክሸፍ ያቀደው ተንኮል ነበር።

የእግዜር በግ! በማለት ለደጀኔ አዘነለት።

ይሁን እንጂ ቀድሞ የሚያውቀውን እንገር ደጀኔ ተዝናንቶ ሲያረጋግጥለት በዘገየ አእምሮ ውስጥ አንዳች የበቀል ስሜት ማንሰራራቱ አልቀረም። የአቶ ክብረትን ተግባር ቢችል ማጋለጥ ባይችል ማክሸፍ ይፈልጋል። ተግባራቸው በስውር እስካካሄዱ ድረስ ማጋለጡ ቀላል ላይሆን ይችላል። የተሰሚነት ጥያቄም አለ። የዘገየ ቀልዱ እንጂ ቁም ነገሩ በመሥሪያ ቤት ውስጥ እንዳይሰማ የሚያደርጉት ሰዎች አሉ። አንዱ አቶ ክብረት ራሳቸው ናቸው።....እና ማጋለጡ ቀላል እንደማይሆን ገምቶ ምኞታቸውን ከማክሸፉ ላይ አተኮረ።

ዘገየን ይህ ስሜት የተፈታተነው አቶ ክብረት ፅጌረዳን ለመቀላጠፍ በአቋራጭ ሰለቀደሙት ብቻ አልነበረም። ከዚህ የከፋ የቆየ ቂም አለው። አንድ ጊዜ ለከፍተኛ የሥራ ዕድገት ታጭቶ በዕድገት ኮሚቴው ሲገመገም ወንደላጤነቱን ተመርኩዘው ፍጹም ዘልዛላና ቀልደኛ አድርገው በማቅረብ ዕድገቱን የተቃወሙት አቶ ክብረት ነበሩ። በወንደላጤነቱ ዕድገቱን ተከለከለ። ለኃላፊ ብቁ አይደለም ተባለ። አቶ ክብረት ግን በኃላፊነት ቦታ ተቀምጠው የሰው አጥር ለመዝለል ከወንደላጤዎች ጋር መወዳደራቸው አለመጠኑ ያናድደዋል።

ሌላው ብሽቀቱ ደግሞ እሱ ወጣትና መልከ መልካም ሆኖ ሳለ በገንዘብና በስልጣን ተበልጦ የሚፈልጋትን ሴት ማጣቱ ነው። አቶ ክብረት በሀብትና መሥሪያ ቤቱ ውስጥ ባላቸው ስልጣን ካልሆነ በቀር በምንም መንገድ ፅጌረዳን ቀድመው ሊጠልፉበት እንደማይችሉ ያውቃሉ።

እነዚህ ስሜቶች ወጥረውት ወጥረውት፤ የአቶ ክብረትን ምኞት የሚያከሽፍበት መንገድ ሲያወጣና ሲያወርድ፤ አንድ ሀሳብ መጣለት። የፅጌረዳን ወይም የባሏን የቅርብ ዘመድ ወይም ጓደኛ ፈልጎ ጉዳዩን በማጋለጥ ማክሸፍ እንደሚቻል ሲያስብ፣ በሀሳቡ ውስጥ አንድ ሰው መጣለት።

ይህ ሰው አብዛኛውን ጊዜ ወደ ማታ አካባቢ፤ ፀደይ ቡና ቤት ጎራ ብሎ ከሮምቦላ መጫወት ያዘወትራል። ከፍተኛ የኮሮምቦላ ሱስ ስላለበት በብዙ የቡና ቤቱ ደምበኞች ይታወቃል። ዘጌ ደግሞ እዚሁ ቡና ቤት ውስጥ ድራፍት ቢራ ለመጎንጨት አዘውርቶ ይገባል። መቼም ወንደላጤና ወንደላጤ መዝናኛ ሥፍራዎችን ከማዘውተር

ብዛት፤ ሲሆን በስም አሊያም በዓይን አይጠፋፋም። ሰውዬውና ዘገየ ለኮንትራት ስራ ትውውቅና የርቀት ሰላምታ አላቸው። ሰውየው ለኮንትራ ስራ እነ ፅጌረዳ መስሪያ ቤት መጥቶ በነበረበት ጊዜ ይተዋወቃሉ። ከፅጌረዳ ጋር መቀራረቡንም አጠያቆይ በደንብ አውቋል። ይህንኑ አስታውሶ አሁን ላሰበው አላማ በስሜቱ ውስጥ አጨው።

ጊዜ ሳያጠፋ፤ ከስራ መልስ በቀጥታ ወደ ፀደይ ቡና ቤት ሄደ። ለሰውየው እንደ ልማዱ ተሽቀዳድሞ የከሮምቦላ ድንጋዮች ይዞ እየወረወረ ነው። ዙሪያውን የከበበው ተመልካች በመደገፍና በመቃወም ስሜት ቢንሾካሾክም ሰውየው ለማንም ጆሮውን አይሰጥም። የማንንም ተመልካች ምክር አያዳምጥም። ዝም ብሎ በራሱ መንገድ ይጫወታል። ሲሳሳት ያለ መብሸቁ ወይም ነጥብ ሲያገኝ ያለ መቦረቁ ብዙዎቻቸውን ሳያስገርማቸው አልቀረም። የፈለገውን ነጥብ ሲመታ ገጹ ርካታ ይታይል እንጂ ድምስጽ አያሰማም ፡

አንዴ ድብን አድርጎ የመታት የጠላቴ ድንጋይ በቀጥታ የተደረደሩትን ሶስት ጠጠሮች ጠርጋ ስምንት አስቆጠረች።

«ብራቮ ኤርሚያስ!» ሲል አንዱ ተመልካች ጮኸ።

ዘገየ ቢራውን በብርጭቆ ይዞ እየተንጎራደደ ኤርሚያስ ቸዋታውን እስኪጨርስ ድረስ ጠበቀው።

ኤርሚያስ እያሸነፈ ሶስት ጨዋታዎችን ተከታትሎ ሲጫወት ዘገየም አምስተኛ ድራፍት ላይ ደረሰ። መጠጣቱ በቅርብ የማያውቀውን ሰው ለማነጋገሩ ድፍረት ሳይረዳው አልቀረም።

«ኤርሚያስ.... ይቅርታ፤ ትንሽ ግራ እንደ መጋባት ብሎ።

«አዎ፤ አንተ ረስተኸኛል መሰለኝ። በቅርቡ ባንተዋወቅም እኔ በርቀት አውቅሃለሁ። ዘገየ ወርቃለማሁ እባላለሁ። አንዴ የስዕል ሥራ ተኮናትረህ መስሪያ ቤታችን ውስጥ ትሰራ እንደ ነበር አስታውሳለሁ።

ኤርሚያስ የዘገየን ገፅታ አስታወሰ። ነገር ግን ብዙ ድርጅቶችና መስሪያ ቤቶች ውስጥ ኮንትራት ስራ ለሰራ፤ ትክክለኛ አድራሻው ጠፋው።

«....ቦታውን ዘነጋሁት።» አለው፤ በለሰለሰ ድምፅ።

«........ወይዘሮ ጽጌረዳ፤ የአቶ ወንዳፍራሽ ሚስት የምትሰራበትን ታውቀዋለህ።.....»

ዘገየ የመሥሪያ ቤቱን ስም በቀጥታ በመጥራት ፋንታ የፅጌረዳን የወንዳፍራሽን ስም የጠራው ሆን ብሎ ነበር። የኤርሚያስን ስሜት በጣም ለመሳብ እንደሚረዳው ያውቃል።

«አሀ!.......አሀ!....አሁን አሳታወስኩ። በደንብ አስታወስኩህ። ፅጌረዳ ቢሮም ውስጥ ዐልፎ ዐልፎ ተያይተናል።.......እንደምን አለህ?» አለው ኤርሚያስ እንደ አዲስ በነቃ አዕምሮ።

«ይኸውልህ ዛሬ፤ የማማክርህ ጉዳይ ስላለኝ ፈልጌህ ነው የመጣሁት።»

«እሺ?.......ምንድ'ነው?»

«መጀመሪያ ድራፍ ይምጣልህ?»ሲል ጋበዘው።

ኤርሚያስ የመጠጥ ግብዣውን አልተቀበለውም። የተግደረደረ መስሎት ቢለምነውም አልተበገረም። ስሜቱ መጠጥ የሚፈልግበት አንዳንድ ወቅት አለ። - በል - በል የሚለው ያለበለዚያ እንዲያው አገኘሁ ብሎ መጠጣት አይወድም።

«.....ምን መሠለህ» ሲል ዘገየ ጨዋታውን ከፈተ። «.......ስለ ፅጌረዳ አንዳንድ ነገሮች ታዝቤ ነበር።

የፅጌረዳን ስም ካነሳ በኋላ፤ ኤርሚያስን ስሜት ለማጥናት ለጥቂት ሴኮንዶች ነገሮች ታዝቤ ነበር።

የፅጌረዳ ስም ካነሳ በኋላ፤ የኤርሚያስን ስሜት ለማጥናት አለው፤ እንዳላዋቂ ሆኖ ሲያውጣጣው።

«አዎ እንተዋወቃለን። የጓደኛዬ ባለቤት ናት» አለ ኤርሚያስ ለወሬው በጓጓ ስሜት።

የቅርበታቸውን መጠን ማሳመኑ ዘገየ ያሰበውን ነገር ነገር በድፍረት እንዲናገር ገፋፋው -

«እንግዲህ የባለቤቷ ጉደኛ ከሆንክ በቤታቸው ውስጥ የተከሰተውን ችግር ሳትደርስበት የቀረህ አይመስለኝም።...... ፅጌረዳ ከባሏ ጋር መጠነኛ ግጭት ውስጥ ገብታለች። መቼም ባልና ሚስት ሆኖ አልፎ አልፎ መጋጨት አይቀርም። ነገር ግን ቀላሉና ግጭት የሚያጠናክሩ አንዳንድ የውጭ ግንኙነቶች ደግሞ ይኖራሉ።.......»

«አሁንም ኤርሚያስ ስሜት ለማጥናት ንግግሩን አቋረጠ። «.......አሁን እንዴት ያሉ?» አለ ኤርሚያስ በጉጉት።

«ሚስት ባሏን አስቀናለሁ ብላ ከሌላ ወንድ ጋር መውጣት የጀመረች እንደሆነ፤ ባልም እንዲሁ በሌላ በኩል መወስለት የጀመረ እንደሆነ፤ ኋላ የማይሽር ቁስል ይፈጠራል። ፅጌረዳ በ በስሪያ ቤታችን ውስጥ የተከበረችና የተወደደች ንጹህ ሴት ነው። እንዲያውም በጸባይዋ ሩህሩህነት የተነሳ «ቅድስት ፅጌረዳ» እየተባለች ነው የምትጠራው። ሰሞኑን ግን ከባሏ ጋር በመጋጨቷ የተነሳ አንድ ስህተት ላይ እየወደቀች ነው። ይህ የምትሰራው ስህተት ሲወደስ የኖረው ስሟን በአንድ ቀን ሊያረክሰው ይቻላል። እንዲያው የቅርቧ ከሆንክ ብትመክራት ከብዙ ጥፋት ታድናለህ ብዬ ነው የምገምተው።»

«ምን እያደረገች ነው?» አለው ኤርሚያስ በድንጋጤ።

«በመስሪያ ቤቱ ውስጥ ስማቸው የጠፋ አንድ ቅሌታም ሽማግሌ አሉ። ከእሳቸው ጋር መውጣት ጀምራለች። ተከብራ በኖረችበት ግቢ ውስጥ መቼም.....ብትፈልግ እኳ ከውጭ ብታደርገው ይሻል ነበር።

ኤርሚያስ የሰማውን ነገር ማመን ያቃተው ይመስል ዘገየን አፍጥጦ ተመለከተ። ያቺ ለትዳሯና ለልጆቿ ፍቅር ራሷን መስዋዕት አድርጋ የቆየች ሴት እንዴት በአንድ ጊዜ ልትለወጥ ትችላለች? ሲል ራሱን በራሱ ጠየቀ። አንድ ቀን ሲያነጋግራት በአኳኋኗ ላይ የተመለከተውን ለውጥ አጢኖ በትዳሯ ተስፋ መቁረጡ ምናልባት አሁን ዘገየ ወደ ነገረው መንገድ ሊመራት እንደሚችል ገመተ። ይሁን እንጂ

ያ ተመልካች ያስቀና ፍቅርና ትዳር ንፋስ ገብቶት የጎረቤት መንቶካቶኪያ ርዕስ መሆኑ አንጀቱን አቃጠለው።

«ፅጌረዳ ከባሏ መጣላቷን አንተ እንዴት አወቅክ?» አለው ድንገት ዘገየ።

«እንኳን እኔ የመሥሪያ ቤቱ ሰው በሙሉ አውቆታል። ከግቢው አልፋ ለከተማው ሕዝብ ማዳረስ ከትችል ቀልቃላ ሴት ጋር አንድ ቢሮ ውስጥ ነው ያሉት። አዲስ ወንድ የማቃጠሩንም ሂደት የምታከናውንላት እሷው ናት።......»

«ማን ናት እሷ?» አለ ኤርሚያስ ሳያውቃት ጥላቻ አድሮበት።

«ፅጌረዳ ቢሮ በምትሄድበት ጊዜ ስላየሃት ታውቃታለህ። ትውሲት የሚሏት ከውካዋ አለች። የእራስዋ መሸርሞጥ አልፎ ሌሎችን ታቃጥራለች።» አለና ድራፍት ለማስጨመር በብርጭቆው ጠረጴዛውን ቆረቆረ።

«ድራፍት አልቋል።» አለው አንድ ወንድ አሣላፊ በርቀት መቅጃያው በርሜል አጠገብ ቆመ።

የድራፍቱ ማለቅ ወሬውንም እንዲያሳጥር ያስገደደው ይመስል ወደ ኤርሚያስ ዞሮ፤ «.....እና ነገሩ ይሄ ነው። ፅጌረዳ ባልዛመዳትም በርቀት ስለማከብራት የተቆርቋሪነት ስሜት ወጥሮ ይዞኝ ነው አንተን ፍለጋ የመጣሁት፤ የቻልከውን ያህል ምከራት።» አለው።

«......ግን በእርግጥ ፅጌረዳ ከሌላ ወንድ ጋር መውጣት ጀመራለች?» አለ ኤርሚያስ፤ የሰማውን ነገር እየቀየ አልዋጥለት እንዳለው ሁሉ አገጬን በትካዜ አይነት ደግፎ።

«ስነግርህ!.....ትክክለኛ ምንጭ ነው ያገኘሁት። ደሞ'ኮ ሰውየው የሚረቡ አይደሉም። ግቢው ውስጥ የሚታወቁት በልክስክስነታቸው ነው።»

«መልካም፤ እንግዲህ የሚቻለውን ሁሉ እናደርጋለን። እኔና አንተም በደንብ እንተዋወቅ። እኔ ብዙ ጊዜ እዚችው ቤት አልጠፋም። አልፎ አልፎ እየተገናኘን ብንዘርክርበት ጥሩ ነው።» አለው ኤርሚያስ፤ ቡና ቤቷን ለቀው ሲወጡ፤ በሀሳቡ መስመጡ ገጹ ላይ እየተነበበ፤

የወንዳፍራሽና የፅጌረዳ ጉዳይ እየከረረ መምጣቱ ክፉኛ አሳሰበው። በመሐል የስነ ልቡና ጠባሳ ይዘው የሚያድጉት ሁለቱ ልጆች፤ ዳኒና ሰብለ፤ በሀሳቡ ታዩት። ለችግሩ አስቸኳይ መፍትሔ እንደሚያገኝለት ዓይነት ከእርምጃው ፈጠን ፈጠን ማለት ጀመረ።

ዘገየ የኤርሚያስን በጉዳይ መስመስጥ ሲመለከት የመንፈስ ርካታ አገኘ። የአቶ ክብረትን ምኞት አክሽፎ የትውሲትን ዕድገት የሚያጨናግፍ አንድ ረዳት እንዳገኘ ቆጠረው። የማክሸፉ ሴራ ተሳክቶለት በመስሪያ በቱ ውስጥ ስሙ ቢነሳ ደስታውን አይችለውም። አቶ ክብረት አይናቸው ደም ለብሶ በጎሪጥ ከማየት ሌላ ምንም ሊያደርጉት አይችሉም። ከሥራው እንደማይባረርም፤ በስራውም እንደማያድግም ካወቀው ቆይቷል።

ከጠዋቱ በሁለት ሰዓት ወንዳፍራሽ ቢሮው ሲገባ ኤርሚያስ አጥምዶ ያዘው። ባልጠበቀው ሰዓት ስለ መጣበት ወንዳፍራሽ ትንሽ መደናገጡ አልቀረም። ያው በፅጌረዳና በእሱ ጉዳይ ላይ እንደሚያነጋግርው ቢጠረጥርም በጠዋት እያስጋለበ ያመጣው አንዳች መርዶ ሳይሆን አይቀርም ብሎ ፈራ።

የቢሮው በር ከፍተው እስኪገቡ ድረስ አንዳችም ቃል አልተለዋወጡም። ወንዳፍራሽ «ደግሞ ምን ሊለኝ ይሆን?» እያለ ሲጨነቅ፤ ኤርሚያስ በበኩሉ «እንዴት ልጀምረው?» እያለ ሲያስብ ጥቂት ቆዩ።

«ትዳርም ምሰሶ ሲናጋ እንዲሁ ቸል ማለትህ ነው?» አለ ኤርሚያስ፤ ቢሮውን ውስጥ ገብተው ከተቀመጡ በኋላ።

በስልክም በአካልም ደጋግሞ ያነሳበትን ጉዳይ ቢሆንም ወንዳፍራሽ የመሰላቸት ስሜት አላሳየም። የግሉ አንገብጋቢ ጉዳይ በመሆኑ ከርዕሱ ጋር ስሜቱም አብሮ ተነሳሳ።

«እኔ ቸል አላልኩም። ነገር ግን እሷ ችግሩን ለመፍታት ፈቃደኛ የሆነች አልመሰለኝም።» አለው በከረረና ብሶት ባዘለ ድምፅ።

ሚስቱን በስሟ አቆላምጦ መጥራቱ ቀርቶ «እሷ» ማለት ከጀመረ ሰንብቷል። ኤርሚያስ አሁንም የግጭታቸው ዕድገት እያሳዘነው ከንፈሩን መጥጦ ጭጭ አለ።

«.......ለአጭር ጊዜ ታገሺኝ አልኳት። ልትታገሰኝ ፈቅደኛ አልሆነችም። ጥፋተኛነቴን አምኘ አርማለሁ፤ ማሪኝ አልኳት። ይህ ሁሉ ግን ችግሩን በመፍታት ፈንታ ቁጣዋን ያባብስባት ጀመር። ቤታችን ውስጥ ፈፅሞ ሰላም ጠፋ። ዳኒና ሰብለን ሳይቀር በመጥፎ አስተሳሰብ እየጠመቀቻቸው ነው። አድራጎቷ ሲውል ሲያድር የእኔንም ትዕግሥት እያስጨረሰኝ ነው። እየህ! ለሷ አዲስ ነገር ሆኖ የሚያመናጭራት ማንም ወንድ በየቀኑ የሚፈፅመው ጉዳይ ነው። ማክበርና መፍራት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። አክብሮቴን በገለፅጉላት ቁጥር በፍርሃት ሳትተረጉብኝ የቀረች አይመስለኝም። »

እንዳዋዛ ጀምሮ ከውስጥ ስሜቱ እየፈነቀለው ወደ ስረ - ነገሩ ሲገባ የግምባሩ ደምስሮች ሁሉ ተገታተሩ። ችግሩን ለመፍታት ሣይሆን፤ ብሶቱን ለማስተጋባት የሚናገር ይመስል ነበር። አኳኋኑ። - እንዲያ ይዋደዱ የነበሩ ባልና ሚስቶች ለዚህ ደረጃ ይደርሳሉ ብሎ ማን ይገምታል?

በወንዳፍራሽ ደምፍላታዊ አነጋገር ኤርሚያስ አልተናደደም። ብሶት ከዚያ የበለጠ እንደሚያደርግ ያውቃል። ሚስት በአንድ በኩ፤ ባል ባንድ በኩል እሱ ላይ ብሶታቸውን መተንፈሳቸውን የቅርብ ጓደኝነት እጣ አርጎ ወሰደው።

«ጥፋተኛው እኮ አንተ እንጂ እሷ አይደለችም። ይህች ሴት ከአሁን በፊት ለትዳሯ ሟች እንደ ነበረች አትርሳ!» አለው፤ ጠንከር ባለ የጓደኝነት አንደበት።

«እሱንማ ብዬ ነው፤ በደለኛ መሆኔን አምኘ ትንሽ እንድትታገሰኝ የጠየቅኳት።.......»

«አንዴዬ?!.......እስከ መቼ ነው የምትታገስህ?» አለው አሁንም ጥፋተኛን በሚገስፅ ዓይነት አነጋገር።

«እንጃ!» በማለት ዓይነት ራሱን ከመነቅነቅ ሌላ ምንም አልተናገረም።

«ምን ማለትህ ነው ወንዳፍራሽ?.....አንተ በፅጌረዳ ቦታ ሆነህ ነገሩን እየው እስቲ፡፡ ከሌላው ሴት ጋር እየወጣህ ታገሺኝ ማለት ይቻላል እንዴ? አንተ እሷን ከሌላው ወንድ ጋር ስትወጣ ብታያት እንዲህ ያስችልሃል?........»

በግዴለሽነት ዓይነት ትከሻውን ነቀነቀ፡፡

«ተው እንጂ.....አያስችልምህ፡፡ ካለዚአይም የናንተ የፅጌረዳ ፍቅራችሁ አልቋል ማለት ነው፡፡ እኔ ግን ሳስበው ሁለታችሁም ዕልህ ውስጥ ገብታችሁ ነው እንጂ የዘጠኝ አመት ፍቅር በአንድ ሳምንት ውስጥ ተሰብሮ የሚያልቅ አይመስለኝም፡፡......» ካለ በኋላ ትንሽ አሰብ አደረገና፤ «ከሮዛ ጋር ከፍተኛ ፍቅር ይዞሀል መሰለኝ፡፡» አለው፡፡

«እንዴት?» አለ ወንዳፍራሽ ደንገጥ ብሎ፡፡

«ታዲያ ግንኙነታችሁን ማቋረጥ እንዴት ያቅትሃል?......»

«አቀቶኝ ሳይሆን፤ ቶሎ ማቋረጥ የማልፈልግበት ምክንያት አለኝ፡፡........»

«አርግዛብሃለች እንዴ?»

«በፍጹም!»

«ታዲያ ምንድነው ችግርህ?»

«ነገርኩህ እኮ! የራሴ የሆነ ምክንያት አለኝ፡፡ ሮዛም የሰው ልጅ ናት፡፡ ስሜቷን ጎድቼ ለአደጋ ላጋልጣት አልፈልግም፡፡ አሁን ግንኙነታችን በአንድ ጊዜ ቢቋረጥ ራሷን ከማጥፋት ወደ ኋላ እንደማትል አውቃለሁ፡፡ ግንኙነታችን ቀስ በቀስ ልገድለው ነው የምፈልገው፡፡.....»

«እና፤ እስከዚያ ፅጌረዳ በቅናት እየተቃጠለች ቤት ውስት ትቀመጥ ነው የምትለው?......»

ወንዳፍራሽ ምንም መልስ አልሰጠውም፡፡

«የሮዛን ሕይወት በፍቅር አለምልመህ ለማቆየት ትዳርህን መስዋዕት ማድረጉን መርጠሃል ማለት ነው፡፡.......» አለው በምፀት ድምፅ፡፡

አሁንም ወንዳፍራሽ መልስ አልሰጠም። አጠገቡ የተቀመጠውን ፋይል ትክ ብለው የሚመለከቱት ዓይኖቹ ጥልቅ ሀሳብ ውስጥ መግባቱ ያሳያሉ።

«እንዳትቆርጥ ያደረገህ ሌላ ምክንያት ይኖራል እንጂ የሰጠኸኝ ምክንያት በቂ አይደለም።....አንድም ከሮዛ ጋር ጥልቅ ፍቅር ውስጥ ገብተሃል። አለያም ከፅጌረዳ ጋር ሳትስማሙበት የኖራችሁት መሠረታዊ ችግር ይኖራል።» አለው በማውጣጣት ዓይነት

«እንዴት ያለ?......»

«እሱንማ አንተ ነህ የምታውቀው።»

ኤርሚያስ የባልና ሚስቱን ፀብ መሠረታዊ መንስኤ የማወቅ ጉጉት ከፍ እያለ ሄደ። ብዙ ትዳሮች ሲናጉ ተመልክቷል። ነገር ግን ለብዙ አዲስ ትዳሮች አርአያ ይሆናል ብሎ የገመተው ትዳር የተናጋበትን ምክንያት ማወቁ ከፍተኛ ትምህርት የሚሠጠው መሠለው። ወንዳፍራሽ ፅጌረዳ ላይ ያጣውና ሮዛ ላይ ያገኘው ነገር ምን ይሆን? ወይም ደግሞ ሮዛ ወንዳፍራሽ ባለ ትዳር መሆኑን እያወቀች ምንጭ ያለችበት ምክንያት ምንድነው? የሚሉት ጥያቄዎች መንፈሱን ወጥረው ያዙት። ሮዛን ቀርቦ የማወቅ ጉጉት አደረበት።

ስሜቱ በዚህ ብቻ አልቆመም። ወደ ሌሎች ማህበራዊ ስንክ ሳሮች ደግሞ ዘመቱ። ፅጌረዳ በእንዲህ ዓይነት ችግር ላይ ባለችበት ሰዓት ችግሯን ተንተርሰው የግል ፍላጎታቸውን ለማሟላት የሚሯሯጡትን ሰዎችም ማወቅ ፈለገ። ዘገየ የነገረውን ሚስጥር በአዕምሮው እያውጠነጠነ አቶ ክብረትና ትውሲት ቀርቦ መከታተል አማረው። ወንዳፍራሽ መቼም ይህን ታሪክ እንዳልሰማ እርግጠኛ ነኝ፤ አለ በልቡ።

«ይልቅ አንተ መቁረጥ አቅቶህ ስታወላውል ፅጌረዳም የአንተኑ መንገድ እንዳትከተል........»

«ምን ማለትህ ነው?........» አለ ወንዳፍራሽ ግንባሩን ከስክሶ።

«አንተ ከሌላ ሴት ጋ እንደትወጣ ሁሉ እሷም ከሌላ ወንድ ጋር መወጣት ከጀመረች፤ ኋላ የማይሽር ቁስል ታተርፋላቺ።»

«የራስዋ ጉዳይ ነው።»

«እንደሱ አትበል። ያኔ ያንተም ጉዳይ ይሆናል። ያም ሆነ ይህ እኔ ነገሩን በቸልታ አልመለከተውም። አንተና ፅጌረድ የቅርቦቼ ስለ ሆናችሁ ብቻ ሳይሆን ትዳራችሁ ያስቀናኝ ስለ ነበር ጥብቅና እቆምለታለሁ። አሁንም የምለምንህ አንድ ነገር ብቻ ነው። ከሮዛ ጋር የጀመርከውን ግንኙነት መበጠስ መቻል አለብህ። ካለበለዚያ ፅጌረዳን ወደ ሌላ ጥፋት እየመራሃት ነው። እና በዚህ መሐል ወላጅ አልባ ሆነው የሚቀሩት ሁለቱ ልጆቻችሁ....ዳኒና ሰብለ.... መሆናቸውንም አትርሳ።» ብሎት ተነስቶ ወጣ፡

ኤርሚያስ ከቢሮው ከወጣ በኋላ፤ የጥንት ጓደኝነታቸው ትዝታ በወንዳፍራሽ አዕምሮ ውስጥ ብልጭ - ድርግም እያለ ታየው። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ውስት የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች በነበሩበት ጊዜ ነው የተዋወቁት። አንድ መኝታ ክፍል ከመጋራታቸው ሌላ አብዛኛውን ጊዜ አብረው ያጠኑ ነበር። ወንዳፍራሽ የኤርሚያስን ችሎታ ለመገምገም የበቃው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነው። ብዙ ተማሪዎችን ያስቸገሩ የተወሳሰቡ የሂሳብ ስሌቶችን፤ ኤርሚያስ አንዴ ቁጭ ካለባቸው፤ ብትንትናቸውን አውጥቶ ነበር የሚለቃቸው። ሌላውንም የትምህርት ዓይነት ቢሆን አንዴ ካነበበ መሠረታዊ ጭብጡን አይረሳም። ችግሩ ግን፤ ከመደበኛው ትምህርት ይልቅ፤ ለመዝናኛ ወደ ሚያነባቸው መጻሕፍትና ወደ ሥዕል ስራው ያዘነብል ነበር። አንዳንድ አስተማሪዎች በሚጠይቁት፤ ከ «ሀ - ፐ» ዝርዝር ዓይነት መሸምደድ አይወድም፤ ለፈተና ብሎ ማጥናት ያስጠላዋል። በተረፈ ግን በአጠቃላይ የአስተሳሰብ አድማሱ በብዙ አስተማሪዎች ዘንድ የተደነቀ ነበር።

ወደ ሁለተኛ ዓመት ተማሪነት ሲሸጋገሩ ወንዳፍራሽ አስተዳደር ሳይንስ፤ ኤርሚያስ ደግሞ የስነ ልቡና ጥናት መስክ መርጠው ተመደቡ። በትምህርት መስክ ቢለያዩም ጓደኝነታቸው አልቀነሰም ነበር። እንዲያውም ከመላመድና በቅርብ ከመተዋወቅ ብዛት ጉደኝነታቸው ጠንክሮ ብዙ ውለታ እስከመዋዋል ደረሱ። ይሁን እንጂ ኤርሚያስ ለአስተማሪና ለፈተና ብሎ የማጥናቱ ነገር ሁለተኛ ዓመት እከገባም በኋላ አልተዋጠለትም። የመረጠውን የትምህርት መስክ ስለ ወደደው በስነ ልቡና ላይ ከአስተማሪዎች ትዕዛዝ ውጭ ብዙ መጻሕፍት አነበበ። በትዳር የሚከሡቱ ችግሮችን ምንጭ ለማጥናት በየሰው ጓዳ ገብቶ እያጠያየቀ ከትምህርት ጋር በማስደገፍ ይመራመርበት ጀመር። ይህን ሲያደርግ ግን ለፈተና መጠናት ያላባቸውን ሌሎች

የትምህርት ዓይነቶች ቸል እያለ ነበር። የመጀመሪያ ሴሚስተር ውጤቱ አላማረም፤ ስለዚህ ሁለት ምርጫዎ ከፊቱ ተደቀኑለት - የሚፈነቅል የውስጥ ስሜቱን ረግጦ የትምህርት ቤቱ ግዴታ በሚጠይቀው ውስጥ ማለፍ፤ ወይም ለስሜቱ ትምህርቱን ማቋረጥ! ቆራጥ ውሳኔ ወሰደ ከሁለተኛ ዓመት አቋርጦ ወጣ።

የቀረበት ነገር ዲግሪ ብቻ ነበር እንጂ ለንባቡ ወደ ኋላ አላለም። የስሜቱንና የፍላጎቱን ተከትሎ ለራሱ እያነበበ የአስተሳሰብ አድማሱን አሰፋው። በሰዓሊነት ሙያውም ታዋቂ እየሆነ ሄደ። በአንድ የማስታወቂያ ድርጅት ውስጥ ተቀጥሮ ይሠራ ነበር። ወንዳፍራሽ የዩኒቨርሲቲ ትምህርቱን እስኪ ጨርስ ድረስ የኤርሚያስ ኪስ - ኩሱ ሆኖ ቆየ። ጥናት ሰልችቶት መዝናናት ሲያምርወ ወደ ኤርሚያስ ዘንድ ነበር የሚሄደው። ኤርሚያስ ጥቂት ዓመታት በማስታወቂያ ድርጅቱ ውስጥ ከሠራ በኋላ፤ የራሱን ስቱዲዮ ከፍቶ፤ ሙሉ ጊዜውን ሥራው በመስጠትና እየተዘዋወረ የኮንትራት ሥራ በመሥራት ይተዳደር ጀመር።

ወንዳፍራሽ ሲያእባ በቅርበቱ መሠረት ኤርሚያስ አንደኛ ሚዜው ሆነ። ከዚያ በኋላ ግን ጓደኝነቱ ለወንዳፍራሽ ብቻ መሆኑ ቀርቶ ለትዳሩ ወይም ለቤተሰቡ እየሆነ መጣ። የሚስቱም ጓደኛ የልጆቹም ጓደኛ የቤቱ ቤተሰብ ሆነ። ይህ አዲስ ግንኙነት አድጎ በአሁኑ ጊዜ ለትዳራቸው ደህንነት ጥብቅና እንዲቆም ገፋፋው።

ወንዳፍራሽ ቢሮው ውስጥ እንደ ተቀመጠ ስለ ኤርሚያስ ትንሽ ካሰበ በኋላ፤ ሁሉንም በመተው ዓይነት «ኤጭ» ብሎ የጠዋት ሥራን ለመጀመር ዶሴውን ገላለጠ። ነገር ግን የቢሮ ሥራ መሥራት ለመጀመር ከቤት ውስጥ ጤናማ ኑሮ ሲኖር ነው። ወረቀቶቹን እያገላበጠ ቢመለከታቸውም ቅሉ ሀሳቡ ዞሮ ዞሮ ከቤቱ ችግር ላይ ቀርቶ ነበር። በተለይም አሁን ኤርሚያስ ቀስቁሶበት የሄደው ነገር መላልሶ ጭንቅላቱ ውስጥ ተሽከረከረ። ፅጌረዳ ከሌላ ወንድ ጋር መውጣት እንደምትችል አስቦ አያውቅም። ወይም ማሰብ አይፈልግም። አሁን «ቢሆን?» የሚል ጥያቄ ራሱን ሲጠይቅ አንዳች ስሜቱን የሚጎዳ ነገር ተሰማው።

የእሱና የፅጌረዳ የቤት ውስጥ ኑሮ የደባል ዓይነት ከሆነ ሰንብቷል። አንድ ገበታ አብረው አይቆርሱም፤። አብረው አይተኙም። በእሱን መኪና መመላለሷ ቀርቷል። ከዓለፋ ገደም የሚያነጋግራቸው ጉዳይ ቢኖር እንኳ በኩርፊያው በንጭንጭ

ዓይነት ነው። እና የፅጌረዳ ልብ በዚህ ሁኔታ ወደ ውጭ ቢሸፍት ምን የሚያግደው ነገር ይኖራል? እንዲህ ሆኖ አብሮ የመኖር ትርጉሙስ ምንድነው?!»....

በብስጭት ዶሴውን ከአጠገቡ ወረወረው።

ወንዳፍራሽ ከሮዛ መውለድ ያለመውለዱን ለማረጋገጥ ትውሲትን ለስለላ ከላከቻት ጀምሮ ፅጌረዳ ሲወራጭ ነው የከረመው። ቢሮ በገባች ቁጥር የትውሲትን ዓይን - ዓይን እያየች «እንዴት ነው?.....ምን ሰማሽ?» እያለች ስታፋጥጣት ከረመች። ትውሲትም በአጭር ቀናት ውስጥ ፅጌረዳ የናፈቀችውን ወሬ ከወዲያ ወዲህ አርገብግባ ከጆሮዋ አደረሰችላት።.....

«ይገርምሻል ፅጌረዳ......ይህን ጉዳይ ለማጣራት ያልገባሁትበት ጉድጓድ የለም።.....»

«እሺ?......እስካሁ ምን አገኘሽ?»

«ስንት ሰው አስቸገርኩ መሰለሽ?!......ሮዛን የሚቀርቧትን ሴቶች ለማግኘት.......»

«በመጨረሻ ግን አገኘሽ?.......»

«በመጨረሻማ ሮዛን ራሷን ማግኘት ባልችልም በአራተኛ ሰው በኩል ወሬውን አገኘሁት።»

ትውሲት ወሬውን አጣፍጣ ማቅረብ ነው የፈለገችው። ፅጌረዳ ደግሞ የጠረጠረችውን ነገር ለመስማት ከመቸኮሏ የተነሳ ሌላውን ዝብዝብ የምታዳምጥበት ትዕግሥት አልነበራትም።

«.......እንዴት ንው?!.....» አለቻት ቁጣ ባዘለ ጥያቄ።

«እንደጠረጠርሽው ነዋ!.....» አለችና፤ ትውሲት በተቆርቋሪነት ስሜት አገጯን ይዛ በረዥሙ ተነፈሰች።

«እንዴት?......»

ፅጌረዳ መስማት የፈለገችውን ነገር ስትሰማ ማመን እንዳቃታት ዓይነት ፍዝዝ አለች። ጥርጣሬዋን ማመን አቃታት። አየሩ ያን ያህል ባይሞቅም የፅጌረዳ ሰውነት ግን ከውስጥ ሲግል ይሰማት ጀመር። ከውስጥ እያቃጠላት ከላይ ብርድ ብርድ ይላታል። ከንፈሯ በቅፅበት ውስጥ ደርቆ እርስ በርሱ እንደተጣበቀ ቀረ። ውብ ገፅታዋ ላይ ያረፈው የሐዘን ደመና ጭፍግግ አደረጋት። ከተቀመጠችበት መነሳትም ሆነ፤ አንገቷን ግራ ቀኝ መነቅነቅ እንዳቃታት ሁሉ ትክ ብላ ሐውልት መሰለች።

«.....ከሮዛ ወልዷል ነው የምትይኝ?» አለች የተጣበቀ ከንፈሯን በግድ አላቅቃ።

«መውለድም ባይሆን......ያው ነው። አርግዛለታለች አሉ። አርግዛእልታለች አሉ። እርግዝናዋ እየገፋ ስለ መጣ ማስወረድም የማይቻልበት ደረጃ ላይ ደርሳለች።

በድንጋጤ እንዳፈጠጡ የቀሩት የፅጌረዳ ዓይኖች አስተያየት፤ ሚስጥር ነጋሪዋን ትውሲትንም የተቆጣቻት አስመስለዋት ነበር። ከንፈሯን እንደነከሰች ከውጥ ጥርሶቿን እርስ በርሳቸው ከፉኛ ስታንቀጫቅጭ የፊቷ ቆዳ እየተጨማደደ ያሳያል። ግንባርዋም ተኮመታትሯል። መናገርም ሆነ መነቃነቅ እንደተሳናት ዓይነት ድርቅ አለች።

«......አየሽ ፅጌረዳ፤ ባለቤትሽ ሮዛን ቢወዳት ነው እንጂ ባይወዳት ኖሮ እከታረግዝ ድረስ ዝም ብሎ አይጠብቃትም ነበር። ወንዶችን መቸ አጣኋቸው! እንኳን ሳይወዱ፤ እየወደዱም ሴት ካረገችባቸው «ዓይንሽ ላፈር» ብለው ዞር ነው የሚሉት። ባልሽ ለዚህ ልጅ ልቡ ጠፍቶላታል ማለት ነው።......አበስኩ! አይ ወንዶች!.....ይገርሙኛል እኮ። ልባቸውን አንዲት ቆንጆ ላይ ከሸፈተ ስንት ዓመት የደከሙበትን ጎጆ በአንዴ እርግፍ ነው!.......»

ፅጌረዳ የትውሲትን ገለጻ መከታተል አልቻለችም። ትክ ብላ የምታያት ትመስላለች እንጂ አታያትም። ጆሮዋን በሰጠቻት ትመስላለች እንጂ አትሰማትም። መጀመሪያ በሰማችው በድን ሆናለች።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ፤ በድንገቱ ለቀቅ ሲያደርጋት፤ አንድ ውሳኔ ላይ እንደደረሰች ሁሉ፤ ቦርሳዋን አንጠልጥላ ድንገት ፍንጥር ብላ ለመሄድ ተነሳች።

«የት ትሄጂ ነው ፅግዬ?»

«መሔድ አለብኝ.....ከዚያ ቤት ዛሬውኑ መውጣት አለብኝ።.... አሁን ወደ ቤት መሄድ አለብኝ!»

«ታዲያ ቆይ እንጂ.....አሁን እኮ የሥራ ሰዓት ነው።.....ለምን ብለሽ ብስጭትሽን ለሰው ታሳያለሽ?......አለቃሽም ከቦታሽ ሲያጡሽ መጠየቃቸው አይቀርም።.....»

አሁንም ፅጌረዳ የትውሲትን ዝብዝብ አላደመጠቻትም። ራስዋን ከፋኛ እየነቀነቀች ከቢሮዋ ወጣች። ትውሲትም ተከትላት ወጥታ ክንዷን ይዛ ልታረጋጋት ሞከረ፣....

«......እሺ እንግዲያ ከሄድችም መልካም። ለአለቃሽ እኔ እነግርሻለሁ። - ራሷን አሟት ሄደች እልልሻለሁ። - ይሁን፤ እንጂ እንግዲ ሆነሽ ብቻሽን አልለቅሽም። ....ባይሆ አቶ ክብረት በመኪና እንዲሸኙሽ ልንገራቸው።.....»

ትውሲት አጋጣሚውን በመጠቀም ተልዕኮዋን ለማላካት የወረወረቻቸው ሐረጎች በሀፍረት ስሜት ቆንጠጥ ስላደረጓት ንግግሯን ገትታ የፅጌረዳን መልስ ትጠብቅ ጀመር። ፅጌረዳ ግን ትውሲት የተናገረችውን ለማጤንም ሆነ ለማላመጥ ያለችበት ሁኔታ አልፈቀደላትም። ሀሳብዋ ሁሉ ቤትዋ ደርሳ ከምትወስደው ውሳኔ ላይ እንዳረፈ ነበር።

«......ተይኝ እባክሽ.....ተይም!.....ተይኝ አልኩሽ!......» እያለች ግቢውን ለቅቃ ወጣች። በውጭው በር ላይ የቆሙት ዘበኞች ሁኒታዋ አስደንግጦአቸው ሊከተሏት ሲሉ ትውስቲ መለሰቻቸው። እና እሷ ተከትላቸው ወጥታ ታክሲ አሳፈረቻት።

ሁኔታዋ በአንድ በኩል ሲያሳዝናት በሌላ በኩል ደግሞ በሆድዋ የሳቃት ነበር። ለወንድም ወይም ለፍቅር ወይም ለትዳር እንዲህ የመታመሙ ነገር ለትውሲት አይዋጥላትም። እንጊህ ዓይነቱን ጉዳይ ቀሚሷን እየነሰነሰች ታክላላበታለች እንጂ፤ አትተክዝበትም። በትዳር ውስጥ ያለ ዘመናዊ ድብብቆሽ አድርጋ ነው የምትወስደው። እና፤ አሁንም በሆድዋ የሚያስቃት የፅጌረዳ «ጅልነት» ነበር።

ምስኪን! ምን ዓይነቷ የዋህ ናት?!.......እያለች ወደ ቢሮዋ ተመለሰች።

የፅጌረዳ በሥራ ሰዓት ወደ ቤት መመለስ እልፍነሽን አስደግንጦአት፤ «እትዬ.....ምን ሆኑ? ምን ነካዎት?.....» እያለች ተከትላት ወደ መኝታ ክፍል ገባች። ራስ ምታት ወይም ሌላ ድንገተኛ ሕመም አሟት ከስራዋ የተመለሰች መስሏት ነበር። ቁም ሳጥኑን ከፍታ ልብሶቿን ማወጣጣት ስትጀምር፤ እልፍነሽ ነገሩን ጠረጠረች።

«እትዬ.....»

«ዝም በይኝ እልነሽ!....ተይኝ!.....ሂጂና ስራሽን ስሪ!......»

«አባክዎ እትዬ.....»

«ተይኝ ብዬሻለሁ.....ተይኝ!»

እልፍነሽ እንባ ተናነቃት። ስለ ባልና ሚስቱ መፋታት ብቻ ሳይሆን ስለ ራሷም ዕድል ነበር ያዘነችው። በግርድና ሥራ ከአንዱ ቤት ወደ ሌላው ቤት መዞ ስልችቶአታል። ከገባችባቸው ቤቶች ሁሉ ሰላም አግኝታ የቆየችው እዚህ ቤት ውስጥ ነበር። ሌሎቹ በአዕምሮዋ ውስጥ መጥፎ ጠባሳ ጥለውባት አልፈዋል። ታደልም፤ በዘመናዊ ልብስና ጫማ ወይም ሽቶና ቅባት ጎልቶ ለመውጣት ባይታደልም፤ ዓይን የሚስብ ቆንጆ የተፈጥሮ መልክ አላት። ሰውነቷም ሞላ ብሎ ፍጥምጥም ያለች ነገር ነች። ታዲያ መልኳ በገባችበት ቤት ሁሉ ሚስቶችን እያስቀና ባሎቻቸውን እንዲጠረጥሩ ያደርጋቸዋል። ወንድየው ከመላመድ ብዛት ያው እንደ ቤተሰቡ አካል ቆጥሮአት፤ ካቆላመጣት ወይም በፈገግታ ካነጋገራት፤ ሚስት በማግስቱ ተነስታ እልፍነሽን ያለ ጥፋቷ መወንጀል ትጀምራለች። የሹሮና ቅቤ ማለቅ በእልፍነሽ ስርቆት ይላከካል። እልፍነሽም ነገሩ ይገባታል። ወንጀሏን አብዝተው ፖሊስ ጣቢያ ከማድረሳቸው በፊት «እትዬ አሰናብቱኝ....» ትለዋለች። አንዳንዶቹ ሚስቶች እሷ እስክትጠይቃቸም አይጠብቁም። በቅናት ወገባቸውን ይዘው እየተቆናጠሩ «በይ ጨርቅሽን ይዘሽ ቶሎ ውጭ እዚህ ቤት ዛሬን አታድሪም!.....እንዴት ሙልጭ ያልሽ ሌባ ነች እባካችሁ?!....ቤቱን እኮ አራቁታ ብዳኦ ዬነ አስቀረችኝ» ብለው ይሸኟታል። የእልፍነሽም ዕድሏን እያማረረች ውበትዋ በማጥቂያ ፈንታ መጠቂያ መሆኑ እያሳዘናት ሌላ በኢት ደሞ ግርድና ፈለጋውን ትቀጥላለች።

ይህ ሁሉ ቁስሏን ያገገመች እዚያ ፅጌረዳና ወንዳፍራሽ ቤት ውስጥ ነው። ሦስት ዓመት አብራቸው ስትኖር እንደ እህትና እንደ ወንድም ከመተያየት በስተቀር ግንባራቸን አኮማትረውባት እንኳ አያውቁም። ልጆቹም የዚያኑ ያህል ይወዱታል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በቤተሰቡ ውስጥ የተከሰተው ችግር ግን የእሷም መንፈስ ማሰቃየቱ አልቀረም። በቤተሰብ ውስጥ የተከሰተው ችግር ግን የእሷንም መንፈስ ማሰቃየቱ አልቀረም። በቤት ውስጥ የሚደረገው ነገር ሁሉ የቀን ተቀን ሰቀቀን ሆነባት። ወንዳፍራሽና ፅጌረዳ አንድ ገበታ ቀርበው አይበሉም። የሚዘጋጀውም ምግብ እንዲያውም አሥሥ ገሥሥ ስለሆነ ሁለቱ ውጭ መብላትን ይመርጣሉ።

«ባልን ለመቅጣት አከታትሎ ሹሮ ማብላት» የሚል ምክር ትውሲት ከለገሰቻት በኋላ፤ ፅጌረዳ ሆነ ብላ ቤት ውስጥ ጥሩ ምግብ እንዳይዘጋጅ ማድረግ ጀምራለች። ሁኔታው ወንዳፍራሽን ከቤት ምግብ አሸሸው እንጂ አልቀጣውም። በዚህ መሐል ግን እልፍነሽ ተጨንቃ ሞተች። የቤት አስቤዛ አሰጣጣጨውና አወጣጣቸው መዝረክረኩ የፅጌረዳና የባሏ የየዕለት ጭቅጭቅና ንጭንጭ መስማቱ በአጠቃላይ የደባል ዓይነት ኑሮ የሚኖር ባልና ሚስቶችን ማስተናገዱ ከቀን ወደ ቀን ሰውነቷን ጨረሰው። ባልና ሚስቶችን ማስተናገዱ ከቀን ወደ ቀን ሰውነቷን ጨረሰው። ይሁን እንጂ ለሦስት ዓመታት የቆየችበትን ቤተሰባዊ ፍቅር እያስታወሰች ይህን ሁሉ ችላው ሰነበተች። አሁን የፅጌረዳ ቤቱን ለቅቆ መውጣት ግን ከፉኛ አሳሰባት። ምናልባት ወንዳፍራሽ ወደ ፊት ሌላ ሚስት ቢያመጣ፤ ከዳኒና ከሰብለ እንጀራ እናት ጋር ሊኖራት የሚችለውን ግንኙነት ስታሰብ ከወዲሁ አንገፈገፋት።.......

«እትዬ.......መጀመሪያ እኔን ያሰናብቱኝ» አለቻት ከሀሳብዋ ስተንቃ እንባዋ ርግፍ - ርግፍ እያደረገች።

ፅጌረዳ የእልፍነሽን ለቅሶ ማየት አልፈለገችም። ይሄ ልመናና ለቅሶ ከውሳኔዋ የሚያዘናጋት መስሎ ታያት። ዳኒና ሰብለ ቤት ውስጥ ያለ መኖራቸው ጥሩ አጋጣሚ ሆኖላታል። ምናልባት በእነሱ ለቅሶ ውሳኔዋን ትለውጥ ነበር። ዳኒም ትምህርት ቤቱ፣ ሰብለም መዋዕለ ሕጻናት እንደሄዱ ናቸው። አሁን የዕልፍነሽ ልመና ማዳመጥ አልፈለገችም።

«ወይጅልኝ ከአጠገቤ እልፍነሽ?.......ምን አጠገቤ ተገትራ እዬዬ ትልብኛለች?!.....ወይጂልኝ ብዬሻለሁ!......»

አኳኋኗ እልፍነሽን አስደነገጣት። ዓይኗን ብልጥጥ አድርጋ አፍጥጣ ግንባሯን አኮመታትራ እንደ አውሬ ስትጮህባት አዲስ ሴት እንጂ ዱሮ የምታውቃት ፅጌረዳ ልትመስላት አልቻለችም። እንባዋን እየጠራረገች ከአጠገቧ ዘወር አለችላት።

ፅጌረዳ የመኝጣ ክፍሉን በር ቆልፋ ዝግጅቷን ቀጠለች። ያቀረበችው ሻንጣ በአንዴ ሞላ። ዕቃዋን ግን ገና ምኑን አልተነካ። ጊዜያዊ መንገደኛ እንጂ ቤት ለቃቂ በሻንጣ ዕቃውን ይዞ መውጣት አይችልም። የትኛውን ይዞ የትኛውን ሊተው?!.....ነገረ ስራዋ ሁሉ እንዳይሆን እንዳይሆን መሆኑን ብታውቅም፤ የወጠራት የዕልህና የጥቃት ስሜት የህሊናዋን ጥያቄዎች ሁሉ ደፍጥቶ መርበትበቱን ቀጠለ። በጣም የሚያስፈልጓትን ዕቃዎችና ልብሶች ብቻ እየመረጠች በሻንጣዋ ከጠቀጠቀች በኋላ፤ አንድ ሀሳብ መጣላት፤ የሰብለንም ልብሶች በአነስተኛ ቦርሳ ውስጥ ጨምራ አዘጋጀች።

ወገቡና ይዛ ቆማ በረዥሙ ከተነፈሰች በኋላ ጥርሶቿን አንቀጫቅጫ «....ለጊዜው ይሄ ይበቃኛል። የቀረውን ደግሞ ወደ ፊት.......ገና ቤቱን ሁሉ መከፋፈላቸው አይቀር!.....ወገቤን አስሬ የሠራሁትን ቤት!.....» አለችና የጠቀጠቀችውን ትልቅ ሻንጣ በትግል ቆለፈችው። ልታነሳው ቀርቶ ልትነቀንቀው ስላልቻለች በሩን እክፍታ ተሸካሚ እንድትጠራላት እልፍነሽ አዘዘቻት።

«ምነው እትዬ?!... እንዳው እባክዎን ለልጆችዎ ብለው.......ለኔ ለድኃዋ ብለው!......»

«አጠገቤ አታላዝኚብኝ.....ሂጂና ተሸካሚ ጥሪልኝ ነው የምልሽ.......»

አሁንም እልፍነሽ አይኖቿን በነጠላዋ ጫፍ እያበሰች ተሸካሚ ፍለጋ ሄደች።

ፅጌረዳም ለብዙ ዓመታት የምታውቃቸውን የቤቷን ሳሎንና ጓዳዎች እንደ አዲስ እየተዟዟረች እየተመለከተች መሰናበቷን ተያያዘች። ከውሳኔ ሊያዘናጓት የሚችሉ ትዝታ አቀፍ ነገሮችን ላለማየት፤ ካየችም ለማቃጠል ወሰነች። ነገር ግን ላስብህ ካሉት ዘጠኝ ዓመት ሙሉ አብረው ያፈሩት ንብረት ሁሉ ትዝታ ማዘሉ

አይቀርም። ይህን ከባድ ትዝታ መራቅ እንደሆነ እንጂ መሸሽ አይቻልም። ......ከወንዳፍራሽ ጋር አብረው የተነሷቸው ፎቶ ግራፎች በተናደደች ቁጥር ጨርሳቸዋለች። በአልበም የተቀመጡበትንና የተረፉትንም ወንዳፍራሽ ደብቆአቸዋል።

የቤቷን ዙሪያ ገብ ስትማትር ከቆየች በኋላ - ያውላት! ሮዛ ከነዲቃላዋ ትግባና ትቦርቅበት.....አለች በሆዷ።

ሮዛን ማስታወሷ የባሰ ስሜቷን አስቆጣው። ብስል ቀይ፤ ረዥም ሰይጣን!..... ‹ባልሽን የልጆችሽን አባት ለምን ትለቂለታለሽ? ቤትሽን ለምን ለቅቀሻላት ትወቻለሽ?› በማለት ቀናተኛው ስሜቷ ተናነቃት። ጥርሷን ነክሳ በቅናት እየተንገበገበች ትኖር ዘንድ ጋበዛት። ነገር ግን ‹.....ከቅናት ርቄ ሸሽቼ በድህነትና በብቸኝነት ብኖር ይሻለኛል።› የሚለው ኩራተኛው ስሜቷ አሸነፈ። ፅጌረዳ ባዶ ቤት ውስጥ በሁለቱ ስሜቶቿ መሐል ፍዝዝ ብላ ቆማ ስትታይ ስዕል ወይም የተቀረፀ ሐውልት ትመስል ነበር።

«....ግቢበት! ያውልሽ..... ከነዲቃላሽ ግቢና ኑሪበት!....» ሮዛ አጠገቧ የቆመች ወይም የምትሰማት ይመስል እንደገና ድምፅ አውጥታ ተነፈሰች።

ወዲያው ደግሞ አንድ ሀሳብ መጣላት። ለወንዳፍራሽሽ በደብዳቤ ወይም በስልክ፤ ልክ ልኩን ነግራ መለየት አሰበች።

ወራዳ ነህ!....ልክስክስ ነህ!.......ቅሌታም በመሆንህ አብሬህ መኖር አልቻልኩም። ካንተ ጋር ያቃጠልኩት የፍቅር ዘመን ሳስበው ያንገበግበናል። የምወዳቸው ሁለቱ ልጆቼ የአንተ ፍሬ መሆናቸው ያሳዝነኛል።....እኔ ፅጌረዳ ለቅሌት ስላተፈጠርኩ ከነ ክብሬ ቤቱን ለቅቄልህ ሄጃለሁ። ውሽማህን ጠቅልለህ ኑርበት! ዲቃላህን አሳድግበት!.....ደግሞ ቤቱን አንጀቴን አስሬ፣ ከአንትው እኩል ሱሪዬን ጠቅልዬ የሠራሁት ቤት መሆኑን አትርሳ! እኩል ለኩል እንካፈላታለን እኒጅ እንዲሁ አንላቀቅም።......

ሀሳቧን አሰበች እንጂ በተግባር ለማዋል ከቆመችበት ሥፍራ አንዲት ስንዝርም አልተንቀሳቀሰችም። በአሁኗ ደቂቃ ለወንዳፍራሽ ለመጻፍ ወይም

ለመደወል ብዕር ወይም የስልክ እጀታ ላንሳ ብትል፤ እጁ በእልህ ስሜት ይንቀጠቀጣል። አትችልም። እና የተወለጋገደ ፊደል ከመጻፍ ወይም የተንተባተበ ቋንቋ ከመናገር፤ መተውን መረጠች።

እልፍነሽ ጥቂት ቆይታ አንድ ጠብደል ተሸካሚ ይዛ ተመለሰች። ፅጌረዳን አለሳልሶ የሚያበርድ ጎረቤት ፍለጋ ከአንዱ ቤት ወደ አንዱ ብትዘዋወርም አላገኘችም። ጎረቤቶቿ የመንግሥት ሠራተኞች በመሆናቸው ሁሉም ወደ የሥራቸው ሄደዋል። በየቤቱ ያገኘቻቸው ገረዶቹን ብቻ ነው። ተስፋ ቆረጠች።

ፅጌረዳ ሻንጣዋን አሸክማ ግቢውን ስትለቅም የቀድሞውን ዓይነት ልብ የሚነካ ስሜት ተሰማት። እንደ ሕፃን ተነከባክባ ያሳደገችው የግቢው አትክልት በንፋስ ኃይል ሲወዛወዝ ሐዘኔታውን የሚገልፅ መሰላት። ግቢው ትንሽ ቢሆንም ንጹህና ነፋሻማ ነው። ቤቱን ያሰሩበት የባንክ ብድር ገና ተከፍሎ አላለቀም። ከእሷም ከወንዳፍራሽም ደመወዝ ላይ በየወሩ ይቆረጣል፤ ወደ ፊት እንዴት እንደሚሆን ፅጌረዳ ማሰብ አልፈለገችም። ይህም ከውሳኔዋ የሚያዘናጋት መስሎ ታያት። እና ጥርሶቿን ነከሳ፤ ለምትወደው ግቢ ጀርባዋን ሰጥታ ወጣች። እልፍነሽም መናገር ፈርታ እንባዋን እያዘነበች የውጭው በር ላይ እንደ ቆመች ቀረች።

ፅጌረዳ ታክሲ ኮንትራት መጀመሪያ በቀጥታ ሰብለ ወደ ምትገኝበት መዋዕለ - ሕጻናት አመራች። ባለ ታክሲው የፊቷን መጨማደድና የጫነችውን ሻንጣ በማየት አንድ ችግር እንዳለባት ገምቶ ሚስጥሩን ለማወቅ ጓጓ። ቢጠይቃት ሰላማዊ መልስ የምትሰጠው አልመሰለውም። የተጨማደደው ግንባሯ አስፈራ፤ ውብ ገጽታዋ ደግሞ ሆዱን አባብቶ ልቡን ሰለበው። ውበቷን በልቡ እያደነቀ፤ ነገር ግን ይህች ውብ ዓለም ሰዎችንም ከማንም እኩል ማናደዷን እንድ እቅጠል ማርገፏ አስገረመው። ሰረቅ አድርጎ እየተመለከታት ችግሯን በመጠየቅና ባለ መጠየቅ ሐሳብ ሲዋልል ማቆያውን ረስቶት ሊያልፈው ነበር።

«በቃ! በቃ!.......እዚህ እኮ ነው።» በማለት ፅጌረዳ መዋዕለ ሕጻናቱ በር ላይ ሲደርሱ አስቆመችው።

በውላቸው መሠረት ባለ ታክሲው የተወሰኑ ደቂቃዎች እንዲጠብቃት ነግራው ልጅዋን ፍለጋ ወደ መዋዕለ - ሕፃናቱ ግቢ ገባች። አንዳንዶቹ ሕጻናት ክፍል

ውስጥ ናቸው አንዳንዶቹ ደግሞ ከግቢው ውስጥ የተለያዩ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ ዥዋዝዌ፣ ሽርተቴ፣ ድብብቆሽ፣ ኳስ። ሰብለን ዥዋዥዌ ከሚጫወቱበት መሐል በርቀት ለየቻት። ከዚያም፤ ለአስተማሪዋ የውሸት ምክንያት ሰጥታ ያለ ሰዓቱ ከግቢው ለማውጣት ፈቃድ ካገኘ በኋላ፤ ወደ ሰብለ ቀርባ ጠራቻት።

የሰብለ ልብ ጨዋታው ላይ ስለ ነበር መጀመሪያ አላየቻትም። ስምዋ ተጠርቶ ዘወር ስትል እናቷ ናት።

«ት - ግ - ዬ..... ትግሽ!.......ት - ግ - ዬ!» እያለች ሮጣ መጥታ አግሮቿ ላይ ተጠመጠመችባት።

ፅጌረዳ አንዳች ስሜት ተሰምቷት ዓይኗ እምባ ቢያቀርም፤ ጥርሷን ነክሳ ውጣ ልጅዋን ጎንበስ ብላ ሳመቻት፡

«ለ - ለምን መታሽ?» አለቻት ሰብለ ሽቅብ አንጋጣ የእናቷን ዓይን እየተመለከተች።

ለወትሮው ከመዋዕለ - ሕጻናቱ የምታመላልሳት እልፍነሽ ስለሆነች የዛሬው የፅጌረዳ መምጣት እንግዳ ሆኖባታል።

«ልወስድሽ ነዋ!» አለቻት ጽጌረዳ፤ ጉሮሮዋ ላይ የሚታገላትን ነገር ወደ ውስጥ እየዋጠች።

«ዛሬ እልፍነሽ የለችም እንዴ?......ሰዓቱም እኮ ገና ነው። ልጆች ሁሉ አልሄዱም።» አለች ሰብለ እየተኮላተፈች።

«እሱን ሁሉ አውቃለሁ፣ አሁን የምወስድሽ ከሩቅ የመጣ ዘመድ ሊያይሽ ስለሚፈልግ ነው። የምንሄደው እነ አባባ ቤት ነው። ይልቅ ቶሎ ብለሽ ሹራብሽን ልበሽና እንሂድ።

ሰብለ ዥዋዥዌ ስትጭወት አውልቃው የቆየችውን ሹራቧን መልሳ ለብሳ ወደ እናትዋ ስትመለስ፤ ሕጻናቱ ከብበው ያስለፈልፏት ጀመር።

«የት ልትሄጂ ነው?»

«እኔን የሚፈልግ ዘመድ መትቷል።......»

«እሳቸው ዘመድሽ ናቸው?»

«ትግዬማ እናቴ ናት።»

«እናትሽ ናቸው?.....ታድለሽ!....ዛሬ እልፍነሽ የት ሄደች?»

ያለ ሰዓቱ ብቻዋን በመውጣቷ ቀንተው በጉጉት ዓይን ሸኟት። ፅጌረዳ የሰብለን እጅ ይዛ ወደ ታክሲው አመራች።

«ትግዬ.....አሁን የምንሄደው እነ አባ ቤት ነው?»

«አዎ ሰብልዬ»

«በኋላ እልፍነሽ ልትወስደኝ ስትመታ........ስታታኝ አትደነግትም?»

«አትደነግጥም። ልጆቹና አስተማሪሽ እኔ እንደወሰድኩሽ ይነግሯታል።»

«.......ግን ማን ነው የመታው ዘመድ?»

«ኣታውቂም። ከሩቅ አገር ነበር።»

«ምን ይዞልን መታ?......ልብስ?......»

«አዎ!.......ሁሉንም ነገር።»

ባለ ታክሲው በሩን ከፍቶ አስገባቸው። አሁንም ፅጌረዳ ምንም ነገር ላለመጠየቅ ግንባሯን እንዳኮማተረች ናት። ባለ ታክሲው አኳኋኗን አይቶ ልጅዋን ይዛ ወደ ሩቅ ሀገር የምትጠፋ ሴት መስለችው።.....ታግሶ መቆየት አልቻለም።

«......ይቅርታ አድርጉልኝና።.....እንዲያው ድፍረት ባይሆንብኝ.....ምን ችግር ገጥሞዎታል?......» አላት ታክሲውን ጎርጉሮ አስነስቶ ጥቂት እንደ ተጓዘ።

«ምንም ችግር የለም።» አለችው ግንባሯን እንዳኮማተረች።

«.....ማለቴ፤......ገፅዎን ሳየው፤......የተበሳጩ ይመስላል፥»

«ስለ ሐዘኔታዎ አመሰግናለሁ።........አልተበሳጨሁም።»

ለውይይት ፈቃደኛ ያለ መሆኗን ሲመለከት ባለ ታክሲው አሁንም ሆዱን እየቆረጠው ዝም ብሎ መሾፈሩን ቀጠለ። ሰብለ ጣልቃ ገብታ ለእናቷ ጥያቄ አቀረበች።

«ትግዬ.......ዳኒ ለምን ከኛ ጋር አልመታም?»

«ይመጣል።.....በኋላ እልፍነሽ ይዛው ትመጣለች።»

«አዎ ከዳኒ ጋል አብለን ነው የምንበላው?»

«አዎ፤ ሰብልዬ......»

«እነ አባባ ቤት ነው ምሳ የምንበላው?»

«አዎ አልኩሽ እኮ ሰብልዬ!......»

አመላለሷ የመሰልቸት ሳይሆን ጥያቄውን የመሸሽ ዓይነት ነበር። የሰብለ ኮልታፋ ምላስ አይገጠብም። ነገር ግን ፅጌረዳ የዳኒ ስም ሲጠራት ሆዷ መንቦጫቦጩን ቀጠለ። ዳኒን ለአባቱ ትታ ሰብለን ይዛ የወጣችበት ግልፅ ምክንያት የላትም። ለፍቅር ከሆነ ሁለቱንም እኩል ትወዳቸዋለች - ዳኒን በበኸር ልጅነቱ፤ ሰብለንም በትንሽነቷ።......ምናልባት ሴት ስለሆነች የጾታ ጓድኛዋን መፈልጓ ይሆን? ወይስ ከዳኒ ይልቅ ሰብለ ስለምታንስ በአብዛኛው የእናት እንክብካቤ ያስፈልጋታል ብላ ይሆን?.....አንዱ ወይም ሁሉም ምክንያት ይሆናል። ለጊዜው ግን ለራሷም ግልፅ አይደለም። ከባል ወይም ወጥቶ ብቸኛ ላለመሆን አንዷን ልጅዋን መውሰዷን ብቻ ነው የምታውቀው። ሁለቱን ልጆቿን መነጣጠሏ የሚያስከትለውን የስነ ልቡና ቀውስ ለጊዜው አላሰበችውም። ምክንያቱም በሰማቸው ነገር አብዳለች፤ እኔነቷ ከውስጥ አግጥጦ ወጥቷል። የሰመጠችው በእሷነቷ ብሶት ውስጥ ብቻ ነው። ለማንም ለምንም ግድ የላትም። እኔነት ከውስጥ አግጥጦ ሲወጣ ለአካባቢያችንና ለቅርብ ሰዎች የሚኖረን ፍቅርና ሐዘኔታ ሁሉ አፈር ይግጣል። አስተዋዩ፣ አመዛዛኙ፣ የአዕምሮአችን ክፍል ይዋጣል ይጨፈለቃል። እኔነቱ ብቻውን ለራሱ ዘብ ይቆማል። የህወትና የሞት ጥያቄ ይሆናል። እኔነት ወደ ዚህ ዓለም ብቻውን መምጣቱንና ወደ መቃብርም የሚወርደው ብቻውን መሆኑን እያስታወሰ አካባቢውን መርሳት ይጀምራል።

ፅጌረዳ በሰማቸው ወሬ ለተወሰነ ቅፅበት አብዳ ሻንጣዋን ይዛ ከቤት ስትወጣ የነበረችበት ሁኔታ ከዚህ የተለየ አልነበረም። አሁን ግን ሰብለ በኮልታፋ ምላሷ ስለ ኮረብታችት፣ ወደማህበራዊ ፅጌረዳነቷ ተመልሳ የእናትነቷ ሆዷ መንቦጭቦጭ ቀጠለ። ዳኒ እሷን ከቤት ውስጥ ሲያጣ የሚሰማውን ስሜት ስትገምት፤ ዓይኖቿ አርግዘው የቆዩትን እንባ ድንገት ፊቷ ላይ ዘረገፉት።

«.....ትግዬ፣......ለምን ታለቅሻለሽ» ስትል፤ የሕጻኗም ዓይኖች እናቷን ተከትለው እንባ እየቋጠሩ ነበር።

ፅጌረዳ ከውስጥ፤ ገንፍሎ የወጣውን ስሜት መቆጣጠር ስላልቻለች ተንሰቅስቃ አለቀሰች። የዋህዋ ሴት፤ ቅድስት ፅጌረዳ፤ ሆደ - ቡቡነቷን አሳየች። ጉዳዩን ንቃ ለመተው ወይም ጥርሷን ነክሳ ለማሳለፍ አልቻለችም። የዋህ አንጀቷ አልፈቀደላትም።

ሰብለም ሚስጥሩ ባይገባትም እናቷን ተከትላ አዬዬውን አቀለጠችው።

ባለ ታክሲው በሐዘን ስሜት የሚሾፍርበት እጁ ይንቀጠቀጥ ጀመር።

«ኃይለኛ ሴት ነዎት።.......ችግርዎን ለሰው ቢያዋዩ ምናልባት?!....መመካከር አይከፋም።» አላት፤ ሲናገርም ድምጹ እየተንቀጠቀጠ።

«.....ብነግርህ ምን ይጠቅምሃል?.......ለኔስ ምን ትፈይድልኛለህ?....ከባሌ ተጣልቼ ጓዜን ይዤ ወጣሁ! ይኸው ነው በቃ!» አለች፣ እልህ እየተናነቃት።

ተንፍሳ እንዲወጣላት ወይም ንግግሩ እንባዋን እንዲያደርቅላት ፈልጋ እንጂ፣ ባለ ታክሲው መፍትሄ ይሰጠኛል ብላ አልነበረም። እውነትም ምላሷን ማነቃነቅ ስትጀምር እንባዋ ጋብ አለላት።

«እኔም ይህንኑ ጠርጥሬ ነው የጠየቅኩዎት፣......በትዳርዎ ላይ ችግር እዳለብዎ አኳኋንዎ ያስታውቃል። ሆኖም እንዲህ መበሳጨቱ ጥሩ አይደለም። በትዳር ውስጥ መጋጨት ያለ ነገር ነው። ታዲያ መቻቻል ያስፈልጋል። እኛ ወንዶች አንዳንዴ እውሮች ነን።.....»

ንግግሩ አቋረጠ። ‹ይችህን መሣይ ቆንጆ ሴት የሚያስቀይም ባል መንፈሱ የታወረ መሆን አለበት› በማለት ለፅጌረዳ ውበት ያለውን አድናቆት ሊገልፅላት ፈልጎ ነበር። ሆኖም አድናቆቴ በሌላ ትርጉም ይወሰዳል ብሎ ፈራና ተወው።

«......ማለቴ በትዳርው ስት አንዱ ሲታወር ሌላኛው መሪ መሆን አለበት እንጂ፤ ደህነኛውም እውሩን ተከትሎ ወደ ገደል የሚሮጥ ከሆነ ትርፉ ጥፋት ነው። እኔ የአራት ልጆች አባትና ባለ ትዳር ነኝ። ባሳለፍኩት የትዳር ዓመታት ውስጥ በእኔም ሆነ በእሷ ጥፋት ከባለቤቴ ጋር የሚያጋጩ ብዙ ነገሮች አጋጥመውኛል። ብዙ ጊዜም ዱላ ቀረ ግጭት ተጋጭተናል። ሆኖም በነዚህ የግጭት ጊዜያቶች በዕልህ ተነሳስተን ትዳራችንን ያለ ማፍረሳችን ከብዙ ስቃይና ጸጸት አድኖናል። የእኛ ብቻ ሳይሆን የልጆቻችንም ሕይወት ቅጥ ያጣ ይሆን ነበር። ልጆች ወላጆቻቸው መሐል ሲያድጉ ነው ፍቅር ይዘው የሚወጡት። ካለዚያ አዕምሮአቸው ስንኩል ይሆናል። ይህንን በራሴ አስተዳደግ አወቀዋለሁ። አልፌበታለሁ.....እና አሁን እኔና ባለቤቴ ከዚያ ሁሉ ጭቅጭቅና ግጭት አልፈን የሚያስቀና ፍቅር ላይ ነን። ሁለታችንም በትዳር ውስጥ ሰከንን። የዕብጠት፤ የማንአህሎኝነትና ትምክህት ዘመናችን አከተመ። ሁለታችንም ልጆቻችን አባትና እናት መሆችንን አምነን በሰላም እንኖራለን።.....እ......በትዳር ውስጥ መቻቻል ያስፈልጋል ለማለት ነው ይህንን ሁሉ ያመጣሁት! መጋጨት መጥፎ አይደለም። ነገር ግን ግጭቱ የቤቱን ምሶሶ ለማጥበቅ እንጂ ለማፍረስ መሆን የለበትም።......»

ፅጌረዳ ባለ ታክሲውን ትኩር ብላ እየተመለከተች ንግግሩን ሳታዳምጥ ቆይታ፤ ድንገት ስላቋረጠባት ‹ቀጥል እንጂ.....› በማለት ዓይነት ግንባሯን ሽብሽባ ራሷን ነቀነቀች። የባለታክሲው ንግግር መቋረጥ እሷም ከራሷ ጋር ወደ ውስጥ እንድትነጋገር ጊዜ ሰጣት፣......

እና ጽጌረዳ ችግሩን ለመፍታት ያልታገሰች ይመስልሃል? ዘጠኝ ወር ሙሉ ውስጥ ውስጡን እየቆሰለች ነበር በትዕግሥት የኖረችው። ነገር ግን የትዕግሥት ውጤቱ መናቅ መዋረድ ሆኖ አግኝታዋለች።

ይህን በመስለው የመከላከያ ሀሳብ ራሷን ለማጽናናት ብትሞክርም፣ ባለ ታክሲው ስለ ትዳር ማፍረስ ጸጸትና ስለ ልጆች በወላጆቻቸው ውስጥ የማደግ አስፈላጊነት የተናገረው ነገር ክብደት ዓዕምሮዋ ውስጥ እያቃጨለ ነበር።

ሰብለ ግን የባለ ታክሲው ዲስኩር በጥልቀት ባይገባትም እንኳ በጆሮዋ ለማዳመጥም ያህል አልታደለችም። የትምህርት ቤቷ ጨዋታ አድክሟት ስለ ነበር ትንሽ እንዳለቀሰች የእናቷን ጭን በተደገፈችበት እንቅልፍ አሸልቦአታል።

«እዚህ ጋ ይበቃኛል። ዕቃ ስለያዝኩ ቢችሉ ወደ ውስጥ ገባ ያድርጉኝ። ቤቱ ያ የሚታየው አረንጓዴ በር ነው።» አለች ፅጌረዳ የአባቷን ቤት በርቀት እያሳየች።

«ኧረ አስገባዎታለሁ። ምንም ችግር የለም።» ብሎ ባለ ታክሲው ከባድ ማርሽ ቀይሮ ወደ ኮረኮንቹ ገባ። «እና......እንዲያው.......አሁንም በውሳኔዎ መግባት ባይሆንብኝ.......ጉዳዩን በበለጠ አስበውበት.......ሌላው ቢቀር ለልጆችዎ ሲሉ ከባለቤትዎ ጋር ቢታረቁ......»

«እሺ......ስለምክርዎ አመሰግናለሁ።» አለችው ነገሩን ለማሳጠር ያህል።

አባቷ ቤት በር ላይ ደርሰው ከባለታክሲው ጋር ተረዳድተው ሻንጣዋን አወረዱ። ሰብለም ከዕንቅልፏ ነቃች። ዕቃ መውረዱን በርቀት የተመለከቱ ተሸካሚዎች እየተሯሯጡ መጥተው ፅጌረዳን ከበቧት።

«አቤት.....የት......እናድርሰው?»

አንደኛው ኩሊ ሳይታዘዝ ተሽቀዳድሞ ሻንጣውን አንከበከበው።

«የት ትወስደው?.......ቤቱ እኮ እዚህ ነው።»

«እናስገባልዎታ እማማ........»

እንደ ባለታክሲው ሁሉ ኩሊዎቹም የፅጌረዳን ብስጭት ከገፅዋ ላይ ማንበብ ቢችሉም፣ ለማዘን ወይም ለማስተዛዘን ጊዜም ደንታም የላቸውም። የበለጠውን መራራ ሕይወት አልፈውበታል፤ እየኖሩበትም ነው። እና እንጀራቸውን ብቻ!......

ፅጌረዳ ከቦርሳዋ ውስጥ ገንዘብ ስታወጣ ባለ ታክሲው በእምቢታ ራሱን ነቅንቆ መኪናውን አስነሳ። በመስኮት ውስጥ ልትወረወርለት ብትሞክርም አሻፈረኝ ብሎ ሄደ። በሁኔታዋ ከልቡ አኖአል። ግን ምንም ማድረግ አልቻለም።

«ትግዬ.....ይሄ እኮ የኛ ሻንታ ነው።» አለች ሰብለ ወደተሸካሚው ጭንቅላት በጣቷ እያመለከተች።

«አዎ፤ የኛ ነው። ሰብልዬ»

«ውስቱ ምንድን'ነው ያለው?»

«ልብስ ነዋ፤ የእኛ ልብስ።.......»

«ይሄ ሁሉ?......»

«አዎ ይሄ ሁሉ።»

«ዘመዳችን ያመቱልን አዲስ ልብስ ነው?»

«አዎ ዘመዳችን የመጡልን።......»

«ለዳኒም አዲስ ልብስ አምትተውለታል?.......»

«ቆይ እስቲ ሰብልዬ.......ከእግሬ ስር ዘወር በይ?......» ብላ የበሩን መዝጊያ ማንኳኳት ጀመረች።

ኳ! ኳ! ኳ! ኳ!

ልብዋም ውስጥ በድንጋጤ የሚንኳኳ ነገር ተሰማት ። ሻንጣዋን አሸከማ የልጅዋን እጅ አንጠልጥላ

ስትገባ እኒያ አባቷ ምን ይሉ ይሆን? የተጨማደደው ግንባራቸው በኃሳብዋ ታያት። መኩሪያ ልጃቸው ትዳሯን አፍርሳ መመጣቷን ማመን አቅቷቸው እንደልማዳቸው «ምንድ'ነው የምሰማው?!.....» ሲሉ ተሰማት። ያም ሆነ ይህ በር ላይ ደርሳለች። የኋሊት መፈርጠጥ አትችልም።

ኳ! ኳ! ኳ! ኳ!

ከዘጠኝ ዓመት በፊት ሻንጣዋን ይዛ የወጣችበትን ቤት አሁን ከነሻንጣዋ ስትመለስበት፤ የሰርጓ ዕለት

እልል እያለ የሸኛት ዘመድ አዝማድ ምን ይል ይሆን?!.....የሠርጓ ዕልት ከድንኳን ወጥታ ስትሄድ እዚችው በር ላይ የተዘፈነላት ዘፈን ለአፍታ ያህል ጆሮዋ ውስት አቃጨለ.....

......አይዞሽ ሙሽሪት አይበልሽ ከፋ

ሁሉም ይሄዳል በየወረፋ።

አይዞሽ ሙሽሪት አይበልሽ ቅር

የማይሄድ የለም የማይዳር......

ትውስቷ እንባዋን ጠራው። የቁጭትና የመንገብገብ ስሜት ሰውነቷን ከታች እስከላይ

ወረራት። እንደ ኤሌክትሪክ የሚነዝር ነገር ተሰማት። እሷ አልቅሳ ሕጻናንም ከማስለቀሷ በፊት ዕንባዋን መግታት መቻል መቻል አለባት። ወላጆቿም ቢሆኑ እንባዋን ማየት አይፈልጉም። እንደ ምንም ታግላ ወደ ውስጥ ምጥጥ አደረገችው። እንባዋን ስትመጥ የአንገቷ ስራ ስሮች ተግተረተሩና እና ባለ በሌለ ኃይሏ ለሦስተኛ ጊዜ በሩን ቆረቆረች።

ኳ! ኳ! ኳ! ኳ! ኳ! ኳ!

ሠራተኛዋ በሩን ከፈተች።

የሥራ ሰዓት ከተቀረ ጀምሮ ወንዳፍራሽም ሆነ ፅጌረዳ አብዛኛውን ጊዜ ለምሳ

ወደ ቤት ስለማይመጡ፤ ዳኔ ቀኑን ሙሉ የፅጌረዳን መሄድ ሳያውቅ ዋለ። ሰብለ ምሳ ላይ ያልተገኘችበት ምክንያት እልፍነሽ ውሸት ፈጥራ ነገረችው። እሷም ራሷ ፅጌረኣ ይዛት መሄዷን ያወቀችው መዋለ - ሕጻናቱ ደርሳ ልጆቹ ከነገሯት በኋ ነበር። ቀኑን በዚህ ዓይነት ተዋለ፤ ማታ ግን የቤተሰቡ መሰብሰቢ ጊዜ ነው። አንድ ቀን ቢዋሹ

ሁለተኛ ቀን መድገም አይቻልም። - ጀምበር ስታዘቀዝቅ፤ እፍልነሽም በጭንቀት ማልቀሷን ጀመረች።

«ለምን ታለቅሻለሽ እልፍነሽ?......ዘምዶችሽ ናፈቁሽ እንዴ?።» አላት ዳኒ በማስተዛዘን አይነት አጠገቧ ቁጭ ብሎ።

«አዎ፤ ዘምዶቼ ናፈቁኝ፤ ዳኒ።.....»

«ታዲያ ለምን ሄድሽ አትጠይቂያቸውም?.......ፅግሽ እንደ ሆነ ትፈቅድልሻለች።»

«አዎ እትዬስ ይፈቅዱልኛል»

«ወንዴም አይከለክልችም»

«እሺ ዳኒዬ.....ቅንቅልፍህ የመጣ ይመስላል። ለምን በጊዜ አትተኛም?»

«አአይ እቆያለሁ።....ቴሌቪዥን አያለሁ።»

ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አካባቢ ወንዳፍራሽ መጣ። ከሮዛ ጋር ሲጨቃጨቅ ቆይቶ ነበር

የመጣው። - የፍቅር ጭቅጭቅ!.....ግንኙነታቸው መላ ቅጡን ያጣ ዓይነት ሆኖአል። ተፈላልገው ተደዋውለው ይገናኛሉ። ተገናኝተው አስር ደቂቃ ሳይጫወቱ ይጣላሉ። በፀብ ውስጥ ፍቅር ሰርተው ያልፉና በመጨረሻ ተኮራርፈው ይለያያሉ። ቆርጠው መቆራረጥ ግን አልቻሉም። ሮዛን ማታ የሚያኮፋት ወንዳፍራሽ አብሮአት በፍቅር አምሽቶ ወደ ሚስቱ መሔዱ ሳይሆን አይቀርም። ከእሷ ጋር ሲቋጭ ያመሸውን ፍቅር ለሊት ሚስቱን የምታረክስባት ይመስላታል። አልጋ ለይተው መተኛታቸውን ሁሉ ልታምነው አልቻለችም። ወንዳፍራሽን የሚያነጫንጨውና የሚያስኮርፈው ደግሞ በትዳሩና በሮዛ ፍቅር መሐል የገባበት ግጭት ነው። ምንም ሆነ ምን ሮዛን ማፍቀሩን ከልቡ ሊፍቅ አልቻለም። እያኮረፈችና እየፈካች፤ ብልጭ ድርግም እያለችበት፣ ፍቅሯ ወጥመድ ውስጥ ጨምራዋለች። እና ፍቅሩ፣ ያነጫንጨዋል። ቤቱ ሲገባ ደግሞ ሰላም የለም።

«......የት ሄዱ?» አለ፤ እልፍነሽ ራስ ስታቀርበልት፡፡ - የፅጌረዳንም የሰብለንም ስም ሳይጠራ፤ በደፈናው፡፡

እልፍነሽ አሁን ዕንባ ያቀረሩ ዓይኖቿን ለመደበቅ እንገቷን አቀርቅራ ወጡን እየጨለፈች «.....የሉም፡፡ ዘመድ ጥየቃ ብለው ሄዱ፡፡» አለችው፡፡

እንባ ካነቀው ጉሮሮ የወጣው ድምጿ ወንዳፍራሽን ጥርጣሬ ውስጥ ጨመረው፡፡ ቀና ብሎ ሲያያት ፊቷም ዳምኗል፡፡

«ወንዴ እልፍነሽ እኮ ዘመዶቿ ናፍቀዋታል፡፡ ለምን ፈቃአድ አትሰጧትም?!.....» አለው፤ ከአባቱ ጋር ገብታ የቀረበው ዳኒ፡፡

«መቸ ጠየቀችን ታዲያ?........መሔድ ፈለግሽ እንዴ እልፍነሽ?.......»

እልፍነሽ መልስ ሳትሰጠው፤ ዓይኖቿ የቋጠሩት እንባ እንጀራው ላይ ጠብ ከማለቱ በፊት ፊቷን አዙራ ወደ ጓሮ ሮጠች፡፡

ወንዳፍራሽ የሚጎርሰው ነገር አፉ ላይ እየተላወሰ አስቸገረው፡፡ የሆነውን ወይም ሊሆን ይችላል ብሎ የሚገምተውን በማሰብ ልቡ ደነገጠ፡፡ ሳያስበው ፊቱ ተጨማዶ ግንባሩ ተኮማትረ፡፡ ግምቱን ጠይቆ ለማረጋገጥ ፈራ፡፡ ነገር ግን ፈርቶ አልቀረም፡፡ ከጓዳ በርቀት የሚሰማው የሰቅስቅታ ድምፅ ገፋፍቶ አስነሳው፡፡ እልፍነሽ ፈቃድ ለመጠየቅ እንደማታለቅስ ያውቃል፡፡ ነገሩ ሌላ ነው ነው! –

«ምንድ'ነው ነገሩ?......ምን ሆነሻል አልፍነሽ?.......» አላት ጓዳ ገብቶ፡፡

«እትዬ......ሄ - ዱ፡፡ ሻንጣቸውን ይዘው ሰብለ - ን - ዘ - ው ሄዱ፡፡.....»

ይሆናል ብሎ የፈራውን ሰማ፡፡ ድንጋጤ ከንዴት ጋር ተደባልቆ ያደረቀው ይመስል ለአፍታ ያህል ዝም አለ፡፡ ዝምታው ስላፈነው ቆይቶ ተነፈሰ፡፡ -

«.......ምን ሆንኩ ብላ ነው የሄደችው?!.......»

የዚህን መልስ የሚያውቀው እሱ እንጂ እልፍነሽ አልነበረችም፡፡ ይህንን ልቡ ስለሚያውቅ መልስ ሳይጠብቅ ወደ ሌላ ጥያቄ ደግሞ ዘለለ፡፡ -

«እሷ የራሷ ጉዳይ ነው፡፡ ህጻኗን ደግሞ ይዛ የሄደው ለምንድ'ነው?!......»

የንዴቱን ለመተንፈስ ያህል ካልሆነ በስተቀር የዚህንም መልስ ከእልፍነሽ አልጠበቀም። እልፍነሽ አፍና የቆየችው ጉዳይ ከወጣላት በኋላ እንባዋም ተግ አለላት።

ሁለቱ የሚያወሩትን በርቀት የሰማው ዳኒ ገበታውን ጥሎ ተነስቶ ወደ ጓዳ ሄደ። አባቱና እልፍነሽ ተፋጠው ቆመዋል። የእልፍነሽ ለቅሶና የአባቱ ንዴት ከምን እንደመነጨ ትንሹ ቆቅ ጠረጠረ።

«በቃ....ፅግሽ እዚህ ቤት ተመልሳ አትመጣም ማለት ነው?» አለ፤ አይኖቹን አባቱ ላይ እያቁለጨለጨ።

«ማነው እንዲህ ያለው?!.......እኛ ሌላ ጉዳይ ነው የምናወራው። ራትህን ከጠገብክ ሂድ ተኛ።»

ዳኒ የአባቱን ቁጣ ፈርቶ ወደ ሳሎን ቢመለስም ነገሩን ችላ ብሎ አልተወውም። ፅጌረዳ ስትበሳች የቆየችበትን ቤት ጥላ መሔዷ በደ መነፍስም ቢሆን ገባው። ግን ወዴት ይሆን የሄደችው? ደግሞስ ለምን ሰብለን ብቻ ይዛ ሄደች? የሚሉት ጥያቄዎች አሳሰቡት። ለወትሮው ቢሆን ከባቱ ጋር በነጻ ከመወያየት ወይም የሚፈልገውን ነገር ከመጠየቅ ወደ ኋላ አይልም ነበር። አሁን ግን የአባቱ ቁጣ ከምንም ዓይነት ውይይት የሚያግድሆነበት። ይሁንና የእናቱን ማጣት በዝምታ ሊቀበል አልቻለም። የባልና ሚስት መጣላት ወይም መፋታትን አስከፊነት ከዘኒ ጋር በሚያደርጉት ጭውውት ተገንዝቧል። አዝማሚያው ዘኒ እንደሆነችው ሁሉ፤ እናት - አልባ ወይም አባት - አልባ አድርጎ እንደሚያስቀረው በልጅነት አዕምሮው እያሰላ ሶፋው ላይ ኩርምት ብሎ ተቀመጦ ሲያለቅስ አባቱ መጣ።

«........በቃ ፅግሽ ሄደች። አሁን ሮዛን ልታገባት ነው አይደል?.....» አለው በድፍረት።

አባቱ በሰማው ንገር ራሱ ዞሮአል። የዳኒ አነጋገር ደግሞ ሌላ ራስ ምታት ሆነበት። ራሱን መቆጣጠር እያቃተው «እናትህ የሄደችው ሌላ ባል ፈልጋ ይሆናል እንጂ፤ እኔ አላባረርኳትም። አሁን ወደ ክፍልህ ግባ ተኛ።» አለው፤ ከአዋቂ ጋር በሚነጋገር ዓይነት ተኮሳትሮ።

«አንተ ባታናድዳት ኖሮ፤ ፅግዬ ቤቱን ጥላ አትሄድም ነበር........»

«ተነስ!.......ክፍልህ ግባና ተኛ ብዬሃለሁ። ይሄ ሁሉ አንተን አይመለከትም!.....» አለና የንዴቱን ጭኑ ስር ገባቶ በቁንጥጫ ለመዘገው።

እናቱን በማጣቱ ሆድ የባሰው ዳኒ ለልቅሶ መንገድ ስለተጠረገለት ፊቱን በእንባ አራሰው። በሚያለቅስበት ጊዜ «ፅግዬ.........ጽግሽ!........» እያለ የእናቱን ስም መጥራቱ ይበልጥ ስላናደደው፤ ይህንን ትንሽ ቆቅ ማስታገሻው ብቸኛ መንገዱ ዱላ አድርጎ በመውሰድ እየቆነጠጠ፤ እጁን ጎትቶ ወደ መኝታ ክፍል አስገባው።

ዳኒ አልጋው ላይ ወጥቶም ቶሎ አልተኛም። አንዳንዴ በቴሌቪዥን ፊልም እንደሚያየው ዓይነት፣ እናቱ ሰብለን ይዛ ከጫካ ውስጥ ብቻዋን ስትጓዝ ወይም በማታውቀው ሀገር ስትንከራተት በሀሳቡ እየተመለከተ ሲያለቅስ ከቆየ በኋላ ለቅሶው ስላዳከመው እንቅልፍ አሸነፈው።

ወንዳፍራሽ የሚሠራውን አጥቶ በኢት ውስጥ መንጎራደዱን ቀጠለ። ራሱን አንድ ቦታ ማስቀመጥ አልቻለም። ብሽቀቱ ከውስጥ እየናጠው በዛቻ ዓይነት ጥርሱን አንቀጫቀጨ። የቤት መፍረስ የንብረቱ መከፋፈልና ፍርድ ቤት የመመላለስ ሀሳብ አዕምሮውን ተጭኖ ሳላስቸገረው ለጊዜው የሚረሳበትን አንድ ዘዴ ፈለገ።

ተንደርድሮ ባፌቱን ሲከፍት ግማሽ ጠርሙዝ መሎቲ ኮኛክ አገኘ። መለኪያ አላስፈለገውም። ከነጠርሙሱ አንዴ ሲጎነጭ ልቡን እየሰጠነጠቀ ወረደለት። እልፍነሽ ዕቃውን አነሳስታው ወደ ክፍሏ ሄዳለች። ዳኒ ተኝቷል። ቴሌቪዥን ተዘግቷል። ጭር ባለው ሳሎን ውስጥ ከኮኛክ ጋር ፍልሚያውን ተያያዘ።

ፅጌረዳ፤ ያቺን ዕልህ እጥፍ መመለስ ያልቻልኩ እንደሆነ እኔ ወንዳፍራሽ አይደለሁም! ትዕግሥትን እንጂ እልህን እንደማልፈራት ታውቂያለሽ!

እየጠጣ ፎከረ። መጠጡ ስራውን መስራት ሲጀምር፤ የፅጌረዳ ቤቱን ለቃታ መሔድ ከሮዛ ጋር ለቀጠለው ፍቅር መልካም የመንገድ መስሎ ታየው። - ልጆቹስ? ንብረቱስ?.......እነዚህን ጥያቄዎች ለመሸሽ የኮኛኩን ጠርሙስ አፉ ላይ ለጎመ።

በሴት ላይ ሴት መውደድ ሐጢያቱ ምንድን ነው?......

በደንብ መስከር ሲጀምር ወደ ሮዛ መደወል ፈለገ። በብስጭት የተብከነከነውና በመጠጥ የጋለው ስሜቱ ሴት አማረው። አጠገቡ የምትሆን ማንኛዋም ሴት!......ሚስቱ አጠገቡ የለችም። ከእንግዲህ አገጠቡ ልትሆን የምትችለው ሮዛ ብቻ ናት።

ወደ ቴሌፎኑ ተጠግቶ ደወለላት።

«ሀ - ሎ......»

«ሮዛ?»

«አዎ!.......ማን ልበል?»

ድምፁ የወንዳፍራሽ መሆኑን ብታውቅም፤ በዚህ ሰዓት ደውሎላት ስለማያውቅ፤ ግራ ገባት።

«ወንዳፍራሽ ነኝ።......»

«የት ሆነህ ነው የምትደውልልኝ?......»

«ቤቴ......»

«ከመቼ ወዲህ?!......ሶስተኛ ውድማህ ቤት ትሆናለሽ እንጂ ምላስህ ሁሉ ተኮላታትፎአል እኮ!......ለዚህ ነው ለካ ቅድም እኔን አካልበህ ገና በጊዜ ቤቴ የወረወርከኝ?!.......»

ከፅጌረዳ ጋር እንዳይጋጩ በማሰብ ቤቱ ውስጥ ቴሌፎን መኖሩን ለሮዛ አልነገራትም ነበር። ከእሷ ጋር የተለያዩት ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ላይ ሰለ ነበር፤ ከዚያ በኋላ ሌላ ቦታ ሲጠጣ ቆይቶ ሲሰክር የደወለላት ነው የመሰላት። ከዚያ ላይ ደግሞ ሲለያኡም ተኳርፈው ነበር።

«ለምን ነገር ነገር ይሸታል ሮዛ? አንቺን ሸኘቼ በቀጥታ ወደ ቤቴ ነው የገባሁት። ቤቴ ስገባ ሚስቴ ዕቃዋን ጠቅልላ ሄዳ አገኘሁ።.....»

«እንኳን ደስ ያለህ!......» አለችው፤ በስካር ምላስ ሊያታልላት መስሏት።

«ይኸው ነው መልስሽ?......»

«ስማኝ ወንዴ! መውደድ ሐጢያት ነው እንዴ? ስለ ወደድኩህ መቀለጃ አደረግከኝ። በዚህ አመናጭቀህ ከቤቱ ወረወርከኝ፤ አሁን ስትሰክር ለአልጋ ፈለግከኝ። ለዚህ አይደል የደወልክልኝ?!.....ከመቼ ወዲህ ነው ቤትህ ውስጥ ስልክ ያስገባኸ?!......ምንም አይደለም! እኔ ጥንቱንም የወንድ እድል የለኝም! ወንዶች ጥንቱንም ሲንቋችሁ እንጂ ሲወዷችሁ እንዳምትወደዱ አውቃለሁ!......»

«ም - ም - ምድ'መው የምታወሪው ሮዛ?......የኔን ችግር አታዳምጪኝም እንዴ?! ምላስ እንጂ ጆሮ አልፈጠረብሽም መሰለኝ!.....»

«አዎ ለፍላፊ ነኝ። ስደበኝ በገዛ እጄ ያመጣሁት መዘዝ ነው። ለማንኛውም ነገ በጤናማ ምላስህ ብታነጋግረኝ ይሻላል። እኩለ ሌት ላይ የሚደውልልኝ ሸርሙጣ አይደለሁም!......» ብላ ጆሮው ላይ ዘጋችበት።

ዓለም ስትከዳው እንዲህ በአንዴ ይሆን እንዴ? ባለበት ፈዝዞ ቀረ። ሰማይ ምድሩ ብዥዥ አለበት። - ቤሽቲያን! አለና የስልኩን እጀታ ወደ ቁፎው ወርውሮ የኮኛኩን ጠርሙስ ጨበጠ።

በሚስት ላይ ሴት መውደድ ሐጢያት ነው ወይ? –

«.....ምን ሆነሃል ዳኒ? ዛሬ ደግሞ ተከዘሃል።»

ፊቱን ጭምድድ አድርጎ፣ በአንድ እጁ ቦርሳውን አንጠልጥሎ ሌላኛውን እጁን ኪሱ ጨምሮ ጠዋት ከትምህርት ቤቱ ግቢ ሲደርስ፣ ዘኒ ሮጣ ተቀበለችው። ማታ ያለቀሰሰባቸው አይኖቹ አባብጠዋል። ዘኒ ጥያቄውን ስታቀርበልት የእሷም ድምፅ በሐዘን ቅላፄ ነበረው። የትንሹ ጓደኛዋ መከፋት እንደ ኤሌክትሪክ ሾቦ በአንድ አፍታ ወደ እሷም ተላለፈ።

«ፅግዬ ሰብለን ይዛ ቤቱን ጥላ ጠፋች።......» አላት ጉሮሮውን እንባ እያነቀው።

«ውይ......በቃ ተፋቱ ማለት ነው?! ኤርሚ እኮ አስታርቃቸዋለሁ ብሎ ነበር።
»

«አልታረቁም። ቤት ውስጥ እንኳ ተነጋግረው አያውቁ። ምግብም የሚበሉት የለብቻቸው ነበር።......»

ዘኒ ከንፈሯን መጠጠችና፤ «አሁን በቃ አንተ ከአባትህ ጋር፤ ሰብለ ከእናቷ ጋር ትኖራላችሁ ማለት ነው።» አለችው።

«እኔ ከወንዴ ጋር አልኖርም። ፅግዬን ፈልጌአት እሄዳለሁ።» «የት እንደሄዱ ታውቃለህ እንዴ?»

«አላውቅም።......ግን እፈልጋታለሁ። በየመንገዱ ሰዎች እየጠየቅኩ እሄዳለሁ፤ ። በፊልም ውስጥ የጠፉ ሰዎች የሚገናኙት እንደሱ አይደል?!......»

«ታዲያ እነሱ ትልልቆች ናቸዋ! አንተ እኮ ትንሽ ልጅ ነህ። ብዙ መንገድ ስትሄድ ትደክማለህ። ደግሞም ይርብሃል።......»

«ቢርበኝም እሄዳለሁ እንጂ ከወንዴ ጋር አልቀመጥም። ትላትና ማታ ስለ ፅግሽ ስጠይቀው ጊዜ ደበደበኝ።.....»

«በምን ደብደቡህ?»

«በቁንጥጫ።....»

«ታዲያ አባትህ ስለሆኑ ነዋ!.....»

«ቢሆንስ?.....ዱሮ ይቆጣኛል እንጂ አይመታኝም ነበር አሁን ፅግሽ ስለ ሄደች። .....»

ዳኒ የማታው ሁኔታ ታውሶት እንደ ገና በዓይኖቹ ሙሉ እንባ ግጥም አለ። እናቱ በሌለችበት ቤት ውስጥ የሚኖረው ህይወት መራራ ሆኖ ታየው። ሰብለ ከእናቷ ጋር በመሔዷ ዕድለኛ አድርጎ ገምታት።

«እሱ ባይመታኝም ሮዛን ሰለማልወዳት አብሬ አልኖርም።......» አለ ሳግ እየተናነቀው።

«ሮዛ ማን ናት?.....»

«አዲሷ የወንዴ ሚስት ናታ! አንድ ቀን ነግሬሽ አልነበር?!»

«እ....አዎ፤ አሁን ቤታችሁ መጥታለች እንዴ?.....»

«መምጣቷ አይቀርም። ፅግሽ እስክትሄድ ነበር የምትጠብቀው። ......እልፍኝሽም አዲሷን ሚስት ስለ ማትፈልጋት ትላንት ማታ ፅግሽ ስለ ሄደች አለቀሰች።

ሲታገለው የቆየውን እንባ ዱብ - ዱብ እያለ ጉንጮቹን አረጠባቸው። ዘኒ አንገቱን አቅፋ በሹራቧ እጅጌ እንባውን እየጠራረገችለት ታባብለው ጀመር።

«በቃ ዝም በል ዳኒ። እኔ እንኳ አባት የለኝም፤ ግን አላለቅስም።.....»

በትምህርት ቤቱ ግቢ ውስጥ የሚተላለፉት ልጆች ለቅሶውን ሲያዩ ዙሪያውን ከብበው ይወተውቱት ጀመር።.....

ምን ሆነህ ነው ዳኒ?

ቁርስህን አልበላህም እንዴ?

ለደብተር መግዥያ የተሰጠህ ፍራንክ ጠፍቶበት ነው መሰለኝ......

አአይ! በጠዋት ጥፋት አጥፍቶ ገርፈውት ይሆናል.....

«እስቲ ወይዱ.....ምን አይነቶቹ ናቸው! ሰው ሲያለቅስ አይታችሁ አታውቁም እንዴ?!....» አለች ዘኒ፤ የዳኒን ክንድ ይዛ ከአጠገባቸው ዘወር አለች።

ዕሑድ ጠዋት፤ ፅጌረዳ ከእንቅልፏ ስትነቃ አጠገቧ ከተኛችው ሰብለ በስተቀር ማንንም አላገኘችም። አባትና እናቷ በሌሊት ቤተ ክርስቲያን ሄደዋል። ታናሽ ወንድሟ ውጭ እንዳደረ አልመጣም። ሠራተኛዋ ለቁርስ የሚሆን ዕንቁላላ ለመፈለግ ወደ ሱቅ ሄዳለች። ሰብለም ብትሆን ድብን ያለ እንቅልፍ ላይ ነች። የመኝታ ክፍሏን መስኮት ከፍታ ውጭውን ስታይ ፀጥ ረጭ ባለው ግቢ ውስጥ አትክልቱ ላይ ያረፈችው ፀሐይ ውበቷን አሳይታ ጋበዘቻት።

የሌሊት ልብሷን አውልቃ ረዥም የቤት ቀሚስ ካጠለቀች በኋላ የፀሐይዋን ግብዣ ተቀብላ ልትሞቃት ወጣች። የተክሎቹ የጠዋት ትንፋሽ አፍንጫዋን አወዳት። የአባቷ ጥንካሬ እያስገረማት ወደ አበቦቹ መሐል ስትገባ የረዥም ዓመታት ትዝታ ፈረሱን ጭኖ በአዕምሮዋ ውስጥ እየመጣ ነበር። ዱሮም እዚህ አባቷ ቤት በምትኖርበት ጊዜ፤ ግቢው እንዲሁ በጥዶችና በአበቦች የተዋበ ነበር። አሁንም ቢሆን

አባቷ ራሳቸው በጠዋት አትክልቱን ውሃ ማጠጣት የመጀመሪያ ስራቸው ነው። ወደ ኋላ መሔድ አይወዱም። ሽንፈትን በመሸሽ የደም ስሮቻቸው እየተግተረተሩ የነበረውን እንደ ነበረ ለማቆየት የሚጥሩ ሰው ናቸው።.....

ፅጌረዳ አንዱን የአበባ ግንድ ጠጋ ብላ በእጆችዋ እየነካካች ከትዝታዋ ጋር መጫዋወቷን ጀመረች። ዕምቡጥ አበቦቹ የራስዋን የልጃገረድነት ዘመን አስታወሷት። ጥብቅነት፣ ድብልብልነት፣ ያለመዘረጋጋትና ለጋ ውበት በዕንቡጥ አበቦቹ ላይ ተመለከተች።

እኒህ ዕምቡጥ አበቦች ወደ ፊት መዘረጋጋት መርገፍና መጠውለግ እንደሚጠብቃቸው ቢያውቁ ጥሩ ነበር፤ በማለት ለራሷ እየተነፈሰች የትዝታዋን ፈረስ ተሳፈረች።

ለወላጆችዋ ሁለተኛ ልጅ ብትሆንም ቅሉ የመጀመሪያ ልጃቸው ፈረንሳይ ሐገር ለትምህርት በመሄዱ በቤት ውስጥ እንደ መጀመሪያ ልጅ ሆና ነበር ያደገችው። በተለይ አባትየው ለፅጌረዳ ልዩ ፍቅር ነበራቸው። የደም ግባትዋ፣ ሰልካካነትዋና የልጅነት ወዘናዋ የሚማርካቸው መንደረተኞች ሁሉ ተልካ በሄደችበት ቤት ጉንጭና ጉንጪን ጥብቅ አድርገው ሳይስሙ አይለቋትም። ያን ጊዜ ትንሿ ፅጌረዳ የሽማግሌዎቹ ፂም ስለ ሚኮሰኩሳት ከአጠገባቸው ዘወር ትልና ጉንጭዋን በእጆቿ ፍትግ አድርጋ ትጠርጋቸዋለች። የቅርብና የሩቅ ዘመዶቿ ከፍቅራቸው ብቻት በየሳምንቱ የዕረፍት ቀናት ቤታቸው እየወሰዱ ለማሳደር ወረፋ ይይዙላት ነበር። የዘመን መለወጫ ዕለት ከዕሷ ጋር «አበባዬ ሆይ» ለመጫወት የሚመጣው ቡድን ከመንደሩ ውስጥ ከፍተኛውን ገቢ ያገኛል። ለቡድኑ ፍራንክ በመስጠት ለፅጌረዳ ያለውን ፍቅር የሚገልፅ ቤተሰብ ብዙ ነበር። የገናን በዓል ምክንያት በማድረግ በትምህርት ቤቱ ውስጥ በሚደረገው ዝግጅት ላይ ተደበቀ ይስሟት የነበሩ ልጆች ምስል እስካሁን ከፊቷ አልጠፋም። መዝሙሩና ጭብጨባው ልቡና ወስዶት ጨዋታው መሐል ገብታ ስትወዛወዝ አንዱ ይመጣና ድንገት ጉንጭዋን ላይ ሳም አድርጓት ይሮጣል። ለጥቂት ጊዜ አፈር ብላ ተቆጥታ ቆይታ እንደ ገና ጨዋታዋን ስትጀመር ደግሞ ሌላው ይመጣና ያም አድርጓት ይሮጣል። ትንሿ ፅጌረዳ ትበሽቃለች። አንዳንዴም ታለቅሳለች። እሷ

የምትወደው «ባልና ሚስት» የምትጫወተውን የአይነ አፋሩን ሄኖክን ነበር። ሄኖክ ግን ስታቅፈው እየፈራ ይሸሻታል።.....

እያደገች ስትመጣ ጡቶቿዋ ሲያጎጠጉጡ፣ ወንዶች አይናቸውን ሲተክሉባት ውበትዋ ታወቃት። መስታወት አጠገብ ብዙ ደቂቃዎች መቆም ጀመረች። - ጠይም ፊቷንና ሰልካካ አፍንጫዋን ለማየት፣ ወንዶች በርቀት ዓይኖቻቸውን በርቀት የሚወነጭፉበትን ውበቷን በራሷ ዓይን ለመገምገም ከመስታወት ጋር ተፋጥጣ ትቆማለች። ከአካባቢዋ የተማረችው የሴትነት ስሜትም ራሱን ለማስከበር ከውስጥ ብቅ፣ ብቅ፣ ማለት ጀመር። ወንዶች ሲያዩዋት እሷ አይኖቿን ሰበር፣ አረማመዷንና አነጋገሯን መጠን! እንደ እንቡጥ አበቦቹ ጠበቅ!.....

ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስትገባ ለአቅመ ሔዋን ደርሳ ነበር። ይህ ጊዜ ከፍተኛ የፈተና ዘመንዋ ሆነ። ዕምቡጧን ፅጌረዳ ለመቅጠፍ ያላሰፈሰፈ ወንድ አልነበረም። አስተማሪዎቿ ሳይቀሩ ክፉኛ ከጀሏት። እንዲያውም እያስተማረ በመሐሉ ወደ ፅጌረዳ ሲመለከት ፍዝዝ የሚል አንድ የጂኦግራፊ አስተማሪ ነበረ። ዕምቡጧ ፅጌረዳ አጠገቡ ኮስተር ትልናውጭ ስትወጣ ከጓደኞቿ ጋር ሆና ትስቅበታለች። በብዙ ወንዶች መወደድ ሊያሳድር የሚችለው ኩራትና ጣዖትነት ቀስ በቀስ እየተጠናወታት መጣ። ይሁን እንጂ በእሷም በኩል አፍላ ዕድሜዋ እሳታዊ ስሜቱን እያነደደ ይፈታተናታል። በውበትዋ ተማርከው በዓይናቸው ከሚሳለሟት መሐል ልቧ የጀከላቸው ይኖራሉ። ትቀርባቸዋለች። ከትምህርት ቤት ወደ ቤቷ ከቤቷ ወደ ትምህርት ቤት የዕግር ሊፍት ይሰጧታል። ከዚያም የከፈር ጓደኝነት ይጀምራል። በመዐዛዋ የተማረከው ጎረምሳ ዕምቡጧን ካልቀጠፍኩ ሲል ጓደኝነት ይፈርሳል። ትንሿ ፅጌረዳ አፍቃሪዎቿን ከከንፈር አላሳለፈቻቸውም። የእነሱ ብቻ ሳይሆን የራሷም ስሜት እየጋለ ሲያስቸግራት ደግሞ የወላጆቿን ምክር እያስታወሰች ታበርደዋለች። «ሰማሽ ፅጌረዳ፤ የምወድሽ ልጄ......በወግ በማዕረግ እንድታድጊልኝ እፈልጋለሁ.....» የሚለው የአባቷ ግርማ ሞገሳዊ ድምስጽ አዕምሮዋ ውስጥ ያቃጭላል። ወግ ማዕረግ ከምን ጋር እንደሚያያዝ ስላስተማራት፣ እሳታዊ የሔዋን ስሜቷን እያፈነች ድንግልናዋን ይዛ ቆየች።

ለሥራ ዕድል የመቻል ተብሎ የንግድ ስራ ትምህርት ቤት ስትገባ፤ አዲሱ የህይወት መንገድ ተጠረገ። ፅጌረዳ በትምህርት ቤቱ የኋላ በር መግባትና መውጣት ታዘወትር ነበር። በዕረፍት ሰዓታ «ቴሌ ባር» ጎራ ብሎ ሻይ ቡና መጠጣቱን ተለመደ። ቴሌ ባር መኪና ውስጥ ከሚያስተናግዳቸው ደንበኝኖች ጋር ከመተያየት ብዛት የዓይን ሰላምታ ተጀመረ። አብዛኛው ባለ መኪና የኋሮውን በር ከሚጠቀሙ ተማሪዎች ጋር በዓይን መቀለዋወጡ የተለመደ ነገር ነበር። አንዳንዱ እንዲሁ የዓይን አዋጅ ሆኖበት የምትገባ፣ የምትወጣውን ወይም ግንቡን ተደግፎ የምትቆመውን ሲቃኝ ይውላል። አስቦበት መጥቶ ተቀለጣጥፎ ለራት የሚያደርስ ሳተናም አለ። ፅጌረዳ የደረሳት የዓይን ቀላዋጭ ግን በዋዛ ፈዛዛ የሚለቃት አልነበረም።

የትምህርት ቤት መግቢያ ሰዓቷ ከመድረሱ በፊት ቀድሞ መጥቶ ብጫ ፊያት 124 ሞዴል በሩ ላይ ይጠብቃታል። ከባለ ቤቱ ጋር ንግግር የላትም፤ ነገር ግን በዓይን ተላምደዋል። አንድ ቀን በድፍረት ክላስክ ነፍቶ በርቀት ሰላምታ ሰጣት እንደማፈርም እንደ መደናገጥም አርጓት አንገቷን ቀለስ አድርጋ ሄደች። አንዴም ስትደነግጥ አንዴም ዕቃ እንደ ረሳ ሰው ቅር - ቅር ሲላት አመሸች። ይባስ ብሎ ሰውየው በህልሟ መጣባት። ከመኪናው ወጥቶ ባትየውም፤ ከወገቡ በላይ ደንደን ያለው ሰውነቱና ግርማ ሞገስ የሚረጨው የደስደስ ያለው ገፅታው አዕምሮዋ ውስጥ ተቀርጿል። ደግሞ ብዙውን ጊዜ የሚመጣው ብቻውን ነው። ከአለፈ ገደም ወንዶች አብረውት ይመጣሉ። ኮረዳ ግን አጠገቡ አይታ አታውቅም።

ሰውየው የሚሠራውን የሚያውቅ ነበር። በርቀትም ቢሆን ባይነጋገሩም፣ ፀባይዋን ባያውቅም፤ ፅጌረዳን ወድዷታል። የቸኮላት ቀለም የያዘው ፊቷ፤ የሚያባብሉ ዓይኖቿና በዕምቡጥነት እጥፍ ዘርጋ የሚለው የተስተካከለው ቁመናዋ ልቡን አጥፍቶታል። ይሁን እንጂ እሱ ስለ ፈለጋት ብቻ ጡንቻውን ወጥሮ አልተጠጋትም። ይብዛም ይነስ ከፅጌረዳ በኩል ደግሞ ፍላጎት መኖር ያለ መኖሩን ለማረጋገጥ በርቀት ይፈትናት ጀመር። መኪናውን ጥሎ በእግሩ ይሄድና ከአንድ ጥግ ን ስፍራ ተደብቆ ወደ ትምህርት ቤቱ ስትገባ ይመለከታታል። ቀጥ ብላ አትገባም። በአይኗ ብጫ ፊያት ትፈልጋለች። ወደ ውስጥ ከገባችም በኋላ ወደ ኋላዋ ዞወር እያለች በአጥሩ አሳልፋ ወደ ውጭ ታያለች። ለጥቂት ቀናት ተሰውሮ ይህን በመሰለ መልክ አጠናት። ዓይኖቿ ብጫ 124 ፊያት ወይም ደንደን ያለው እንድ በመፈለግ

መንከራተታቸውን ከገመገመ በኋላ የዓይን ቅልውጦሹንና የርቀት ሰላምታውን ወደ ቅርብ ግንኙነት ለመለወጥ ወሰነ። ወንዳፍራሽ በቀለ ይህን የድብብቆች ሚስጥር የነገራት ከተጋቡ በኋላ ነበር።

ሲቀራረቡ ይበልጥ ተዋደዱ። የወንዳፍራሽ አርቆ አስተዋየንትና ትህትና ከደንዳና ሰውነቱ ጋር የፅጌረዳን ልብ አሰረው። በቁንጅናዋ ላይ ወርቅ የሆነውን ፀባይዋን ቀርቦ ሲያውቅ እሱም በፍቅር ከነፈ። ከቢሮው ወጥቶ ፅጌረዳን ወደ ትምህርት ቤቷ የሚያደርስበት ወይም ከትምህርት ቤት ወጥታ ወደ ቤቷ የሚመልስበት ሰዓቶች ወርቃማ ጊዜው ሆኑ። ማታ ሲለያዩ ጨለማን ተገን አድርገው ከንፈር ለከፈር መሳሳሙ የየዕለቱ ተናፋቂ ጉዳይ ሆነ። ለአንድ ዓመት ተኩል ያህል ቀለበት አስረው ቆይተው ፅጌረዳ የፀሐፊነት ሳይንስ ትምህርቷን ጨርሳ ስትመረቅ ተጋቡ። እዚሁ አባቷ ግቢ ውስጥ ቅልጥ ያለ ሠርግ ተሰርጎ ፅጌረዳን «አይዞሽ ሙሽሪት.....» እየተባለች ወጣች። ወንዳፍራሽ አጃቢዎቹን «ሀይ......ሎጋ» እያዘፈነ ይዞአት ሄደ።.......

ፅጌረዳ ትዝትዋ እንዳቃጠላት ሁሉ በረዥሙ ተነፈሰች። ጠይሙ ፊቷ ድሮ የነበረውን፤ አሁን ግን የጠፋን ወርቃማ ጊዜ በማስታወስ ዳመና ለብሷል። ከንፈሮቿ እንደተከደኑ ናቸው። ዓይኑቿ ግን ከአበቦቹ ላይ አልተነቀሉም። ይልቁንም የህይወቷን የትዝታ ምዕራፍ ተከትለው ከእምቡጦቹ ወደ ፈኩት አበቦች ተሸጋገሩ።.....ዕምቡጥነት ሲያከትም......ፍካት ሲከተል።.....አበቦች ተዘርግትው፤.....ሚስጥራቸውን ገልጠው.....ዘራቸውን....ፍሬያቸው ሲያሳዩ፣.....ሴምግቡ........የዓይን የተስፋ፣ የፍቅር ማረፊያ ሲሆን.....ዘር ሲሰጡ፣........ፅጌረዳ እንደገና የትዝታዋን ፈረስ ተፈናጠጠች።

ወንዳፍራሽ ፅጌረዳን ሲያገባ ተከራይቶ የሚኖርባት አነስተኛ የወንደላጤ ቤት ነበረችው። ከዚያ ውጭ የሚኮራባት ያቺው መኪናው እንጂ የረባ የቤት ዕቃ አልነበረውም። ቤቷን በፍቅር አሞቋት። የሆቴል ምግብ ቀርቶ እሳት አነደዱበት። በጎረቤትም በጉዳኛም ዘንድ የሚያስቀና ዕፁብ ድንቅ ፍቅር ሆነ። እሱ «ፅግሽ» እሷም «ወንዴ» ከማለት ፍቅራቸውን በቁልምጫ ገለጹ።

ቀስ በቀስ ስሜታዊ ፍቅር ለቤተሰባዊ ፍቅር ቦታውን ለቀቀ። መተሳሰብ መማማር መተራረም፤ ለጋስ ጎጆ ጠንክሮ መቆም! - ትንሿ ቤት በረዥምሙ ላቀዱት

ፍቅርና ትዳር ልትበቃ አልቻለችም። ዳኒ ሲወለድ ሶስተኛ የቤተሰቡ አባል ሆኖ የፍቅሩን ምሰሶ አጠበቀው። ሁለቱም በከፍተኛ የፍቅርና የጉጉት ዓይን የሚያዩት ድንቡሽቡሽ ያለ ሕፃን ነበር። ሶስተኛው የቤተሰብ አባል መፈጠር ከባንክ ተበድሮ የራሱን ጎጆ የመቀለሱንም ሀሳብ አስከተለ።

የፅጌረዳ ቁንጅና ከስራ ፍቅርና ትዳሯን ከማክበር አላገዳትም። ከውጭ የሚከተላንት በመቶ የሚቆጠር የወንድ ዓይን የቤቱ ውስጥ ፍቅር ያበርርላት ነበር። አዲሱን ቤት ሲሰሩም ያሳየችው ጥረትና ድካም ከወንዳፍራሽ ይበልጥ እንደሆነ እንጂ፤ አያንስም። ከመስሪያ ቤቷ ስትመለስ ወይም በዕረፍቷ ቀን ሱሪዋን አጥልቃ ከአናጢዎች ከግንበኞች ጋር ስትሰራ ትውል ነበር። የወንዳፍራሽ የቢሮ ስራ ፀባይ ፋታ ስለሚነሳው አብዛኛውን የቤቱን ሥራ ተከታትላ ያስጨረሰችው እሷ ናት።

የተመጣጠነ የልጆች አስተዳደግ እንዲኖራቸው ባቀዱት መሠረት ዳኒ በተወለደ በሶስት ዓመት ልዩነት ሰብለ አዲሱ ቤት ውስጥ ተወለደች። የልጆቹንም ሆነ የእነሱን ኑሮ በአቅማቸው የተሟላ ለማድረግ ሰብለ የመጨረሻ ልጅ እንድትሆን ወሰኑ። አስፈላጊውን የህክምና ጥበብ ተጠቅመው መውለድ አቆሙ።

በዕቅድ የተመራ ኑሮና ፍቅር ስምንት ዓመት ያህል ኮሽ ሳይልበት ቆየ። እና አሁን በስተመጨረሻ ከውጭ እንቅፋት ተፈጠረ። ሮዛ!.....ሮዛ!......ሮዛ!.......የቤት ውስጥ ፅጌረዳ ፍካቷን ጨርሳ፣ ፍሬዎቿን ሰጥታ ስትዘረጋ፤ ወንዳፍራሽ ዕምቡጥ ፅጌረዳ ፍለጋ ወደ ውጭ ወጣ። የውጭ ፅጌረዳ አይኑንም ልቡንም አወረው። የደከመበት የቤቱ ምሰሶ ሲናጋ ፈዝዞ ይመለከት ጀመረ።......

የፅጌረዳ ዓይኖች እንባ አቀረሩ። አበቦቹ መሐል እድነቆመች ስቅስቅ ብላ ማልቀስ ፈለገች። ዕንባዋ አበቦቹ ላይ እየረገፈ የልቧን ሚስጥር የሚያዋይላት መሰላት። በሀሳብዋ የውስጥ ሰውነቷን ስትመለከት የዱሮውን እንቡጥ ገላዋን ሳይሆን፣ ሁለት ልጆች ከወለድች በኋላ የላሉት ጡቶቿ እንዲሁም የሸንተረር መስመር ያበጁት የሆድና የጭን ቆዳዎቿ ታዩዋት። ወጣትነት ሸሽቶአት ጉልምስና፤.....ጉልምስና ወደ እርጅና አሻግሮ ሊወረውራት መሰላት። ዓይኖቿን ከፈኩትና ከተዘረጉት አበባዎች ላይ ነቅላ ጠውልገው መሬት ላይ የረገፉ አበቦች ትፈልግ፤ ጀመር። ያ ውበት ዕምቡጥነትና ፍካት ጠፍቶ ከፊሎቹ ደራርቀዋል፤ ከፊሎቹ ጠወላልገዋል። ቀይ ቀለማቸው ወደ

አመዳምነት ተለውጧል። ጥቂት ቆይተው ከቆሻሻ ጋር አብረው ይጠረጋሉ። .....የፅጌረዳ አይኖች የጠወለጉትንና የደራረቁትን አበቦች የፀየፉ። በፍራቻና በጥላቻ የግንባሯን ስራስሮች ተግተረተሩ። እናም እኔነቷ ራሱን ሲመከት አዕምሮ ውስጥ የሆነ ነገር ሲያቃጭል ተሰማት........

ገና ነሽ ፅጌረዳ! ገና ነሽ!.......ራስሽን እንደ ረገፉት ወይም እንደ ጠወለጉት አበቦች ልትቆጥሪ አይገባም። አሁንም ውብ ነሽ! ወንዳፍራሽ ቢቀር ሌሎች ሺህ ጠምበለል ወንዶች ይፈልጉሻል። የዕምቡጥነት ዘመንሽ አልፏል፤ የፍካት ዘመንሽ ግን አላለቀም። ገና ብዙ ዓይኖች ይስባል ይማርካል ያሳብዳል። መጠጥ ያለው ውበትሽን የሚቋምጡ ብዙ ናቸው። እና ራስሽን አትጣውይ! - ጠብቂው ተንከባከቢው ከፍ አድርጊው!....

አንዳች ኃይል እንደገፋፋት ሁሉ በድንገት ከፈኩት አበቦች መሐል አንድ ዝንጣፊ ቀጥፋ ወደ ላይ ከፍ አድርጋ ያዘቻት። ከእናቷ በላይ ከፍ አድርጋ በአምልኮትና በፍቅር ዓይን አየቻት።

ከአበባዋ ጋር በመጫወት ላይ ሳለች ከኋላዋ ድምፅ ሰማች ዘወር ስትል ሰብለ የቤቱን ትንሽ ደረጃዎች ወርዳ እየሮጠች ወደ እሷ ስትመጣ ተመለከተች።

«ት - ት - ዬ!.......ትግዬ!.....ት....ግ.....ዬ!......»

እየተንደረደረች ሄዳ እናቷ ላይ ተቀመጠችባት። ፅጌረዳ ጥብ አድርጋ ከሳመቻት በኋላ ፊቷንና ዓይኖቿን በነጠላዋ ጫፍ ጠራረገችላት። ከእንቅልፍ እንደ ተነሳች ነበር እናቷን ፍለጋ የወጣችው።

«እንቅልፍሽን ተገበሽ?......ሰብልዬ።»

«አዎ! ትግዬ......የያዝሻት አበባ ደስ ትላለች።»

«ልስጥሽ እንዴ?.....»

«አዎ፤ በናትሽ........»

«የማትጥያት፤ የማታጠወልጊያት የማታረግፊያት ከሆነ ብቻ ነው የምሰትሽ።

»

«ትግዬ ሙች፤ አላተወልጋትም.....አለላግፋትም።»

«እንኪ በይ፤ እንዳትጠወልግብሽ በረንዳው ላይ ከሚገኙት አፈር የተሞሉ ቆርቆሮዎች ውስጥ ተከያት። ፀሀይና አየር ታገኛለች። አንቺ ደግሞ ጠዋት፤ ጠዋት ውሃ ታጠጫታለች።

እናትየዋ በራስዋ የቀን ሕልምና ትርጉም ተመስጣ በጥንቃቄ የሰጠቻትን አበባ ሕፃንዋ እንደ ዋዛ ተቀብላ በፍቅር ዓይን ትመለከታት ጀመር፤ ዓይኖቿ ሁሉ በሩ። ፈንድቂ ፈንድቂ የሚል ስሜት ተሰማት። ብዙም ሳትቆይ ግን አንድ ሌላ ስሜት ስለ ተጫጫናት ከፍት፤ ጭምድድ! አደረገችው።

ቆንጆ ነገር ስታይ ወይም ስታገኝ ሮጣ ለዳኒ ለማሳየት ልማድ አድሮባታል። አሁንም አበባዋን እያቁለጨለጨች «ይሄውልህ ትጌዬ የሰጠችው አበባ!» ማለት ፈልጋ ስታስታውስ ዳኒ በቅርብ የለም። ከተለያዩ ጥቂት ቀናቶች አልፈዋቸዋል። ዓይኖቿን ከአበባዋ ላይ ነቅላ በትካዜ ወደ እናትዋ እየተመለከተች ብሶቷን ገለፀች.....

«ትግዬ.....ዳኒ ናፈቀኝ።»

«እኔም ናፍቆኛል፤ ሰብልዬ።»

«መቼ ነው ወደ ቤታችን የምሄደው?»

የሰብለ ጥያቄ የእናትየዋንም ስሜት ለዋወጠው። የአንገቷ ጅማቶች ተግተረተረ። ገፅታዋ ተለዋወተ። ጉሮሮዋ ላይ የሚታገላት ነገር ለመግታት ምራቋን ደጋግማ ዋጠች፤ እና ዓይኖቿንም ጨምቃ ጥርሶቿን አንቀጫቀጨች።

«ትግዬ......አልሰማሽኝም እንዴ?»

«ሰምቸሻለሁ ስብልዬ አይዞሽ፤ ዳኒ ዛሬ ከእልፍነሽ ጋር ይመጣል.......»

«ወንዴስ.....አብሮ ይመታል?»

«አባክሽ ወደ ቤት እንግባ ሰብልዬ.....ፀሐዩ እየበረታ ነው።»

«ብዙ ቀን እኮ ሆነን......ወደ ቤታችን ሳንሄድ.....»

«ዝም በይ እባክሽ፣ ሰብልዬ......»

እናትና ልጅ ዳኒን በመጠበቅ ውጭ ውጭውን ሲያዩ አረፈዱ። ነገር ግን አልመጣም። አባትየው ከልክሎ እዳስቀረው ፅጌረዳ ጠረጠረች። ቢመጣ በጠዋት ይመጣ ነበር።....እና በናፍቆት ሲላወስ የከረመው የእናትነት አንጀቷ ይብስ መንቦጫቦጩን ቀጠለ። በሌላ በኩል ደግሞ «በገዛ ልጄ......» የሚል ዕልህ ተናነቃት። ብርር ብላው ወደ ቤቷ ሄዳ፣ ወንዳፍራሽን ሙልጭ አድርጋ ሰድባ፤ የዳኒን እጅ ጎትታ ማምጣት አማራት። የእናትነት መብቷ ያን ያህል የሚያስኬድ መሠላት።

ሰውነቷ በዕልህ ተወጣጥሮ ይህን በመሰለው ሀሳብ ስትዋዥቅ ያልተጠበቀ እንግዳ ከተፍ አለ። - ኤርሚያስ ዘለቀ ነበር። ፊቱ ተጨማድዷል። ፀጉሩ በቅጡ አልተበጠረም። አንድ እጁን ኪሱ ከትቶ በሀሳብ ሰውነቱን እያወራጨ በግዴለሽነት አረማመድ ወደ ግቢ ሲገባ ላየው ሰው፤ ቤተኛ እንጂ እንግዳ አይመስልም። ፅጌረዳ ከቤቷ ወጥታ አባቷ ቤት በሄደች ማግስት ወሬውን ከዘኒ ሰምቶ መጥቶ ጎብኝቷት ነበር። ሁኔታዋ ለውይይት አልተመቸውም። በብሽቀት ተብከንክና፤ ብቻዋን መኝታ ቤቷን ዘግታ የምታለቅስበት ጊዜ ነበር። በዚያ ላይ ደግሞ ወላጆቿም ሆኑ ሌሎቹ የከበቧት ዘመዶቿ የወሰደችውን ስሜታዊ ውሳኔ በመደገፍ «አይዞሽ......አይዞሽ» የሚሉ ነበሩ። ኤርሚያስ እዚያ መሐል ገብቶ «አደፍርስን» መሆን አልፈለገም። እርሷም የስሜት እሳት እስኪበርድ፤ ዘመዶቿም አሟሙቀው ዘወር እስኪሉ ለመጠበቅ ጥቂት ቀናቶች ማሳለ ነበረበት። ይሁን እንጂ ከዘመዶቿ መሀል አንድ አንኳ «ተሳስተሻል» ወይም «ታገሺ» ብሎ ወደ ትዳሯ ለመመለስ የሞከረ ባለ መኖሩ ኤርሚያስ እየበሸቀ ነበር ወደ ቤቱ የተመለሰው። ንግግራቸው በንዴት አዕምሮ ውስጥ ተቀርጾ ቀርቷል።......

ወንዳፍራሽም ለዚህ ደረሰ?!.......የሚያሳዝን ጊዜ ነው!

ቀለበት ያሰረልሽ ጊዜ በፍቅር አብዶ እግርሽን መላስ እንዳልቀረው ሁሉ።......

የዘንድሮ ወንድ ምኑ ይታመናል?!......

ደግ አደረግሽ!........እንኳን ቤቱን ለቀቅሽለት ወጣሽ!.......ለምን ብለሽ ትቃጠያለሽ ልጄ!.....

ኧረ ለምን ብለሽ?! ምን ጎድለብሽና! አንቺ ከፈለግሽ ገና አስሩን ወንድ እንደ በግ ትነጂዋለሽ......

ኤርሚያስን ያስገረመው ይህ ብቻ አልነበረም። ሰሞኑን የፅጌረዳ ታናሽ ወንድም «ጆንትራውን» ተበጥሮ ከንዱን ጠቅልሎ፤ ወንዳፍራሽ ካልደበደብኩ እያለ መስሪያ ቤቱ ድረስ ሄዶ መጋበዙን የሰማ ዕለት ማታ፤ እንቅልፍ አጥቶ ሲመራመር ነበር ያደረው።

እስቲ አሁን ባልና ሚስት ይህን ያህል ዓመት አብረው ኖርወ ከወለዱ ከከበዱ በኋላ የኋሊት ከፋፍሎ ወገናዊነት ማሳየትን ምን አመጣው?! እኒህ ጥንዶች እኮ በአንድ ታዛ ስር ከዋሉ ጀምሮ ሁለትነታቸው ቀርቶ አንድ ሆነዋል! ከዚያም በላይ ደግሞ በልጆቻቸው አማካይነት ተጣምረዋል። ደማቸውን ቀላቅለዋል። እና ቢጣሉም፤ ቢፋቀሩም የውስጥ ጉዳያቸው በመሆኑ የውጭው ህዝብ በአንድ ዓይን ሊመለከታቸው ይገባ ነበር። አሁን ነገ ባልና ሚስቱ ታርቀው፤ ወደ ጥንቱ ፍቅራቸው ቢመለሱ የውጭው አቾፈቻፌ ሁሉ ምን ሊውተው ነው?!......የሚያሳዝን ነገር ነው። ስለ ህጻናቱ አስተዳደግና የወደፊት ህይወት የሚያስብ የለም። ሁሉም የባልና ሚስትን የስሜት ፈረስ እየተፈናጠጠ መጋለብ ብቻ! ምን ዓይነት ጉድ ነው?!......ሀይ! ሀይ! ብለን ማጋባት! እንደገና ደግሞ መፍሰስ.....ማግባትን ግዴታ አድርጎ መስበክ!.......እና ደግሞ መልሶ ማፋታት!.........ታዲያ የትክክለኛ ዕምነታችንና የስብዕናችን ነፀብራቅ የቱ ነው?!.......

«ኤልሚ......ለምን ዳኒን ይዘኸው አልመታህም?.....» አለችው፤ ሰብለ እየሮጠች ወጥታ፤ እግሮቹ ላይ ተጠምጥማ።

እጁን ከኪሱ አውጥቶ ሰብለን እንደ ልማዱ ወደ ላይ ከፍ አድርጎ አቅፎ፤ «ዳኒ.....ይመጣል።» አላት ለማረጋጋት ያህል።

«መቼ?....አሁን»

«አዎ!......አሁን»

ፅጌረዳ እንደ ወትሮዋ ኤርሚያስን በተዘበራረቀ ስሜት አስተናግዳ ወደ ቤት ውስጥ አስገባችው። ሳሎን ውስጥ ከሚገኘው ሶፋ ላይ ተራርቀው ተቀመጡ። ግልፅ

ባልሆነ ምክንያት ወይም በተራ ጥርጣሬ ለኤርሚያስ የነበራት የእህትነት ፍቅር ቢቀንስም ሙሉ በሙሉ አልጠላችውም። የቤተሰቡ አንድነት እንዲጠበቅ የሚያደርገው ጥረት ትክክለኛነት ይሰማታል፤ በመሠረቱ የወንዳፍራሽ ጓደኛ በመሆኑ ደግሞ በተፈፀመባት በደል ውስጥ ተባባሪ አድርጋ ትጠረጥረዋለች። ከዚህም ሌላ ማንኛውም ሰው ከንፈሩን እየመጠጠ ብሶቱን የሚካፈልለትን ይመርጣል። ኤርሚያስ ግን ብሶት ማባባስ አይወድም - ይልቁንም የሚበጀውን ነገር በመነጋገሩ ላይ ያተኩራል። ይህም ፅጌረዳን ያስከፋታል። በጠቅላላው በኤርሚያስ ላይ ያላት ስሜት የተዘበራረቀ እየሆነ መጥቷል።

«እነ አባባ የሉም እንዴ?» በማለት ኤርሚያስ የክፍሉን ፀጥታ ሰበረው። ለጥቂት ሴኮንዶች ያህል በዝምታ ተፋጠው ተቀምጠው ነበር።

«ቤተ ክርስቲያን ሄደዋል።....አሁን እንኳ መምጫቸው እየተቃረበ ነው።» አለች ፅጌረዳ ሰአቷን ተመልክታ።

«ቤተ ክሲያን ሄደዋል።» አለች ሰብለም ተደርባ፤ ኤርሚያስ እግር ላይ እየተሻሸች።

«አባባ እንዴት ሆኑ?......ማለቴ፤ ያንቺን ነገር ሲሰሙ...» አላት ወደ መጣበት ጉዳይ መንደርደሪያ እንዲሆነው ድምፁን እያሰላ።

«ምን ይሆናል!?.....» አለች ፅጌረዳም በደረቀ ጉሮሮ።

«.....ማለቴ፤ በንዴት ብዛት ያማቸዋል ብዬ ፈርቼ ነበር።»

«ምንም አልሆነም። የባልና ሚስት መፋታት አዲስ ነገር አይደለም።»

ነገሩን ልታሳጥረው ፈልጋ ነው እንጂ አባቷ በንዴት ሲብከነከኑ ነው የሰነበቱት። ሰብለን ይዛ፣ ሻንጣዋን አስቀድማ ግቢያቸው የገባች እለት፣ በልኳንዳው መስኮት በርቀት የመለከቱ ስለ ነበር፤ ልባቸው ጠርጥሮ ቢላዎቻቸውን ወርውረው ተከተለዋት ወደ ቤት ገቡ። ውብ የሆነውን የፅጌረዳን ፊት በእንባ ጠቋቁሮ ሁለመናዋ በግድየለሽነት አያያዝ ተጎሳቁሎ ሲመለከቱት ነገሩ ገባቸው። በዚያ ሁኔታ ፅጌረዳን ማነጋገር ስለ ማይቻል እናትም አባትም እንዲሁ ውስጥ ውስጡን ሲያምጡ ውለው

ወደ ማታ ብስጭቱ በረድ ሲልላት ከእሷው አፍ ሰሙት። ወንዳፍራሽ ከውጭ ሌላ ሴት መወሽሙን ሲሰሙ ስለሚወዷት ልጃቸው ጥቃት ገባቸው። ጭራሹንም ውሽማው እንዳረገዘችለት ስትነግራቸው ተብከነከኑ። ጨሱ። በጥቁር ገፅታቸው ላይ የደምስሮቻቸው ሁሉ ተገታትረው በየሴኮንዱ እብጠታቸው እየጨመረ የሚሄድ ይመስሉ ነበር። ዓይኖቻቸው ደም ለበሱ። እና እንደልማዳቸው «ምንድ'ነው የምሰማው?!» እያሉ ተወራጩ። ምን ማድረግ ይቻልላ?! እንደ አምላክ ያወደሱትና ያምኑት የነበረው ወንዳፍራሽ እንዲህ ይሆናል ብለው በፍጹም አይገምቱም ነበር። - ግን ሆነ። በብስጭት ቢላዋቸውን እያፏጩ ከመቀመጥ ሌላ ምንም ማድረግ አልቻሉም። ብስጭታቸውን ጋብ የሚያደርላቸው በስራ መወጠሩ ብቻ ነው። እዚያው ልኳንዳቸው ውስጥ ውለው ማደሩን ሳይመርጡት አልቀሩም። - ነገር ሲከነክናቸው ቢላዎቻቸውን እያፏጩ!

«ለማንኛውም ጥሩ አላደረጋችሁ።» በማለት ኤርሚያስን ወደ አርእስተ - ጉዳዩ ስተት ብሎ ገባ።

«እንዴት?.....ማ?»

«ሁለታችሁም። አንቺም፤ ወንዳፍራሽም። የሁለታችሁም ዓይኖች ተጋርደዋል። ወንዳፍራሽን አዲስ ፍቅር ጋርዶታል። አንቺን ቅናት ጋርዶሻል። ሁለቱም ስሜታዊ ነው። እና፤ ይህ ስሜታዊ ግርዶሽ፤ በኋላ ያለፋችሁበትንና ወደ ፊት የምትሄድበትን መንገድ እንዳታዩ አድርጓቸኋል።.....ህይወት የምትጣፍጠው በኋላ በትዝታ፤ ከፊት በተስፋ እያጣጣሙ ሲኖሯት ነው። ዛሬን ብቻ መኖር ትርጉም አይሰጥም። ዛሬን ብቻ ማሰብና መኖር ጠባብና ስሜታዊ ነው።»

«ስለዚህ ጉዳይ ከሱው ከጓደኛህ ጋር ብትነጋገር ይሻላል። በኔ በኩል ጨርሻለሁ። እና ደግሞ የምወቀስበት ምንም ምክንያት የለም!»

ግንባሯን አኮማትራ ስትናገር የሴት ነብር መሰለች። በገፅታዋ ላይ ታላቅ ለውጥ ይታያል። - በብስጭት ውስጥ መብሰል ዓይነት ነገር! ይሁን እንጂ ኤርሚያስም በቁጣዋ የሚበር አልሆነም። አስቦበት ታጥቆ ነው የመጣው። ብስጭቱም ቢሆን ከባልና ሚስቱ ይበልጥ በሱ ብሷል። የሚወዷቸው ልጆቻቸውን ጉዳይ ቸል ብለው፤ ለራሳቸው ብቻ በመቆም መፋታታቸው ክፉኛ አናድዶታል። ከባልና ሚስቱ ይልቅ

ለልጆቹ ተቆርቁሮ ነው ሽንጡን ይዞ የተነሳው! ለዚህ ደግሞ የራሱ የሆነ ምክንያት አለው።......

«ወንዳፍራሽንም አነጋግሬዋለሁ። ነገር ግን የሰጠኝ መልስ የተራ ብስጭትና እሮሮ ውጤት ነው። እንዲያውም ተራ ድንፍታ ነው ማለት ይሻለኛል። አንቺ በፍላጎትሽ እንዳወጣሽ እንጂ እሱ ምንም እንዳልበደለሽ አድርጎ ነው ያቀረበው። በዕልህ የተወጣጠረው ስሜቱ ድክመቱን አምኖ ሊቀበልለት አልቻለም። እና፤ ይህን ጉዳይ እንዳነሳበትም ባለ መፈለጉ የተቀመጥኩበት ጥሎኝ ሄደ። ሁለታችሁም ምን ዓይነት እብደት ውስጥ እንደሆናችሁ አይገባኝም።.....»

«እኔን ምን አድርጊ ነው የምትለኝ ኤርሚያስ?»

«የለም.......ምን መስለሽ ፅጌረዳ.....እኔ አንቺን የማይበት ዓይኔ ለየት ያለ ነበር። ከብዙ ሴቶች የተለየሽ አድርጌ ስወድሽ ቆይቻለሁ። ውብ መልክሽ ወደ ሴታዊ እብደት አለምራሽም። በደፈናው መልክሽ ፀባይሽን አላበላሸውም ማለቴ ነው። በዚህም ምክንያት «ሔዋን 1999» ውስጥ ከቀረፅኩት ባህሪ ከፊሉ ያንቺ ነበር።.......»

ፅጌረዳ ግር አላት። የሚያወራው ነገር እንግዳ ስለ ሆነባት ግንባሯን በጥያቄ መልክ አጨማደደችው። ኤርሚያስም ግርታዋ ምን ላይ እንደሆነ አላውጣም -

«አዎ፤ ‹ሔዋን 1999› ገና ተስላ ያላለቀች አዲሷ የፈጠራ ስራዬ ናት። ያረጀና ያፈጀ ጎታች ባህል በሴቶች ላይ የጣለውን እንከን ለቅማ የምትጥል፤ ያልበሰለ ስልጣኔ በሴቶች ላይ የሚጥለውን ብልጭልጭ ካባ የምትገፍፍ፤ በሞዴልነት ነጥራ የምትወጣ አዲስ የሴት ምስል ናት።....እና እዚያ ውስጥ ያንቺም ባህሪይ ይገኝበታል። አሁን ስመለከትሽ ግን አንድ ነገር ገባኝ። አዎ፤ ውበት ታማኝነትና ትህትና ብቻ ለአንዲት ሴት በቂ አይደሉም። ከዚህ ሁሉ በላይ የአዕምሮ ጥንካሬ ያስፈልጋል። - ልበ ሙሉነት ያስፈልጋል። ከጥፋት መሸሽ ብቻ ሳይሆን አጥፊንም ማረቅ፤ ችግርን መሸሽ ብቻ ሳይሆን ተቀብሎ መመከትም ያስፈልጋል። አንዱ የጥንካሬ መለኪያችን ይሄ ነው።

«አሁን ምን አድርጊ እንደምትለኝ አይገባኝም።»

«......ቆይኝ እንጂ ፅጌረዳ አንድ ጥያቄ ልጠይቅሽ። ከወንዳፍራሽ ጋር አብረሽ ደክመሽ የሰራሽውን ቤት ጥለሽ መውጣትሽ ትክክልክ ነው? ሴት ልጅ ስትናደድ በቤቷ ጥላ ወጥታ ወላጆቿ ላይ ማኩረፍ ያረጀ ያፈጀ ባህል አይመስልሽም?......»

«አይ ኤርሚያስ! ‹ያልተነካ ግልግል ያውቃል›......»

«እንደሱ አይደለም። ሌላ ጥያቄ ደግሞ ልጠይቅሽ። በእናንተ የግል ጉዳይ ምክያት ምንም በማያውቁት ልጆች የወደፊት ህይወት ላይ መፍረድስ ትክክል ነው!......»

እዚህ ላይ ፅጌረዳ ብልጭ! አለባት። የኤርሚያስን ጥያቄ ትንሿ ሰብለ በትክክል አጢናው ጭንቅላቷ ውስጥ የምትመርገው መሰላት። ከውስጧ በመነጨው ግጭት ፊቷን ኩምትርትር አድርጋ ወደ ሰብለ ስትመለከት፤ ቂም አርግዛ የምታድግ አደገኛ ልጅ ሆና ታየቻት። ለኤርሚያስ መልስ መስጠቷን ትታ ልጇ ላይ ትክ እንዳለች ቀረች።

ሰብለ ነገሩ ሁሉ ግራ ገብቷት አንዴ ወደ ኤርሚያስ አንዴ ወደ እናቷ ዓይኑቿን ስታቁለጨለጭ ነበር የቆየችው። ኤርሚያስና ፅጌረዳ የሚነጋገሩበትን ጉዳይ የባልና የሚስት መጣላት መሆኑን በደመ ነፍስም ቢሆን ገብቷታል። ይሁን እንጂ ይህ ፀብ ወደ ፊት በእሷና በዳኒ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ችግር ለመገንዘብ ዕድሜዋ አልፈቀደላትም። የእናቷና የኤርሚያስን የብሶት ፊት በማየት ብቻ አብራ ስትተክዝ ቆይታለች።

«.....እንዲህ ዓይነት ጥያቄ አልፈልግም። እኔ ለልጆቼ ፍቅር አጥቼ አንደለም። - ትዕግሥቴ አልቆ ነው!» አለችው ፅጌረዳ፤ ኤርሚያስ ፍጥጥ ብሎ መልሷን መጠባበቁ አናድዷት።

«የለም። እኔ አሁን የምናገረው ስለ ወንዳፍራሽ ጥፋት ወይም ስለ አንቺ ትዕግሥት ሳይሆን ስለ ልጆቹ መብት ነው!»

አነጋገሩ ክርር ያለ ሆነባት። ዱሮ የምታውቀው ኤርሚያስ ሳይሆን ለህጻናት እንግዳ ፍጡር መሰላት።

«ታዲያ ምን ልሁን ኤርሚያስ?!.......የወንዳፍራሽን ዲቃላ እያሳደግሽ ተቀመጪ ነው የምትለኝ?!......»

ድምጿ በሐዘን ቅላፄ ያዘ። ሆዷ እንደገና መንቦጫቦጩን ቀጠለ። በኤርሚያስ ጥያቄ ስለ ተነካች ‹እውነት እኔ ለልጆቼ ጨካኝ ሆኘ ነው ትዳሬን ያፈረስኩት?› የሚል ጥያቄ ራሷን እየጠየቀች ተጨነቀች። ጭንቀቷን የሚያሳየው ፊቷ የኤርሚያስንም ንዴት አረገበው።

«አዎ፤ ምናለበት?!......ለልጆችሽ ስትይ ይህችን ታህል መስዋዕትነት ብትከፍይ ምናለበት። ቅድም ያልኩሽ እኮ ይሄንኑ ነው። ወንዳፍራሽ ጥፋት ፈጽሟል። አንቺ ደግሞ በጥፋቱ ላይ ቆመሽ ሌላ ጥፋት ከምትፈጽሚ በትንሽ መስዋዕትነት የጠቅላላውን ጥፋት ደብዛ ማጥፋት ትችያለች። ጥንካሬን የሚያሳየውም ይሔ ነው። ትዕግሥትሽ ለወደፊቱ የፍቅር እግር ብረት ሆኖ ወንዳፍራሽን ያስረዋል እንጂ፤ አንቺ እንደገመትሽው አያሸሸውም ወይም አያኮራውም። አሁን በብስጭት የሚያሳየውን ድንፋታ ልጥ አንቺ የምታውቂው ነው።....እና፤ ብዙ ደካሞች ያለፉበት መንገድ ከመከተል፤ ለጥቂት ጠንካሮች አርአያ ብንሆን ይሻላል። ዕልህ፤ ራስንም ሌላውንም ያጠፋል እንጂ እርባና የለውም።»

«ተው እንጂ ኤርሚያስ.......»

«ማለቴ የዲቃላው ነገር ግምት ነው እንጂ ገና በውል አልታወቀም።»

«ታውቋል እንጂ! እኔ የማምናት ጓደኛዬ ናት አረጋግጣ የነገረችኝ።»

«እኔ ደግሞ ወንዳፍራሽን ጠይቄው አስተባብሎኛል።»

«.......ታዲያ ቅሌቱን ሊያምንልህ ኖሮአል እንዴ!?»

«እሱ እውነትም ይሁን ውሸት እንደርስበታለን። ተደብቆ የሚቀር ነገር የለም። ......»

በር ሲንኳኳ ሰምተው ሁለቱም ጆሮዎቻቸውን ወደ ውጭ ጣሉ። ሠራተኛዋ ወጥታ በሩን ስትከፍት ፅጌረዳ የአባቷን ጎርናና ድምፅ ሰማች።

«እነ አባባ ከቤተ ክርስቲያን ተመልሰው ነው።» አለችው የኤርሚያስ ጉጉት አጢና።

«አባባ መቱ!.....እማማ መቱ!......አባባ እማማ.....» እያለች ሰብለ የሳሎኑ በር ከፍታ እየሮጠች ወጣች።

አያቶቹ ግራና ቀኝ እጇን ይዘው ወደ ቤት ሲያመሩ፤ ሰብለ በኮልታፋ ምላሱ የኤርሚያስን መምጣት ካበሰረቻቸው በኋላ በጥያቄ ማፋጠፏን ቀጠለች -

«አባባ፤ ዛሬ ወደ ቤታችን እንሄዳለን አይደል?»

«የእኛን ቤት ጠላሽው እንዴ?» አሉ ወንድ አያትየው የሚመሉስላት ጠፍቷቸው።

«እወደዋለሁ።»

«ታዲያ ለምን ትሄጃለሽ?»

«ዳኒ ወንደኢ እልፍነሽ ናፈኩኝ። ደሞ ዛሬ እሁድ አይደል?!.....ከወንዴ ጋል ሽልሽል እንሄዳለን።

«እሺ.....ትሄዳላችሁ።»

ወደ ሳሎን ሲገቡ ኤርሚያስና ፅጌረዳ ብድግ ብለው ተቀበሏቸው። የፅጌረዳ አባት ለኤርሚያስ ያልቸው አመለካከት ጤነኛ አይመስልም። ግንባራቸውን ሳይፈቱ ጨብጠውት ተቀመጡ።

«ዛሬስ ቤተክስቲያን ብዙ ቆያችሁ።.....» አለች ፅጌረዳ አባቷን እየተመለከተች።

«አዎ፤ የሊቀ ካናቱን ሰበካ ስንሰማ ቆየን። ቅዳሴ ከወጡ እንኳ ቆይተዋል።» በማለት እናቷ መለሱ።

አባትየው ምንም መናገር አልፈለጉም። የወንዳፍራሽን ጓደኛ በማየታቸው ደማቸው የፈላ ይመስል ስሮቻቸው ቀስ በቀስ ይግተረተሩ ጀመር። ኤርሚያስ ቢሆን ቆቅ ነው። የቁጣቸው መንስኤ እሱ መሆኑን ትከሻው ነግሮታል። - የልቤን ባያውቁ ነው፤ አልፈርድባቸውም፤ አለ በሆዱ።

ሠራተኛዋ እንደየዕድሜያቸው ቅደም ተከተል እጃቸውን አስታጥባ ቁርስ አቀረበች።

እህል ላይ ንግግር የተከለከለ ይመስል ሁሉም ተፈራርተው ዝም አሉ። እናትየዋ ኤርሚያስን መኖር ልባቸው ወዶታል። - ልጃቸውን ከባሏ ለማስታረቅ እንደ መጣ ጠርጥረዋል። አባትየው ግን ኤርሚያስ የወንዳፍራሽ አማላጅ ሆን እንደመጣ አድርገው በመገመት እጃቸውን ላለመስጠት ነበር የተኮሳተሩት። ዝምታውም የዚህ የርስበርስ መፈራራት ውጤት ነው። መሐላቸው ሆና የፈለገችውን የምትናገረው ምንም የማታውቀው ሰብለ ብቻ ነበረች።

«ብላ እንጂ፤ ምን ትቆነጥራለህ?» አሉት የፅጌረዳ እናት ወደ ኤርሚያስ እያስተዋሉ።

«ይገኤአለሁ።» አላቸው ከገበታዋ ላለመለየት ያህል ብቻ እየቆነጠረ። - ወስፋቱን የምግብ ፍላጎት አልነበረውም። ይልቁንም በቤት ውስጥ የሰፈነው ፀጥታ በሀሳብ ጭልጥ አድርጎ ወስዶ ስለ ትዳር ፍቺ ጉዳይ ያመራምረው ነበር። -

ይገርማል እኮ! በስሜት እሳት ቀልጦ እፍፍፍፍ! ብሎ መጋባት!.....ያንን ልጅ ካላገባሁት እታነቃለሁ ብሎ መዛት!...... ያቺን ልጅ ካላገባኋት እገላታለሁ ብሎ መደንፋት!.......እና ተዋክቦ መጋባት!........ያ በወረት ያንገበገበን የስሜት የስሜት እሳት ሲበርድ ደግሞ በንዴት እሳት እፍፍፍፍ ብሎ ጨሶ መፋታት!.......አይኗን ላፈር!......አይኑን ላፈር!......የትዝታን ረመጥ እየሞቀ ወይም የወደፊትን ብሩህ ተስፋ እየተመለከተ መኖር የሚፈልግ ጥቂት ነው። አብዛኛው ለቅፅበታዊው የስሜት እሳቱ ተገዥ ነው።.....ታዲያ እንዲህ ለስሜት እሳት ብቻ ተገዥ ከሆንን ማህበራዊ ሀላፊነታችንን የምንወጣው እንዴት ነው?!.......የማህበራዊ ዋስትና ተጠቃሚ ሆነን ለሌሎች ማህበራዊ ዋስትና የምንሰጠው መቼ ነው?! ትዳር!........ፍቺ!......ትዳር!........ፍቺ!........

የፅጌረዳ እናት ሰብለን አቅፈው ሲያጎርሷት አባትየው ደግሞ ፅጌረዳን ራሷን ማጉረስ ጀመሩ። የአባትየው ጉርሻ ነገር አዘል በመሆኑ የኤርሚያስን ዓይንም ሀሳብም ጠለፈው። ለልጃቸው ለፅጌረዳ ያላቸውን ፍቅር በባሏ ጓደኛ ፊት የማሳየት የዕልህ

እንቅስቃሴ ይታይባቸው ነበር። የኤርሚያስ ግምት ትክክል ሆነ። አባትየው ከጉርሻቸው ጋር የሆነ ነገር ወርወር አደረጉ -

«እኔ አባትሽ፤ ክንዴን ሳልንተራስ፤ ላንቺ መሆን አያቅተኝም።.....በህይወቴ እስካለሁ ድረስ ጥቃትሽን ማየት አልፈልግም!.....»

ኤርሚያስ በሆዱ ሳቀ። - አጉል ግብዝነት መቼ ይሆን የሚለቀን?!.....የፅጌረዳስ ወደ ልጅነት መመለስ ምን ይባላል።

የበሉትን ያህል በልተው ገበታው ተነሳ። ሻይ ቀረበ ፡ አባትየው እጃቸውን እስኪታጠቡ መቆየት እንኳ አላስቻላቸውም። ኤርሚያስን የጎድን እያዩት፤ አምቀው የቆዩትን ነገር ተነፈሱ -

«ጓደኛህ እንዲህ ያርገን?!.....ፅጌረዳ እኮ ለእሱ እመቤቱ እንጂ ሚስቱ አትሆንም ነበር!......»

ኤርሚያስ በሸቀ። የወንዳፍራሽ ሚዜና ጓደኛ በመሆኑ ብቻ ለምን የጥፋቱ ተባባሪ አድርገው እንደሚወስዱት ሊገባው አልቻለም። - መናገር ፈለገ። ነገር ግን የፅጌረዳ አባት ፋታ አልሰጡትም።

«ደግሞ እንዲሁ አንላቀቃትም!.....በህግ ፊት እንፋረዳታለን!.....ልጄ ከነልጆቿ በህግ ፊት ትጠይቀዋለች!......»

ኤርሚያስ ስሜቱን አምቆ መቆየት አልቻለም።ድ ንገት ግልፍ አለውና «እሱ እንኳን ዋጋ የለውም። - መጓተት ነው ትርፉ!.....ነገር ማራዘም ነው ወጤቱ!.....በቤተሰብ ማስታረቁ የሚሻል ይመስለኛል። ፀባቸው ህግ ፊት የሚያደርስ አይነት አይደለም።» አላቸው።

«እንዴት እባክህ?!......በላይዋ ላይ ወሸሞ ዲቃላ ከመውለድ ሌላ ምን እንዲያደርጋት ትፈልጋለህ?!.....ከዚህ ወዲያ ጥቃት ምን አለ?!......ጓደኛህ መርሆኑን አውቃለሁ።»

የአባቷ ተቆርቋሪነት ብሶቷን እንደ ቀሰቀሰባት ሁሉ ፅጌረዳም ዓይኖቿን ኤርሚያስ ላይ አፍጥጣ ጥርሶቿን አንቀጫቀጨች።

ኤርሚያስ እዚህ ቤት ውስጥ በአባቷ ፊት ነጻ ውይይት ማካሄድ እንደ ማይቻል ተረዳ። ሻዩን ቶሎ ቶሎ ጠጥቶ ከጨረሰ በኋላ «ለማንኛውም በእኔ በኩ አንድ ነገር እንዲረዱልኝ እፈልጋለሁ። ለወንዳፍራሽ ብቻ የነበረኝ ጓደኝነት የሥርጉ ዕለት አከትሟል። አሁን ጓደኝነቴ ለቤተሰቡ በሙሉ ነው። የፀቡን ነገር በሚያመለክት የባልና ሚስቱ የግል ጉዳይ ይሆናል። እኔ ግን በማያውቁት ምክንያት የጉዳቱ ተካፋይ ለሚሆኑት ለሁለቱ ህጻናት ስል ጉዳዩ ውስጥ እጄን አስገባለሁ። ጥብቅና የምቆመው ለሁለቱ ልጆች ነው!....» አለና ለመሔድ ተነሳ።

«የሁለቱ ህፃናት ከፅጌረዳ በኋላ የተገኙ ፍጥረቶች ናቸው።......ደሞም፤ አፈር ሳይጫነኝ የልጅ ልጆቼን ማሳደግ አይሳነኝም!.......» እያሉ አባትየው አብረውት ተነሱ። ብስጭቱ ገፋፍቶ አስነሳቸው እንጂ የሚሄዱበት አልነበራቸውም። ወይም ኤርሚያስን ማባረር አስበው አይደለም።

«ኧረ ቁጭ በልና ተጫወት ልጄ። በጎ በጎውን እንዳናወራ....እንዲያው በነገር ያዝንህ እኮ!......» አሉት የፅጌረዳ እናት ጨንቋቸው። ባላቸውን ፈርተው ነው እንጂ ኤርሚያስን በልባቸው ደግፈውታል። ዛሬ አካኪ ዘራፍ! የሚሉት ባላቸው ዱሮ በእሳቸው ላይ የፈፀሙትን ነገር ስለሚያውቁና ሁሉንም ችለው ስላሳለፉ፤ ፅጌረዳ ከባሏ ታርቃ ወደ ቤቷ ብትመለስ ፈቃዳቸው ነው።....

«የለም፤ አልቆይም። አሁን ጉዳይ አለኝ.....ሌላ ቀን እመጣለሁ» እያለ ወደ በሩ አመራ።

«ኤልሚ.....ከአንተ ጋር እሄዳለሁ።»እያለች ስብለ ተከትላው ሱሪውን ያዘች።

«ሽርሽር ነው?.....ዛሬ መኪና የለማ።»

«እሺ በቃ ቤታችን ውሰደኝ.....»

«እናትሽን ጥለሽ?.........»

«እሷም ትሄዳለች።.......ዳኒ ናፍቆናል። ወንዴ ሽልሽል ይዞን ይሄዳል።

«እሺ የኔ ቆንጆ። በኋላ መኪና አምጥቼ እወስድሻለሁ።.......»

«እንዳትቀር!........እሺ? ኤልሚ.......»

«አልቀርም ሰብልዬ፤........» ብሎ ግንባሯን ስሞ ተለያት።

ጉሮሮው ላይ የሚታገለው መጥፎ ስሜት ወደ ውስጥ እየዋጠ፤ የውጭውን በር ሲወጣ፤ አዲሱ ህገ መንግሥት ላይ ስለ ልጆች መብት የሚጠቅሰውን ድንጋጌ በአዕምሮው እያሰላሰለ ነበር።

ሮዛ ከውጭ ገብታ የሌሊት ልብሷን ለብሳ ቴፕሪኮርደሩን እያዘፈነች አልጋዋ ላይ ጋደም እንዳለች፤ የውጭውን በር የደወል ድምፅ ተሰማት። ከምሽቱ አራት ሰዓት ሆኖአል። ቤተሰቡም በሙሉ ተሰብስቧል። ሮዛን የሚፈልግ ሰው ከሆነ የመኪናውን ክላክስ ይነፋል እንጂ በር አያንኳካኡም - ለዚያውም ቀጠሮ ካላት ነው። ከወንዳፍራሽ ጋር አብረው አምሽተው ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት በር ላይ አድርሷት ተመልሷል። ሌላ ቀጠሮ የላትም። ቤተሰቦቿ ጋ የመጣ እንግዳ መስሏት ቸል ብላው ሙዚቃውን ማዳመጧን ቀጠለች።

«ሮዛ.......አንቺን የሚፈልግ ሰው ነው።» አሉ ሽማግሌው ዘበኛ ከውጭ ገብተው የመኝታ ክፍሏን በር እያንኳኩ። ዘበኛው ብዙ ዓመታት አብረው ከመኖራቸው የተነሳ እንደ ቤተሰብ ነው የሚታዩት።

«ማ - ማነው?» አለች ከአልጋዋ ተስፈንጥራ ወርዳ የመኝታ ክፍሏን በር እየከፈተች።

«እንጃ....እንግዳ ሰው ነው። በሩን ስከፍትለት አንቺን እንደሚፈልግ ነገረኝ።»

«ታዲያ አያስገቡትም ነበር እንዴ?»

«እምቢ አለኝ።»

በለሊት ቀሚስዋ ላይ ጋቢ ደርባ ስትወጣ ምክንያቱ ግልፅ ባልሆነላት ድንጋጤ፤ ልቧ ከበሮውን ይደልቅ ጀመር። የጭለማ መርዶ ነጋሪ በር ላይ የተገተረ መሰላት። ምንም ጥሩ ነገር ሊታያት አልቻለም። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት የተለያት ወንዳፍራሽ በሀሳቧ መጣበት። - ምን ሆኖ ይሆን?....ምን ሆኖ ይሆን?......ምን ሆኖ ይሆን?......አዕምሮዋ ይህን እየጠየቀ፤ የመወርወር ያህል እየተራመደች ከውጭው በር ደረሰች። የግቢውም የውጭውምመብራት ፏ ብሎ ስለ በራ ሁሉ ነገር ግልፅ ሆኖ

ይታያል። በተጨማሪ ጨረቃም ትብብሯን አልነፈገችም። ዘበኛው የሮዛ ሁናቴ ስላላማራቸው ከኋላዋ ተከትለዋት ወጥተው በሩ አካባቢ ሲደርሱ ሚስጥር እንዳይሰሙ ለመጠንቀቅ ያህል፤ ራቅ ብለው ቆሙ።

ሰውየው ከበሩ አጠገብ የሚገኘው የስልክ እንጨት ተደግፎ የሮዛን መውጣት በመጠባበቅ ዓይነት ወደ ውስጥ እየተመለከተ ቆሟል። ሬኖልት 16 መኪናውን በማዶ ጥግ አቁሟታል። ሮዛን ቀርቦ በመልክ ባያውቃትም፤ ጋቢ ለብሳ የወጣችው ሴት እሷ መሆኗን በመገመት ከቆመበት ተነቃነቀ።

«ጤና ይስጥልኝ......» አለችው ፈራ - ተባ በሚል ድምፅ።

«ጤና ይስጥልኝ። ሮዛ - ነሽ?»

«አዎ፤ ማ - ማን ልበል?......»

ድንጋጤዋ እየጨመረ ሄደ። የማታውቀው ሰው በጭለማ የሚመጣበት ምንም ጥሩ ነገር አይኖርም!....ልቧ የጠረጠረውን ክፉ ነገር ወይም አደጋ ጆሮዋ እንዳይሰማ ትመክትበት ይመስል የግንባሯን ቆዳ ኩምትር አደረገችው።

«ከእኔ ጋር እንኳ አንተዋወቅም።......» አለ ሰውዬው በእንግዳ ድምፅ፤ «ወንዳፍራሽ.....»

የመጣበትን ጉዳይ እንዴት እንደሚናገር ግራ ገብቶት የወንዳፍራሽን ስም ጠርቶ አቋረጠ። ይህ ሁኔታ የሮዛ ጥርጣሬ አጉልቶ አሳሰባት።

«እ?......ምን ሆነ? ተ - ተ - ተገለበጠ?» አለች፤ አጠገቧ ያለን ሳይሆን፤ የሩቅ ሰው እንደምትጠይቅ ዓይነት በድንጋጤ ድምጿን አጉልታ።

እና በኋሳቧ ጥርጣሬዋ እውን ሆኖ ታያት። ከስልክ እጨት ከግንብ ወይም ከተመሳሳይ መኪና ጋር የተደረገ ቀላል ግጭት ሳይሆን፤ ድልድይ ውስጥ ተገልብጦ የገባ መኪና ከባድ አደጋ ነው የታያት። ብጫ ጊያ 124 ጭምትምቷ ወጥቶ መስታወቷ ደቅቆ፤......የወንዳፍራሽን አጥንት ለመልቀም እንኳ እስኪያስቸር ድረስ ድልድይ ስር ተበታትኖ፤......ዓላፊ አግዳሚው በዚያ በጭለማ ድልድይ ላይ ቆሞ የተጨረማመተ

መኪና የተበታተነ አጥንትና ከውሃው ጋር የተደባለቀ ደም ቁልቁል በኤሌክትሪክ ብርሃኑ እየተመለከተ ከፍንፈሩን እየመጠጠ ስለ ወንዳፍራሽ አሟሟት ሲንኮካሾክ -

ውይ አፈር በሆንኩት! ምን ነክቶት ይሆን?....

ሰክሮ የሆናላ! አይ አልኮል የሚሰራው ስራ!

ሰክሮ አይመለኝም.....ብስጭት ነው። ፍቅረኛው አበሳጭታው ይሆናል። አሁን እኮ ነው በዚህ አልፎ አድርሷት የተመለሰው!

አዎ፤ ብዙ ጊዜ ማታ ማታ በዚህ መንገድ የሚያደርሳት ፍቅረኛ አለችው......እሱን ለሞት ዳርጋ እሷ ይሄኔ የሞቀ እንቅልፍዋን ትለጥጣለች።

አይ ሴት!.......

«ን....ገረኝ እንጂ!.....ወንዴ ምን ሆነ?» አለች ሮዛ በሀሳቧ ያየችው ሰቀቀን እውነት ይሁን ውሸት ሰውየው እንዲያረጋግጥላት ቸኩላ። - ድንጋጤዋና ከችኮላዋ የተነሳ እንግዳውን ሰውዬ የምትመለከተውና የምትጠይቀው ረዥም ጊዜ እንደምታውቀው ዓይነት አፍጥጣበት ነበር። ሰውዬው ደግሞ በበኩሉ በሁኔታዋ ተገርሞ፤ የመጣበትን ጉዳይ በመናገር ፈንታ ክት ብሎ እንደ ልዩ ፍጥረት ይመለከታታል።

በዚያች አጭር ቅፅበት ውስጥ ሮዛ ብዙ ነገሮች አሰበች። ወንዳፍራሽ፤ ከሚስቱ ተጣልቶ ቤቱን ለቅቃለት ከወጣችበት ጊዘ ጀምሮ፤ እያሳየ የመጣው የባሕሪ ለውጥ አንድ በአንድ በአዕምሮዋ ውስጥ ተመላለሰ። በጣም መጠጣት ጀመሯል። ሮዛ አጠጣጡ አንገፍግፏት «ተው እንጂ ወንዴ! - ራስህን አትግደል!» ብላ ብርጭቆውን ከአፉ አስክትነጥቀው ድረስ ይጠጣል። መኪና ሲነዳም በጣም ይበርራል። ውስጥ ውስጡን የሚያቃጥለውን ነገር ለመሸሽ የህሊና ጥያቄውን ለማምለጥ የተጋጨ ሰውነቱን ለማዘናጋት ከፉኛ ይበርራል። እንቅስቃሴው ሁሉ በጣም ፈጣን ሆኖ ብድን ነው። - ራስንም አካባቢንም ለመርሳት የሚያደርግ በድን ፍጥነት!.......በዚያ ላይ ደግሞ የነገሩትን ይረሳል፤ ሲነግሩትም ይፈዝዛል። ፅጌረዳ ከቤት ከውጣች ጀምሮ ከሮዛ ጋር በቀን አንድ ጊዜ ሳይገናኙ አድረው አያውቁም። ብቸኝነቱን ለመሸሽ የሮዛን ፍቅር ፈልጎ ይሄዳል፤ ከሮዛ ጋር ሲሆን ደግሞ አዕምሮው ውስጥ የሚያቃጭለውን፤ የልጁን፤

የዳኒን ድምፅ ወይም የፅጌረዳን እሮሮ ላለመስማት ራሱን እስኪስት ድረስ ይጠጣል። በጠጣው መጠጥ ግፊት በድን ፍጥነቱ ይጨምራል።

ሁኔታው ሮዛን ከዕለት ወደ ዕለት እያሳሰባት መጣ። ወንዳፍራሽ ከሚስቱ ጋር መፋታቱ ፍቅሩን በሞኖፖል ይዞ፤ የግሏ ብቻ ለማድረግ የሚረአት መስሏት መጀመሪያ ፈንጥዛ ነበር። ለሁለት የተከፈለ ፍቅሩን ለብቻዋ ይዛ ውስጣዊ ሰላም የምታገኝበት ጊዜ ስታልም ነው የቆየችው። ፅጌረዳ ቤቱን ለቅቃ ትንሿን ልጇን ይዛ መውጣቷን ከወንዳፍራሽ አፍ ስትሰማ መጀመሪያ አላመነችም ነበር። በሌላ በኩል አጠያይቃ ካረጋገጠች በኋላ እንኳ ህልሟ ዕውን መሆን አልዋጥልሽ ብሏት ደግሞ ደጋግማ እሱኑ ትጠይቀው ነበር። ይሁን እንጂ የፅጌረዳ ከቤት መውጣት እሱኑ ትጠይቀው ነበር። ይሁን እንጂ የፅጌረዳ ከቤት መውጣት ሮዛ የጠበቀችውን ውስጣዊ ሰላም መስጠቱ ቀርቶ ሌላ ስጋትና ሀሳብ ውስጥ ይጨምራት ጀመር። ፅጌረዳ የለቀቀችውን ቤት ሰተት ብላ ልትገባበት ቀርቶ አንድ ሌት እንኳ ሄዳ አላደረችበትም። የወንዳፍራሽ ውስጣዊ ሰላም ማጣት እሷንም ሰላም ነሳት።

ወንዳፍራሽ ውስጣዊ ሰላም የነሳው በፅጌረዳ ላይ የፈፀመው በደል አልነበረም። በድርጊቷ ዕልህ ውስጥ ስለ ገባ በዳይነቱን ዕልሁ እየሸፈነለት ጥርሱን ሲያንቀጫቅጭ ከርሟል። እሱን ክፉኛ የረበሸው እቤት በገባ ቁጥር የዳኒን የሚያሳዝን ፊት ማየትና የሚያሳዝን ንግግር መስማቱ ነው። የዳኒ ንግግር ከህሳን አፍ የወጣ ነው ተብሎ አይናቅም፤ ወይም ደቅሞ እንደ አዋቂ ሆኖ አይመርርም፤ ዕልህ ውስጥ አይጨምርም። የዳኒ ንግግር በምናምን የተሸፈነ ህሊናን አስገልጦ ያስጠይቃል። የበስለ ንግግር ከልጅ አፍ መውጣቱና ባገጠጠ እኔነት ላይ መሰንዘሩ ለጊዜው ቢያስቆጣም፤ እየቆየ ጭንቅላት መቆርቆሩ እረፍት መንሳቱ አይቀርም። ዳኒ ከእናቱ በመነጠሉና ከእናቱ እንዳይገናኝ በመከልከሉ በግልፅና በተዘዋዋሪ በኩርፊያ ወይም በንግግር የሚገልፀው ብሶት የወንዳፍራሽን አዕምሮ ሰላም ነሳው። የልጅነት ምላሱ በጣፋጭ ነገር የሚደለል ያለ መሆኑ አናደደው። የዳኒን ሁናቴ ለሮዛ ሲያጫውታት «....እሳት ወልጄ እኔኑ መልሶ ያቃጥለኝ ጀመር።» እያለ ነው። ሮዛም የዳኒን ሁኔታ በመስማቷ ቀድሞ ያለመችውን የወንዳፍራሽ ቤት ልትገባ ቀርቶ በበሩ ማለፍ አስጠላት።

የወንዳፍራሽንና የሮዛን ፍቅር ሰላም የነሳው ሌላው ነገር ደግሞ የከተማው ወሬ ነው። ወንዳፍራሽን በሚመለከት፤ «......የሁለት ልጆች እናቱን ያቺን ቅድስት ሚስቱን ፈትቶ ከዚች ቀውላላ ጋር መንቀዋለሉን እስቲ ምን ይባላል?! አይ ሰው ከንቱ!......» ሲባል፤ ሮዛን በሚመለከት ደግሞ፤ «.......ይቺ ቅሌታም፤ ጨዋውን ሰውዬ ከሚስቱ አፋትታ ስትወሽመው ትንሽ እንኳ አታፍርም እንዴ!? ምን ይሉኝታ ቢስ ነች እባካችሁ!......» መባሉ እንደ ዋዛ ከጆሮዋቸው ይደርሳል። እንወደድ ባይ ወሬ አቀባዮች ሁለቱም አላጡም።

ይህ ሁሉ ሆኖ ግን የወንዳፍራሽና የሮዛ ፍቅር ሰላም አጣ እንጂ ቅንጣት ያህል አልቀነሰም። ይልቁንም የአካባቢው ሐሜት ማገዶ ሆኖ ለፍቅራቸው የነደደ ይመስል በዕልህ ስሜት ግንኙነታቸው እየጠበቀ ሄደ። ሲገናኙ በፍቅር ይከንፋሉ ሲለያዩ በነጋታው እንደ ማይገናኙ ሁሉ፤ በሀሳብ፣ በስጋት፣ በሰቀቀን ሲወራጩ ያድራሉ።......

«እ - እባክህ የሆነውን ንገረኝ!.....ለመሆኑ ህይወቱ ተርፏል?......» አለች ሮዛ ለሶስተኛ ጊዜ፤ የሰውየው ‹ጋግርትነት› ትዕግሥቷን አስጨርሷት እየተመናጨቀችና፣ ወንዳፍራሽ እሷን በርዋ ላይ አድርሷት መኪናውን በፍጥነት ሲጠመዘዝ ሲጢ ሲጢጥ! ያሉት ጎማዎች በረራ አሁንም አይኗ ላይ እየመጣ.......

«......ግን እንዴት ብትወጂው ነው?......» አላት ሰውዬው አኳኋኗን ገምግሞ ሲያበቃ፤ ረጋ ባለ ድምፅ፤ «እኔ እኳን መርሶዶ ይዤ አልመጣሁ።»

«ሰውዬው!......ቀልድ ነው እንዴ የመጣኸው!»

«ኧረ ለቁም ነገር ነው እመቤቴ!......»

ሮዛ የሰውየውን መረጋጋት ስትመለከት ድንጋጤዋ በረድ ብሎላት፤ ቁጣዋ ብቻ አይሎ፤ ወደ ቤቷ ለመመለስ ከትከሻአዋ ዘወር አለች።

«ቆይ እንጂ ሮዛ።.... የመጣሁበት ጉዳይ እንዴት እንደ ምጀምረው ግራ ገብቶኝ እኮ ነው።»

«ታዲያ ተናገራ......»

አንዴ የወንዳፍራሽ ስም ስለ ተጠራ የተያያዘውን ነገር ሳታውቅ ወደ ቤቷ ለመግባት የሷም ልብ አልደፈረም።

«አሁን በአጋጣሚ ነው የመጣሁት። ቀጠሮ ስጥተሽኝ ጉዳዩን በርብርሃን ቁጭ ብለን ብንነጋገርበት ደስ ይለኛል። በአንቺና በወንዳፍራሽ ግንኙነት ላይ መነጋገር እፈልጋለሁ።........»

«ለመሆኑ አንተ ማን ነህ.....በኛ ጉዳይ ላይ መነጋገር የምትፈልገው?» አለችው በከፊል ብቸቀታዊ ንቀት፤ በከፊል ደግሞ ማንነቱን የማወቅ ጉጉት አድሮባት ግንባሯን እንዳኮማተረች።....»

«ስሜን ብነግርሽ አታውቂኝም ብዬ ነው። ኤርሚያስ ዘለቀ እባላለሁ። ለወንዳፍራሽና ለፅጌረዳ ጓደኛም፣ ቤተሰብም ነኝ። እና፣ በንቀት - አ.......»

ጉዳዩን መጀመር ስላልፈለገ አመንትቶ አቋረጠ።

ሮዛ አጠገቧ የቆመው ሰው ኤርሚያስ መሆኑ ስትሰማ ጥላቻና ፍርሃት ተቀላቅለው ፊቷን አጨማደዱት። ጠላትነት ታያት። ሰሞኑን የአዕምሮ ሰላም ከነሱት ሰዎች አንዱ ኤርሚያስ መሆኑን ወንዳፍራሽ ራሱ ነግሯታል። አጥላልቶም ባይሆን ለትዳራቸው ተቆርቋሪ ሆኖ የህሊና እረፍት እንደ ነሳው አጫውቷታል። እሷ ግን ይህን ከሰማችበት ጊዜ ጀምሮ ኤርሚያስ የሚባለውን ሰውየ የጀርባ ጠላቷ አድርጋ ጠምዳዋለች። አሁንም ኩራቷን የሚቀንስ መስሎ ስለ ታያት በስም እንደምታውቀው እንኳ ልትነግረው አልፈለገችም።

«ለመሆኑ ቤቱን ማን አሳየህ?......በጭለማ!......» አለችው ጥላቻዋን በሚገልፅ አስተያየት እያየችው።

የአጠያየቋ መንፈስ ‹ለምን መጣኸብኝ!.....ሰላማዊ እንቅልፍ እንዳልተኛበት!› የማለት ያህል መሆኑን ኤርሚያስ አላጣውም። ሆኖም ምንም ዓይነት የቅያሜ ፊት ከማሳየት ተቆጥቦ፤ «ፈልጌ አስፈልጌ ነዋ!» አላት በርጋታ

«ታዲያ ምን ቀጠሮ ያስፈልጋል!? የመጣህበትን ጉዳይ አሁኑኑ ልትነግረው ትችላለህ።»

ሁኔታዋ እንዲናገር ገፋፋው። ለሊላ ቀን ቢቀጥራት የማትገኝለት፤ ፈልጓት ቢመጣ የምትሸሽግበት መሆኗን ከአኳኋኗ ገመተ። ሮዛን አኝቶ ለማነጋገር ሲያምጥ ከርሞ በዛሬው ምሽት ቤቷን ያገኘው ከወንዳፍራሽ ጋር ሲከንፉ በስውር ሲከታተላቸው ቆይቶ ነው። አንድ ቀን እንዲሁ አሳድጄ እይዛለሁ ብሎ ከሸፎበታል። ዛሬ ግን እሱነቱ እንዳይታወቅ ቮልስ ዋገን መኪናውን ቤቱ አስቀምጦ፤ ከጓደኛው ሬኖ 16 ተውሶ፤ ወንዳፍራሽ ከስራ ወጥቶ በሄደበት መንገድ በርቀት ተከትለው። ይሁን እንጂ ብርሃኑ ስለሚያጋልጠው ወንዳፍራሽ ሮዛን ለማማት በገባእት የውስጥ መንገድ ተከትሎት ሊገባ አልቻለም። መውጫያና መግቢያ መንገዶችን ማየት በሚችልበት ርቀት ቆሞ ጠበቀው። እንደ ገመተውም ሮዛን ይዞ እየከነፈ ወጣ። ተከተላቸው። ጨለምለም እስኪልለት ድረስ ከቀረባቸው እንዳያውቁት፤ ከራቃቸው እንዳይጠፉበት ሲጨነቅ ቆይቶ እንዳያውቁት፣ ካራቃቸው እንዳይጠፉበት ሲጨነቅ ቆይቶ ከጨለመ በኋላ ተረጋጋ። የተጨናነቀ ትራፊክ ስላለነበረ መኪናቸውን በርቀት ለይቶ ለማሳደድ አልተቸገረም። ይልቅ ትዕግሥቱን ያስጨረሰው አንዳንድ መዝናኛ ቦታ ገብተው እስኪወጡ ድረስ ተደብቆ መጠበቁ ነበር። ፍቅረኛው እንደተወሰደችበት አፍቃሪ ሌባና ፖሊስ መጫወቱ ራሱን ቢያስቀውም፤ የዳኒና የሰብለ ድምፅ በየደቂቃው አዕምሮው ውስጥ እያቃጨለ በድርጊቱ እንዲቀጥልበት ገፋፋው። በትዕግሥትና በዘዴ ተከታትሎ ወንዳፍራሽ ሮዛን በጭለማ ቤቷ በር ላይ ሲጥላት ከተመለከተ በኋላ፤ ቤቷን በማግኘቱ ብቻ ረክቶ እምመለስ አልቻለም። ያየውን ለማመን ወደ በሩ ተጠግቶ ሮዛን አስጠርቶ ቀጠሮ ለመውሰድ ፈለገ። ሲያምጥ በሰነበተበት ነገር ላይ ቀጠሮ ወስዶ ሲያምጥ ማደሩንም አልወደደውም። የሮዛን አኳኋን ሲያይ ደግሞ ጊዜ መስጠቱ የባሰ የብዛዋን እንደሚያጠፋው በመገመት፤ ጉዳዩን ወዲያውኑ ለመተፈስ ተገደደ -

«ነገሩ እንኳ አዲስ አይደለም።.....በ - አንቺና በወንዳፍራሽ መሐከል የተፈጠረው ግንኙነት በትዳሩ ላይ ትልቅ ችግር መፍጠሩን ሳትሰሚ አልቀረሽም.......» አላት ጉሮሮውን እየሳለ።

«የምን ችግር?!.....» አለች ነገሩን እንዳልሰማችው ላይሆን፤ ሰምታ እንደናቀችው በሚያሳይ የእልህኝነት ድምፅ።

«ሚስቱ.....ፅጌረዳ - ቤቷን ጥላ መውጣቷን ሳትሰሚ የቀረሽ አይመስለኝም። ......»

«እና?....በኔ በሮዛ ምክንያት ነው ቤቷን የለቀቀችው?!.....ይህን ልትነግረኝ ነው በጭለማ የመጣኸው? - ይህንማ ከተማው ሁሉ ብሎት - ብሎት የበቃው ነገር እኮ ነው።.......»

«እንደዚያ ሳይሆን......»

«ነው እንጂ! ሌላ ምን አዲስ ነገር ትነግረኛለህ?!.....ማወቅ የምትፈልገው እኔና የወንዳፍራሽን ፍቅር ከሆነ፤ አሁንም እወደዋለሁ። ይሄ ይህያውነት መብቴ ነው። ማንም ሊከለክለኝ አይችልም። በተረፈ ግን ስልክ ደውዬ ሚስቱ ቤቷን እንድትለቅልኝ አልጠየቅኳትም።.......» አለችው ሲቃ አፍኖት በሚንቀጠቀጥ ድምፅ።

«ያም ሆነ ይህ ለችግሩ ምክንያት መሆንሽ አልቀረም።.......» አላት ኤርሚያስ አሁንም በደረቀ ድምፅ።

ሮዛ አንዳች ነገር ከሰውነቷ ውስጥ ሲፈላ ተሰማት። ስለ ፅጌረዳ መጎዳት ሳይሆን፤ ስለ ራሷ በፍቅር መቃጠል ብቻ ነበር የምታስበው። ማፍቀሯ ለምን ወንጀል ሆኖ እንደሚታይባት ሊገባት አልቻለም። የእልህ እንባ ጉሮሮዋ ላይ ተናነቃት። ምንም ሳትናገር ከውስጥ የሚያስቸግር ስሜቷን ስትታገል ከቆየች በኋላ በረዥሙ ተነፈሰች።

«አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ?......»

«እሺ፤ ጠይቂኝ።»

«ፅጌረዳ፤.......»አለችው ስሟን ስትጠራ፤ በዝና ብቻ እንደምታውቃት ሴት ሳይሆን፤ አዕምሮዋ የሳለው ምናባዊ ምስል በዓይኖቿ ላይ እያለፈ፤ «.......ፅጌረዳ ፍቅርን በሚመለከት በወንዳፍራሽ ላይ ከእኔ የበለጠ ምን መብት አላት?......»

ጥያቄዋ ኤርሚያስን አስደነገጠው።......ፍቅር ጅል ያደርጋል የሚባለው እውነት ነው መሰለኝ። የሌላዋን ባል የማፍቀር መብት ደግሞ አለ እንዴ! እያለ ሲያስብ ጥያቄዋን በብሶት ድምፅደ ገመችለት -

«ንገረኝ እንጂ! ወንዳፍራሽን ሚስቱ ብቻ እንድታፈቅረው - እኔ እንዳላፈቅረው የሚያግድ ህግ አለ እንዴ?......»

አኳኋኗ ኤርሚያስን አሳዘነው። ወንዳፍራሽን ከልቧ እንደ ምታፈቅረው ገመተ። የጥቅም ግንኙነት ብቻ ቢሆን ኖሮ እንዲህ አያብከነክናትም ነበር ሲል አሰበ። ብስል ቀይ ፊቷ በንዴት ይበጥ እየቀላ ሲሄድ በጨረቃዋ ብርሃን እንኳ ለመለየት ይቻል ነበር። ወደ ሰማያዊ ቀለም የሚያደሉት የዓይኖቿ ብሌኖች በጭንቀት ስሜት ከወዲያ - ወዲህ ሲንከባለሉ ያሳናሉ። የድምጿም ስልት በትክክል የውስጥ ስሜቷን ይገልጻል።

«ችግሩ'ኮ ከአንቺ ጋር መፋቀሩ ጎጀው ውስጥ ተንፀባርቆ የትዳሩን ምሰሶ መነቅነቁ ነው።» አላት በሚያበብል አነጋገር። «በዚህ ላይ ደግሞ የማፍቀር መብትና ግዴታ በወረቀት ላይ ተደንግጎ ባይገኝም፤ በባህላችን መሠረት በሚስት ላይ ተደርቦ መውደድ ይወገዛል። ለሐሜት፣ ለዘለፋ፣ ለትችት፣ ይዳረጋል። ይህ እንግዲህ በጽሑፍ ያልሰፈረ በጋራ መግባባት ላይ የተመሠረተ ማኅበራዊ ደንብ ነው።........»

«ማፍቀሬ ወንጀል ከሆነ፤ ማፍቀሬ ደንብ መጣስ ከሆነ ልሰዋበት ዝግጁ ነኝ። ምንም ዓይነት ህግ ወንዳፍራሽን ከልቤ ፍቆ ማፍቅሬን ሊያስተወኝ አይችልም። ከአጠገቤ ቢርቅ እንኳ ልቤ የትም ቦታ ተከትሎት ሄዶ ያፈቅረዋል። ማፍቅሬን ማገድ የሚችል ምንም ኃይል የለም።......» አለችው አሁንም እያንቀጠቀጣት።

«ልክ ነሽ፤ በመሠረቱ ማፍቀር የህያውነት ምልክት ነው። ፍቅር ወንጀል አይደለም። ወንጀል የሚሆነው ፍቅር ከኋላ የሚያስከትለው ወይም ከፊት የሚያስቀድመው መዘዝ ነው።» አላት እሱም በምፀት ድምፅ።

ሮዛ መልስ በመስጠት ፋንታ ዝም ብላ ኤርሚያስን በትኩታ ተመለከተችው። የምትናገረውን ሊረዳላት የሚችል ሰው አልመሰላትም። አንጎሏ ውስጥ የሚመላለሰው ቃላት ‹ምቀኛ!.....ምቀኛ!....ምቀኛ!.....› የሚል ነበር። አንጎሏን ጽሑፍ የጥላቻ እሳት የሚተፉት ዓይኖቿ ይናገራሉ።

«ለማንኛውም......» አለ ኤርሚያስ ትንሽ ሲያምጥ ቆይቶ፤ «ለማንኛውም ስለ ፍቅር መብትና ግዴት ብቻ መከራከሩ ብዙም ረብ የለውም። የባልና ሚስቱ መፋታት

በወለዷቸው ልጆች ላይ የሚያስከትለውን የስነ ልቦና ቀውስ ለማጤን መቻል አለብን። ሁለቱ ልጆች - ዳኒና ሰብለ - በአሁኑ ጊዜ ለመብታቸው ለመከራከር ዕድሜያቸው አልፈቀደላቸውም። እኔ የምከራከረው ስለ እነሱ ጥብቅና ነው። የአንቺን አድራሻ ፈልጌ የመጣሁትም ለዚሁ ነው። የእናንተ፤ የአዋቂዎቹን፤ በዕልህ የላሸቀ ፍቅር ትተን፤ ልጆቹን ከወደፊት ስንኩል ህይወት ለማዳን አንድ መላ መምታት አለብን።.......»

«እኔ'ኮ ምን አርጊ እንደምትለኝ አይገባኝም። ፅጌረዳ ከቤቷ እንድትወጣ..... ወንዳፍራሽ ሚስቱን እንዲፈታ አልጠየኩም። ስለ ፍቅር ከሆነ ግን ወንዳፍራሽን ምንጊዜም፤ የትም አፈቅረዋለሁ።......»

«ፍቅሩ ብቻ ሳያሆን.....ከወንዳፍራ ማርገዝሽ ከተሰማ በኋላ ነው ትልቁ ችግር የተፈጠረው......»

«ማነው አርግዛለች ያለው?!....ማነው ማህፀኔን የፈተሸው?!......ምን ነው ከተማው ሌላ ወሬ አጣ?!.....ለዚያውም ደግሞ ከምወደው ሰው ባረግዝ አላፍርበትም!......» አለችው ከአፉ ቀምታ።

ጋቢ ስለ ለበሰች የሆዷን መጠን መለየት አልቻለችም። ለዚያውም የደረሰ እርግዝና ካልሆነ ላያስታውቅ ይችላል። ‹ግን ማፍቀሯን እስካልደበቀች ድረስ ማርገዟንም የምትደብቅበት ምክንያት የለም። ዕውነቷን ይሆናል።› የሚል ግምት ወሰደ። በፍቅር ረገድ ግን ከሮዛ የሚሰማው ሁሉ ድግግሞሽ ሆነበት። ድርቅ ያለ ‹ፍቅሯን› በአንድ ምሽት ሊለውጠው አይችልም። የሷን ስሜትና ሁኔታ ብቻ አጥንቶ መሄዱን በቂ አድርጎ መሰናበቱን መረጠ።

«እሺ፤ የኔ እመቤት። በምሽት ስላስቸገርኩሽ ይቅርታ እጠይቃለሁ። - በተረፈ አመሰግናለ።» ብሏት በፍጥነት ርምጃ አስፋልቱን ተሻግሮ፤ ሬኖልት 16 መኪናውን አስነስቶ በረረ።

ጠባቡን መንገድ ወጥቶ ከእይታ እክሲርቅ ድረስ ዓይኖች በጥላቻ ተከተሉት -

ምቀኛ! .....ምቀኛ!.........ምቀኛ!........

ኤርሚያስ የጀመረውን ጉዳይ ፈር ሳያስይዝ ወደ ስዕል ስራው መመለስ አልቻለም። «ሔዋን 1999» እርቃኗን እንደተንጋለለች ቀርታለች። ሰሞኑን የኮንትራት ስራም አላጋጠመውም። - ቢያጋጥመውም በተመስጦ መስራት የሚችልበት ሁኔታ ላይ አልነበረም። የወንዳፍራሽና የፅጌረዳ ችግር ይበልጥ እየሳበው፣ የዳኒና የሰብለ ፍቅር እየገፋፋው፣ አዕምሮውን ፋታ ነስቶታል። - ለስዕሉ ተንተርሶ በጉዳይ ላይ የሚያወያየው ሰው በሀሳቡ ሲፈልግ ዘገየ ወርቃለማሁ ትዝ አለው። አሁን በፊት በጉዳዩ ተቆርቁሮ፣ ስራዬ ብሎ ፈልጎት እንዳዋየው አስታውሶ አሁንም ትብብር ሲያደርግለት ይሚችል ሰው አድርጎ ገመተው። እሱው በነገረው መሠረት ትውሲትና አቶ ከብረትም ጭንቅላቱ ውስጥ መጡበት። ከፅጌረዳ ጀርባ የሚሽርቡት ሽር እንደገና ታወሰው። ዘገየ ግን ክብሪቱን ለኩሶ ከሄደ በኋላ፣ እዚያው ቡና ቤት ውስጥ አንዳንዴ በርቀት ቢያየውም ቸል ብሎ ትቶታል። ኤርሚያስ እንኳ አንዴ ኮሮምቦላ ጨዋታው ላይ ካተኮረ ዘወር ብሎ ሰው አያይም።

ከሥራ ሰዓት ውጭ ዘገየን ለማግኘት አስቦበት ወደ ፀደይ ቡና ቤት ሄደ። ወዲያውም የደመወዝ ሰሞን ስለሆነ እንደማያጣው ተማምኖ ነበር። ነገር ግን የድራፍት ቢራ ሰዓት ሳላልደረሰ ቡና ቤቱ ውስጥ ብዙ ሰዎች አልነበሩም። ዘገየም አልመጣም።

ኤርሚያስ ከወደ ጓዳ የኮሮምቦላ ድንጋይ ድምፅ ስለሳበው ዘገየንም ለመጠበቅ እንዲያመቸው፣ ወደ ውስጥ ገባ። አንደኛው የኮሮምቦላ ጠረጴዛ ተይዟል፣ ሁለተኛው ግን ባዶ ነበር። አንዱ ሱሰኛ ኤርሚያስን ሲያይ ደስ ብሎት ወደ ባዶው የመጫወቻ ጠረጴዛ በአገጩ እያመለከተ ጋበዘው። ኤርሚያስም በኮሮምቦላ አይጨክንም፣ ግብዛውን ተቀብሎ ሊገጥመው ተጠጋ።

የሰውየው ችሎታ የሚናቅ አልነበረውም። አዘውትሮ ከመጫወት የተነሳ ተክኖታል። ኤርሚያስን ሲያይ የተደሰውም ጥሩ ተፎካክሮ አገኘሁ ብሎ ነው። ኋላ ግን አጨዋወቱ አላስደስተውም። በኤርሚያስ አጨዋወት መብሸቁን በቁጣ የተጨማደደው ገጹና ድንጋይ አወራወሩ ያንፀባርቁ ነበር።

ኤርሚያስ ሌላውን የአጨዋወት ስልት ሁሉ ትቶ፣ ጠጠር በመጣሉ ላይ ብቻ አተኮረ። ቢያገኝም፣ ቢስትም በጠላቱ ድንጋይ ወይም በባሊና ጠጠሮቹን ገጭቶ

ለመጣል ብቻ ነበር የሚሰነዝረው። በሀሳቡ አምስቱንም ጠጠሮች በአምስት ሰዎች መስሏቸዋል። አራቱ ዙሪያ ጠጠሮች በወንዳፍራሽ፤ ሮዛ፤ ትውሲትና አቶ ክብረት ተመስለዋል። መሐል የቆመችዋ አምስተኛ ጠጠር ደግሞ ፅጌረዳን ተመስላለች። መትቶ የመጣሉም ሆነ የነጥቡ ክብደት ያለው እዚች መሐለኛዋ ጠጠር ላይ ነው። በእጁ የያዛቸውን አራት ድንጋዮችም የዓላማው ማሳኪያ አድርጎ ወሰደ፤ በሀሳቡ ጭልጥ ብሎ ሰሞኑን ወዳተኮረበት ጉዳይ ገባ።

የተወሰኑ ምቶች ከሳተ በኋላ፤ አንዴ ጠንከር ያለ ምት ሲሰዝር፤ በአንድ ረድፍ የተተከሉትን ሁለት ጠጠሮች በባሊናዋ የደርሶ መልስ ጉዞ ጣላቸው።

የወንዳፍራሽና ሮዛ ነገር አከተመ፤ አለ በሀሳቡ።

እንደገና በሌላው ረድፍ የተተከሉትን ሁለት ጠጠሮች ደግሞ ለመጣል ሙከራና ቀጠል። አሁንም ከተወሰኑ ሙከራዎች በኋላ፤ ባነጣጠረበት ረድፍ የነበረችው አንዷ ጠጠር ተመትታ ስትወድቅ ተንከባልላ፤ በመስመሯ የነበረችውንም ጠጠር ገፍትራ ጣለቻት።

የመሐለኛዋን ጠጠር ማግኘቱ ግን አስቸገረው። ‹ፅጌረዳ ከደረሰባት በደል አንፃር በቀላሉ የማትደራደር ሆና ብትገኝ ምን ያስደንቃል?!› ብሎ እያሰበ ሙከራዎቹን ቀጠለ።

የኤርሚያስ አጨዋወት የንቀት ስለመለሰው የተጋጣሚው ብስጭት ከደቂቃ ወደ ደቂቃ እየጨመረ ሄደ። በዕልህ ስሜት እሱም እንደ ኤርሚያስ  ለምት ብቻ ይሰነዝር ጀመር። ሆኖም የሰው የውን ብሽቀት ኤርሚያስ አልተረዳለትም። የጀመረውን የስሜት ጨዋታን ቀጠለ።

«ም - ምን ማድረግህ ነው? ከተጫወትክ በደንብ እንጫወት!» አለ ሰውየው ትዕግሥቱ አልቆ፤ ጨዋታውን እንዳይተወውም ሱስ ሆኖበት እየተመናጨቀ።»

«ምን አጠፋሁ?......እየተጫወትኩ ነው።» አለው ኤርሚያስም ከተመስጦ ነቃ ብሎ።

«ጨዋታህ ጠጠር መጣል ብቻ ሆነ እኮ!»

«ይቅርታ......አሁን ጥሩ ጨዋታ እንቀጥል።»

ኤርሚያስ በተጋጣሚው ብስጭት ተነቃቅቶ ጥፋቱን አወቀ። በተመስጦ የቆየበትን ሀሳብ ግን ማሳወቅ ስላልፈለገ የአጨዋወት ስልቱ እንደ ተዛባበት አስመስሎ ሽፋፍኖት አለፈ።

በመሠረቱ የኮሮምቦላ ጨዋታ ጠጠሮች መምታትን ብቻ ሳይሆን በዘዴ ባሊናዋን (አጫዋቿን ድንጋይ) እየቀረቡና የጠላትን ድንጋይ እያሻሹ ነጥብ ማስቆጠርንም ያጠቃልላል። እንዲያውም ጨዋታው ውበትና ርዝመት የሚያገኘው በዚህ የአጨዋወት ስልት ነው። ምት የሚያምረው አልፎ - አልፎ ሲሆን ነው። የኤርሚያስን ተጋጣሚ ያበሸቀውም ይኸ ሁኔታ ነበር። የጨዋታ ችሎታውን ስለሚያውቅ የአሁኑ አጨዋወቱ የንቀት ወይም ያለመፈለግ መሰለው።

ኤርሚያስ የሰውየውን ስሜት መጉዳት ስለተሰማው ለተወሰነ ጊዜ ለምት ብቻ መሰንዘሩን አቋርጦ በስልት ባሊናዋን እየቀረበ መጫወት ቀጠለ። ይሁን እንጂ በዚህ አጨዋወቱ ብዙ አልቆየም። ሳያስበው እንደገና ወደ ቀድሞው ተመስጦ ገባ። እና ወደ መሐከለኛው ጠጠር ማነጣጠሩን ቀጠለ።

ለፅጌረዳ ጉዳይ ፋታ መስጠት አልፈለገም። ሁለቱም በጀመሩት ዕልህ ከቀጠሉና ጉዳዩ ከፍርድ ቤት ከደረሰ ድካሙ ሁሉ ከንቱ ቀረ ማለት ነው። ንብረት ክፍፍል ላይ ከደረሱ የወደቀውን ምሰሶ መልሶ ማቆም አይቻልም። ዳኒና ሰብለም ያለ አባት ወይም ያለ እናት ፍቅር መቅረታቸው ነው። ስለዚህ ቀድሞ ማስታረቅ መቻል አለበት። ጊዜ መስጠት አያስፈልግም። ዘዴና ስልት እየቀየሱ በመቅረብ ጊዜ ማቃጠል አጓጉል ነው።.....

ደጋግሞ ጠንከር ያሉ ምቶች ሰነዘረ። በመጨረሻ የጠላቱን ድንጋይ ክርር አድርጎ መትቶ፤ በግጭቱ የመሐለኛዋንም፤ ዙሪያዋን የከበቧትንም፤ አምስቱንም በታትኖ ጠላቸው።

«ቪቫ!.....አስራ ሁለት!» አሉ ዙሪያውን የከበቡት ተመልካቾች።

«ቪቫ!» አለ ኤርሚያስ፤ ሞቅ ካለ ፈገፍታ ጋር አውራ ጣቱን ቀስሮ።

ብዙ ጊዜ ማሸንፍ ልማዱ ቢሆንም እንደዚህ ሲደስት ፈፅሞ ታይቶ ስለማይታወቅ ለብዙዎቹ እንግዳ ስሜት ሆነባቸው።

ተጋጣሚው ግን በሸቀ። በአንድ በኩል አምስቱም ጠጠሮች ወድቀው በርካታ ነጥብ በመቆጠሩ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በአጨዋወት ስልቱ በሽቆ፤ ጨዋታው ሳያልቅ እጁ ላይ የቀሩትን ድንጋዮች ጠረጴዛውላይ ጥሎ፤ ኮቱን ለብሶ ሄደ።

«ምነው......ተጫወት እንጂ።»አለው ኤርሚያስ ዘወር ብሎ በዓይኑ እየተከተለው።

«በቃኝ!.....እነኢ ከሰካራም ጋር አልጫወትም።» አለ ሰውየው፤ ፊቱን ሳያዞር ወደ ፊቱ እየሄደ።

«ተወው!......ተወው!.......እሱ መሸነፍ አይወድም፤ ሁልጊዜ ማሸነፍ ነው የሚፈልገው።» አሉ መጫወቻውን የከበቡት ተመልካቾች - ስፍራው እንዲለቀቅላቸው ስለ ፈለጉ።

ኤርሚያስ በደስታ ፈዘዝ ብሎ ቆይቶ፤ ተጋጣሚውን ማፅናናት እንዳለበት በመገመት ተከትሎት ሲሄድ፤ ሰውየው በፍጥነት ሂሳቡን ከፍሎ እየተመናጨቀ ከቡና ቤቱ ስለ ወጣ ሲደርስበት አልቻለም። ይልቁንም ዘገየ ወርቃለማሁ ድራፍት ቢራ መቅጃው አጠገብ ተሰይሞ አገኘው።

«ከመቼው መጣህ?......ወደ ውስጥ ስገባ አለነበረክም። አንተን ፈልጌ ነበር የመጣሁት።.......ሳጣህ ጊዜ የሱሴን ላድርስ ብዬ ወደ ኮሮምቦላው ክፍል ገባሁ።» አለው ኤርሚያስ፤ ዘገየን አጥብቆ ጨብጦት እጁን እየወዘወዘው።

«አዎ፤ ገና አሁን መምጣቱን ነው። ምን......ድራፍቱን ቶሎ አይጀምሩት። ........» አለ ዘጌም፤ በብሶት አነጋገር ወደ ድራፍት ቀጂው እየተመለከተ።

ሰውየው ደረቅ ፈገግታ አሳይቶ ዝም አለ።

«ቀዝቃዛ ቢራ ቤቴ ውስጥ አዘጋጅቼልሃለሁ። መልካም ፈቃድህ ቢሆን፣ ቤቴን ላሳይህ አስቤ ነው የመጣሁት።»

ዘገየ ትንሽ ግር አለው። የኤርሚያስ ግብዣ ድንገተኛ ሆነበት፡

«መቼ?......ዛሬ?.......»

«አዎ ዛሬ፤ ማምሻችንን የማይዋህይም ጉዳይ አለኝ። ለቁም ነገር ወሬ ከቤት የተሻለ ፀጥታማ ቦታ አይገኝም ብዬ ነው።»

«አንተ ቤት የማገኘው የጠርሙስ ቢራ ነው። ቆይ እባክህ እዚህ አንድ - ሁለት ድራፍት ልላፍ......» አለው ዘጌ፤ ኤርሚያስ ቤት ደርሶ እስኪመለስ ድረስ ድራፍት ቢራ እንደሚያልቅ በመገመት፤ ከወዲሁ ኮታውን ለመውሰድ አሰቦ።

ፍላጎቱ እንደሚሟላለት ኤርሚይስ ቆሞ ጠበቀው። ድራፍት ሲጀመር የመጀመሪያው ብርጭቆ ጨብጭ ዘገየ ሆነ። አንዷን ለውኃ ጥም ጅው! አድርጎ፤ ሁለተኛዋን አጣጥሞ ከጠጣ በኋላ «አሁን መሔድ እንችላለን።» አለው። - የማይጣጣ ሰው አጠገቡ በማቆሙ ይሉኝታ ይዞት ነው እንጂ መደጋገም አምሮት ነበር።

«....አንድ ቀን በነገርከኝ ጉዳይ ላይ እንድንመክርበት ብዬ ነው የፈለግኩህ።» አለው ኤርሚያስ አሮጌ መኪናው ውስጥ ገብተው ወደ ቤቱ ጉዞ ሲጀምር።

«እም!.....የፅጌረዳን ነገር ነው?» አለ ዘጌም የወሬ ጉጉቴ ተቀስቅሶ።

«አዎ.....ስምተኸው ይኾናል.......»

«ምን?.......ተፋቱ እንዳትለኝ ብቻ!?»

ፅጌረዳ ትዳርዋን ጥላ መውጣትዋን እንኳንስ ዘገየ ሌሎችም የመሥሪያ ቤቷ ባልደረቦች ሰምተዋል። ቤቷን በለቀቀች በሶስተኛው ቀን የአመት ዕረፍቷን ለመውሰድ መስሪያ ቤቷ ስትሄድ ፊቷ ክፍት ብሎት፤ አለባበሷም ግድየለሽነት የተሞላበት ስለ ነበር ብዙ ሰዎች ዓይን ውስጥ ገባች። ከቤቷ መውጣቷን የተናገረችው ለትውሲት ብቻ ቢሆንም በትውሲት አማካይነት ወደ ብዙ ሰዎች ጆሮ ደርሷል። «ይቺ ፅጌረዳ ምን አይነቷ የዋህ መሰለቻችሁ!.........ስንት ዓመት የደከመችበትን ቤት እንደ ዋዛ ለባሏ ጥላለት ወጣች እኮ!.......ሲበዛ ልጅ ናት! ያንን መሣይ መልከ ይዛ በቅናት መቃጠሏ ይገርመኛል። ቤቷን ከመልቀቅ ይልቅ ቤቷ ድረስ እየተነዳ ሊመጣ የሚችለውን ወንድ ብታየው ባሏ እንዲህ አይቀብጥም ነበር። ምን ያረጋል! ምስኪን ናት!» እያለች ለምትቀርባቸው የመሥሪያ ቤቷ ሰዎች ሁሉ አውርታዋለች። ዘገየ ይህን ወሬ እንደሰማ

በመሐሉ የትውሲትን ተንኮል እንደሚኖርበት በመገመት በሽቆ የበለጠ መረጃ ለማግኘት አነፍንፎ ነበር። የፅጌረዳ እረፍት ወስዶ ከመስሪያ ቤቷ መቅረት ሁኔታውን ሁሉ አደበዘዘበት። ምናልባ አቶ ክብረት በድብቅ ያወጧት እንደሆነ ለማወቅ መኪናዎችን ባየበት ሁሉ ቢሰልልም ምንም አላገኘም። የነገሮች ገፅጣ መደብዘዝ ጉዳዩን ቸል እንዲለው አድርጎት ቆየ። አሁን ግን ከኤርሚያስ ጋር ለዚሁ ወሬ መገናኘቱ እንደገና ስሜቱን አነሳሳው።.......

«ያው ነው.......» አለ ኤርሚያስ፤ ትንሽ ሲያምጥ ቆይቶ «የጋብቻ ፊርማቸው ቀድደው በፍርድ በኢት ንብረታቸውን አልተከፋፈሉም እንጂ፤ ተነጣጥለው ነው የሚኖሩት። እሷ ቤቱን ጥላ ወላጆቿ ቤት ነች።......»

«ያሳዝናል!.....» አለ ዘገየ ከአንጀቱም ባይሆንን ወሬውን ለማጠናከር። «የዓመት እረፍቱን የወሰደችው ለካ ለዚህ ነው?! ያቺ ሸረኛ ያሰበችው ሁሉ ተሳክቶላታል ማለት ነው!»

«ማን ናት እሷ?»

«ትውሲት ናታ!........ባለፈው ጊዜ እንደነገርኩህ ፅጌረዳን ከአቶ ክብረት ጋር ለማገናኘት ስታቃጥር የነበረችው ትውሲት ነች። የእሷ አላማ የምትቀናበትን ትዳር ማፍረስ ነው። በዚህ ላይ ደግሞ በአቶ ክብረት በሉ የምታገኘው ጥቅም አለ።......»

«ምን ዓይነት ጥቅም?!.......» አለና ኤርሚያስ አቋረጠ።

«የሥራ ቦታ ዕድገት ነዋ!......ትክክለኛ መረጃ አጥቼ ነው እንጂ አቶ ክብረት ትውሲትን ለማሳደግ እንደሚፈልጉ ከሰማሁ ቆይቻለሁ።»

ኤርሚያስ ዘገየን ገፋፍቶ የሚፈልገውን ነጥብ ላይ በማድረሱ ደስ አለው። ሁለቱ ሰዎች ከፅጌረዳ ጀርባ የሚጫወቱትን በደንብ ማወቅ ይፈልጋል።

«የሚያስገርም ቅሌት ነው። እስቲ ቁጭ ብለን እናወራዋለን።

የጓጓለንት ወሬ መንገድ ላይ እንዳያልቅበት የፈራ ይመስል በፍጥነት እየሾፈረ ከቤቱ ደረሱ። ዘኒ ከሰፈሯ ልጆች ጋር እየተጫወተች ነበር። የኤርሚያስን መኪና ከርቀት ተመልክታ የውጭውን በር ከፍታ አስገባቻቸው።

«ዘኒዬ.....ከአዲሱ ጓደኛዬ ጋር ላስተዋውቅሽ። ዘገየ ይባላል። አላት ኤርሚያስ ከመኪናው ከወረዱ በኋላ፤ ተከትላ ገብታ ስትጨብጣቸው።

«እኔ ዘነበች ፀሐይ» በማለት ፈገግ ብላ ራሷን አስተዋወቀችና ከፊት፤ በፊት ቀድማ የሳሎኑን በር ደግሞ ከፈተች።

ሠራተኛዋ ተመላላሽ ስለሆነች የቀን ስራዋን ጨርሳ ወደ አስር ሠዓት አካባቢ ሄዳለች። ምን ጊዜም ማታ፤ ማታ ኤርሚያስና ዘኒ በሳስሎ የቆያቸውን ምግብ ራሳቸው አሙቀውና አቀራርበው ነው የሚመገቡት።

«ዳኒ ሰላም ብሎሃል። አለችው ሁለቱ ከተቀመጡ በኋላ ወደ ኤርሚያስ እያየች።

«እሱ ደህና ነው?»

«ደህና ነው.....ሽርሽር እወስዳችኋለሁ ያልከውን እንዳትረሳ ብሎሃል።»

«እሺ አልረሳም ዘንዬ.....አሁን የምንጠጣውን ነገር አቅርቢልን። - ለእንግዳዬ ቢራ፤ ለኔ ኮካኮላ።»

«አልኮል ነገር ጭራሽ አትጠጣም እንዴ?» አለው ዘጌ ገርሞት።

«የለም፤ በጣም ሲያምረኝ ብቻ ነው የምጠጣው።»

ዘኒ በታዘዘችው መሠረት ከማቀዝቀዣው ውስጥ አውጥታ ከርብጭቆዎች ጋር አቀረበችና ከፍታ ቀዳችላቸው።

ከዘገየ ጋር ለብቻው መወያየት ፈልጓል። ዘኒም ልቧ ጨዋታው ላይ ቀርቶ ስለ ነበር አልተግደረደረችም። ፈቃዱን ስታገኝ ወዲያው ወጥታ ሄደች።

«እንዴት ደስ የምትል ልጅ ናት!» አለ ዘጌ ቢራውን ጨብጦ፤ የቤቱን ዝምታ ለመስበር።

«አዎ፤ የእህቴ ልጅ ናት። ወንደላጤነቴ እንዳይቀዘቅዘኝ እሷን አምጥቼ እያሳደግኩ ነው።»

«ቤትህ ግን የወንደላጤ ቤት አይመስልም።» አለው የምሩን ኮስተር ብሎ

ትንሽና አሮጌ ይሁን እንጂ በጥንቃቄና በንፅህና የተያዘ ቤት ነው። ብዙም ውድ ዕቃዎች የሉበትም። የምግብ ጠረጴዛውም ሆነ ሶፋው ዘመን ያለፈባቸው ናቸው። ነገር ግን በንፅህና ተይዘዋል። ኤርሚያስ ምንም ነገር ተዝረክርኮና ቆሽሾ ማየት ስለማይወድ፤ ይህ ፀባዩ ሠራተኛዋንም ሆነ ዘኒን ንቁ አድርጓቸዋል።

«አዎ፤ ደህና ተይዟል። አንዳንዴ እኮ ከአጓጉል ትዳር ወንደ ላጤነት ይሻላል። » አለው ፈገግ ብሎ።

«እንዴታ! - በሚገባ እንጂ!» አለ ዘጌም የልቡ እንደተነካለት ዓይነት የፈገግታውን ስልት እየተከተለ።

«አንተም አላገባህም መሰለኝ።»

«አላገባሁም። - አንድ ነን።»

«አዎ፤ አንዳንድ ትዳሮችን ስታይ ትዳር አያስመኝህም። የፅጌረዳና የወንዳፍራሽ ትዳር እንዴት ያምር እንደ ነበር ልነግርህ አልችም። አሁን የሚያደርጉትን የህፃን ልጅ ተግባር ስታይ ደግሞ ታዝናለህ።» አለና ኤርሚያስ ወደ ሚፈልገው ጉዳይ ፈጥኖ ለመግባት መንገድ ጠረገ።

«......ግን ምንድ'ነው ያጣላቸው?»

«ወረትና ዕልህ ነዋ!»

«እንዴት ማለት?.......»

«የጽጌረዳ ባል ከትዳሩ ውጭ በወረት ሌላ ሴት ወደደ። መቼም ለወረት ካልሆነ በቀር ትዳሩን አፍርሶ አዲስ ትዳር ሲመሰርት አለመሰለኝም። ይህን ስትሰማ ፅጌረዳ ደግሞ ቅናት አብከነከናት። ቅናቱ ዕልህ ውስጥ ጨመራት። እና አንተ እንደነከርከኝ እሷም እሱን ለማስቀናት ከአቶ ክብረት ጋር ወጥታ ይሆናል። ከዚያ በኋላ ቅናትና ዕልህ በሁለቱም አናት ላይ ወጥቶ ይጨፍር ጀመር። ፅጌረዳ ቅናቱ ስለ በዛባት ቤቷን ጥላ ወጣች። ወንዳፍራሽም ዕልሁ ስለ ተጫነው አባብሎ ሊመልሳት አልቻለም። ይኸውልህ ችግሩ ቀላልና ትንሽ ነው። ነገር ግን ትዳርን ያህል ትልቅ ነገር በትንሽ ጊዜያዊ ችግር ሲፈርስ አያሳዝንም?!.......»

«በጣም እንጂ!......ትዳር ለመመስረት የሚወጣው ወጪ፤ ከዚያ በኋላ ጎጆዎን ለማሞቅ የሚፈሰው ጉልበት፤ ይሄን ሁሉ የሚሸከመው ትዕግሥት.......ይህን ሁሉ አስብና፤ አንተ እንዳልከው፤ የተደከመበት ትዳር በጣም በትንሽ ነገር ሲፈርስ ስመለከት ተስፋ እቆርጣለሁ።......»

ኤርሚያስ ከአንጀቱ ተቆርቁሮ የሚናገረውን ነገር ተንተርሶ ዘጌ ስለ ራሱ ወንደ ላጤነትም መከላከያ እየሰጠ ነበር እንጂ፤ እውነት የወንዳፍራሹና የፅጌረዳ መፋታት ያን ያህል አንገብግቦት አልነበረም። ቀድሞም ሆነ አሁን ዋነኛው ምኞቱ የትውሲትንና የአቶ ክብረት ዕቅግ ማክሸፍ ነው።

«ሌላው የሚያሳዝንህ ነገር ደሞ.....» አለ ኤርሚያስ ወደ ውስጠ - ጉዳዩ ሲገባ ስሜቱ እየፈነቀለው «በጣም የሚያሳዝንህ፤ በትዳሩ ዙሪያ የሚሰባሰቡት ሰዎች ትንሿን ችግር የበለጠ አሳንሰው በማስታረቅ ፈንታ፤ ለሲቷ ወይም ለወንዱ ወገናዊ ይሆኑና ችግሩን ያግሉታል። አሁን ለምሳሌ ፅጌረዳ ቤቷን ለቅቃ እስከ መውጣት የደረሰችው ጣውንቷ - ሮዛ - ለወንዳፍራሽ አርግዛለታለች የሚል ወሬ ከሴት ጓደኛዋ ከሰማች በኋላ ነው። እንዲህ ዓይነቷ መካሪ ማን እንደሆነች ማወቅ እፈልጋለሁ። ፅጌረዳ እኔ የማውቃት ሌላ የቅርብ ሴት ጓደኛ ስለ ሌላት ምናልባት ትውሲት የምትኋት ትሆናለች የሚል ጥርጣሬ አድሮብኛል። ለማንኛውም እርግጠኛ አይደለሁም።....»

የትውሲት ስም በመጥፎ መነሳቱ ዘጌን አስደስቶት ከኤርሚያስ አፍ ነጠቀው

-

«......ታደርጋለች! ትውሲት እንዲህ ዓይነት ሸር ለመፈፀም ወደ ኋላ እንደማትል እኔ በአስር ጣቶቼ እፈርማለሁ። በቅርብ ጊዜ ስለ እሷ የሰማሁትን ብነግርህ በጣም ትገረማለህ......»

«ምንድን ነው እሱ? ከፅጌረዳ ጋር የተያያዘ ነገር ነው?» አለው ኤርሚያስ በጉጉት።

«አይደለም። ቆይ ብቻ፤ የአንተን ጨዋታ ጨርስና እንገርሃለሁ።.......»

«......እና አንዳንዴ ‹የቅርብ ወዳጅ› የሚባሉትም ሰዎች ከመገንባት ይልቅ ማፍረሱ ይቀናቸዋል ማለቴ ነው።»

የዘጌን ወሬ ለመስማት በመቸኮሉ የራሱን ንግግር አሳጥሮ ተንስቶ፤ ሌላ ቢራ ከጨመረለት በኋላ በጥያቄ መልክ ዓይን - ዓይኑን ያየው ጀመር።

«ምን መሰለህ....» አለ ዘጌም ጉንጬ ውስጥ የነበረውን ቢራ አጣጥሞ ውጦ፤ «የትውሲትን የተደበቁ ጉድ የነገረችኝ ጅማ ከተማ ውስጥ አብራት ትሰራ የነበረችው አንድ ጓደኛዋ ነች።.......»

ዘገየ ትውሲትን ለማሳጣት የተፈጠርለት አጋጣሚ ቢያስደስተውም፤ የሚያወራው ነገር ፈጠራ ወይም ውሸት አልነበረም። ከትውሲት ጋር ከተጋጩ ጀምሮ እሷን በግላጭ አቶ ክብረትን ደግሞ በስውር የሚያዋርድበትን መንገድ ሲያሰላ ነበር የከረመው። በዚሁ ምክንያት ጅማ ውስጥ ወዳጅዋ የነበረችውንና አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ የተጣላቻትን ጓደኛዋን ፈልጎ አገኛት። ጥሩም ሆነ መጥፎ ሚስጥር ገሀድ የሚወጣው የቅርብ ሆኖ ከሚርቅ ጓደኛ መሆኑን ያውቃል። ከዚች ሴት ጋር ዘገየን ያስተዋወቀችው ፍቅር በነበሩበት ጊዜ ትውሲት ራሷ ነበረች። ዛሬ ሚስጥሯን አባካኝ ጣውንቷ ሆናለች። ዘገየ እንኳንስ እንዲህ ያለ አጋጣሚ አግኝቶ፤ ቀድሞውንም ሴቶችን ሲያወጣቸው ሚስጥር ለመበዝበዝ ተዘጋጅቶ ነው - ቢጠቅመውም፤ ባይጠቅመውም ወሬ ይወዳል።

«......እና ልጅቷ እንደ ነገረችኝ።» ሲል ቀጠለ ዘገየ፤ «.......ትውሲት ጅማ ከተማ ውስጥ በጣም የሚወዳት ባል ነበራት፤ እንዲያውም አንድ ሴት ልጅ ወልዶላት ነበር። ሰውየው በዕድሜው በሰል ያለ ሆኖ አስተዋይና ትሁት ሰው ነበር አሉ። እሱን ቤት ውስጥ አቀምጣ ከማንም ጎረምሳ ጋር ስትዘል፤ ሰውየው በቅናት ይቶፍና ካልገደልኩ ይላል። እሷ ግን አትታረምም። እንዲያውም ይበልጥ ልታሰቀናው ትሞክራለች። ቤቱንም፤ ህይወቱንም ብጥብጥ ታደርግበታለች። በመጨረሻ ትዕግሥቱ አለቀና፤ አንድ ጠዋት ሽንኩርት የምትልጥበት ቢላዋ እጅዋ ላይ ሰክቶ አባረራት። ሰውየው እበሷ ምክንያት ቀውስ ሆኖ ቀርቷል ይባላል።....»

«ልጇን ጥላት ወጣች ወይንስ ይዛት?......» አለ ኤርሚያስ ጣልቃ ገብቶ።

«ፐ!....ትውሲት ነች ለልጇ የምታስበው?! ክስም እንዳትጀምር በሰውየው ላይ የፈፀመችውን በደል ስለምታውቅ የማያዋጣት ሆነና ልጇንም ባሏንም ጥላ፤ ሹልክልክ ብላ አዲስ አበባ ገባቻታ! ልጇን የሰው ቤተሰቦች ወስደው ያሳድጓታል አሉ። ባሏም

እንደነገርኩህ የደከመለት ትዳር ባለመሳካቱ ቀውሶ ቀርቷል። ትውሲት እዚህ ትዳርን እንዳልቀመሰች አዲስ ሴት ትሽከረከራለች። በቅርቡ ጓደኛዋ እስከትነግረኝ ድረስ እኔ ራሴ ጋለሞታነቷን አላውቅም ነበር።» አለው፤ ሐጢያቷን ለማጉላት በተቻለው መጠን ፊቱን አጨማዶ ድምጹን እያሻከረ።

ኤርሚያስ ይህን ሲሰማ፤ በሚስቱ ምክንያት አብዶ ጅማ ከተማ ውስጥ የሚንከራተተውን ሰውየ በዓይነ ህሊናው እየተመለከተ፤ ሀሳብ ውስጥ ገባ። ህሊናው ሰውየውንም ከመወንጀል አልተቆጠበም። - እሱስ ቢሆን መጀመሪያውኑ እንዲህ ዓነቷን ሴት ለምን ያገባል? ሲል አሰበ። - የጥንት ጋብቻ እንኳ ምርጫውም በወላጆች በኩል ስለሚፈፀም፤ ለመጠናናት ቀርቶ በዓይን ለመተዋወቅም ዕድል አልነበረም። አሁን፤ ዘመን ተሻሽሎ ሴቷም፤ ወንዱም መምረጥ ስንችል ምን እንደሚያደናብረን አይገባኝም። ተጋብቶ ከመፋታት መጀመሪያ መጠናናት ይሻል ነበር። ዓይንን ታውሮ፤ ዝም ብሎ መጋባቱ ዋጋ የለውም። ከሆነም ደግሞ፤ አብረው ቢኖሩም፤ በደንብ እስኪጠናኑ ድረስ ያለ መወለዱ ይመፈረጥ ነበር። ችግሩ ግን ከመጋባቸው በፊት ውስጣዊ ማንነታችንን ማሳወቅ ያለ መፈለጋችን ነው። ሴቷ፤ ወንዱ ሳያገባት ውስጣዊ ማንነቷን እንዲያውቅባት አትፈልግም - እንዳይተዋት ትፈራለቻ! እሱም ከወደዳት ውስጣዊ ግንኙነቱን ገልጦ አያሳያትም። - እንዳትተወው ይፈራል! በፍራቻው ሳቢያ፤ ሁለቱም ሲገናኙ ጭምቡል አጥልቀው ይቀራረባሉ። ተደባብሶ መጋብቱን የመርጣሉ፤ መሠረት የሌለው ምሰሶ ያቆማሉ። በኋላ ምሰሶው ሲወድቅ፤ መዘዙ ከእነሱ አልፎ ወደ ሚወልዳቸው ልጆች ይተላለፋል።

በዚህ ረገድ፤ የሰማችውና ያያቸው አንዳድ እንገሮች ትዝ አሉት። ለአምስት አመታዊ ያህል አንድ ጎጆ ውስጥ እየኖሩ ከተጠናኑ በኋላ፤ ህጋዊ የጋብቻ ሰርቲፊኬት አውጥተው መውሰድ የጀመሩትን ስዊድናውያን አሰበ። ኢትዮጵያ ውስጥ ለኮንትራት ስራ መጥተው የተጣሉትን ጀርመናውያን ባልና ሚስቶችም አስታወሰ። እኒህ ጀርመናውያን ሁለት ልጆች ወልደዋል። ሴትየዋ ሌላ ጀርመናዊ ወንደላጤ ወደደች። ባልየውም ይህን ያውቃል። እስካሁን ድረስ ከወንደላጤው ጋር እየወጣች፤ ለልጆቻቸው ሲሉ ብቻ፤ ከባሏ ጋር ትኖራለች።

ይህ እንኳ ምናልባት ከባድ ይሆናል። ቅናት ተፈጥሮአዊ ነው ይሉናል፤ ሲል አሰበ፡ - ነገር ግን ቅርናትና ዕልህ፤ ተፈጥሮአዊም ሆኑ አካባቢያዊ፤ በዕድገትና በስልጣኔ የማይሞረዱበት ምክንያት አይታየኝም። -

«......ለነገሩ ግን ትውሲት ሲበዛ ርኩስ ናት።» አለ ኤርሚያ ከጎሳቡ ተመልሶ ወደ ዘገየ እየተመለከተ፤ «ምናልባትም በሌሎች ትዳር ላይ እኩይ ተግባር የምትፈጽመው፤ በባሏ ላይ የፈጸመችው በደል አእምሮዋን ሰላም እየነሳት ይሆናል። ......»

«አትጠራጠር፤ ቅናት ነው! ምቀኝነት ነው! ሽረኝነት ነው! ሴቱ ሁሉ እንደ እሷ እያደዘደዘ እንዲኖር ነው የምትፈልገው።.......የፅጌረዳን ውበት ደግሞ ሌሎች በማቃጠር ልትጠቀምበት ትፈልጋለች። ለዚህ ነው እንቅልፍ አጥታ ከባሏ ጋር ያጣላቻት።»

ኤርሚያስ ለጥቂት ሴኮንዶች ያህል አገጩን በእጁ ደግፎ ሲያስብ ከቆየ በኋላ፤ «እንግዲያው ሮዛ ለወንዳፍራሽ ‹አርግዛለታለች› ብላ የነገረቻት ትውሲት መሆን አለበት። - አይመስልህም?» አለው ዘገየን በማውጣጣት አይነት።

«መሆን አለበት! እሷ ለተንኮል አትተኛም እያልኩህ። ሰሞኑን ተጣልተን አንነጋገርም እንጂ እንደ ዱሮአችን ብንሆን ከራስዋ አፍ በዘዴ አጣራልህ ነበር።»

«ም - ምን አጣላችሁ?»

«በዚያ በነገርኩህ ነገር ምክንያት ነዋ።.....እሷና አቶ ክብረት ለተንኮል እንደማይተኙልኝ አውቃለሁ። እኔም እነሱን ለማጋለጥ ወደ ኋላ አልልም። ግቢው ውስጥ የጎሪጥ ነው የምንተያየው። ከአቶ ክብረት ጋር አንኳ ፀባችን ቆይቷል። ከትውሲት ጋር መነጋገር ያቆምነው ግን ከፅጌረዳ ጀርባ የምትሰራውን ሸር ከነቃሁባት በኋላ ነው። የሷን ትተህ ያ ጅል ደጀኔ እንኳ አኩርፎኛል።......»

«ደጀኔ?......ደጀኔ?.....»

«ውሽማዋ ነዋ! ስለሱ አልነገርኩህም እንዴ?! ‹ሞትኩልሽ› እያለ ገንዘቡን የሚከሰክስላት አንድ ጅል አለ። በግ በመሆኑ ያሳዝነኛል። ካለሷ ሴት የቀመሰም

አይመስለኝም። እሷም ይህንኑ አውቃ በነፍሱ ትጫወትበታለች። በእሷ ሳቢያ አሁን እሱም አያነጋግረኝም። ሰላምታ ብንለዋወጥም ከአንገት በላይ ነው።......»

ኤርሚያስን የደጀኔና የትውሲት ግንኙነት አላስጨነቀውም። ዘገየ ስለ እነሱ ሁኔታ ሲያወራለት፤ እሱ ከገጹ ላይ የሚያነበው በትውሲትና በአቶ ክብረት ላይ ያለውን ጥላቻ ነበር። የፅጌረዳን ጉዳይ ቀድሞም ስራዬ ብሎ ፈልጎ የነገረው፤ አሁንም የተባበረው፤ ምናልባትም ለፅጌረዳ በመቆርቆር ብቻ ሳይሆን፤ እኒህን ሁለት ጠላቶቹን ለማጋለጥ ወይም ምኞታቸውን ለማክሸፍ መሆኑን ኤርሚያስ ከአኳኋኑ ጠረጠረ። ያም ሆነ ይህ ለጀመር ዓላማው ስለ ሚረዳው ጥያቄውን ገፋበት።

«ለመሆኑ ፅጌረዳን ከአቶ ክብረት ጋር መውጣቷን ቀጥላ ይሆን ወይንስ ግንኙነታቸው ተቋርጧል?.....» በማለት ጨዋታውን በቀጥታ ወደ መስመሩ አጠፈው።

እዚህ ላይ ዘገየ ቶሎ መመለስ አልቻለም። ምላሱን ያዝ አደረገው። ከአሁን በፊት ፅጌረዳ ከአቶ ክብረት ጋር መውጣት እንደ ጀመረች አስመስሎ መናገሩን ያስታውሳል። በአንድ በኩል ያንኑ አቋሙን ማጠናከር ፈለገ። በሌላ በኩል ደግሞ እርግጠኛ ያልሆነበትን ነገር ‹ነው› ብሎ ማውራቱ፤ በተለይ ኤርሚያስን ከቀረበውና ስብዕናውን ካወቀ በኋላ፤ ትዝብት ላይ የሚጥለው መሰለው።

«ፅጌረዳ የአመት ፈቃዷን ከወሰደች በኋላ እንኳ ግቢው ውስጥ አይቻት ስለማላውቅ፤ ግንኙነታችውን ለመከታተል አልቻልኩም።.......ሆኖም ሳስበው አቶ ክብረት እንደሆኑ አያርፉም። ሲበዛ ሂያጅ ናቸው።.......ፅጌረዳም ትዳሯን እስከፈታች ድረስ......ህም!......» አለ በይሆናል ዓይነት አንገቱን ወደ አንድ ጎን አዝምሞ፤ ግንባሩን ኮስትሮና ለንቦጬን ጥሎ።

«አቶ ክብረት የምትላቸው፤ ባለ ትዳር ናቸው ወይስ ወንደላጤ?»

«ባለትዳር ናቸው እንጂ! እንዲያውም እኩያ ወንድ ልጅ አላቸው። እንደ ሰማሁት ከሆነ፤ አባትና ልጅ አንዳንዴ ሴት ለመጥበስ አብረው ይወጣሉ አሉ። -ሚስታቸውን እቤታቸው ጎልተው!......»

ኤርሚያስ ባገኘው የ ‹ይሆናል› መረጃ አልረካም። ፍንጭ ማግኘቱ ባይከፋም፤ እርግጠኛ መሆን አይቻልም። እርግጠኛ ባልሆኑበት መንገድ መሮጥ ደግሞ ጉድጓድ ሊጨምር ይችላል።

«በል እንጂ ያዝ።....ቢራውን እየጠጣህ.....»

ዘገየን በአፉ እያስተናገደ፤ በኅሳቡ ርቆ መጓዙን ቀጠለ። ስሜቱ የፈለገውን ነገር ለማወቅ ተቁነጠነጠ። ኮሮምቦላ ጨዋታው ላይ መትቶ የጣላቸው ጠጠሮች እንደ ገና በሀሳቡ ታዩትና ፊቱ ወገግ አለ።

ስለ ሌሎቹ ጉዳይ አንተን እንዲህ እንቅልፍ የነሳህ ምክንያት ምድን ነው?

ኤርሚያስ በጠዋት ተነስቶ ወደ ትውሲት ቢሮ ለመሄድ ፀጉሩን ሲያበጣጥር፤ በመስታወቁ ውስት የሚያየው ምስሉ በድንገተኛ ጥያቄ አፋጠጠው። ከውስጡ የመነጨቀውን ጥያቄ ቸል ብሎ፤ ተበጣጥሮ ለባብሶ ወጣ።

ለፅጌረዳ ለወንዳፍራሽ የቅርብ ጓደኛ ከመሆኑ ባሻገር፤ በዳኒና በሰብለ ፍቅር ከመገፋፋቱ ሌላ፤.....የትዳርን መፍረስ አስቀያሚ ቀፅታ በአንክሮ እንዲመለከት የሚያደርገው ስውር ምክንያት ከአእምሮው ጓዳ ተደብቆአል። ይሄው ስውር ምክንያት፤ እንዲህ ዓይነት የሚያሳዝን አጋጣሚ ሲያገኝ፤ ውስጣዊ ግፊቱ እየጨመረ ተቃውሞውን ገሀድ ያወጣል። የትዳርን መፍረስና የቤተሰብን መበታተን ለማውገዝ ክንዱን አንስቶ፤ ከተደበቀበት የአዕምሮ ጉዳ ወደ አደባባይ ይወጣል። ከጀርባ ታሪኩ ላይ ያረፈው ጠባሳ ነፍስ ይዘራና አዲስ ቁስል ሆኖ ህክምና ይጠይቃል። በመጨረሻም በሊሎች መዳን እሱም ጊዜያዊ ፈውስ ያገኝና፤ ወደ ነበረበት አዕምሮ ጓዳ ይመለሳል።

ኤርሚያስ መኪናውን አስነስቶ ጉዞ ከጀመረ በኋላ፤ ቀዝቃዛው የጠዋት ስሜቱ፤ የህይወትን ግጭት ሙቀት ለማግኘት፤ የአዕምሮውን ጓዳ እየሰረሰረ የተደበቀ ጠባሳውን በሀሳቡ ያሳየው ጀመር -

አባቱ አቶ ዘለቀ ባህር ዳር ከተማው መሐል አንድ የታወቀች የጨርቃ ጨርቅ መሸጫ ሱቅ ነበረችው። የሱቋ ዝነኝነት ባለቤቱም ዝናን ስላተረፈችለት በከተማው ውስጥ ዘለቀን የማያውቅ ሰው በቁጥር ነበር። ከህግ ሚስቱ ከወይዘሮ አልማዝ የወለደው አንድ ወንድ ልጅ ኤርሚያስ ብቻ ቢሆንም፤ እዚያው ከተማ ውስጥ በድብቅ

ከሌላ ሴት መውለዱ ይወራ ነበር። እያደር ሚስጥርነቱ ገሀድ ወጣ። ከውጭ የተወለደችው ልጅ ፀሐይ ዘለቀ ተባእልች። የኤርሚያስ እናት በሚስትነት፤ የፀሐይ እናት ደግሞ በውሽምነት ይኖሩ ጀመር። ይሁን እንጂ ኤርሚያስና ፀሐይ የተላየየ ቤት ውስጥ በተለያዩ እናቶች እጅ ይኖሩ ስለ ነበር እንደወንድምና እንደ እህት ተቀራርበው፤ አፈር ፈጭተው፤ ፍቅር ይዘው ለማደግ አልታደሉም። በሁለቱ እናቶች መጠላላትና በአባትየው ግዴለሽነት ሳቢያ ተገቢውን የወንድምና እህት ፍቅር ሳያገኙ ቀሩ።

ኤርሚያስ ያኔ ገና ልጅ ቢሆንም እናቱ ታሰማው የነበረው የብሶት እንጉርጉሮ፤ ከድግግሞሹ ብዛት፤ አዕምሮው ውስጥ ተቀርጿል። ወፍጮ ስትፈጭ፤ እህል ስታበጥር፤ ወይም እሳት ዳር ቁጭ ብላ ወጥ ስታማስል -

«አልማዛቸው ነበርኩ - ለናትና አባቴ

ክብር አሳጣኝ እንጂ ዛሬ ባልተቤቴ

በላዬ ወሽሞ አንዲት ጋለሞታ

እህህ እያሰኘኝ ጠዋትና ማታ

በልቤ አሳድሮ የቅናት በሽታ

ምርኮው አደረገኝ - እሰሬን የማልፈታ፤.......»

እያለች ማንጎራጎር ልማድ አድርጋ ነበር። ነገር ግን ምርኮው እንደ ሆነች አልቀረችም። አቶ ዘለቀ ከውጭ አንድ ውሽማ አንሳው፤ ብዙ ቅምጦች ማስቀመጡ ይነገር ጀመር። ቤቱን ችላ አለው። ከሐብቱ ማደግ ጋር የፀባዩ መበላሸት እየከፋ ሄደ። የወጣለት መሸተኛና ሴሰኛም ሆነ። አልማዝ ቤቱ ውስጥ እስከመኖሯም ረሳት። እሷም ተረስታ፤ ተንቃና ተዋርዳ መርኖር አልቻለችም። አንገፈገፋት! እናም አንድ ሌሊት፤ ጎህ እንኳ ሳይቀድ፤ ጨርቄን ማጤን፤ ልጄን ሳትል ብርር ብላ ወጥታ ሄደች። አልተመለሰችም፤ በዚያው እንደ ወጣች ቀረች።

ከብዙ መንገላታት በኋላ ዘመዶቿ ወዳሉበት ወደ ደብረ ማርቆስ ተመልሳ ሌላ ባል ግብታ ትኖር ነበር። ሆኖም ዘለቀ ላይ ባደረባት ጥላቻ የተነሳ ከዚያ በኋላ ልጁን እንኳ ብቅ ብላ አይታው አታውቅም። በደመነፍስም ቢሆን የእናቱ መበደል

የተስማው ትንሹ ኤርሚያስ ግን አልማዝ ሁልጊዜም ሀሳቡ ውስጥ ነበረች። አንዳንዴ ሁለመናዋ ዓይኑ ላይ ድቅን ይልበትና በሩ ላይ ተቀምጦ ስቅስቅ ብሎ ያለቅሳል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ጃንጥላ ይዘው ጥበብ ለብሰው በመንገድ የሚያልፉ ሴቶች በርቀት ሲመለከት፤ የእናቱ ምስል እየታወሰውና እሷን ያገኘ እየመሰለው ተከትሎአቸው ብዙ መንገድ ይሄዳል።......ሳይጠግባት የተለየችው የእናቱ ፍቅር ድበቅ ጠባሳውን አዕምሮው ውስጥ ያኔ ነው። አልማዝ ከሁለተኛው ባሏ ጋር ስትኖር፤ የጡት ካንሰር ያለ ዕድሜዋ አሰቃይቶ እንደ ገደላት እንኳ ኤርሚያስ የሰማው ካደገ በኋላ ነበር። መቼም የሚወዱትን ሰው ሞት ማመን ያስቸገራል። ኤርሚያስም የእናቱን ሞት ማመን አቅቶት ለብዙ ጊዜ እሷን መሳይ ሴት ሲመለከት ልቡ ሲደነግጥ ኖሯል። የበአል ቀን የምትለብሰው ጥበብና፤ ገበያ ስትወጣ የምትይዘው ጃንጥላ ሁልጊዜም በአይኑ ላይ ያልፋሉ።

አልማዝ ከሔደች በኋላ ዘለቀ ቤት ውስጥ ሌላ ሚስት አልገባችም። ቅምጦችም እንደቅምጥነታቸው በውጭ ተይዘው ኤርሚያስ በገረዶች ያድግ ጀመር። አባቱ በገንዘብ ረገድ ቸር በመሆኑ ለልብስ መግዣም ሆነ ለቤት ጣጣ ከሚገባው በላይ ቢበትንም ትንሹን ኤርሚያስ የሚገባውን የአባትነት ወግ አላሳየውም። አዲስ ልብስ ገዝት ይወረውርለትና ወደ መሸታ ቤት ሩጫውን ይቀጥላል። ቤቱ ውስጥ ቸር የመሆኑን ያህል ውጭም ብኩን በመሆኑ ሐብቱ እያቆለቆለ ሄደ። መሸተኛነቱና ሴሰኛነቱ በፈጠረበት ግዴለሽነት ሳቢያ የሱቁ ገበያ እየቀዘቀዘ ወርዶ አደገኛ ኪሳራ ላይ ጣለው። «ያደቆነ ሰይጣን ሳያቀስስ አይለቅም» ሆነና መኖሪያ ቤቱን ሳይቀር ወለድ አገድ አስይዞ መጠጣቱን ቀጠለ። በመጨረሻም ንብረቱን ሁሉ ሸጦ ጨርሶ፤ ከቡና ቤት ውስኪ ወደ መንደር ካቲካላ ወርዶ፤ ፊቱ በአልኮል ብዛት ማዲያት አውጥቶ፤ ተከብሮ በኖረበት ሰፈር ተዋርዶ ሞተ።

ይህ ሲሆን ኤርሚያስ የአስራ ሁለት ዓመት ልጅ ነበር። ከዚያ በኋላ የአባቱ ዘመዶች ወደ አዲስ አበባ አምጥተው እያስተማሩ አሳደጉት። ዘመዶቹ ምንም ያህል ጥሩ ቢሆኑለት፤ ከእናትና ከአባታቸው ጋር በሚኖሩ የጎረቤት ልጆች መቅናቱ አልቀረም። እንዲያውም እያደገ ሲሄድ በዚህ ቁስሉ ሳቢያ ሆደባሻና ነጭናጫ ሆነ። ከእሱ ፍላጎት ውጭ ወደዚህ ዓለም አምጥተው ወርውረርውት የሄዱትን እናትና

አባቱን መርገም ጀመረ። አባቱን በብኩንነቱ፤ እናቱን ደግሞ ጥላው በመጥፋቷ አማረረ።

በአዕምሮው በስሎ ነገሮችን ማመዛዘን ባይችል ኖሮ፤ ይህ የስነ ልቡና ቀውስ ወዴት ሊያደርሰው እንደሚችል መገመት አያዳግትም። አሁንም ይህን ሲያስብ ነው የትዳር መፍረስና መዘዙ ጉዳይ ራስ ምታት የሚሆንበት። እሱን የረዳው በአዕምሮ መብሰሉ ወይም በትምህርት መሞረዱ ብቻ ሳይሆን፤ ሳያስበው ከውስጡ ብቅ ያለው የስዕል ችሎታው ነው። የስዕል ችሎታውና ፍቅሩ የእንጀራ ምንጩ ብቻ ሳይሆን የስነ ልቡና ሐኪሙም ሆነለት። ሙያውን ለማዳበርና የኪናዊ አስተሳሰብ አድማሱን ለማስፋት ብዙ ባነበበ ቁጥር ራሱን እየሞረደ መጣ። የወላጆቹን ስነ ልቡናዊና ስሜታዊ ችግሮች ወደ ኋላው ዘወር ብሎ በመመርመር አዕምሮው ውስጥ የነበረውን ጥላቻ ፋቀ። የእናቱም ሆነ የአባቱ የህይወት መንገድ በማይምነት የተደናበረ እንጂ፤ ሆነ ተብሎ እሱን ለመጉዳት ያልታቀደ መሆኑን ተገነዘበ። ያም ሆኖ፤ በወላጆቹ ላይ የነበረውን ጥላቻ ቢፍቅም ቅሉ፤ ችግሩ ከአዕምሮው ጀርባ ተደብቆ በእንዲህ ዓይነቱ አጋጣሚ ግፊት መፈጠሩ አልቀረም።.......

እነ ፅጌረዳ መሥሪያ ቤት ሲደርስ ኤርሚያስ ጭንቅላቱ ውስጥ ሲመላለስ የቆየውን ትዝታ ገትቶ፤ መኪናውን ወደ አንድ ጥግ አቆመና፤ ትውሲትን እንዴት እንደሚያነጋግራት ያሰላስል ጀመር። ሰአቱን ሲመለከት ሶስት ሰዓት ከሩብ ሆኗል። ማታ ከዝገየ ጋር ተነጋግሮ እንዳበቃ ነበር ትውሲትን አነጋግሮ አንዳድ መረጃዎችን ለመውሰድ የወሰነው። በዚህም መሠረት ለህሳቡ ፋታ ሳይሰጥ በጠዋት ወደ መስሪያ ቤቷ መጣ። ትውሲትን ለመጥላት ዘገየ የነገረው ብቻ ብቂ ቢሆንም፤ ጥላቻውን ሳያሣይ እሷን ደግሞ ቀርቦ ማነጋገሩን መረጠ። የሮዛን ማርገዝ ጉዳይ ለፅጌረዳ የነገረቻት እሷ መሆኗን ከአፏ መስማትም ፈልጎ ነበር።

«ጤና ይስጥልኝ.......» አለ ወደ ቢሮ ገብቶ ወደ ፀሐፊዋ እየተጠጋ።

«ጤና ይስጥልኝ።» አለችው ትውሲት ከመቀመጫዋ ተነስታ፤ ልትጨብተው እንጇን እየዘረጋች።

«.......ታስታውሺኛለሽ?» አላት፤ ሲጨባበጡ የግዱን ፈገግ ብሎ።

«እንዴታ! .....ሠዓሊው አይደለህም እንዴ?! እዚያ ክበባችን ውስጥ የሳልካቸውን ስዕሎች ስመለከት ሁሌም ትዝ ትለኛለህ.....ቁጭ በል።»

ወንበር ጋበዘችውና ተቀመጠ። ከስድስት ወራት በፊት የመሥሪያ ቤቱ መዝናኛ ክበብ ተሰርቶ እንዳለቀ ኤርሚያስ አንዳንድ ሥዕሎችን በኮንትራት ሰርቶ ነበር። በዚያን ወቅት ወደ ፅጌረዳ ቢሮ ብቅ ሲል ከትውሲትም ጋር ተዋውቀዋል። ፀባይዋንና ማንነቷን አሁን ዘገየ በነገረው መልክ ለማወቅ ዕድል አልገጠመውም እንጂ የውጭ ገጹን በደንብ አስታወሰ።

«......ባልሳሳት - አንድ ቀን ከፅጌረዳ ጋር ሆነን አብረን ሻይም የጠጣን ይመስለኛል።» አላት ወደ ኋላ በማስታወስ ዓይነት ግንባሩን ሸብሸብ አድርጎ።

«ታዲያስ! ልክ ነህ። እንዲያውም ፎቶዬን በእጅ ሥራ ልትስልልኝ ቃል ገብተኸልኝ ነበር።» አለችው ፈገግ ብላ።

ይህን እንኳ ኤርሚያስ አያስታውስም። ከተዋወቃቸው ውስጥ ብዙ ሰዎች፤ በተለይም ሴቶች ምስላቸውን እንዲስልላቸው ስለሚጠይቁት፤ ይህ ጥያቄ ወደ አዕምሮው ከመድረሱ በፊት ጆሮው አንጥሮ ይመልሰዋል። ጠያቂዎቹን እንደ ቀልድ «እሺ» ይላቸዋል እንጂ፤ በቁም ነገር አዕምሮው ውስጥ አይፅፈውም። በመሠረቱ እሱ ሰአሊ እንጂ ፎቶ ግራፍ አንቺሺ አይደለም። ብዙ ሰዎች ይህንን ስለማይረዱለት ተከራክሮ ከማሳመን ይልቅ ስቆ በእሺታ መለያየቱን ይመርጣል።

«......ረስተኸዋል አይደል?» አለችው፤ ከእሱ መልስ በማጥቷ።

«አ - አልዋሸሽም፤ ስራ በዝቶብኝ ስለ ነበር ረስቼዋለሁ።» አላትና፤ ዘገየ ስለ እሷ የነገረውን ሁሉ ከፊቷ ላይ ማንበብ የሚችል ይመስል፤ ትክ ብሎ ከተመለከታት በኋላ - የድሮው እንኳ ቀልድ ይሆናል፤ አንቺን መሳል ያለብኝ አሁን ነው፤ አለ በሀሳቡ።

የታይፑ ጠረጴዛ ስለከለለው የእጇን ጠባሳ ማየት አልቻለም።

የኤርሚያስ አመላለስ ለዘብ ያለና ይቅርታን የሚጠይቅ ዓይነት ስለመሰላት፤ ያለፈውን ቢረሳውም ለወደፊቱ ምስሏን እንደ ሚስልላት ተስፋ በማድረግ የትውሲት

ልብ መቁነጥነጥ ጀመረ። ምስሏን አሳምሮ በትልቁ ቢስልላት፤ ቤቷ ውስጥ ፊት፤ ለፊት ትሰቅለውና.....ወንዱን ሁሉ በጉጉት እንዲከጅላት.....ሴቱ ሁሉ በቅናት እንዲቋምጥላት......ደጀኔ ተንበርክኮ እንዲሳለማት.....መመለኪያ እንዲሆናት......ትልቅ ፍሬም ውስጥ አስገብታ ትሰቅለውና፤......

ይህን ስታስብ ፊቷ የደስታ ብርሃን እየረጨ ሄደ። ሆኖም የጥቅም ስሜቷን ፈጥና ማሳወቅ እንዳያስገምታት በመፍራት የስዕሉን አርዕስት ቸል ያለች አስመስላ ወደ ሊላ ጨዋታ ተሸጋገረች።

«ለመሆኑ ዛሬ እንዴት ብቅ አልክ?»

«ልጠይቃችሁ ነዋ......ፅጌረዳ የለችም እንዴ?» ስለ ፅጌረድ ብዙ ላያወቀ መስሎ ትውሲትን ማነጋገር ሆነ - ብሎ ከቤቱ ሲወጣ ያቀደው ዘዴ ነበር።

«ፅጌረዳማ ዕረፍት ላይ እኮ ናት።......አልሰማህም እንዴ?» አለችው፤ ግንባሯን በአትኩሮት ጨምድዳ።

«ምንኑ?......» - እሱም አውቆ የመደናገር ዓይነት ስሜት አሳየ።

«ከ - ባልዋ ገር ተጣልተው....»

«እህ! - አዎ፤ ከወንዳፍራሽ ጋር ተጋጭተው እንደ ነበር እንኳ ሰምቻለሁ። ከዚያ በኋላ የኮንትራት ስራ አግኝቼ ወደ ገጠር ሄጄ ነበር። ገና ትላንትና መመለሴ ነው።»

«ቤታቸውም አልሄድክማ?!»

«አልሄድኩም። ፅጌረዳን ቢሮዋ አገኛታለሁ ብዬ ነው የመጣሁት።»

«ገና እንግዳ ነሃ!.....ብዙ ወሬ አምልጦሃል። እሲ ለማንኛውም ፅጌረዳ በሌለችበት እንግዳዬ ስለሆንክ፤ ሻይ ልጋብዝህና......» ብላ የሱን ፈቃደኝነት ሳትጠይቅ ቁልፎቿን ይዛ ተነሳች።

«ተይ ግድ የለሽም፤ የስራ ሰዓት ስለሆነ......»

«ምን ስራ አለ ብለህ ነው! አለቃዬም የሉም - ለሴሚናር ወደ ናዝሬት ሄደዋል። ለእኔም የሻይ ሰዓቴ ተቃርቦአል። ይልቅ ተነስ።

ቀድማው ወደ በሩ አመራች። ኤርሚያስም እንደ ልማዱ ፂሙን እየጎነታተለ ተከተላት።

«ለፅጌረዳ ቤተኛ ትመስለኝ ነበር እኮ.....» አለችው ቢሮዋን ቆልፋ መንገድ ሲጀምሩ።

አስተያየቷን የጎድን ጥያቄ ያዘለ ነበር። የኤርሚያስ ጓደኝነት ለፅጌረዳ ይሁን ለወንዳፍራሽ ትውሲት የምታውቀው ነገር የለም። ፅጌረዳም የነገረቻት ከኤርሚያስ ጋር የቤተሰብ ያህል ጓደኝነት እንዳላቸው ብቻ ነበር እንጂ ዝርዝር ጉዳይ ውስጥ አልገባችም። አሁን ትውሲት ወንዳፍራሽን ከመወንጀሏ በፊት የኤርሚያስን አቋም ማወቅ ፈለገች።

«ኧረ ቤተኛ ነኝ።......እንዳልኩሽ ለተወሰነ ጊዜ ገጠር በመሄዴ ከመሐላቸው ራቅኩኝ እንጂ፤ ቤታቸው ቤቴ ነው።»

«ሰውየው ግን ምን ዓይነት ሰው ነው?» አለች ጥላቻም ሆነ ፍቅር በማያሳይ አነጋገር።

«የቱ ሰውየ?.......»

«ባሏ ነዋ!......እኔ መቸም ያንተን ያህል ቀርቤ አላወቀውም። ነገር ግን ፅጌረዳን የሰራትን ስራ ሳስበው.......»

እዚያ ላይ ሳይታወቃት የጥላቻ ገጽዋን አሳየች። ኤርሚያስም አዝማሚያዋ ስለገባው መንገዱን ጠረገላት -

«አዎ፤ ለፀባቸው መንስኤ የሆነው እሱ ነው። በስተ እርጅና መቅበጥ ጀምሮ.....»

«መቅበጥ ብቻ?!........መቅለል ነው እንጂ! በላይዋ ላይ ከመወሸም ሌላ ምን ሊያደርጋት ይችላል?!.......አሁንማ ቤቱን ጥላለት ወጣች።

«ትይኝም?!......» አለ ኤርሚያስ፤ ለማስመሰል መሞከሩ ከብዶት ስራስሮቹ እየተግተረተሩ።

«ምን ታደርገው?!.....ሌላው ሌላውን ሁሉ ችላው ስትቀመጥ ጭራሹን ክወጭ መውለዱን ሰማች። ያኔ ነው ጨርቋን ጠቅልላ ከቤቱ የወጣችለ።»

«ከውጭ ወልዶ?.....»

«ያው ነው። የተረገዘ መወለዱ አይቀር። ውሽማው አርግዛለታለች። ይህን ስትሰማ ነው ፅጌረዳ የተብከነከነችው።»

«ያሳዝናል!» አለ ኤርሚያስ፤ የሆዱን በሆዱ ይዞ ጭንቅላቱን እየነቀነቀ። የትውሲት አነጋገር የ «ይሆናል» ዓይነት ጥርጣሬ እንኳ የለበትም። በአይኗ ያየችው የምታወራ ነው የምትመስለው እና፤ በተዘዋዋሪም ቢሆን የፅጌረዳን ብሶት አባባሳ ከቤቷ ያስወጣቻት ሴት መሆኗን ለመገንዘብ ኤርሚያስ ብዙ ጊዜ አልወሰደበትም።

ትንሿ ሻይ ቤት ደርሰው ሲገቡ፤ «መዝናኛ ክበቡ እስካሁን ስራ አልጀመረም እንዴ?» ሲል ጠየቃት።

«ጀምሯል እንጂ። ግን የምግብ አገልግሎት ብቻ ነው የሚሰጥበት። ለሻይ የምንመጣው እዚችኛዋ ቤት ነው። ከፈልግክ እስከምሳ ሰዓት ቆይና ልጋብዝህ......»

«የለም፤ አመሰግናለሁ። እኔ እስከዚያ ድረስ አልቆይም።

«ስዕሎችህ ናፍቀውህ እንደሆነም እንድታያቸው ብዬ ነው» ስትል በቀልድ መልክ ጎሸም አደረገችው።

«ግድለይሽም፤ ኮፒያቸው (ቅጂያቸው) ልቢ ውስጥ አለ» በማለት እሱም ቀልዱን በቀልድ መለሰላት።

ሳቀችና፤ «ሻይ ወይስ ቡና?» አለችው።

«ቡና - እንደወረደ።»

እሱን ወንበር ጋብዛው፤ እሷ ቡናውን ልታመጣለት ወደ ቲኬት ማስቆረጫው ስትሄድ፤ እንደ ልማዷ ዳሌዋን ግራ ቀኝ እያስጠረገች የኤርሚያስን ዓይኖች ሳበች።

ሰውነትዋ ላይ ልጥፍ ያለ *ሥሥ* ቀሚስ ስለለበሰች የውስጥ ሱሪዋ ቅርጽ በደንብ ይታያል። ደንደን ያለ ሰውነትዋ ከረዥም ቁመቷ ጋር ይሂዳል። ተፈጥሮ ከሰጣት ውበት ሌላ የጎዳደሉት ነገሮች በአለባበስ ተሟልተው፤ የሰውነቷ አወራረድ አንዳች መስህብ እንዲኖረው አድርገውታል። ይሄ ደግሞ ለራሷም ይታወቃታል። አንዳንድ ሰዎች ትክ ብለው ሲመለከቷት፤ «ዛሬስ ወንዶቹ መንገድ ላይ ቀሚሴን በአይናቸው ሊገልቡት ነው።» እያልች ትመፃደቃለች።......

«አመሰግናለሁ።.....አስቸገርኩሽ።» አላት፤ ኤርሚያስ በዓይኑ ሲከተላት ቆይቶ፤ ለእሱ ቡና፤ ለራስዋ ሻይ አምጥታ አጠገቡ ስትቀመጥ።

«ምንም አይደለም። እንግዳዬ እኮ ነህ።» አልችው እሷም ፍርጥም ብላ።»

«አይ ፅጌረዳ!.......ለመሆኑ ከቤቷ ወጥታ ወዴት ይሆን ይሄደችው?»

ቡናውን እያመሰል በዝግታ ወደ ጨዋታው አመራ። ትውሲትም፤ እጇን ያስገባችበት ጉዳይ፤ የምትወደው አርዕስት በመሆኑ ተከተለችው።

«ወላጆቿ ቤት ነው አሁን ያለችው። ወደ እንትን አካባቢ......»

«አውቀዋለሁ፤ አውቀዋለሁ።»

«እዚያ ነው የሄደችው። የሚያኮሩ ወላጆች እያሏት ለማን ጀቴ ብላ በቅናት ትጠበስ!?......»

«እሱስ ልክ ነሽ፤ ግን እንዲያው የነዚያን የምትወዳቸውን የሁለቱን ልጆቿን ነገር......» አለና፤ የምትለውን ለመስማት የጎድን እያያት፤ አቋረጠ።

«ባሏ ያልተጨነቀበትን ጉዳይ እሷ ብቻ ስለ ልጆቿ ብታስብ ምን ዋጋ አለው?! ከንቱ ድካም ነው! ደግሞም ራሷ ጤናማ ኑሮ ሳይኖራት ለልጆቿ ስትል መሰቃየቱ ምንም ትርጉም የለውም።......ለነገሩ እንኳ ሴት ልጇን ይዛ ነው የወጣችው።»

«ያሳዝናል......» ብሎ እንደ ገና ጭንቅላቱን በሐዘኔታ እየነቀነቀ ቡናውን ጠጥቶ ከጨረሰ በኋላ፤ «ለመሆኑ......በደንብ ተረጋግጧል?» ሲል ጠየቃት።

«ምኑ?» አለችው፤ እግሮቿን አነባብራ እንደ ተቀመጠች፤ የሻይ ብርጭቆውን ከወደቂጡ በኩ በቄንጥ ይዛ፤ ወደ ከንፈሯ በጥንቃቄ እያስጠጋች።

«ማለቴ......ሮዛ ለወንዳፍራሽ ልጅ የማርገዟን ነገር በደንብ ካልተረጋገጠ በስተቀር.......አየሽ፤ አንዳንዴ አንዳንድ ሴቶች የሚወዱትን ወንድ ለማሰር ሲሉ ብቻ ውሸታቸውን «አረገዝን» ማለት ይወዳሉ። ሮዛም እንዲህ አርጋ አስወርታ እንዳይሆን ብዬ ነው.......»

ትውሲት ወደ ከንፈሯ ያስጠጋችውን ሻይ ፉት ሳትል መለሰችው። እሷን የሚመለከት ጉዳይ በመነሳት አንዳች ስሜት ሰውነቷን ነዘራት። ይህ የኤርሚያስ አነጋገር ባልና ሚስቱን የማስታረቅ አዝማሚያ ስላዘለበት አልወደደችውም። ፅጌረዳን በሀሳቧ ለብዙ ወንዶች ስላጨቻት ወደ ቀድሞው ትዳሯ እንድትመለስ አትፈልግም።

«ምን ማለትህ ነው ኤርሚያስ?...ይችን ታህል ሳታረጋግጥ ቤቷን ጥላ ትወጣለች እንዴ?!» አለችው ኮስተር ብላ።

«አዎ፤.....ሆድ የባሰው ትንሽ ይበቃዋል። ስለኢዝ ሳታጣራ ልትወጣ ትችላለች። እንደኔ፤ እንደኔ - መቼም አንቺ የቢሮ ጓደኛዋ፤ ያው የቅርብ ጓደኛዋ ስለሆንሽ ይህን ጉዳይ ብታጣሪላት ጥሩ ነበር።»

«አጣሪቼላታለሁ።.....እምልህ፤ በግልፅም ባይሆን በተዘዋዋሪ አጠያይቄ እውነት መሆኑን ደርሼበታለሁ። ከዚያ በኋላ ነው ባሏ እንዴት ቢንቃት ነው ብዬ የበሸቅኩት።.....»

የእርግዝናውን ጉዳይ ለፅጌረዳ ያሳወቀቻት እሷ መሆኑና ልትደበቀው ፈልጋ ነበር። ነገር ግን አጠያየቁ እንድትነግርው ጋበዛት። ከዚህም ሌላ፤ በአንድ በኩል ኤርሚያስ ይህን ወሬ ከፅጌረዳ ከራሷ ሊሰማው እንደሚችል በመገመት፤ በሌላ በኩል ደግሞ ለፅጌረዳ ወገናዊ መሆኗን ማሳየቷን ኤርሚያስ የሚደግፍላት ስለመሰላት በማወቅም ሆነ ባለማወቅ እኩይ ተግባሯን ገሀድ አወጣችው።

ኤርሚያስም፤ እሁድ ሰንበት መሆኑኑን እስትነግረው ድረስ መጠበቅ አልነበረበትም። ማንነቷን በደንብ አወቀ። ማንነቱን ሳታውቅ የሰጠችው እያንዳንዷ መረጃ ልቡን እንደ እሳት እየለበለበው ጥላቻውን ያጠናክርበት ነበር። ከውስጥ

ገንፍሎ ሊወጣ የደረሰ እውነተኛ ስሜቱን ታግሎ እየደበቀ የውሸት ስሜቱ ማሳየቱን እንደምንም ገፋበት።

«ለመሆኑ ከቤቷ ከወጣች በኋላ አግኝተሻት ታውቂያለሽ?......እንዲያውም እንዴት ሆና ይሆን?»

«ሲበዛ ተከዛለች። አንድ ጊዜ ወላጆቿ ቤት ድረስ፤ አቅጣጫውን አጠያይቄ፤ ሄጄ ጠይቄአት ነበር። ሁለት ጊዜ ደግሞ በስልክ አግኝቻታለሁ። ያው ነች። የዋህ ፍጥረት! ከባሏ ስለተጣላች ዓለም የጨለመባት ይመስል፤ ቤት ውስጥ ነጠላዋን ተከናንባ ስትተክዝ ነው የምትውለው። የዓመት ፈቃድዋን ከወሰደች ወዲህ መሥሪያ ቤትም፤ ውጭም ብቅ ብላ እንኳ አታውቅም።» አለችና፤

የፅጌረዳ ሁኔታ እንዳናደዳት ዓይነት ከንፈሯን ለጥጣ ራስዋን ነቀነቀች።

ኤርሚያስም አብሯት ጭንቅላቱን ነቀነቀ።

«የወላጆቿን ቤት አወቀዋለሁ ብለሽኝ የለ?! እስቲ በናትህ ሂድና ምከራት። ምንድ'ነው እንደዚህ ራስን መጣል?! ሴት ልጅ ራሷን ከጠላች እኮ ተመልካችም አይኖራትም።......እሺ ወንድ ሊያስከትል የሚችል ውበት አላት። ዕድሜም ቢሆን ገና ናት። ሁለት መውለድ እንዲህ ይጥላል እንዴ?.....እሷ እንዲያው የዋህ ሆና ነው እንጂ፤ ባሏ እንደሆነ ኩርምት ብላ ቤት ውስጥ መዋሏን ሲሰማ አንጀቱ ቅቤ ነው የሚጠጣው። - ቅስሟን የሰበራት ነው የሚመስለው። እና፤ እባክህ ምከራት።....»

ሳይታወቅባት ኤርሚያስ ፅጌረዳን እንዲቀሰቅስላት መገፋፋቷ ነው። እንደተናገረችውም፤ አንድ ጊዜ ወላጆቿ ቤት ድረስ ሄዳ፤ ሁለት ጊዜ በስልክ ደውላ ፅጌረዳን አግኝታት ይዛት ልትወጣ ሞክራ ነበር። ፈፅሞ የማይቻል ነገር ሆነባት። የፅጌረዳ ከባሏ ተጣልቶ ከቤቷ መውጣት፤ ትውሲት ለአቶ ክብረት የገባችላቸውን ቃል ሁሉ የሚያፋጥንላት መስሏት ነበር። ነገር ግን እንዳሰበችው አልሆነም። ፅጌረዳ የውስጥ ሰላም ስላጣች፤ ከወንድ ጋር ለመዘር ቀርቶ፤ ለአንዳፍታ እንኳ ከወላጆቿ ግቢ መውጣት አልፈለገችም። የአመት እረፍቷን የወሰደችውም ለዚሁ ነው። ግቢው ውስጥ ኩርምት ብላ፤ ሰብለን ጭንና ጭኗ መሐል አስገብታ አቅፋ እንዴ ያለፈ ትዝታዋን ስታስብ፤ አንዴም ወደ ፊት ምን ሊሆን እንደሚችል ስታልም ይመሻል።

ይህም ቢሆን ትውሲትን ሙሉ በሙሉ ተስፋ አላስቆረጣትም ፅጌረዳ ቀስ በቀስ ባሏንና ትዳሯን እየረሳችው ስትሄድና አሁን የተጫናት ስሜት ሲለቃት፤ የፍላቶቷ መሣሪያ እንደምትሆንላት ተስፋዋ የፀና ነው። ያ - ጊዜ ነው የራቀባት። በፅጌረዳ ውበት የሆንለለውና ከትዳር «እስር ቤት» መውጣቷን የሰማው ወንድ ሁሉ፤ ለአማላጅነት ትውሲት ቢሮ ድረስ ሲንጋጋ የሚውልበትን ቀን በተስፋ ትጠብቃለች። - መጀመሪያ ግን አቶ ክብረት!.....

«ምነው ፈዘዝክ?.....»

«ፈዘዝኩ እንዴ?.......»

ኤርሚያስ በሀሳቡ ከፍኖ፤ ዓይኖቹን ቡዝዝ አድርጎ ሲመለከታት፤ የትውሲት ቅንዝረኛ ልብ ሌላ፤ ሌላ ያስብ ጀመር። ውበቷ ወይም ቁመናዋ ያፈዘዘው መስሏት፤ እንደ ልማዱ ቀሚሷን መነስነስ፤ ዳሌዋን መነቅነቅ ከአንገት በላይ ማክላላክት አማራት።

ኤርሚያስ በተቀመጠበት ገመገመችው። ዙሪያውን በፂሙ የተከበበው ሰልካካ ፊቱና፤ ጠልቀው የሚታዩት ውብ ዓይኖቹ ጎልትወ ታዩዋት። ‹በተለይ ይህን ጫካ ፂሙን ቢላጭው!› ስትል አሰበች። ከፂሙ ጥቁረት ጋር ንፅር የሚፈጥርውን በረዶ መሣይ ጥርሱን ግን ለማየት አልቻለችም። - ቢኮረኩሩት እንኳ ፈገግ ይላል እንጂ ጥርሱን ገልጦ አይስቅም። ከረዥም ቁመቱ ጋር የማይጣጣመው ቅጥነቱን አልወደደችለትም። አለባበሱም አልማረካትም። ብቻ፤ ‹ምን ቸገረኝ አብሬው አልኖር!› የሚለው ስሜቷ ያፅናናታል።

አንድ ቀን ትማስ ቀርቄን ቢቀምስ እኮ አንድ ስዕል ቀርቶ ሶስት አራት ቀን በአንድ ምሽት ስሎልኝ ያድር ነበር፤ አለች በልቧ። ሰዓሊውን ምርኮኛዋ አድርጋው፤ ከራሷ አልፋ ተርፋ፤ ሴት ጓደኞቿን ሁሉ እያመጣች ‹እስቲ ይቺን ደግሞ ሳላት......› እያለች ስታስላቸው በሀሳቧ ታያት።.....

በቀን ህልሟ መደናበሩን አልገፋችበትም። የሻይ ሰዓት ደርሶ ሰራተኞቹ እየተንጠባጠቡ ወደ ሻይ ቤቷ ውስጥ መጡ ትውስቲ ቶሎ ለመውጣት ተነሳች። ከኤርሚያስ ጋር ሆኖ አንዳንድ ሰዎች እንዲያይዋት አልፈለገችም።

«ኧረ እንዲሂ፤ ቢሮዬን ባዶ ትቼ......ስልክ እንኳ ቢደወል የሚያነሳ የለም፡፡» አለችው፤ ኤርሚያስ በድንገተኛ አነሳሷ ሌላ እንዳያስብ ለማወናበድ።

የፈራችው ግን አልቀረም። ዓይናቸውን ለመሸሽ የፈለገችው ሁለት ሰዎች ፊትና ኋላ ተከታትለው ወደ ሻይ ቤቱ ሲመጡ በርቀት ተመለከተቻቸው። እነሱም ስላዩዋት መንገድ ብትጀምርም፤ ጭራሹኑ መሸሽ አልቻለችም።

መጀመሪያ የመጣው ዘገየ ነው። ስለተኳረፉ መሬት፤ መሬት እያየች ዘግታው አለፈች። ኤርሚያስና ዘገየ ቆም ብለው ከተጨባበጡ በኋላ ተጠቃቅሰው ቶሎ ተለያዩ።

«ከዚህ ጋር ደሞ......የት ትተዋወቃላችሁ?» አለችው፤ ኤርሚያስ ወደ እሷ ሲመጣ ጠብቃ - ፊቷን እንዳጨማደደች።

«እዚሁ ለዚህ ለሥዕል ሥራ የመጣሁ ጊዜ ነው የተዋወቅኩት። አላት፤ እሱም ሌላውን ሁሉ ዋጥ አድርጎ።

«ሰው አይምሰልህ! - እርኩስ ነው!» አለችው፤ ጥላቻዋን ሊገልፅ በሚችል የመፀየፍ ስሜት ተኮመታትራ።

ኤርሚያስ ምንም አልመለሰም። አሁንም ስሜቱን ዋጥ አድርጎ ዝም አላት።

ትንሽ እንደተራመዱ ደጀኔ ደግሞ እየቀረበ መጣ። ምንጊዜም አንገቱን አቀርቅሮ፤ ወደ አንድ ጎን አጋድሎ ነው የሚራመደው።

ምንም ነገር ማየትና መስማት አይፈልግም። የትውሲት ነገር ከሆነ ግን ሰውነቱ ሁሉ ዓይንና ጆሮ ይሆናል። አሁንም ከርቀት አይቷታል። ከወንድ ጋር ስለሆነች ቅናቱ ተነስቶበት፤ ጅማቶቹ እየተግተረተሩ፤ ዓይኑን ሰበር አድርጎ አልፏት ሊሄድ ፈለገ። አዝማሚያው ስለ ገባት ትውሲት በልቧ፤ ‹አይ የኒ በግ!› አለችና ስሙን ጠርታ አስቆመችው -

«ደጁ!.....»

እንዳላያት ሁሉ፤ ጥሪዋ እንደተደናገጠ ሁሉ፤ ግንባሩን ኮስኩሶ ቀና አለ።

«ና!......ሰው ላስተዋውቅህ።»

ይሉኝታ ይዞት መጣ።

«ከኤርሚያስ ጋር ተዋወቁ።...ሰዓሊ ነው። ያንን መዝናኛ ክበብ ውስጥ ያለውን ስዕል ሁሉ የሠራው እሱ ነው።» አለችው፤ በዓይንና የተኮማተረ ፊቱ ላይ የሆነ ነገር እያነበበች።

ግንባሩን ሳይፈታ እጁን ዘርግቶ፤ «ደጀኔ» በማለት ራሱን አስተዋውቆ ተጨባበጡ።

እና፤ ወዲያው ዘወር ብሎ መንገዱን ቀጠለ።

«አይ እዳዬ!....በኋላ እንግዲህ ይነጫነጭብኛል» አለች ከአጠገባቸው ከራቀ በኋላ።

«ምነው?.....ለምን?» አላት ኤርሚያስ።

«ቅናት ነዋ!......ከናተ ጋር ስላየኝ ይሄኔ በንዴት ጦፏል።»

«እ - እጮኛሽ ነው እንዴ?» አላት እንዳላወቀ ሆኖ።

«ኤ - ጭ!.....እንዲያው ፈርዶበት ነው እንጂ። ጥሎበት - አቅፎኝ ተኝቶም ሳይቀና አይቀርም። እኔ ደግሞ ዕድል ብሎብኝ፤ የሚገጥመኝ ወንድ ሁሉ ቀናተኛ ነው። ....»

«እኔ የለሁበትም።.....በይ ልሰናበትሽ።» አላት ኤርሚያስ በቀልድ ቅላፄ።

«ምነው?!......ወንድ አይደለህም እንዴ?!»

«ብሆንም.....በአግባቡ የምሞት ወንድ ነኝ። ይልቅ ቻዎ!»

«ቆይ እንጂ፤ እስከ ውጭ በር ድረስ ልሸኝህ።»

«መኪናዬ በዚህ በኩል ነዋ ያለችው።»

«እሺ እንግዲያው እስከመኪናህ ድረስ ልሸኝህ።» ብላ ተከተለችው።

«......ስማ እንጂ»

«አቤት......»

«የስዕሉን ነገር እንዳለፈው ጊዜ እንዳትረሳ.......እሺ?»

ይህንኑ ለማስታወስ እንደተከተለችው ገባው።

«አልረሳም፤ ግድ የለሽም።»

«ታዲያ ጉርድ ፎቶግራፌን ልስጥኃ?......»

«የለም፤ የኔ አሠራር የፎቶ ግራፍ ቅጂ አይደለም። - ፊት ለፊቴ ትቀመጪና እያየሁ ነው የምስልሽ። ቢያንስ ሁለት ሰዓት ያህል ሳትነቃነቂ ለመቀመጥ መቻል አለብሽ።»

«ይሄማ እስረኝነት ነው።.....ግዴለም ይሁን ብቻ!.....ታዲያ መቼ ነው አስቀምጠህ የምትስለኝ?......»

«ሲመችኝ እኔ እነግርሻለሁ። አድራሻሽን ብትሰጪኝ?......»

ስልክ ቁጥሯን ነግራው በማስታወሻ ደብተሩ ላይ ፃፈ።

«አደራህን እንግዲህ። ደሞ በትልቁ ነው የምትስለኝ። የምትፈገውን........ገንዘብም ቢሆን እከፍላለሁ።»

ተሰናብቷት መኪናው ውስጥ ገባ። መኪናው ባትሪዋ ደክሞ ስለ ነበር ቶሎ ልትነሳለት አልቻለችም። እያላዘነች ትጠፋለች።

«እንግፋ እንዴ?» አለችው ትውሲት መለስ ብላ፤ በምፀት ድምፅ።

«ግድለየም ትነሳለች።.......» ብሎ ቁልፍ መኮርኮሩን ቀጠለ።

ትውሲት መስታወቱ አጠገብ ቆማ ትንሽ አከላላች። ኤርሚያስ እንዲያያት ሆና ዳሌዋን እየነቀነቀች፤ በመኪናዋ ዙሪያ ተወዘወዘች።

መኪናዋ እንደ ምንም ስትነሳለት ኤርሚያስ፤ «ቤሽቲያ!» አለና ወደ ፊቱ በረረ።

መኪናዋን የተሳደበ መስሏት ትውሲት ከት - ከት - ብላ ሳቀች።

ወደ ሻይ ቤት የሚያልፉት ሰዎች አሣሣቋ ጆሮዋቸውን ጠልፏቸው ትክ ብለው ተመለከቷት።

እሷ ግን ሰዎቹን ከምንም አለቆጠረቻቸውም። «ደሞ ለሰው!» በምትለው የአረማመድ ስልቷ ወደ ቢሮዋ አመራች። - ዳሌዋን በስልት አንዴ ወደ ግራ አንዴ ወደ ቀኝ እያነጠረች፤ በዚያው ስልት ሚዛኗን ጠብቃ እግሮቿን በየተራ እየወረወረች -

ደ - ሞ- ለ - ሰ - ው !.....

ማምሻውን ኤርሚያስ ሶስቱን ሕፃናቶች አሰባሰበ። ባልና ሚስቱ ከጠጣሉ በኋላ ዳኒና ሰብለን

አልፎ አልፎ እያገናኘ ወደ ሽርሽር በመውሰድ ጣፋጭ ይገዛላቸው ስለ ነበር፤ ዛሬም ተቃውሞ አልተሰነዘረበትም።አባትና እናትየው ቢቃወሙ እንኳ፤ ልጆቹ አሻፈረን ስለሚሉ፤ ከኤርሚያስ ጋር ወጥቶ መዝናናት መብታችወ ሆኗል።

ከትምህርት ቤት እንደ ወጡ፤ ዘኒና ዳኒን እቤቷ ድረስ ይዛው መጣች፤ ኤርሚያስ ደግሞ ሰብለን ከአያቶቿ ቤት ሄዶ አመጣት።

«አቀማመጣችሁ በቁመት እምሆን እንዳለበት ብዙ ጊዜ ነግሬያችሁ ነበር። ረሳችሁት እንዴ?» አላቸው ኤርሚያስ፤ የመኪናውን የፊት ወንበር ለመያዝ ሲሻሙ አይቶ።

ሰብለ ፍላጎቷ ስለተሟላላት በደስታ እየቦረቀች ከፊት ተቀመጠች። ዘኒና ዳኒ ከኋላ ተቀመጡ።

«ዛሬ አዲስ መዝናኛ ቦታ አስያችኋለሁ።» አለ ኤርሚያስ ጉዞ ከጀመሩ በኋላ።

«የት ነው?» አለችው ዘኒ።

«የት ነው?» ሰብለም ዘኒን ተከትላት ጠየቀች።

«አታውቁትም እኮ፤ ዛሬ ላሳያችሁ ነው።»

«ሩቅ ነው እንዴ ኤርሚ?.....ሳይጨልም ወደ ቤት መመለስ አለብን እኮ። ትላንትና ከእልፍነሽ ጋር አምሽተን ገብተን፤ ወንዴ ተቆጥቷል።» አለ ዳኒ በሚያሳዝን ድምፅ።

«የት ሂዳችሁ ነበር ያመሻችሁት?»

«ከትምህርት ቤት ስወታ ከእልፍነሽ ጋር ተደብቀን ትልቁ አባባ ቤት ሄደን ነበር - ፅግዬን ልንጠይቃት። እዚያ ስንጫወት መሽብን።

«ፅጌረዳ ጋ መሄዳችሁን ለወንዳፍራሽ ነገራችሁት እንዴ?»

«አአይ፤ ተደብቀን እኮ ነው እኔና እልፍነሽ የምንሄደው። ወንዴ ከሰማ ይቆጣል። ያለፈው እሁድ ለታ ፅግዬ ጋ እንደምሄድ ስነግረው ጊዜ ከለከለኝ። ከዚያ በኋላ ሳንነግርው እየተደበቅኩ ነው የምሔደው። አንድ ቀን ለትም ደሞ ሄጃለሁ።»

«ዳኒ እኮ ብዙ ከን እኛ ጋ መትቷል።» አለች ሰብለም ጣልቃ ገብታ።

«አይዞህ፤ ከእኔ ጋር መሆንህ ካወቀ ብታመሽም አይቆጣህም።» አለው ኤርሚያስ፤ በልቡ እያዘነ።

በአባትና እናት እልሽኝነት ምክንያት ወንድምና እህት በድብቅ እየተሰራረቁ መተያየታቸው አናዶት ውስጥ ውስጡን እየበገነ በዝምታ ሲሾፍር የዘኒ ጥያቄ ደግሞ አባነነው -

«ኤርሚ.......ጋሽ ወንዳፍራሽና እትዬ ፅጌረዳ በቃ እንደ ተጣሉ መቅረታቸው ነው?» አለችው እዝን ብላ፤ ከጀርባው ወደ ፊት ኤርሚያስን ለማየት፤ በሰብለ መቀመጫ በኩል እየተንጠራራች።

ለጥያቄዋ መልስ እንደጓጉ ሁሉ፤ ሰብለና ዳኒም ዓይኖቻችውን ኤርሚያስ ላይ ያቁለጨልጩ ጀመር።

«ግድየለሽም፤ እንደ ተጣሉ አይቀሩም።......እልሀቸው ሲበርድላቸው ይታረቃሉ።» አለ ጥርሱን እያንቀጫቀጨ።

«መቼ ነው.....እ....ም...ሚበልደው?» አለችው ሰብለ «ዕልህ» የሚለውን ቃል እምድገም አቅቷት። - የእልህ መብረድ ግን ወላጆቿን ሊያስታርቅ እንደሚችል ከኤርሚያስ አነጋገር ገብቷት።

ኤርሚያስ መልሱ ችግሮት ሲያምጥ ዳኒ ደግሞ ሌላ ጥያቄ ሰነዘረ -

«እልህ ምንድ'ነው?»

»እልህ አታውቅም እንዴ ዳኒ?!....እንትን ነዋ!.....ሰይጣን።» አለችው፤ ከጎኑ የተቀመጠችው ዘኒ በማስረዳት አይነት ትከሻውን ያዝ አድርጋ።

«ብራቮ! የኔ ርግብ፤ ሙከራሽ ጥሩ ነው። ለመልሱ ቀርበሻል።» አላትና ኤርሚያስ ፊቱን ለአፍታ ያህል ዘወር አድርጎ ፤ «ሰይጣን ምንድን'ነው?» ሲል ጠየቃት።

«እንትን ነዋ!......እ - እንትን.......»

«ምን?......»

«ሠይታን!» አለች ሰበለ ጣልቃ ገብታ።

ዘኒ አዕምሮዋ የሚያስበውን ምስል ወይም ስለ ሰይጣን የሰማችውን ነገር በቃላት መግለፅ አቅቷት ዓይኖቿን ስትጨፍንና ስትገልጥ ቆየች።

«ስለ ሰይጣንና ስለ ዕልህ መናፈሻ ውስጥ ከተቀመጥ በኋላ እኔ እነግራችኋለሁ።» አለ ኤርሚያስ፤ የልጆቹ ጨዋታ ከተልዕኮው ጋር የሚገናኝ አንዳች ስሜት ቀስቅሶለት።

በሹሮ ሜዳ መንገድ ወደ ተሰራው አዲስ የመናፈሻ ስፍራ ወሰዳቸው። ቦታው ፀጥታማና ለግል ጨዋታዎች ከመሆኑም በላይ ሙሉ የመዝናኛ አገልግሎት ይሰጥበታል።

«እንዴት ነው? ጥሩ መናፈሻ አይመስላችሁም?» አላቸው፤ ኤርሚያስ ከአንዱ ጥግ በኩል መቀመጫውን ከያዙ በኋላ።

«ቆንጆ ነው።» አሉ ሶስቱም በአንድ ድምፅ። አሳላፊው መጥቶ ከፊታቸው ቆመ።

ዘኒና ዳኒ አይስክሬም አዘዙ። ሰብለም እነሱን ተከትላ «አይክሬም።» አለች።

«ለኔ አንድ ቡና» አለ ኤርሚያስ።

አሳላፊው ከአጠገባቸው ሲርቅ፤ ኤርሚያስ ሰበካውን ቀጠለ። መቼም ነገር ይዞ መቆየት አይሆንለት፤ ስሜቱ ከውስጥ ይገፈትረዋል።

«እንግዲህ ቅድም የጠየቃችሁኝን ጥያቄ አሁን ልመልስላችሁ።......» አላቸው፤ አዕምሮአቸውን ወደሱ ለመሳብ ሶስቱንም በየተራ እየተመለከተ፤ «ዕልህ ማለት ምን ማለት እንደሆነ በምሳሌ ላስረዳችሁ።.....ለምሳሌ አንድ ሰው መሸነፉን ልቡ እያወቀው ‹አልተሸነፍኩም› ብሎ ከአቅሙ በላይ ሲፍጨረጨር፤ ጥፋቱን ልቡ እያወቀ ለምታረም ዝግጁ ሳይሆን ሲቀር፤ ተው የሚሉትን፤ የሚጎዳውን ነገር ላለ መተው ድርቅ - ግትር ሲል «እልህ ተናንቆታል» ይባላል። እና ደግሞ እልህ ምን ጊዜም ወደ መጥፎ ነገር ወደ ጥፋት የሚያመራው። ምክንያቱም በዕልህ ወቅት ማንኛውም ሰው የዕውር ድንበሩን ወደ ጥፋት መጋለብ ነው እንጂ፤ ሁኔታዎችን ማመዛዘን አይፈልግም። ጆሮው ክፍት ይሆናል - ነገር ግን አይሰማም። ዓይኑም ግልፅ ይሆናል - ነገር ግን አያይም። እልህ ብዙ ህይወት አጥፍቷል......ብዙ ጦርነቶች ከፍቷል.....ብዙ የጥፋት እሳት አቀጣጥሏል።

«ለምሳሌ፤ አንዳንድ ህፃናት ወላጆቻችው ‹ታድርጉ› የሚሏቸውን ለማድረግ ወይም ‹አትንኩ› የሚሏቸውን ለመንካት መሬት ላይ ወድቀው እየተንፈራፈሩ ሲያለቅሱ አይታችሁ ይሆናል።......የህፃናቱ ካለማወቅ የመጣ ሲሆን፤ የአዋቂው ደግሞ ከግትርነት የመነጨ ነው። የሁለቱም መንገድ ግን ያው ጥፋት ነው። ይሄ ከአውሬነት ይዘነው የመጣነው፤ አሁንም ከአውሬዎች ጋር የምንጋራው ባህሪይ ነው። ለምሳሌ ውሾች ሲጮህባችሁ በዱላ ስትከላከሉት ወይም ስታስፈራሩት ይብሱን ዕልህ ይይዘውና እያጉዋራ ዱላውን ለመንከስ ይታገላል፤ ይፍጨረጨራል - ዱላው ቀጥቅጦ መግደያው መሆኑን እያወቀ።......»

የዋህዋ ዘኒ የኤርሚያስን ተመስጦ አልተከተለችውም። ይልቁንም አቀራረቡና ምሳሌ አሰጣጡ የኮረኮራት ይመስል አሳቃት። ሰብለም እሷን ተከትላ ትንንሽ ጥርሶቿን እያሳየች ሳቀች። ትንሹ ቆቅ ግን ኤርሚያስ የሚናገረውን በንቃት ወደ አዕምሮው እየመዘገበ ነበር።

«አሁን ያልከው አልገባኝም ኤርሚ......እኛ ሰዎች ነን እንጂ አውሬዎች ነን እንዴ?.......» አለ ዳኒ እንደ አዋቂ ግንባሩን ኩምትር አድርጎ።

«አዎ ዳኒ፤ ከብዙ ዘመን በፊት አውሬዎች ነበርን። ቀስ በቀስ ነው ወደ ሰውነት የተለወጥነው። ብዙ የአውሬ ባህሪያችንን በትምህርቱ፤ በሥልጣኔ፤ በዕድገት አስወግደን ሰው ሆነናል። ሆኖም ፈጽመው ያልጠሩ አንዳንድ ድብቅ የአውሬ ባህሪያት አሉብን። እነኒህ ድብቅ የአውሬ ባህርያት ናቸው እርስ በእርስ የሚያፋጁን.....የሚያስተላልቁን......የሚያስተናንቁን!.......»

ኤርሚያስ አርዕስተ - ነገሩን ውስጥ እየሰመጠ በሄደ ቁጥር ፈገግ ማለቱን እንኳ ረስቶት፤ ከአዋቂዎች ጋር እንደሚያወራ ሁሉ፤ ገጹ ስሜቱን ያሳይ ነበር። ልማደኛ ጣቶቹም ፂሙን መቆፈር ጀምረዋል። አሳላፊው የታዘዘውን ነገሮች ይዞ ሲመጣ አይቶ ባያቋርጥ ኖሮ በራሱ ንግግር ውስጥ ሰምጦ ቀርቶ ነበር።

አሳላፊው አቅርቦ ከተመለሰ በኋላም ኤርሚያስ ሀሳብ ውስጥ ገብቶ፤ ቡናውን ዝም ብሎ ማማሰሉ ቀጠለ።

«በቃህ እንጂ ኤርሚ፤ ቡናው ይቀዘቅዝብሃል።» አለችው ዘኒ፤ ድርጊቱን ተከታትላ። መኖሪያ ቤቱም ውስት ሀሳብ ይዞት አንዳንድ እንገር ሲረሳ አስታዋሹ እስዋ ናት። የረሳውን እንገር አስታውሳው። «......አንቺ ባትኖሪልኝ እኮ!......» ሲላት ደስ ይላታል።

አሁንም ፤ «እሺ የኔ አስታዋሽ.......» አላትና ቡናው ማግ - ማግ ማድረግ ጀመረ።

ልጆቹ አይስክሬሙን ሲሉ ለአፉ ያህል፤ «እንዴት ነው? ጥሩ ነው?.......» እያላቸው፤ ውስጥ ውስጡን ግን፤ የጀመረውን አርዕስት እንዴት ከሚፈልገው ጉዳይ ጋር እንደሚያያላቸው ያሰላስል ነበር።

«አሁን እንግዲህ መጀመሪያ ወዳነሳነው ነጥብ እንሂድ.....» አላቸው ትንሽ ሲያስብ ቆይቶ፤ «ወንዳፍራሽና ፅጌረዳ ልጆቻቸውን በጣም ይወዳሉ። እነሱም እርስ በርስ ይዋደዳሉ። ሁለቱንም ለየብቻ አነጋግሬያቸው ይህን ለመታዘብ በቅቻለሁ። አሁን የመነጣጠላቸው ነገር እልህ ነው። ወንዳፍራሽ ጥፋቱን አምኖ ይቅርታ እንዳይጠይቅ እልህ ተናንቆታል። ፅጌረዳም ብትሆን ለጊዜው ትናደድ እንጂ በዚህ በቀላል ጉዳይ ያንን መሣይ ትዳሯን እስከመጨረሻው ማፍረስ አፏም ባይሆን ልቧ አይፈልግም። ነገር ግን ወንዳፍራሽ እግሯ ስር ቀድቆ ‹ማሪኝ› እንዲላት እልህ ይዞአታል። ይህ እልህ ቤታቸው ውስጥ በርዶ እንዳይቀር የሚያባብስ ሰይጣን ደግሞ ከውጭ አለ።......»

«ሰይጣን ምን ማለት እንደሆነ እነግራችኋለሁ ብለኸን ነበር እኮ.....» በማለት ዳኒ አቋረጠው።

«ረሳሁት ልጄ፤.......አዎ፤ ሰይጣን ማለት፤ ክፉ፤ ለሌላው ጥሩ የማያስብ፤ ሸረኛ በመጥፎ ተግባሩ የታወቀ በጥሩ ሰዎች የተጠላ ማለት ነው።......»

«መልኩ ግን እኔም አወቀዋለሁ።» አለች ዘኒ ጣልቃ ገብታ ውብ ዓይኖቿን ከኤርሚያስ ላይ ሳትነቅል።

«የምኑን?......የሰይጣኑን መልኩ?!....በይ እስቲ ንገሪን ደሞ ምን ዓይነት ነው?» አላት ኤርሚያስ ፍርጥም ብሎ።

«መልኩ አስጠሊታ፤ ፊቱ ጭምድድ ያለ፤ ትላልቅ ጥርሶች ግጥጥ ያሉ፤ ሁለት ቀንድ ያለው ነዋ!» አለች የእናቷ፤ የወይዘሮ ፀሐይ፤ የነፍስ አባት የነገሯትን እየስታወሰች።

«ሠይታን ያስፈላል።» አለች ሰብለም የዘኒን መግለጫ ስትከታተል ከቆየች በኋላ ፊቷን አጨማዳ።

«ማነው ለሰይጣን እንዲህ ዓይነት ሥዕላዊ መግለጫ የሰጠሽ?» አላት ኤርሚያስ፤ በልቡ ማን ሊነግራት እንደሚችል እያወቀ።

«አባባ ቄሱ ናቸው። የእማዬ የነፍስ አባት።»

«እሳቸው ሰውዬ ስንት ቀን ነው የሚያታልልሽ ዘኒ?!.....ውሸታቸውን ነው። ሰይታን የሚባል እንዲህ ዓይነት ልዩ አስደንጋጭ ፍጡር የለም።»

«ታዲያ ሰይጣን ምን ይመስላል?»

«እኔንም፤ አንቺንም፤ ሰብለንም፤ ዳኒኤንም ሊመስል ይችላል። ሰይጣንነት በተግባር እንጂ በመልክ አይደለም። መጥፎ የሚሰራ ሰው ሁሉ ሰይጣን ነው።.......»

«የሠይጣን መኖሪያ እዚሁ ምድር ላይ ነው ማለት ነው?»

«ታዲያስ! ዘኒዬ.....»

«አባባ ቄሱ እንደነገሩኝ ከሆነ ግን መልአከት የሚኖሩት፤ ሠማይ ቤት ገነት ውስጥ፤ ሲሆን፤ ሰይጣን የሚኖረው ግን ሲዖል ውስጥ ገሀነም ውስጥ መሆኑ ነው።»

«ይኸውልሽ ዘኒ፤ አባባ ቄሱ ለመኖር መዋሸት አለባቸው፤ ሌላ ስራ የላቸውም። ሌላ የእንጀራ ምንጭ የላቸውም። የሚነግሩሽ ሁሉ እሳቸው ያላዩትን፤ ላንቺም ሊያሳዩሽ የማይችሉትን ነገር ነው። እናንተ ደግሞ አዲስ ልጆች በመሆናችሁ፤ የወደፊት ፈላስፋዎች፤ ተመራማሪዎች፤ ዶክተሮች፤ ስለምትሆኑ በማይታይ ወይም በማይጨበጥ ነገር ላይ ተሰብካችሁ የማይታይ እንገር አምላኪ መሆን የለባችሁም። .......»

«እኔ ዶክተል እሆናለሁ።» አለችው ሰብለ፤ ከአፉ አቋርጣ፤ ወንበሩ ላይ እየተንጠለጠሉ እግሮቿን በጨዋታ ስሜት አያወዛወዘች። ‹ዶክተር› ሲባል ሁልጊዜ ትዝ የሚላት ሆስፒታል ውስጥ ያየችው ነጭ ጋዋን የለበሰ፤ ባለ መነፅር ሐኪም ነው። ለሕጻናት መጫወቻ እያሳየ ሰለ ሚያክም ወድዳዋለች።

«እሺ የኔ ቆንጆ! የፈለግሽውን ትሆኝያለሽ።.....» አለና ኤርሚያስ ገለፃውን ቀጠለ፤ «እና እናንተ የማይታይ ነገር የምትፈሩ ከሆነ፤ ማወቅ መመራመር መፈላሰፍ አትችሉም። ሲዖልም ሆነ ገነት የሚባሉት ነገሮች ያሉት እዚሁ የምናየው ምድር ላይ ነው። መጥፎ፤ አሰቃቂና መራራ ኑሮ የሚካሄድባቸው ቤቶች ሁሉ ሲዖል ናቸው። ጥሩ፤ የተከበረና የተፈቀረ ኑሮ የሚካሄድባቸው ቤቶች ገነት ናቸው። ለምሳሌ የነዳኒ ቤት ለብዙ ዓመታት ገነት ሆኖ ቆይቷል። ምክንያቱም በወንዳፍራሽ እና በፅጌረዳ

በልጆቻቸው መካከል ፍቅርና መከባበር ነግሶ ሰላማዊ ኑሮ በመኖራቸው ነው። ወንዳፍራሽና ፅጌረዳ ተጣልተው ከቀሩ፤ ዳኒና ሰብለ ተለያይተው ከኖሩ፤ ያ የዱሮው ፍቅርና ሰላም ከጠፋ ግን ሲያል ይሆናል። ስለዚህ ቤቱ ሲያል እንዳይሆን ወንዳፍራሽና ፅጌረዳ ታርቀው የዱሮው ሰላም መመለስ አለበት ማለት ነው።.....»

ዳኒ የሰማውን በሙሉ አዕምሮው ውስጥ መዘገበ። አንዳንዶቹ የኤርሚያስ አነጋገሮች ቢከብዱትም መሠረታዊ ጭብጦቹ አላመለጡትም። የዳኒ በአንክሮ ማዳመጥና በአትኩሮት መመልከት በኤርምያስ ልብ ውስጥ ተስፋ ስለ ረጨለት፤ ይበልጥ ወደ ደቀመዝሙሩ ጆሮ እየተጠጋ ንግግሩን ቀጠለ -

«እንግዲህ ወደ ቁም ነገሩ ልመለስና.... የፅጌረዳ እና የይወንዳፍራሽ ፀብ ያባበሰችው አንዲት ሴት ሰይታን።......»

«ይችህን ሰይጣን ሴት እኔ አውቃታለሁ።» አለ ዳኒ፤ በድንገት ግልግ ብሎት፤ የልጅነት ፊቱ በቁጣ እየተነፋፋ።

ዳኒ ሲቆጣ ወይም ሲያዝን የዘኒም ስሜት አብሮ ይለዋወጣል። አሁንም ቁጣው ሆዷን አባብቶት ትክዝ ብላ ዓይን - ዓይኑን ታየው ጀመር።

«ማን ናት እሷ?» አለው ኤርሚያስ አስገርሞት።»

«ሮዛ ናታ! በደንብ አውቃታለሁ።......ሽጉጥ ቢኖረኝ ተኩሼ እገድላት ነበር!» አለ፤ ከፈሩን ጣል አድርጎ።

«ሎዛን በሽጉት ግትል!......» አለች ሰብለም የዳኒን ስሜት ተከትላ።

ሁለትም ህፃናት ሮዛን በስም እንጂ በመልክ አያውቋትም። ነገር ግን ከጥላቻቸው ብዛት፤ ስሙና ባነሱ ቁጥር በዓይነ የሚያውቋት ሆኖ ይሰማቸዋል።

ኤርሚያስ ሮዛን ካነጋገራት ጀምሮ አኳኋኗን አይቶ ከጥላቻ ይልቅ ሐዘኔታ አድሮእብታል። በፊትም ቢሆን የጥቅምና የሸር ሰው ያለ መሆኗን ከወንዳፍራሽ ሰምቷል። የበለጠ ያወቃት ግን በዚያ በጭለማ ለወንዳፍራሽ ያላትን ፍቅር እየተርገፈገፈች ስትነግረው ነው። እና፤ በኤርሚያስ አመለካከት ሮዛ የክፋት የምቀኝነትና የተንኮል ሰው አይደለችም። የፍቅር ሰው አንት። ፍቅሯ (በማይሆናት)

በማይገባት ሰው ላይ በማረፉ ታሳዝናለች እንጂ አትረገምም። ሁኔታውን በስሜታዊነት ከተመለከቱት የሮዛ ተግባ ፀያፍ ሊመስል ይችላል። ህጉም ቢሆን «የሰው ባል በማባለግ......» ሊቀጣት ይችላል። ነገር ግን የሮዛ ውስጠ ባህሪያት ፍቅር እንጂ ተንኮል አዘል ያለ መሆኑ ለአመዛዛኝ ህሊና ግልፅ ሆኖ ይታያል።......ታዲያ ይህን እምነት ጠምቆ፤ ህፃናቱ በሮዛ ያላቸውን ጥላቻ መፋቅ እንዴት ይቻላል?!.....ህፃናቱ ስሜታዊ ናቸው! ኤርሚያስ ዋሽቶም ሆነ ቀበጣጥሮ፤ ልጆቹ ጥላቻቸውን እንዲፍቁ ለማድረግ ሞከረ -

«ተሳስታችኋል ዳኒ። ሰይጣኗ ሮዛ አይደለችም። ሌላ ትውሲት የምትባል ሴት ነች።......»

«አይደለችም ኤርሚ። ብዙ ጊዜ ፅግሽ ስትናገር ሰምቼአለሁ። ከወንዴ ጋር ያጣላቻቸው ሮዛ ነች።......»

«ቆይ እኮ አዳምጠኝ ዳኒ። ለመሆኑ ትውሲትን ታውቋታላችሁ?» አላቸው፤ ቅንድቡን ሸብሸቦ ወደ ሶስቱም እየተመለከተ።

«የት ነው ያለችው?» ስትል ዘኒ ጠየቀች።»

«ከፅጌረዳ ጋር አንድ ቢሮ ውስጥ ነው የምትሰራው።»

«እኔ አላውቃትም።»

«እኔ አውካትም።» አለች ሰብለም እንደቅድም እግሮቿን በተንጠለጠሉበት እያወዛወዘች።

«እ - እ! እኔ አውቃታለሁ። ከፅግሽ ጋር መስሪያ ቤቷ ሂጄ ሁለት ቀን አይቻታለሁ።» አለ ትንሹ ቆቅ።

ሰብለ ጠረጴዛውን በሁለት እጆቿ እየደበደበች፤ «ዳኒ አወካት!......» ብላ «ብራቦ» የማለት ያህል ጮኸች።

«በጣም ጥሩ። እንግዲህ ትውሲትን ካወቅካት፤ ሰይጣኗ እሷ መሆኑና ላስረዳህ። ለምሳሌ ያህል «ኦቴሎ» የተባለውን ቴአትር ሶስታችሁም አይታችሁታል አይደል?» አላቸው። - ከጥቂት ወራት በፊት እሱ ራሱ ነበር የጋበዛቸው።

ሶስቱም በአዎንታ ራሳቸውን ነቀነቁ።

«.....እያዳያችሁት፤ ኦቴሎ የሚወዳትን ዴዝዴሞናን የገደላት ኢያጎ የነገረውን ሰምቶ ነው። እዚያ ቲያትር ላይ ሰይጣኑ ማነው?»

«ወቴሎ!» አለች ሰብለ እየተኮላተፈች፤ «ወቴሎ....ግትል አደለጋት።» አለች፤ እንደገና ቲያትሩ ላይ ያየችው ነገር ዓይኗ ላይ እየመጣ።

«ዳኒ፤ እስቲ አንተ መልስልኝ።...... እዚያ ቲያትር ውስጥ ውሸታምና ተንኮለኛ ማነው?»

«ኢያጎ ነው።» አለ ዳኒ።

«በጣም ጥሩ። አሁንም አየህ፤ ፅጌረዳና ሮዛ አይተዋወቁም። ፀባቸውን የፈጠረችው ትውሲት ነች። አባትና እናታችሁም የተጣሉት ይህችው ሰይጣን መሐላቸው ገብታ ነው። ሁልጊዜም ቢሆን ወዳጅ መስሎ፤ ቀርቦ የሚያጠቃ ጠላት አደገኛ ነው። ስለዚህ ነው የትውሲት መጥፎነት ያልታወቀባት።......»

ዳኒ በሮዛ ላይ ያሳደረውን ከፍተኛ ጥላቻ መፋቅ ያለመፋቁን ከግንባሩ ማንበብ የሚችል ይመስል፤ ኤርሚያስ ንግግሩን አቋርጦ ትክ ብሎ ተመለከተው። ዳኒ በፊት ከእናቱ የሰማውን አሁን ኤርሚያስ የሚነገረውን ተምታተውበት ግንባሩን እንደቋጠረ ቀርቷል።

«ትውሲት ሰይታን! - ሎዛ ሰይታን!» እያለች ሰብለ ቀበጣጠረች።

«ሌላው እንገር ደግሞ.....» አለ ኤርሚያስ «ቅድም እንደነገርኳችሁ፤ ወንዳፍራሽ እና ፅጌረዳ እናንተን ልጆቻችውን በጣም ይወዷችኋል። እናንተም እነሱን በእኩል ዓይን መውደድ አለባችሁ። ባልና ሚስት ሲጣላ አንደኛው ሌላውን መጥፎ አድርጎ መናገሩ የተለመደ ነው። ሠይጣን ከመሐል ወጥቶ፤ እልሁ ሲበርድለት ቤቱ ተመልሶ ገነት ሲሆን ፀቡ ሁሉ ይጠፋል።» አለና ፂሙን እየቆፈረ እንደገና ሁለቱ ህፃናት ትክ ብሎ ተመለከታቸው። ምኞቱ፤ የልጆቹ ፍቅር የፀቡ ሰሞን እንደታየው ወደ እናታቸው ብቻ እንዳያደላ ለማድረግ ነው። ነገር ግን አነጋገሩ ለራሱም ደረቅ ሆነበት። የማግባባት ስልቱን የቻለበት አልመሰለውም። ለማንኛውም የወላጆቻቸው

ፍቅር ወደ ቀድሞ ቦታው ከተመለሰ የልጆቹም ወገናዊነት እየጠፋ እንደሚሄድ በመገመት ለጊዜው ችግሩን አሳጠረው -

«አሁን በጠቅላላው ስለ አራት ሰዎች ተነጋግረውን ሰይጧኗ የትኛዋ እንደሆነች ለይተን አውጥተናል። ወላጆቻችሁን እንዲታረቁ እኔ ሰይጣኗን እገድላታለሁ።

«ኤልሚ፤ ሽጉት አለህ እንዴ?»

«አለኝ እኮ! አላሳየሁሽም እንዴ ሰብልዬ?»

»አላይሁትም'ኮ። ት - ል.....ክ ነው?»

«እኔም አላየሁትም። ሽጉጥ አለህ እንዴ ኤርሚ?!» አለች ዘኒም፤ ቤቷ ውስጥ ሳታየው በኖረችው ነገር ተደንቃ።

«ቆይ፤ ሰይጣኗን ስገድልበት ለሁላችሁም አሳያችኋለሁ።.......» አላቸው ኤርሚያስ፤ ፍርጥም ብሎ።

እና፤ ዓይኖቹ ቅርብ የሚያዩ መስለው፤ ወደ ሩቅ መመልከታቸውን ቀጠሉ።

ጊዜው ጨለምለም ብሏል። አየሩም ቀዝቀዝ ያለ ነው። ፅጌረዳ ጥቁር ካፖርት ለብሳ፤ አቶ ክብረት የላኩትን አምባር ቀኝ እጇዋ ላይ አድርጋ፤ ተኳኩላ ወጣች። እጅግ ዘመናዊ የሆነች መኪና፤ ሞተሯ ሳይጠፋ፤ አጭር መብራት አብርታ ትጠብቃት ነበር። መኪናዋ አጠገብ ደርሳ በሩ ሲከፈትላት፤ ግራ ቀኝ ገልመጥ - ገልመጥ ብላ ገብታ ከፊት ተቀመጠች። መሪውን የያዙት አቶ ክብረት ናቸው። ከኋላ ደግሞ ትውሲት ተቀምጣለች።

እንግዳቸው በሞቀ ፈገግታ ተቀብለው ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ፤ አቶ ክብረት ወደ ንፋስ ስልክ መስመር መሾፈራቸውን ቀጠሉ። ፅጌረዳ ልታስቀና የምትፈልገውን ብጫ 124 ፊያት መኪና በዓይኗ እየፈለገች ወደ ፊታቸው እመጭ! ከፊትም፤ ከኋላም፤ ከግራም ከቀኝም ያቺ ብጫ ፊያት የለችም።

«ስርቆሽ አዳራሽ ማለት ይሄ ነው እንዴ?» አለች ፅጌረዳ፤ መኪናቸውን አቁመው ወደ መዝናኛ ቤቱ ሲገቡ። አቶ ክብረት በአለባበሳቸው ዝንጥ ብለዋል።

ሙልጭ አድረገው የተላጩት ፂማቸው ከራሳቸው በራ ጋር ተመሳስሎ ያብረቀርቃል።

«አዎ፤ ይሄ ነው። ታውቂዋለሽ እንዴ?» አለቻት ትውሲት፤ እንደ አጋፋሪ ከፊት፤ ከፊት ቀድማ ወደ መቀመጫ እየመራቻቸው።

«እንዲያውም!...... ያለ ዛሬ አልመጣሁበትም።»

አቶ ክብረትና ፅጌረዳን ጎን ለጎን አስቀምጣ፤ ትውሲት ከፅጌረዳ አጠገብ ተቀመተች።

«በሉ እንግዲህ ተጫወቱ የምን ዝም ማለት ነው?! አዝማሪዎቹም አሁን ይጀምራሉ።»

ትውሲት በደስታ እየተወራጨች፤ በተቀመጠችበት መፍለቅለቋን ቀጠለች። ፅጌረዳ አዳራሹ ውስጥ ለመዝናናት ከተቀመጡት ሰዎች መሐከል ሮዛንና ወንዳፍራሽን በመፈለግ ዓይኖቿ ቃተቱ። ለአዳራሹ ውበት እንዲሰጠው፤ መብራቱ በተለያዩ ቀለማት ደብዘዝ ያለ ነበር። ያም ሆኖ ግን የተፈላለገን ሰው በደንብ ያሳያል። - ወንዳፍራሽ እና ሮዛ የሉም።

«ተጫወቺ እንጂ ፅጌረዳ .......» አሉ አቶ ክብረት፤ ፈራ ተባ በሚልና ለመጠበቅ ከውስጥ በሚታገል ጎርናና ድምፅ።

«እሺ፤ እየተጫወትኩ ነው።» - ፅጌረዳ የግዷን ፈገግ አለች።

«እንዴት ነው..... አምባሩ ተስማማሽ?»

ፅጌረዳ አምባሩን ያጠለቀችበት እጇን ከፍ አድርጋ ከማሳየት በስተቀር ምንም አትመልስም።

«አታዩትም እንዴ አምሮባት?!...... ፅግሽ ሙሽ፤ በጣም ነው የተስማማሽ።» በማለት ትውሲት ጣልቃ ገብታ መለሰች።

«መርጬ እኮ ነው የገዛሁት - ለቆንጆ ሴት የሚሆነውን።» እያሉ አቶ ክብረት፤ ቀስ ብለው ክንዳቸውን ፅጌረዳ ትከሻ ላይ ጣል አደረጉ።

የፅጌረዳ ሰውነት የተባዕት እጅ ሲነካው በስሜት በመነሳሳት ፈንታ ህዋሳቶቿ ሁሉ ኩምሽሽ አሉ። ትከሻዋን የነካት ነገር የሚንቀጠቀጥ አሮጌ የባዕድ ክንድ ሆኖ ተሰማት። ስሜቷን ቀዘቀዘው። እና ደግሞ፤ አዳራሹ ውስጥ የተቀመጠው ሰው ሁሉ ወደ እነሱ እየተመለከተ፤ «ምነው ይቺን መሣይ ሴት!?.....አሁን ሰውየው አባቷ አይሆኑም?! እንዴት ያለው መቅለል ነው እባካችሁ?!....» የሚል መስላት። ሆኖም አቶ ክብረትን ላለማስቀየም የግዷን ፈገግ ማለቷ አልቀረም።

የሐገር ባህል ምግብ በቀይ ጨርቅ ተሸፍኖ በመሶብ አጠገባቸው ቀረበ። ወዲያው ሶስት መለኪያ ውስኪ ተከተለ። ገና እንደ ገቡ፤ አሳላፊው ቆሞ የሚፈልጉትን ሲታዘዝ፤ ፅጌረዳ ጣውንቷን ፍለጋ አዳራሹን ትማትር ስለ ነበር፤ ከአቶ ክብረት እና ከትውሲት ምርጫ በመስማማት ራሷን ከመነቅነቅ በቀር ምን እንደታዘዘ ልብ አላለችውም ነበር።

መሶቡ ተከፍቶ፤ በዓይነቱ ከተዘረጋው ምግብ ሁሉም እንደ የምርጫው መቆራረስ ጀመሩ። ትውሲት እንደ ልማዷ እያከላላች ታጋፍራለች። አጉራሽም፤ አፋቃሪም፤ አጫዋችም ሆናለች። አቶ ክብረትና ፅጌረዳን ማስተቃቀፍ ነው የቀራት። ፅጌረዳ ግን ምግቡን እየቆነጠረች ዓይኖቿን አዳራሹ ውስጥና መግቢያው በር ላይ ማንከራተቷን አላቋረጠችም።

«......የታሉ ታዲያ?» አለች በዝግታ ወደ ትውሲት ጆሮ ተጠግታ።

«ይመጣሉ አይዞሽ። ምሽቱ እኮ ገና መጀመሩ ነው።» አለቻት እሷም በሹክሹክታ ድምፅ።

የበሉትን ያህል በላልተው ማዕዱ ከፍ አለ። ውስኪው እዲደገማቸው አቶ ክብረት አዘዙ። ጥቂት ቆይቶም፤ አንድ ሴት ክራርና መሰንቆ ከያዝሁ ሁለት ወንዶች ጋር ወደ አዳራሹ መዝፈን ጀመረች።

ሶስት ያህል ዘፈርኖች ከተዘፈኑ በኋላ የአዳራሹ ህዝብ ነቃ - ነቃ ማለት ጀመረ። በተቀመጡበት መነቃነቅ፤ ዘፋኝዋን በጭብጨባ ማገዝ፤ ብጫ ወይም ቀይ የብር ኖት አውጥቶ መሸለም ተጀመረ። ዘፋኟም መሐል ከመቆም ይልቅ ወደ ህዝቡ መቀመጫ እየተጠጋች፤ ስሙን የምታውቀውን በስሙ እየጠራች የማታውቀውን

እየጠየቀች በዘፈርን ማሞጋገሷን ቀጠለች። አቶ ክብረትም ከዜማው ጋር ሰውነታቸውን እየነቀነቁ ፅጌረዳን በማጫወት ዓይነት ነሸም ነሸም አደረጓት።

ፅጌረዳ ወይ ፍንክች! ሰውነቷ እንደ በደን ሁሉ ደረቅ ፈገግታ ከማሳየት በስተቀር በሙዚቃውም ሆነ በአቶ ክብረት ግፊት፤ የስሜት መቀስቀስ አይታይባትም።

«ኑ እንጂ ወደዚህ!......አንድ አካባቢ ብቻ ነው እንዴ የምትዘፍኑት?»

የፅጌረዳና የአቶ ክብረትን ወዳጅነት ለማድመቅ፤ ትውሲት ዘፋኝዋን ጠራቻት። ዘፋኟም የአቶ ክብረትን ግርማ ሞገስ ተመልክታ፤ ለመሸለም ወደ ኋላ እንደማይሉ በመገመት አጃቢዎቿን አስከትላ ቀረበች። እሷ ወገቧን ይዛ በመጠኑ ትከሻዋን ሰበቅ እያደረገች አጃቢዎቹ ከውዝዋዜ ጋር ማሲንቆና ክራራቸውን እያጫወቱ መዝፈን ጀመሩ -

ከወደዱም አይቀር ይወዳሉ በራ

መላጣ ውበቱ ከሩቅ የሚጣራ።

ከዘንድሮ ወጣት ሽማግሌው ይሻል

በጊዜ አስነጥፎ ሲያዘግም ያመሻል።......

የአዳራሹ ሰው ክትክት ብሎ ሲስቅ፤ ፅጌረዳ በድንጋጤ ላብ አጠመቃት። የእሷና የአቶ ክብረት ዕድሜ ልዩነት በዘፋኞቹ ቋንቋ ገሀድ መውጣቱ አስፈራትና። ከዚያ በኋላ ጆሮዎቿ የሚሰሙት የዘፋኞቹን ግጥም ሳይሆን የሰውን ሹክሹክታ ነበር። «ምን ቅሌታሟ ናት። አሁን ከኝህ ሽማግሌ ጋር.......ገንዘባቸውን ለመብላት ነው እንጂ፤ እውነት ለፍቅር መስሏችሁ ነው?!» የሚል ሐሜት የሰማች መሰላት።

አቶ ክብረትም ቢሆኑ የአዝማሪዋን ግጥም አልወደዱትም። በግንባራቸው በኩል መወረድ የጀመረውን ላብ በመሐረባቸው ጠረግ - ጠረግ አድርገው ሲያበቁ፤ ከኪሳቸው ሁለት ባለ አሰር ብር ኖት አውጥተው ለዘፋኟ ሰጧት። አሰጣጣቸው የሽልማት አይነት ሳይሆን «ወጊዱ ከአጠገቤ» ብሎ የመወርወር ያህል ነበር።

«ምንድን'ነው እሱ?......ሌላ ግጥም አትችሉም እንዴ?» አለች ትውሲት ችግሩ ገብቷት ወደ ዘፋኞቹ እያፈጠጠች።

አዝማሪዎቹ ሽማግሌን ለማወደሻ ያጠኑት ግጥም በሙሉ ተመሳሳይ በመሆኑ፤ አቶ ክብረትን ማስደሰት ቀርቶ ፈገግም አላደረጋቸውም። እነ አጅሬም ገንዘባቸውን ካገኙ በኋላ ብዙም አልተጨነቁም። «......ታዲያ እንግዲህ ‹የማነህ ለግላጋ!› አይባልልዎት ነገር!» በማለት አይነት፤ እንደዋዛ ከአጠገባቸው ዘወር ብለው፤ ወደ ሌላ ሽላምሚ ተሰማሩ።

ብዙም ሳይቆይ፤ የፅጌረዳን ድንጋጤና ሐፍረት በአንዴ ከላይዋ ላይ የሚገፍ ነገር ተፈጠረ። አደን ላይ የቆዩት ዓይኖቿ የሚፈልጉትን ነገር ሲያገኙ ፈጥጠው ቀሩ።

«እነኚያው!......መጡ!» በማለት ሳታስበው ተነፈሰች።

ትውሲትም የፅጌረዳን ዓይኖች ተከትላ ወደ አዳራሽ መግቢያ ተመለከተች። ወንዳፍራሽ እና ሮዛ ተቃቅፈው እየገቡ ነበር። በፅጌረዳ አዕምሮ ውስጥ የተሳልችው ብስል ቀይ፤ ረዥም ሴት የሰው ባል አቅፉ እየተጀነነች ገባች።

አቶ ክብረት ለነገሩ እንግድ በመሆናቸው ግራ ተጋብተው በዝምታ ዓይኖቻቸውን አቁለጨለጩ።

ፅጌረዳ እንዳየቻቸው፤ ወንዳፍራሽ እና ሮዛ ፈጥነው አላዩዋትም። ከአንድ ጥግ በኩል መቀመጫ ይዘው፤ የሚጠጡትን ነገር አሳላፊውን ካዘዙት በኋላ፤ አዳራሽ ውስጥ ያለውን ሰው ገልመጥ፤ ገልመጥ ማድረግ ሲጀምሩ ነው የተያዩት። ወንዳፍራሽ በድንጋጤ ፍጥጥ ብሎ ሲያያት፤ ሮዛ ነገሩ ከንክኖአት የአይን ትርኢቱ ውስጥ ገባች። ከዚያ በፊት በዓይነ - ሥጋ የማይተዋወቁት ሁለቱ ሴቶች ጣውንትነታችውን በደመ እንፍስ የተረዱት ይመስል ለቡጭሪያ እንደ ተዘጋጀ ድመት በርቀት ተፋጠጡ።

ሮዛ የወንዳፍራሽን ክንድ ነቅነቅ አድርጋ፤ ወደ ጆሮው ተጠግታ የሆነ ነገር ጠየቀችው። ወንዳፍራሽም በአዎንታ ራሱን ነቀነቀ። አቀማመጣቸው ርቀት ስለ ነበረው፤ ምን እንደጠየቀችው ፅጌረዳ መስማት አልቻለችም። ነገር ግን በግምቷ «ሚስትህ ያቺ ናት እንዴ» ብላ የጠየቀችው መሰላት። ሮዛ በአዎንታ መልስ ካገኘች በኋላ፤ ፅጌረዳን ለማብሸቅ፤ እንደ ገና ወንዳፍራሽን አቅፉ እየተሻሸች መጫወት ጀመረች።

ፅጌረዳ በርቀት እንዳፈጠጠች ጥርሶቿን አንቀጫቀጨች። ፊቷ ከደቂቃ ወደ ደቂቃ እየፋመ፤ ልቧ እየጋመ፤ ፀጉሯ እየቆመ የደም ስሯ እየተግተረተረ ሲሄድ ይታይ ነበር። ከደሟ ውስጥ ቅንአት ጦሩን እየሰበቀ ወጥቶ ለፍልሚያ ገፋፋት።

«አንቺም አቶ ክብረትን አቅፈሽ አሳያት። ባልሽም በቅናት ድብን የሚለው ያኔ ነው። እቀፊያቸው!» አለቻት ትውሲት ወደ ፅጌረዳ ጆሮ ጠጋ ብላ።

ፅጌረዳ ግን ምን እንዳለቻት እንኳ አልሰማቻትም። ለጊዜው የመስሚያ ህዋሶቿ በድነዋል፤ የመናገሪያ አንደበቷም ተዘግቷል። የጥርሶቿና የጥፍሮቿ ህዋሶች ብቻ ሰልተው ቆመዋል። የሰውነቷን ጡንቻዎች ሁሉ የተሸከሙት እነኚህ ሁለት የሰውነቷ ክፍሎች ሆነዋል። ዓይኖቿን እንዳፈጠጠች የሮዛን ብስል ቀይ ፊት በጥፍሮቿ ቦጫጭራ፤ በጥርሶቿ ቦጫጭቃ ስትጥል፤ ዓይኖቿን ጎልጉላ ስታፈስ፤ ጥፍሮቿ በሮዛ ደም ሲቀሉ በሀሳብዋ ተመለከተች ፡

እንዲህ በጥፍሯና በጥርሷ ስታስብ ቆይታ፤ አንዳች ኃይል ከኋላዋ እንደገፋት ሁሉ፤ ድንገት እመር ብላ ተነስታ ወደ ሮዛ ለመሮጥ ስትንደረደር፤ ትውሲት ተከትላት ልብሷን ጭምድድ አድረጋ ይዛ ጐተተቻት። አቶ ክብረትም ከተቀመጡበት ተነስተው በወዳጅነት ሳይሆን በአባትነት ዓይነት፤ ክንዷን ጠበቅ አድርገው ያዟትና -

«ም - ምንድ'ነው ነገር?» አሉ ወደ ትውሲት እየተመለከቱ።

«የድሮ ባሏን አይታ ነው። እባክዎ እርስዎ ተቆጥተዋት።......ፅጌረዳ፤ ምነው እባክሽ! ለምን እንዲህ መሣቂያ ትሆኚያለሽ?! ወንዳፍራሽን! ይህን ልክስክስ ወራዳ!.....ልቀቁኝ - ልቀቁኝ!.....»

ሮዛም በበኩላ ከወዲያ ማዶ ተነስታ፤ በረዥም ቁመናዋ እየተሰበቀች፤ ወገቧን ይዛ ተጋበዘች -

«ልቀቋት! ኧረ ልቀቋት! ውርደት አምሮሽ ነው እንጂ ቢለቁሽ ምን ልትሆኚ ነው?!.....ባልሽ እንደሆነ አይፈልግሽም! ትቶሻል!.....በግድ ነው እንዴ?! አይሆንማ! እሱ የሚወደው እኔ ነዋ! ይሄውልሽ ከፈለግሽ......»

እዚያ ሁሉ ሰው መሐል፤ ክንዷን ይዞ ሊያረጋጋት የሚሞክረውን የወንዳፍራሽ አንገት በሁለት እጆቿ ጥምጥም አድርጋ አቅፋ፤ ከንፈሩን ምጥጥ አድርጋ እየሳመችው።

«ይሄውልሽ! ሳምኩት - ሳመኝ! እንግዲህ ምን ትሆኚ? በቅናት እርር ደብን በይ!......» አለቻት።

ዘፋኝዋ ማቀንቀኗን አቋረጠ፤ የማሲንቆና የክራሩም ድምፅ ቀጥ ብሎ ቆመ። የአዳራሹ ሰው ሁሉ «ጉድ!» እያለ እያጉረመረመ በፅጌረዳ እና በሮዛ መካከል የሚካሄደውን ትርኢት መመልከት ያዘ።

የአዳራሹ ባለቤት የሆኑት አጭር ወፍራም ሴትዮ ከወደ ጓዳ ወጥተው፤ ወገባቸውን ይዘው እየተውረገረጉ ይንጣጡ ጀመር።

«እንዴ.....ምንድን'ነው እሱ?!....»

«የለም፤ ጉዳዩ ቀላል ነው።....እሷ ባሏን ከሌላ ሴት ጋር አይታው ነው። .....እባክሽ ታገሽ ፅጌረዳ! እባክሽ ራስሺን አታዋርጂ።»

«የኔ ቤት መዝናኛ እንጂ መደባደቢያ አይደለም እኮ!......» ሲሉ ቀጠሉ ባለቤትየዋ፤ «ቀናተኛ ቀድሞውንም ከቤቱ ያለመውጣት ነው! አርፎ ቤቱ መቀመጥ!......»

«አዳሜ ስትሰራረቂ ትከርምና ቅናቱ ሲብሰባት ጥፍሯን አሹላ ትነሳለች! እንዲህ ነኝና!......ደሞስ ለዘንድሮ ፍቅር ነው እንዴ ይህ ሁሉ?!.......ድንቄም እቴ!.......ፖሊስ ጠርቼ ነው እያንዳንድሽን የማሳፍስሽ! ይልቅ አርፈሽ ብትቀመጭ ይሻልሻል - አዳሜ!......»

ፅጌረዳ በድናለች። የሴትየዋን ቁጣ ከቁብም አልቆጠረችው። ይልቁንም፤ ግራና ቀኝ ጨምድደው የያዟት እጆቹ አዘናግታ መንጭቃ ወደ ጠላቷ እንደ ጦር ተወርውራ ደርሳ፤ ባለ - በሌላ ኃይሏ የሮዛን ፀጉር ጭምድድ አደረገች።

«ዋ - አ - እ - እ - እ - እ - ይ!.......ትግዬ!......ዋ - አ -ይ! ተጉሌን! .....ተጉሌን!.....»

ሰብለን እሪታዋን አቀለጠችው። ፅጌረዳ ከእንቅልፏ ብንን ብላ ስትመለከት፤ እየጨመደደችው ፀጉር፤ አጠገኡባ የተኛችው የልጇ፤የሰብለ ሆኖ አገኘችው።

«አይዞሽ ሰብልዬ......ሳላውቅ ነው።»

በህልም የተበጠበጠው ጭንቅላቷ ከብዷት፤ እየተጨናበሰች መብራቱን ካበራች በኋላ ልጇን አቅፋ ማባበል ጀመረች። ሰብለ ህመሙ ስለጠነከረባት እንባዋ ዝርግፍ እያለ ጮኸች።

«አሳመምሽኝ እኮ፤ ትግዬ....»

«አይዞሽ በቃ፤ የኔ ቆንጆ......አውቄ አይደለም። አይዞሽ.....»

አያቶቿ የልጆቿን ጩኸት ሰምተው ከመኝታ ክፍላቸው እየተሯሯጡ መጡ።

«ፅጌረዳ......ምንድ'ነው እሱ?.......እስቲ በሩን ክፈች!.....» አሉ ባቷ።

«አንዴ! .......ምንድነው ነገሩ!.....ህፃን በሌሊት ይቀጣል እንዴ?!.....ምን ማድረግሽ ነው? አሉ እናትየዋም በበኩላቸው፤ ፅጌረዳ ልጇን ደብድባ ያስለቀሰቻት መስሏቸው።

«ቃዥታ እኮ ነው እማምዬ......ቅዠት ነው፤ አሁን ትቷታል፤ ተመለሱኡና ተኙ» አለቻቸው ፅጌረዳ፤ በሩን ሳትከፍት ከውስጥ እንደሆነች።

ወላጆቿ ተመልሰው ተኙ። ሰበልንም ጡቶቿ መሐል አስገብታ አቅፋ እያባበለች አስተኛቻት። እሷ ግን ያንን ከመስለ አሰቃቂ ቅዠት በኋላ፤ መብራቱን አጥፍታ፤ ተመልሳ መተኛት አልቻለችም። ዓይኗች አፍጥጣ ከግድግዳው ባዶነት ላይ እንደተከለች ቀረች።

በህልሟ ያየችውን ነገር ስታስበው ዘገነናት። ሮዛን በዓይን የማወቅ ጉጉት እያደረባት፤ ነገር ግን ጉጉቷን አፍና ዛሬ፤ እንገር ስትል የቆይችውም ይህንኑ ፈርታ ነው። ሰዉን ብታገኛት ዘልላከማነቅ የምትቆጠባትመስልም።.....እንደ አጠላሏ። እና ዛሬ ይህንንኑ አዕምሮዋ ውስጥ የሚመላለስ ጉዳይ በህልሟ አየችው። የወሩ መጀመሪያ አርብ በመሆኑ ትውስቲ ሰሞኑን ስልክ እየደወለች በዚህ ዕለት ወደ «ስርቆት አዳራሽ» እንዲሄዱ ወትውታት ነበር። ምክንያቱም ብዙ ሰው ለማዝናናት ወደ አዳራሹ

የሚመጣው ያው በልደታ ሰሞን ስለሆነ፤ እና ወንዳፍራሽንም የማግኘት ዕድሉ ሰፊ መሆኑን በመገመት ነበር። ይህ የቀን ምኞትና በሀሳብ መዋዠቅ ሌሊት በቅዠት ተከሰተ።

በመሠረቱ ፅጌረዳ በትውሲት ምክር መሠረት ወንዳፍራሽን የማስቀናት ስሜት ስለ ተጫጫናት እንጂ፤ አቶ ክብረትን መንፈሷ አልፈለጋቸውም። አንዳንዴ ብቻዋን ቁጭ ብላ ከእሳቸው ጋር የመውጣቱን ነገር ስትስብ፤ ከወዲሁ ሰውነቷን ሐፍረት ይወርረዋል ይህንኑ የተደበቀ የውስጥ ስሜት ጥላቻ በህልሟ አየችው። ይህልሙ ትርዒት የተካሄደበት አዳራሽ በአፍላ ፍቅር ወቅት ከወንዳፍራሽ ጋር ትሄድበት የነበረው የክራር ቤት እንጂ፤ ትውሲት «ስርቆሽ አዳራሽ» የምትለው ቦታ አልነበረም። አዝማሪዋና ግጥሞቹም በዚያው ጊዜ ወንዳፍራሽ ጋር በየክራሩ ቤት እየዞሩ ያወቁዋቸውና የሰሟቸው ነበሩ።

ህልሟ ይህን የመስለው የቀን ስሜቷ ነፀብራቅ መሆኑን ልቧ ቢያውቅም፤ ለጊዜው መንፈሷ አልተረጋጋም። በቅዠት የተጨናበሰ አዕምሮዋ ከስሜትዋ ፍላጎት ጋር ተዳምሮ ህልሟን በአንዳንድ ገንቢና አፍራሽ ሀሳቦች ለመፍታት ስትፈላሰፍ ብዙ ቆየች። በኋላም ደግሞ እንዲህ እንቅልፍ አሳጥቶ የሚረብሻት የትዳሯ መፍረስ መሆኑን ስታስብ በሌሎች ጤናማ ትዳሮች ትቀና ጀመር። በውን የምታውቃቸው ጐረቤቶቿ ወይም የርቀት ጓደኞቿ የሆኑ ባልና ሚስቶች፤ የሞቀ ጎጆ ውስጥ፤ በሞቀ ፍቅር ተቃቅፈው፤ ሰላማዊ እንቅልፍ ተኝተው ታዩዋት። ባልና ሚስቶች ጥንድ ጥንድ ሆነው፤ የፍቅራቸውን መጠን ለማሳየት እየተላለፉና እየተሳሳቁ በዓይኗ ላይ አለፉ። በግድግዳው ባዳነት ላይ የቦዘኑት ዓይኖቿ ይህን ሲመለከቱ፤ አዕምሮዋ ደግሞ ለስምንት ዓመታት ያህል ሌሎችን ያስቀና የነበረውን የትዳሯን ጣፋጭነት ወደ ኋላ ተመልሶ ይቃኝ ነበር። - ነበር እንደዋዛ!.......

ከቅዠት በኋላ እንዲህ ዓይነት ሌላ ዕውን ቅዠት ውስጥ ገብታ ስትባዝን፤ በዓይኗ እንቅልፍ ሳይዞር ነጋ።

ጠዋት ቶሎ አልተነሳችም። እንቅልፍ መልሶ ባይወስዳትም ጭንቅላቷን ስለከበዳት ከመኝታዋ መውጣት አልፈለገችም። ሠብለ ተሰናብታት ከሠራተኛዋ ጋር

ወደ ትምህርት ቤት ሄደች፤ አባትየውም የቀን ስራቸውን ለመጀመር ወደ ልኳንዳቸው ገቡ።

ረፈድፈድ ሲል የፅጌረዳ እናት የመኝታ ክፍሏን በር አንኳኩተው ገቡ። ፅጌረዳ የበሩን ድምፅ ስትሰማ አንሶላና ብርድ ልብሱን ከራስዋ ላይ ገልጣ ቀና አለች።

«ምነው ፅጌረዳዬ?.......ደህናም አይደለሽ እንዴ?» አሉ እናቷ፤ ያለ ወትሮዋ ተኝታ ማርፈዷ አስደንግጦአቸው።

«ልጅሽ ደግሞ ያቃዣት ጀመር እንዴ?.....ድሮም ያውቃታል ወይስ አዲስ ነገር ነው?.......አጯጯኋ እኮ እንዲህ አይምሰልሽ?.......» አሏት አልጋው ጠርዝ ላይ እየተቀመጡ።

ፅጌረዳ ቶሎ መልስ አልሰጠቻቸውም። በአንድ በኩል ቅዠት የራስዋ መሆኑን ነግራቸው ህልሟን እንዲፈቷልት ፈለገች። ‹እንዲህ ዓይነት ህልም ያየሁት ለጤና አይደለም።› የሚል ስነ ልቦናዊ ሰቀቀን ስላደረባት ህልሟን ለሌላ ሰው ማዋየቱ መፍትሔ መሰላት። በሌላ በኩል ደግሞ ህልምም ቢሆን ከአቶ ክብረት ጋር መውጣቷንና በቅንአት ከሮዛ ጋር መደባደቧን ማውራት የሚያሳፍር ሆነባት። ለጥቂት ደቂቃዎች ከራዋ ጋር ስትከራከር ከቆየች በኋላ፤ መቼም ከእናት የበለጠ ቅርበት ያለው የለምና፤ ራስዋን ትዝብት ላይ በማይጥል መንገድ ሸፈንፈን አድርጋ ለማዋየት ወሰነች።

«ቅዠቱስ የሰብልዬ አልነበረም። እኔው ስቃዥ ነካከቼአት ነው ያስጮህኳት......» አለችና አቋረጠች።

«ውይ! አንችኑስ መቼ ጀመረሽ ልጄ?......ድሮ እንኳ አያውቅሽም ነበር እኮ!......»

ምናባቴ አውቄ!.....ከዚያች ወንዳፍራሽ ከወሸማት ጣውንቴ ጋር አንድ ጨዋታ ቦታ ተገናኝተን ስንደባደብ አመሸን። - ያውም ሰው በተሰበሰበት።.....»

«ልትታረቁ ይሆናል፤ ፅጌረዳዬ......» አሏት ከአፏ ነጥቀው፤ «.....መቼም በህልም ፀብ፤ በውን ሲፈታ ፍቅር ነው። እንዲያውም እኮ እነግርሻለሁ

እያልኩ......በቀደም ወንዳፍራሽን አግኝቼው ‹አረገዘች› የሚባለው ነገር ውሸት መሆኑን ነግሮኝ ነበር።.....»

የፅጌረዳን ሁኔታ ለማጥናት ንግግራቸውን አቋረጡ። ትዳሯን ጥላ ከቤቷ ከወጣች አስር ቀናት አልፈዋል። እናትየዋ ከባሏ ታርቃ ወደ ትዳሯ እንድትመለስ ቢፈልጉም፤ የፅጌረዳ ቁጡነት ነገሩን በሆዳቸው አምቀው እንዲያቆዩ አደረጋቸው። የተናነቃት ዕልህ እስኪለቃት ድረስ ማንም ሰው ስለዚህ ጉዳይ እንዲያነሳባት አትፈልግም ነበር። የወላጆቿ የነፍስ አባት አንድ ቀን ከሁለት ሽማግሌዎች ጋር ሆነው ሊመክሯት ቢመጡ አሻፈረኝ ብላ ወደ ጓሮ ሸሽታ መልሳቸዋለች። ከመሰንበት ጋር እልሁ ገለል ብሎላት፤ ዛሬ ይህንን ርዕስ እርሷ ራሷ መክፈቷ ለእናትየው መልካም አጋጣሚ ሆኖላቸው ሊነግሯት እየፈለጉ ፈርተው ሲያምጡ የሰነበቱትን ጉዳይ ለመተንፈስ ተነሳሱ።

በተለምዶ የአብዛኛው ህልም ፍቺ ተቃራኒው ተደርጎ እንደሚነገር የፅጌረዳ ልብ ቢያውቅም፤ በእናቷ አቀራረብ ተሳበች። ሰውን የባዕድ አምልኮ ተገዥ የሚያደረገው ችግሩ መሆኑን እያሰላሰለች ወደ እናቷ ወሬ አተኮረች -

«አይ እማማ!......ዱሮውንስ ታዲያ የውጭ ሴት ማስረገዙን ሊያምንልሽ ኖሮአል እንዴ?!......» በማለት የጨዋታውን በር በዘዴ አሰፋቻው።

«የለም.....ኧረ ምሎ ነው የነገረኝ። አድርጎት ከሆነ ምን አስፈራው ብለሽ ነው። መወሸም ቢሆን ያው ቅሌት ነው።.......»

«ለመሆኑ አንቺ የት አገየሽው?......»

«ማንን? ወንዳፍራሽን?......ቤቱ ድረስ ሄድኳ!......አባትሽም ኃይለኛ ሆነ፤ አንቺም ኃይለኛ ሆንሽ።.......መቼም ሰው ከወለደ ከከበደ በኋላ ተኮራፍሮ ዝም - ዝም ማለት አይበጅም። ደግሞ ጥንትም ቢሆን በትዳር ውስጥ ግጭት ያለ ነገር ነው። ሁሉም ‹ይቅር ለእግዚአብሔር› እየተባለ ነው ለዚህ የደረሰው። ይህን ሁሉ አስብኩና በቀደም ወደ ማታ አካባቢ ወንዳፍራሽ ቤት ሄድኩ። የሌሊት ልብሱን ለብሶ ቴሌቪዥን ሲመለከት አገኘሁት። ታዲያ ይገርምሻል! ልጄ ሙች እልሻለሁ! ያው የጥንቱ ወንዳፍራሽ ሆኖ ነው ያገኘሁት። - ሰላምታው፤ መስተንግዶው፤

ጨዋታው....በአንዱም የተለወጠበት ነገር የለም። እና፤ እንዳልኩሽ ሁሉንም ነገር በግልፅ አንድ በአንድ ተነጋገርንበት። እሱ እንዳለኝ ከሆነ የአርግዝናው ነገር ተራ ግምት ካልሆነ በቀር ውሸት ነው። በተረፈ፤ ከተባለችው ሴት ጋር መቅበጡንም፤ ጥፋተኛነቱንም አልደበቀኝም።......»

‹እህህህ! የልብን ሰርቶ ይቅር በሉኝ!......» አለች ፅጌረዳ፤ ዜማ በተቀላቀለበት ድምፅ።

«ቆይ እኮ አስጨርሺኝ፤ ፅጌረዳዬ። እናንተ ደህና ዘመን ላይ ደርሳችሁ ነው እንጂ፤ እኛ ስንቱን ችለን መሰለሽ ለዚህ የደረስነው!.......እንግዲህ ዛሬ፤ ሆዴ ውስጥ ተደብቆ የኖረ አንድ ምስጢር ልነግርሽ ነው።......»

ፅጌረዳ በድንጋጤ የግንባሯን ቆዳ ዘበሸበች።

«ዛሬ በወንዳፍራሽ ጥፋት ተናዶ ‹አካኪ ዘራፍ!› የሚለው አባትሽ በዘመኑ ከአንድም ሁለት ሴት ወሽሞ እርር ድብን ሲያድርገኝ ነበር የኖረው። ይህንን ሰምተሽ ኑሯል?.......»

«ኧረ እንዲያውም አልሰማሁም እማምዬ.......»

«አዎ፤ እናንተ ያኔ ገና ትናንሽ ልጆች ናችሁ። ካደጋችሁም በኋላ ወሬውን እንድትሰሙት ስላልፈግኩ ደብቄያችሁ ኖርኩ።..... ያኔ አባትሽ በየክፍለ ሐገሩ እየተዟዟሩ ይሰራ ነበር። ደሴ ውስጥ አንዷን፤ ወለጋ ውስጥ አንዷን መወሙን የወሬ ወሬ ሰማሁ። እውነት መሆኑንም አጣርቼ ደረስኩበት። ለጊዜው አብከነከነኝ። ጥለሽው ብረሪ - ብረሪ አሰኘኝ። ነፍሷን ይማርና፤ ታላቅ እህቴ አስተዋይ ሰው ነበረች። ‹ትዳሩን እስካልበደለ ድረስ ተይው። ጉርምስና ይዞት ነው። ዘሎ - ዘሎ ሲበቃው ይሰበሰባል። ደሞም አንቺ ማሰብ ያለብሽ ስለ ልጆችሽ ነው። ነገ ልጆችሽ አድገው የድካምሽን ውጤት ማየቱ ያፅናናሻል።› ብላ ብዙ ነገር መከረችኝ። እውነትም ከጊዜ በኋላ እሱም እየተሰበሰበ፤ የእናንተ ማደግ እያጓጓው፤ ትዳሩን እያፈቀረ መጣ። በኋላ እኔም ሆንኩኝ እሱ ይህንን ነገር ለልጆቻችን ላለመንገር ቃል መሐላ ፈፅመን ነበር። አሁንም ይህ ሚስጥር ከእኔና ካንቺ ማለፍ የለበትም። ዛሬ ቃለ መሐላዬን ሰብሬ የነገርኩሽ ወደ ኋላ ተመልሰሽ አባትሽን እንድትጠይ አይደለም። ነገር ግን ያን

ጊዜ በብስጭት ከቤት ወጥቼ ብሆን ኖሮ የእናንተን የልጆቼን ዓለም ለማየት ባልበቃሁ ነበር፤ እናንተም ተበታትናችሁ ፍቅር አጥታችሁ ለማየት ባልበቃሁ ነበር፤ እናንተም ተበታትናችሁ ፍቅር አጥታችሁ ታድጉ ነበር ለማለት ነው።......»

«.......እና፤ በባል መደበል የሴቶች ዕዳ ክፍላችን ነው ማለት ነው?» አለች ፅጌረዳ በጥሞና ስታዳምጥ ከቆየች በኋላ በረዥሙ ተንፍሳ ስታበቃ።

«አይደለም! ትዳራቸው ውስጥ አንዳች ነገር ኮሽ ሳይል ዐምሳ ስድሳ፤ ዓመት የቆዩም ሞልተዋል እኮ! ነገሩን ያነሳሁት በአንቺ ላይ የደረሰው ችግር አዲስ አይደለም ለማለት ነው!......በተረፈማ የዘመኑ ሕግ እንዲያውስ ለሴቶች ሳያደላ ቀረ ብለሽ? በዚያ ሰሞን እዚህ ታች ያለች ጎረቤታችን ሰካራም ባሏን በህግ ከስሳ ከቤቷ አስወጥታ ልጆቿን እያሳደገች ቁጭ ብላ የለም እንዴ! ያውም ደሞዙ ተቆራጭ እንዲያደርግ ተገድዶ!......የተወለዱ ልጆችንም እያዩ ማመዛዘን ያስፈልጋል ለማለት ነው እንጂ፤ ዝመኑስ የሚያደላው ወደ ሴቶች መብት ሆኗል።......»

ፅጌረዳ ለጥቂት ሴኮንዶች በዝምታ ቆየች። እናቷ ያርከፈከፉባት ፀበል ጋቤኑን ከላይዋ ላይ ሙልጭ አድርጎ ባያጥበውም፤ በመጠኑ እየተፈታተነው ነበር።

«ዕውነት እልሻለሁ ፅጌረዳዬ፤......ወንዳፍራሽ እንደፈራሁት የተለወጠ ሆኖ አላገኘሁትም። ትህትናውም፤ ነገርነቱም እንዳለ ነው።.......መቼም አንዴ የሆነው ሆኗል፤ አያድርስ ነው!.......» አሏት በማባበል ዓይነት ዓይናቸውን አይኗ ላይ እያንከባለሉ።

«ለመሆኑ ፅጌረዳ ምን በድላኝ ነው ሌላ ሴት ፍለጋ የሄድኩት አለ?»

«ምንም በደለችኝ አላለም። ምንም ጥፋት!......»

«እውነቱን እኮ ነው እማማ.....እንዲያው ምን ብድየው ነው ልቡ ውጭ የኮበለለው?......»

«ጥሎሽ ነዋ ልጄ! - ጥሎሽ!»

ዕለቱ የእስላሞች በዓል በመሆኑ፤ ትምህርትም፤ ሥራም የለም። ወንዳፍራሽ የጠዋት ዕንቅፍሉን ቢጨርስም የሚሄድበት ስላልነበረው፤ ከአልጋው መውጣቱን

አልፈለገውም። እንዲሁ መኝታው ውስጥ ሲገላበጥ፤ ከሳሎን የሚሰማው ከፍተኛ የሙዚቃ ድምፅ አናዶት ከነፒጃማው ተነሳ።

ዳኒ ስራዬ ብሎ ቴፕሬኮርደሩን እያስጮኸው ነበር።

«አንተ ዳኒ፤ ጋሽ ወንዳፍራሽ ቴቡን እንዲህ አታስጩህ በለውህ አልነበረም?......» አለችው እልፍነሽ ከማድቤት መጥታ።

ዳኒ ሌባ ጣቱን ከንፈሩ ላይ አድርጎ ‹ዝም በዪ› እንደ ማለት ያህል «እሱስስ.....» አላት።

«......ጥሩ ልጅ ነበርክ፤ አሁን ፀባይህ ሊበላሽ ነው።» አለችና ተንደርድራ ቴፑን ዘግታበት ወደ ስራዋ ተመለሰች።

ዳኒ እንደገና ቴፑን ከፍቶ ያስጮኸው ጀመር።

«ምነው ዳኒ! ስንት ቀን ነው የምነግርህ!? ቴፑን ለምን እንዲህ ታስጮኸዋለህ?!.....» አለውና ወንዳፍራሽ ከመኝታ ክፍሉ ወጥቶ ተቆጣ።

«ዕልህ ይዞት እኮ ነው።.....» አለ ዳኒ የቴፑን ድምፅ እየቀነሰ።

«የምን ዕልህ ነው የሚይዝህ?.....እምቢ ካልክ እኮ ትገረፋለህ።»

«እሺ በቃ፤ ሁለተኛ አላስጮህም። ዕልህ ደግሞ የአውሬ ፀባይ መሆኑን አስተማሪዬ ነግረውኛል።»

«አዎ እልህኛ ልጅ ከሆንክ እኔም አልወድህም።»

«......ግን ወንዴ? እኔን የማይገባኝ ምን መስለህ.....»

«እ? ምንድ'ነው። እሱ?»

«እኔን ያልገባኝ......እ - ልጆች እልኸኛ ሲሆኑ ወላጆቻቸው ይገርፏቸዋል። አዋቂዎች እልኸኛ ሲሆኑስ ማን ይገርፋቸዋል?»

ዳኒ፤ ቤት ውስጥ ማኩረፉን ትቶ ጨዋታ መጀመሩ አባቱን ደስ አሰኝጦት፤ ውይይቱን ለመቀጠል ፈገግ ብሎ ወደ ረዥሙ ሶፋ ሄደና ተቀመጠ። የዳኒ አይኖች በጥያቄ አስተያየት እየተቁለጨለጩ የአባቱን ርምጃ ተከትለው ወደ ሶፋው አመሩ።

«መጀመሪያ ነገር፤ አዋቂዎች እልኸኛ አይሆኑም.....» አለው ወንዳፍራሽ፤ ፈገግታው ከፊቱ ሳይጠፋ።

«ይሆናሉ!.......ከፈለግህ እንወራረድ.......በሙቶ በሙቶ ብር!.....አለው ትንሹ ቆቅ ሳያመነታ።

«ደሞዝ ሲደርስ ነዋ ታዲያ.......አሁን ሙቶ ብር ከየት አመጣለሁ ዳኒ?»

«እሺ በቃ፤ እንዲሁ እንወራረድ.....»

«እንዲሁ.....እሺ።»

«አሁን ለምሳሌ አንተ ፅግዬን፤ እኔን፤ ሰብለን፤ ትወደናለህ አይደል?!.....»

«አዎ፤ እወዳችኋለሁ።......»

«ታዲያ.....አንተ እና ፅግዬ ለምን አትታረቁም?»

ወንዳፍራሽ ደንገጥ አለ። የልጁ ጥያቄ ወዴት እንደሚያመራ በመገመት፤ የጀመሩትን ጨዋታ ለማቋረጥ ፈለገ። ነገር ግን ዳኒ ፋታ አልሰጠውም። ጥያቄውን አደባብሶ በማለፍ አርዕስቱን መዝጋት የሚችልበትን መንገድ ሲያስላስል፤ ትንሹ ቆቅ አጨናገፈበት።

«የሚዋደዱ ባልና ሚስቶች በዕልህ እንደሚጣሉ አስተማሪዬ ነግረውኛል። ከተጣሉም የማይታረቁት ዕልህ ስለሚይዛቸው ነው ብለውኛል።»

«የምን ትምህርት አስተማሪ ናቸው ይህንን የነገሩህ?......» አለው ወንዳፍራሽ፤ ድምፁ እየሻከረ።

«የ - የ - እንትን.....»

ዳኒ ያላሰበበትን ጥያቄ ስለተጠየቀ ተደናግጦ የሚመልሰውን አጣ።

«መዋሸት ጀመርክ እንዴ ዳኒ?»

«አአይ፤ አልዋሽሁም።......»

ምክሩ የኤርሚያስ መሆኑን ለመገመት ወንዳፍራሽ ብዙ ጊዜ አልወሰደበትም። የዛሬው ብቻ ሳይሆን ከሚስቱ ከተጣላ ጀምሮ፤ አልፎ አልፎ ከዳኒ ንግግር ጀርባ የሚያነበው የኤርሚያስን ጭንቅላት ነበር። ከፅጌረዳ ጋር የፀባቸውም ሆነ ያለመታረቃቸው ምክንያት እልህ መሆኑን ኤርሚያስ ከአሁኑ በፊት ለወንዳፍራሽ ለራሱ በሽቆ ነግሮታል።

«ስማኝ ዳኒ አባትህ መሆኔን አትርሳ። እንድትዋሸኝ አልፈልግም። ይህን ነገር የነገረህ ኤርሚያስ ነው አይደለም?......» አለው ቁጣና ማባበልን አቀናብሮ በያዘ አነጋገር።

«ስማኝ ዳኒ፤ እኔ አባትህ መሆኔን አትርሳ። እንድትዋሸኝ አልፈግም። ይህን ነገር የነገረህ ኤርሚያስ ነው አይደለም?.......» አለው ቁጣና ማባበል አቀናብሮ በያዘ አነጋገር።

ዳኒ ከንፈሩን ጣል አድርጎ፤ በአዎንታ ራሱን ነቀነቀ።

ወንዳፍራሽ ምን እንደሚናገር ወይም ምን ማድረግ እንዳለበት ግራ ገብቶት በሀሳብ ግንባሩን እንዳጨማደደ ቀረ። ዳኒም አይኖቹን ከአባቱ ገፅ ላይ ሳይነቅል፤ በትካዜ ትኩር ብሎ ሲያየው ቆይቶ -

«ወንዴ........» አለው።

«ወዬ.....»

«ለምን ከፅግዬ ጋር አትታረቁም?»

«ዳኒ.......ስንት ቀን ነው የምነግርህ!........እናትህ ቤቷን ጥላ ሄደች እንጂ እኔ አላባረርኳትም። እንግዲህ ምን አድርግ ነው የምትለኝ?!.... ከናፍቀችህ በፈለግክ ጊዜ እየሄድክ እንድትጠይቃት ከዛሬ ጀምሮ ፈቅጄልሃለሁ፤ በቃ!......»

«......ብትታረቁ ነበር ጥሩ። ካለዚያ ፅግዬ ጋ ስሄድ አንተ ትናፍቀኛለህ፤ አንተ ጋ ስሆን ደግሞ ፅግዬ ትናፍቀኛለሽ።» አለው፤ ድምፁ ወደ ለቅሶ እያደላ።

ወንዳፍራሽ በልጁ አነጋገር ሆዱ ባባ። እንደገና አገጩን በመዳፉ ደግፎ ተከዘ።

«ዱሮ ቤታችን ገነት ነበረ። አሁን ደግሞ ሲዖል ሊሆን ነው። ሠይጣን እኮ በአንተና በፅግዬ መሐል ገብቶ ነው።.....»

አባትየው አሁንም ምንም ሊመልስለት ወይም ሊጠይቀው አልቻለም። ልጁን ትኩር ብሎ የሚመለከተው እንደ እንግዳ አስደንጋጭ ፍጡር እንጂ፤ ከአብራኩ እንደወጣ ዓይነት አልነበረም። የልጁ ትንሽ ሰውነት ትልቅ ጭንቅላት ተሸክሞ ታየው። እና ይህ ጭንቅላት ቂም አርግዞ እንዳያድግ ፈራ።

ድንገት ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ ወደ መኝታ ክፍሉ ከገባ በኋላ፤ ፒጃማውን አውልቆ፤ ቀለል ያሉ ልብሶች መርጦ ለበሰና ወደ ውጭ ለመሄድ ተነሳ።

«ወንዴ፤ ወዴት ልትሄድ ነው?»

«አንድ ቦታ ደርሼ እመለሳለሁ።»

«እኔ እኮ አንተንም፤ ፅግዬንም እኩል እወዳችኋለሁ።.......»

«አውቃለሁ ዳኒ።......»

«ዛሬ እኮ የዕረፍት ቀን ነው። ሽርሽር አትወስደኝም?......»

«ስመለስ......ከሰዓት በኋላ እወስድሃለሁ።»

መኪናውን ለማስነሳት ሞተሩን ሲያሞቅ ሰምታ እልፍነሽ ከጓዳ ወጣች።

«ቁርስ ይብሉ እንጂ ጋሼ......»

«የለም፤ ቶሎ እመለሳለሁ።.....»

የውጭውን በር ከፍታ አወስወጣችው። እየከነፈ በቀጥታ ወደ ኤርሚያስ ቤት ሄደ።

ኤርሚያስ ቤት ሲደርስ በሩን ከፍታ ያስገባችው ዘኒ ነበረች። ገና ከውጭ የወንዳፍራሽን መኪና በቀዳዳ አሾልካ ስትመለከት፤ ዳኒ ያለ መስሎአት ደስ ብሎአት ነበር።

«ለምን ዳኒን ይዘኸው አልመጣኽም ጋሽ ወንዳፍራሽ?» አለችው እጁን ይዞ ጉንጮቿን ከሳማት በኋላ።

«ዳኒ ገና ከእንቅልፉፍ አልተነሳም።» ብሎ ከዋሻት በኋላ እጁን ይዞ ወደ ቤት ውስጥ እየገባ «ኤርሚያስ የለም እንዴ?» አላት።

ለአፉ ያህል ጠየቀ እንጂ፤ መኪናውን ግቢው ውስጥ ስላያት፤ ቤት ውስጥ እንኳ ባይኖር ርቆ እንዳልሄደ ልቡ አውቋል።

«አለ፤ ስዕል ክፍሉ ውስጥ ነው።......» አለች ዘኒ።

ሁለቱ ንግግራቸወን ሳይጨርሱ፤ ኤርሚያስ ድምፅ ስለሰማ የክፍሉን በር ከፍቶ ብቅ አለ። የመጣው እንግዳ ወንዳፍራሽ መሆኑን ሲመለከት፤ ከጉዳዩ ጋር የተያያዘ መሆኑን በመገመት ልቡ የደስታ ደም መርጨት ጀመረ።

«ገና በጠዋቱ ብሩሽህን አንስተሃልና ጃል?!......» አለው ወንዳፍራሽ፤ ሲጨባበጡ።

«ምን ዋጋ አለው!...... ከጀመርኩት ስዕል ጋር ተፋጥጬ ቆየሁ እንጂ ምንም ሀሳብ ማፍለቅ አልቻልኩም።.....አዕምሮዬ የተረጋጋ ሰላም አላገኘም።»

«ምነው?.....ምን ተፈጠረ?......»

ወንዳፍራሽ አዲስ ችግር የሚሰማ መስሎት ግንባሩን አኮማትሮ ሽፋሽፍቱን ሰበሰበ።

«የአንተና የሚስትህ ከንቱ እልህ እያናደደኝ!.......የልጆቻችሁ ነገር ደግሞ እያሳዘነኝ ነዋ!......እኔ ደግሞ እንደምታወቀኝ አንድ ነገር ከጀመርኩ ቶሎ ፍፃሜውን ለማየት የምቸኩል ፍጡር ነኝ።.....» አለው አጠገቡ ያገኘው ወንበር ላይ ተቀምጦ፤ ወንዳፍራሽን ፊት ልፊት እየተመለከተ።

«እኔ ሌላ ችግር የገጠመህ መስሎኝ ነው እንጂ፤ ይሄማ ከቅርብ ጓደኛ ከሚጠበቅ መስዋዕትነት በጣም ትንሹ ነው።......» አለ ወንዳፍሽም የተኮሰኮሰ ፊቱን በግድ ለማፍካት እየሞከረ።

ይህ አነጋገሩ በኤርሚያስ ልብ ውስጥ አንዳች ተስፋ ይረጭ ጀመር። ድምጹ ራሱ ቀና መሰለው።

«እንዲያውም አሁን ወዳንተ የመጣሁት ያ ልጅ እየረበሸኝ አስቸግሮኝ ነው። » አለው፤ ጉዳዩን በሌላ መንገድ እንዳይጀምር ኩራት ታግሎት።

«የቱ ልጅ?......» አለው ኤርሚያስም ስለማን እንደሚያወራ ልቡ እያወቀ።

«ዳኒ ነዋ!......»

«ከትዬ ፅጌረዳ ጋር ለምን አትታረቁም? ዳኒ እኮ መናደድና ማኩረፍ የጀመረው እናንተ ስለተጣላችሁ ነው።» አለች ዘኒ ጣልቃ ገብታ።

ወንዳፍራሽ የዘኒን ውብ ዓይኖች እየተመለከተ ፈገግ አለ ፡

«እውነቴን እኮ ነው፤ ጋሽ ወንዳፍራሽ.....» አለችው እንደገና ፊቷን እዝን አድርጋ።

«ዳኒ ምን አለህ?......» አለ፤ ኤርሚያስ ቸኩሎ።

«ያው አንተ የመከርከውን ነዋ! ጥሩ ደቀመዝሙር አግኝተሃል። ሰሞኑንማ ማታ ስገባ፤ ጠዋት ስወጣ እንዲሁ እየጨቀጨቀኝ ነው።.......»

«እኔ ምን አልኩት?......»

«ፐ!.....እሱን ተወውና ይልቅ.....ምን ማድረግ እንደምንችል እንነጋገር። .....እናቷም በቀደም ለታ ቤቴ ድረስ መጥተው ነበር።» አለ አሁንም የፅጌረዳን ስም እንዳይጠራ ኩራት ጨምድዶት።

«እና?......ምን ተባባላችሁ?»

«ምንም አዲስ ነገር የለም። ያው፤ እኔ በዳይ እሷ ተበዳይ መሆናችንን ሊያሳምኑኝ ነበር የመጡት።......»

«እና......አመንካቸው ወይስ?.....»

ወንዳፍራሽ እልሁ እንደገና ከውስጥ አገረሸበት። ሆኖም በጠዋት የጀመረውን መንገድ ለመጨረስ ዕልሁን መዋጥ ነበረበት። ለኤርሚያስ መልስ ሳይሰጠው በዝምታ የውስጥ ስሜቱን ሲታገል ቆየ።

«እኔም ብሆን ከአሁን በፊት ከተነጋገርነው ሌላ ምንም አዲስ መፍትሔ ልፈጥርልህ አልችልም። - መፍትሔው ከሮዛ ጋር ያለህን የግንኙነት ገመድ በጥሰህ ከፅጌረዳ ጋር መታረቅ ብቻ ነው!......»

«ይገባኛል።......ግን እንዴት አድርጌ ነው ለሮዛ የምነግራት?! በህይወቷ የምፈርድ እኮ ነው የሚመስለኝ.....ሶስት ጊዜ ያህል ልነግራት ወስኘ ሂጄ አጠገቧ ስደርስ አቃተኝ።......አየህ ኤርሚያስ፤ አንተ ሮዛን አታውቃትም።.......»

«አውቃታለሁ። ምን ያህል እንደምትወድህም ለመገመት ችያለሁ። አንተም የዚያኑ ያህል ትወዳት ይሆናል። ነገር ግን እንዲህ ዓይነቱን መሠረት - አልባ ፍቅር አዝኖ ከማፍረስ ሌላ ምርጫ የለም። ሮዛ ነጠላ በመሆኗ የግል ውሳኔ መወሰን ትችላለች፤ አንተ ግን ባለ ትዳርና የልጆች አባት ነህ። ውሳኔህ የሚጠቅመውም ሆነ የሚጎዳው አንተን ብቻ ሳይሆን ቤተሰብህንም ጭምር ነው።......»

«ይህ ሁሉ አላጣሁትም እኮ፤ ኤርሚያስ......»

«እሺ እንግዲያው፤ በይሉኝታ ተይዘህ ከሆነ፤......ልብህ ለመቁረጥ ወስኖ አፍህ ብቻ መናገሩን ከፈራ......የሮዛን ጉዳይ እኔ ልጨርስልህ እችላለሁ።»

«እንዴት አድርገህ?......»

«እሱን ለእኔ ተወው።»

«እ - ምልህ.....ውሳኔዬ ሳይጎዳት፤ ጥላቻ ወይም ቂም ሳታረግዝ የምንለያይበት መንገድ ቢሆን ጥሩ ነው።......» አለ የሮዛ ስሜት ሲጎዳ ከወዲሁ እየታየው ልቡን ጨንቆት።

«መቼም ተፋቅረው ቆይተው ሲለያዩ ልብ መቁሰሉ የማይቀር ነገር ነው። የሚወዱትን ነገር ማጣቱ ራሱ የልብ ህመም ነው። ሆኖም የመለያየቱ ምክንያታዊነትና

የጊዜ ብዛት ቀስ በቀስ ቁስሉን እያሻሩት ይሄዳሉ የሚል ግምት አለኝ።» አለ ኤርሚያስም የወንዳፍራሽ ፍራቻ ተጋብቶበት።

«ይቺ ሮዛ ግን ምን አይነቷ ሴት ነች?!......» አለች ዘኒ በርቀት ተቀምጣ ጨዋታቸውን ስታዳምጥ ከቆየች በኋላ፤ «ባልና ሚስት ስታጣላ አታፍርም እንዴ?!.....»

«አሁን በቃ ወንዳፍራሽ ከፅጌረዳ ጋር ለመታረቅ ዝግጁ ነው። ይልቅ የፍንጥር ጥሩ ሻይ አፍይልን።» አላት ኤርሚያስ ነገሩን ለማሳጠር አስቦ።

ዘኒ ወደ ታዘዘችበት ገባች።

«አየህ ወንዳፍራሽ፤ የአንተና የፅጌረዳ መታረቅ የብዙ ምቀኞችን ልብ እንደሚሰብር ማወቅ አለብህ። ሮዛ ልጅ እንዳረገዘችልህ ተደርጎ የተወራው ፀባችሁን ለማክረር ሆነ ተብሎ ነው።......»

«ማነው ግን ይህን የሚሰራው?! እኔ'ኮ የፅጌረዳ ያልተጨበጠ ግምት መስሎኝ ነበር።.....»

«አይደለም!......ሥራዬ ብለው ነግረዋት ነው። ጠላቶችህን ወደ ፊት ታውቃቸዋለህ። ያንተን ድክምት ምክንያት አድርገው ሚስትህን ለማስኮብለል የሚፈልጉ አሉ። አንተና ፅጌረዳ በዕልህ የምትጫወቱት ድብብቆሽ በፍጥነት ማክተም አለበት።» አለው ግንባሩን ቋጥሮ።

ወንዳፍራሽ በትዳሩ ዙሪያ የሚገኙትን ጠላቶች አስቦ ለማግኘት በሚስጥር ስሜት ለተወሰኑ ደቂቃዎች በሀሳብ ሲዋዥቅ ቆየ። ስለሲሁ ጉዳይ ብዙም አስቦ አያውቅም ነበር። ፅጌረዳና እሱ በጊዜው በተፈጠረው ችግር መጣላታቸውን እንጂ፤ የፀቡ መክረር የባዕድ እጅ እንዳለበት አላወቀም፤ ወይም አልጠረጠረም። አሁን፤ በስተ መጨረሻው፤ አዲስ ቁስል ሆኖ ታየው። ነገር ግን ተራ ጥራጥሬ ካልሆነ፤ ያንን የባዕድ እጅ በውል ማግኘት አልቻለም።

«እንዲያው ለነገሩ.....እስቲ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ?» አለው ኤርሚያስ፤ ወንዳፍራሽ የገባበትን ሀሳብ ሳያጤን።

«ምን?» አለ ወንዳፍራሽም፤ ከሀሳቡ በመባነኑ ተደናግጦ።

«እንዲያው ለነገሩ.......ፅጌረዳን የመሰለች ሚስት እያለችህ ሌላ ፍቅር ያስጀመረህ ሚስጥር ምንድ'ነው?»

«በፍቅር ላይ ፍቅር ነዋ!......» አለ ወንዳፍራሽ ፈገግ ለማለት እየሞከረ።

«ቀልዴን እኮ አይደለም።.....ማለቴ፤ የፅጌረዳ ፍቅርና ታማኝነት ሳያንስህ ልብህ እንዴት ሌላ ሊያፈቅር ቻለ?......»

«ተወኝ እባክህ.....ለራሴም እንቆቅልሽ ነው።»

«......የድፍረት ባይሆንብኝ......የግብረ ሥጋ ግንኙነታችሁ ሁኔታ እንዴ ነው?......»

«አይ ኤርሚያስ! ደሞ አልጋችን ላይ ወጣህ?!.....»

ዕሁድ ከቀትር በኋላ ኤርሚያስ ተልዕኮውን ለመፈፀም ቅድመ - ዝጅቱን አጠናቆ ተቀመጠ። በዘጠኝ ሰዓት ላይ ትውሲትን ቤቱን ድረስ ቀጥሮአታል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ዳኒና ዘኒ ደግሞ ወደ ሮዛ ቤት እንዲሄዱ አዘጋጅቷቸዋል። ታክሲ የሚይዙበትንና ከታክሲ ወርደው ወደ ሮዛ ቤት የሚታጠፉበትን መንገድ አንድ ቀን ቀደም ብሎ አሳይቷቸዋል። የመነቃቂያቸው ሰዓት ሲደርስ ሁለቱ ህፃናት በችኮላ የመቁነጥነጥ ስሜት አሳዩ።

«ሰዓታችን እኮ ደርሷል።......እንሂድ እንጂ።» አለ ዳኒ፤ ከኤርሚያስ ፊት ቆሞ።

«እሺ ትሔዳላችሁ።.....እንግዲያ ዳኒ፤ ያው እንደነገርኩህ ለሮዛ የጥላቻ ፊት ማሳየት የለብህም። እሺ?»

ሰሞኑን ሲመከረውና ሲያሰለጥነው የቆየበትን ጉዳይ አሁንም በፍርሃት ደገመለት። ትንሹ ቆቅ በእሺታ ሱን ነቀነቀ።

«ከታክሲ ወርዳችሁ አስፋልቱን ስታቋርጡ ደግሞ ቀስ ብላችሁ።......መቸኮል አያስፈልግም። ዘኒ መቸም ይህን ጥንቃቄ ማድረግ የሚያቅትሽ አይመስለኝም።»

«ውይ! ደሞ ያቺን አስፋልት መሻገር ሊያቅተን?!....» አለች ዘኒ በኩራት መንፈስ።

«እሺ፤ በጣም ጥሩ።......ይህንን ደብዳቤ እንደታሸገ ለሮዛ ትሰጧታላችሁ። ሚስጥር ስለሆነ ከፍታችሁ ማንበብ የለባችሁም።»

በፖስታ የታሸገውን ደብዳቤ አስይዞ ሁለቱን ህፃናት ሸኛቸው።

ታክሲ አስከሳፈሩ ድረስ ዘኒ ታላቅነቷን ለማሳየት ወይም ባለ አደራነቷን ለመወታት የዳኒን እጅ ያዝ ስታደርግ፤ እሱ ደግሞ እንደ ልማዱ ታናሽነቱን ላለመቀበል እጁን ያሸሽ ነበር። ታክሲ ውስጥ ገብተው ከተቀመጡ በኋላ፤ በፍቅር ስሜት ክንዱና ትከሻው ላይ ጣል ስታደርግ ግን በደስታ የበለተ ተጠጋት። ባለታክሲው ልጅነታቸውን ተመልክቶ በጨዋታ አይነት የቆጥ የባጡን ሲጠይቃቸው በየዋህነት የምትመልሰው ዘኒ ነበረች እንጂ ዳኒ በኩራት መልስ ለመስጠት እንኳ ተቆጠበ።

ኤርሚያስ ያሳያቸውን ምልክቶች አስታውሰው ትክክለኛው ቦታ ከታክሲ ወረዱ። ወደ ኮረኮንቹ ከገቡ በኋላ ግን ሁለት መንትያ መታጠፊያዎች ስለ ነበሩ ትንሽ ግር አላቸው።

«በዚህ በኩል መሆን አለበት።.....» አለች ዘኒ አንዱን መታጠፊያ እያሳየች።

«አይደለም ዘኒ። በዚህኛው በኩል ነው። ያቺን ሱቅ እንኳን ምልክት እንድትሆነን ኤርሚያስ ሳይቶን አልነበረም?......»

«አሃ!......እውነትም......»

ዳኒ በመራው መታጠፊያ ሲገቡ የሮዛን ቤት የውጭ በር በርቀት ስለተመለከቱ ደስ አላቸው። የበሩ ቀለም በአካባቢው ካሉት የተለየ ስለ ነበር ለማግኘት አላስቸገራቸውም።

ዳኒ በወሬ ብቻ የሚያውቃትን፤ ለእናትና አባቱ ፀብ ምክንያት የሆነችውን፤ ሮዛን፤ በዐይነ ሥጋ ለማየት ጓጓ። ዘኒ በሩን ስታንኳኳ እሱ ሮዛን ቀድሞ ማየት የሚችል ይመስል፤ በበሩ ቀዳዳ አጨልቆ ወደ ውስት ሲመለከት ቆየ ፡

አዛውንቱ ዘበኛ በሩን ከፍተው አንገታችውን ብቅ አደረጉ።

«ሮዛ አለች?» በማለት ሁለቱ ህፃናት በአንድ ድምፅ ጠየቁ።

«አዎ አለች። ከየት ነው የመጣችሁት?......» አሉ ሽማግሌው።

«ከ....ተልከን ነው።» አለች ዘኒ።

«ማን ነው የላካችሁ?»

«ኤርሚ።»

«ኤርሚ?......ማነው እሱ?!......»

«ሮዛ ታውቀዋለች።.....»

ዘበኛው ልጆቹን ወደ ውስጥ አስገብተው፤ የውጭውን በር መልሰው ዘጉት። ዳኒና ዘኒ በዘበኛው እየተመሩ ሳሎን ገብተው ከተቀመጡ በኋላ ሮዛ ከወደ ጓሮ ተጠርታ መጣች።

«እኔ ጋ ነው የመጣችሁት?» አለቻቸው፤ በጣፋጭ የአነጋገር ስልትና ለልጆች በሚቀርብ ፈገግታ ቀይ ፊቷን አብርታ።

«አዎ፤ አንቺ ጋ ተልከን ነው።» አሉ ሁለቱም በአንድ ድምፅ።

ዳኒ የሮዛ ገፅን ለማየት የነበረው ቂም - አዘል ጉጉት ከውስጥ እየገፋፋው ትክ ብሎ ሲመለከታት፤ እሷም በአስተያየቱ ተስባ ወደ እሱ አተኮረች። ይሄን አንዳች ስሜት ጭንቅላቷን ጠቅ አድርጎ ወጋት፤ የምታየው ልጅ ዓይኖቹ አካባቢ ወንዳፍራሽን ይመስላል። ይበልጥ አተኩራ ስታየው መላምቷ ጎልቶ ድንጋጤ ሰውነቷን ወረረው ፡ በእጁ የያዘው የታሸገ ደብዳቤ ደግሞ በቅፅበት ውስጥ ብዙ ነገር እንድታነብ አድርጓት የግንባሯን ቆዳ በድንገት ተሸበሸበ።

ዳኒ ደብዳቤውን ሊሰጣት እጁን ዘረጋ።

«ማ - ማን ነው የላካችሁ?......» አለቻቸው፤ ደብዳቤውን ከዳኒ እጅ ተቀብላ፤ ፖስታው ላይ የላኪውን ስም እየፈለገች።

«ለሮዛ መክብብ» የሚል ፅሁፍ ብቻ አገኘች። የላኪው ስም የለም። የእሷም አድራሻ አልተፃፈም። በእጅ እንዲሰጣት የተዘጋጀ ደብዳቤ መሆኑን ገመተች። ከየት

እንደተላከላት እንኳ የልጆቹን መልስ ሳትጠብቅ የፖስታውን እጥፋት ተጣድፋ ቀደደችው። ወንዳፍራሽ የስንብት ደብዳቤ በልጆቹ በኩል የላከላት መስሎ ስለ ተሰማት፤ የደብዳቤውን መልዕክት በመፍራት፤ ወይም ለመመከት በሚሞክር ስሜት፤ ስራስሮቿ ከወዲህ ተግተረተሩ።

«እንደምን አለሽ ሮዛ።.......ስምሽን እንደማውቀው ሁሉ ስሜንም ታውቂው ይሆናል። እኔ፤ በርቀትም ቢሆን መልክሽንና ፀባይሽን ጭምር ለማጥናት ችያለሁ። አንቺ ግን ይህን ያህል ስለ እኔ ማወቅሽን እንጃ! ምናልባት ገፄን ካስታወስሽ፤ አንድ ምሽት በጭለማ በራፍሽ ላይ ቆሜ አነጋግሬሽ ነበር። ኤርሚያስ ዘለቀ እባላለሁ። ደብዳቤውን በእጅሽ የሚሰጥሽ ልጅ ደግሞ ዳንኤል ወንዳፍራሽ ይባላል። - የወንዳፍራሽ የበኸር ልጅ!......»

ሮዛ ለአፍታ ያህል አይኗን ከደብዳቤው ላይ ነቅላ ዳኒን ተመለከተችው። የፍቅር ይሁን የጥላቻ ግልፅ ባልሆነ አመለካከት ስሜቷ ተለውጦ፤ እንደገና ወደ ደብዳቤው ተመለሰች -

«ሮዛ፤ የዋህነትሽን፤ ግልጽነትሽንና የፍቅር ሰው መሆንሽን ስሰማ ከልቤ አዘንኩልሽ። ያንቺን ዓይነት ሴት ስሜት መጉዳት ለህሊና ይከብዳል። ነገር ግን የማይቀር ዕዳ ሲሆን ደግሞ ምን ይደረጋል?!......ወንዳፍራሽ አንቺን ማፍቀሩ፤ ወይም አንቺ ወንዳፍራሽን ማፍቀርሽ ጥሎሽ ነው። የሁለታችሁ ፍቅር የሌሎችን ህልውና እስከጎዳ ድረስ ጤናማ ሆኖ ሊዘልቅ አይችልም። ዙሪያውን በበቀል እሳት ይከበባል፤ እና የሰቀቀን ፍቅር ይሆናል። የእናንተ ፍቅር ፅጌረዳን ጎድቶ ከቤቷ አስወጥቷታል፤ ሁለቱን ህፃናት ነጣጥሎአቸዋል። ይህ ችግር ካደገ በግልፅም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጠያቂ የሚያደርገው እናንተኑ ነው። እስቲ አጠገብሽ የቆመውን ህፃን - ዳኒን - ተመልከቺው። የደስ ደስ ያለው ወብ ልጅ ነው፤ ከዚያ በላይ ደግሞ ብሩህ አዕምሮ የያዘ፤ የሐገርና የወገን መመኪያ የሚሆን ልጅ ነው። በእናንተ ፍቅር ምክንያት ከእናቱ ተነጥሎ ካደገ ስንኩል አዕምሮ ይዞ ከወጣ ግን፤ የሐገር ሸክም፤ የህብረተሰብም ጠንቅ ይሆናል። ቂም አርግዞ የሚያድግ ጭንቅላት አደገኛ ነው። በመሠረቱ፤ የከፋ ችግር ካልተከሰተ በስተቀር፤ ልጆች በእናትና በአባታቸው መዳፍ ውስጥ ማደግ አለባቸው። ይህን ፍቅርና እንክብካቤ ሲያገኙ ነው እነሱም የወገን ፍቅር የሚኖራቸው። እና አሁን፤

የዚህ ህፃን የወደፊት ህይወት በከፊል በአንቺ ውሳኔ ላይ ወድቋል። አጠገብሽ ቆሞ ውሳኔሽን ይጠብቃል።......

«ወንዳፍራሽ እንደሚወድሽ ነግሮኛል። የንጹህ ፍቅርሽና የየዋህነትሽ ምርኮኛ ሆኖ ቆይቷል። በፍቅርሽ ታውሮ፤ ሚስቱ የቤቱን ምሰሶ እንድትነቃነቅ ጋብዟታል። አሁን አይኑን ሲገልጥ ግን ፍቅራችሁ በባዶ መሠረት ላይ እንደ ተገነባ ተገነዘበ። ህይወቱን ሙሉ ለፀፀት የሚዳርጉት ሁኔታዎች መሠረታቸውን እየጣሉ መሆኑ ገባው። እና፤ እየተፋቀሩ መለያየት አስፈላጊ መሆኑ ታየው። ነገር ግን ይህን አቋሙን ለአንቺ ለመንገር ፈራ። ምክንያቱም፤ ከላይ እንደገለፅልሽ፤ የአንቺ አይነት የየዋህ ሴት ስሜት መጉዳት ይከብዳል። ወንዳፍርሽ አሁንም ያከብርሻል አሁንም፤ ያፈቅርሻል። በአንቺ ፊት መግለፅ ያቃተውን ይህን ስሜቱን እንዳስተላልፍለት ወክሎኛል።......

«እንግዲህ ጠንከር በይ ሮዛ። በፍቅር የታወሩ ዓይኖችሽን ለአንድ አፍታ ገልጠሽ፤ በፍቅራችሁ ዙሪያ ያቆጠቆጠውን ማህበራዊ እሾህ ተመልከቺው። በፍቅር የተደፈነ ልብሽንና አዕምሮሽን ከፍተሽ አመዛዝኚበት። በቅርበትና በዕልህ ሳይሆን፤ በርቀትና በአትኩሮት ተመልከቺ። ጊዜያዊ የስሜት እሳት ለዘለቄታዊ አስተውሎት ቦታውን ይልቀቅ። ከፀፀት ለማዳን ጊዜያዊ የስሜት እሳትን ረግጦ መሰቃየት የግድ ይሆናል።......

«በኔ በኩል ጨረስኩ። አጠገብሽ የቆመው ህፃን ግን በህይወቱ ላይ የምትሰጪውን ውሳኔ እየጠበቀ ነው። ውሳኔሽ የወደፊት የህይወት መስመሩን ሊያለማውም፤ ሊያጠፋውም ይሽላል። ውሳኔሽ ካለማው እሱም አልሚ ይሆናል፤ ውሳኔሽ ካጠፋው እሱም አጥፊ ይሆናል። - ምርጫውን ላንቺ ትቼዋለሁ።.......

አክባሪሽ፤ ኤርሚያስ ዘለቀ።»

የደብዳቤው መንፈስ ልቧን እያቆሰለና እያከመ አንብባ ጨረሰችው። ለጊዜው የተዘበራረቀ ስሜት ተሰማት። በአንድ በኩል የፍቅር ዕልህ ሲታገላት፤ በሌላ በኩል ደግሞ የደብዳቤው ክብደት የፈጠረባት ፍርሐት ልቧን አንቀጠቀጠው። አንዳንድ ጠንከር ያሉ ሐረጎች በፍቅር እሳት የታወሩ ዓይኖቿን ቢገልጥላትም ቅሉ፤ እውነታውን አሜን ብላ መቀበልና መወሰን ከበዳት። ልዩ ሚስጥር ታገኘበት ይመስል «......እየተፋቀሩ መለያየት!» የሚለውን ሐረግ ደጋግመማ ተመለከተችው።

በሀሳብ ተወጥሮ የፈዘዘ ገጿ ሳይፈካ፤ በዝግታ ደብዳቤውን አጥፋ ዓይኖቿን ወደ ልጆቿ መለሰች። የዳኒ ዓይኖች በአይኖቿ ላይ ሲቁለጨለጩ፤ እውነትም ውሳኔዋን የሚጠበቅ ይመስል ነበር። ዓይኖቿ ብልቃጥ ሆነው፤ በአዕምሮዋ ስትመለከተው፤ ዳኒ የሚያሳዝን ትንሽና ውብ ፍጥረት መሆኑ ቀርቶ፤ የሚያስፈራ ግዙፍ ፍጥረት ሆኖ ታያት። የእናቱን በደል የመበቀል ስሜት በገጹ ላይ የምታነብ መሰላት።

ዳኒም ኤርሚያስ በመከረው መሠረት በሮዛ ላይ ያለውን ጥላቻ ለመደበቅ ቢሞክርም፤ አልፎ አልፎ የውስጥ ስሜቱ እያሸነፈው ዓይኖቹን አፍጥጦ ፊቱን ማሻከሩ አልቀረም።

«አንቺስ......ስምሽ ማነው?» አለች ሮዛ፤ ከዳኒ ጋር የገጠመችውን የዓይን ጦርነት በመሸሽ ዓይነት፤ ወደ ዘኒ እየተመለከተች።

«ዘነበች ፀሐይ።» ስትል ዘኒ መለሰች።

እሷም ብትሆን በሮዛ ላይ ያላትን ጥላቻ ሙሉ በሙሉ መደበቅ አልቻለችም። ለፅጌረዳ እና ለወንዳፍራሽ መጣላት ምክንያት የሆነችው ሮዛ ነች የሚለው ስሜት ቀድሞ አዕምሮአቸው ውስጥ ስለ ተፃፈ፤ የኤርሚያስ ምክር የልጆቹን ጥላቻ በአንዴ መፋቅ አልቻለም።

«አቶ ፀሐይ ማለት......»

«ኧረ!......ወይዘሮ ፀሐይ ነች እናቴ።»

«ታዲያ......በናትሽ ስም ነው እንዴ እምትጠሪው?»

«አዎና!......»

«ለምን?......አባትሽስ?......»

«አባት የለኝም።.....የሚያሳድገኝ ኤርሚ ነው። ነገር ግን ወላጅ አባቴን በማጣቴ ሁልጊዜ አዝናለሁ።» አለች፤ እንደወትሮዋ ውብ ዓይኖቿን ፊት ለፊት እያንከባለለች ሳይሆን፤ በትካዜ መሬት መሬቱን እየተመለከተች።

«ወንጼና ፅግዬ ተጣልተው ከቀሩ እኔም ወደ ፊት እናት አይኖረኝም። ሰብለ ደግሞ አባት አይኖራትም።» አኔ ዳኒ ጣልቃ ገብቶ።

ሁለቱም ልጆች በኤርሚያስ ተመክረው፤ ተዘጋጅተው የመጡ መሆናቸውን ሮዛ ገመተች። ይሁንና የልጆቹ ውበት ከአንደበታቸው ጣፋጭነት ጋር ተደምሮ አንዳች ሆዷን የሚያንቦጨቡጭ ስሜት ፈጠረባት። ልጆቿ አጠገብ ተቀምጣ፤ ዳኒን ጭንና ጭኗ መሐል አስገብታ፤ እቅፍ አድርጋ ግንባሩን እየሳመች ለማጫወት ልቧ እየከጀለ፤ ነገር ግን የባዕድነትና የፍርሃት ስሜት ወደ ኋላ እየጎተታት፤ እንዲሁ ፍዝዝ ብላ ስታየው ቆየች።

«በቃ......እንሂድ?» አለች ዘኒ፤ ፈቃድ በመጠየቅና በመወሰን መሐል የሚወላውል ድምፅ።

«ቆይ እንጂ......ገና ሻይ ተፈልቶ ተጥታችሁ፤ ብስኩት በልታችሁ ነው የምትሄዱት።» አለችና ሮዛ ወደ ኋላ የጨመደዳትን ስሜት ታግላ አሸንፋ ዳኒ አጠገብ ሄዳ ተቀመጠች።

ዳኒ፤ የመሸሽም ሆነ የመቅረብ እንቅስቃሴ ሳያሳይ፤ በነበረበት ረጋ። ሮዛ፤ ከእጇ ተመንጭቆ እንዳያመልጣት ስትፈራ ስትቸር ቆይታ፤ በዝግታ አንገቱን እቅፍ ካደረገች በኋላ ግንባሩ ላይ ሳመችውና «.....ት - ትወደኛለህ?» በማለት በለስላሳ ድምፅ ጠየቀችው።

ዳኒ ምንም ያህል ጥላቻውን ደብቆ ቢቆይ «እወድሻለሁ።» የማለትን ያህል ቃል ለማውጣት ጉሮሮው እሺ አላለውም። የእናቱን ጣውንት «እወድሻለሁ» ለማለት ጉሮሮውን ስለተናነቀው፤ መልስ በመስጠት ፈንታ ወደ ግድግዳው ባዳነት ይመለከት ጀመር።

ሮዛ ደግማ ጉንጩ ላይ ሳመችውና «......እስቲ እኔ እንደሳምኩህ አንተም ሳመኝ?» በማለት ለመነችው።

«አንድ ነገር እሺ የምትይኝ ከሆነ እስምሻለሁ።......» አላት፤ ዓይኖቹን ከግድግዳው መልሶ በሮዛ ገፅ ላይ እያንከባለለ።

«እሺ የኔ ጌታ፤ .......ምንድ'ነው እሱ?»

«ወንዴና ፅግዬ እንዲታረቁ የምታደርጊ ከሆነ እስማሻለሁ።»

«እሺ ዳንኤል......እንዲታረቁ አደርጋለሁ። በላ ሳመኝ!......»

ግራና ቀኝ ጉንጮቿን አፈራርቃ ስትሰጠው፤ በትንሽዬ ለስላሳ ከንፈሩን ሳማት።

ዳኒ ከሮዛ ጋር መሳሳሙ ዘኒን አናድዷት በአንዳፍታ ስሜቷ ልውጥውጥ አለ። በቅናት ሽፍሽፍቶቿ እየተርገበገቡ፤ ዓይኖቿ የሚያዩትን ነገር ለመሸፈን በደመ ነፍስ ይታገሉ ጀመር።

ሮዛ የዘኒን ስሜት አላጤነችውም። በተመሰቃቀለ የፍቅር መንፈስ የዳኒን ጉንጮች ገመጠቻቸው።

ትውሲት ለዕሁድ ቀጠሮ ዝግጅቷን የጀመረችው ቅዳሜ ከቀትር በኋላ ነበር። ፀጉሯን ተተኩሳ፤ ለፎቶግራፍ የምትመርጠውን ልብሷን አዘጋጅታ፤ የአንገትና የጆሮ ጌጦቿን አውጥታ የዕሁዷን ዘጠኝ ዓመት በናፍቆት ጠበቀቻት። ለስዕል የሚሆን ፈገግታ ለመምረጥ መስታወት ፊት ቆማ በማለማመድ ያጠፋችው ጊዜም ቀላል አይደለም። ዝግጅቷ ለምስል - ሰዕሉ ብቻ ሳይሆን ሰዓሊውንም ለመሳብ ነበር።

ኤርሚያስ ስልክ ደውሎላት መኖሪያ ቤቱ ድረስ እንድትመጣ ከቀጠራት ጀምሮ መንፈሷ በራሷ ህልም ውስጥ ሲወራጭ ከርሟል። አንዳንዴ ብቻዋን በምትሆንበት ጊዜ ቀጠሮውን ታስታውስና ‹.....አሁን ሌላ ቦታ አጥቶ ነው ቤቱ ድረስ የቀጠረ? አዬዬ! የስዕሉን ካሳ እዚያው ቤቱ ውስጥ ሊያካፍለኝ ነው እንጂ.....በደንብ አድርጎ ከሳለኝ እቸገርለታልሁ።......ከዚያ በኋላ......አንዴ ከቀመሰ በኋላ፤ በጠራሁት ጊዜ ሁሉ ከተፍ ይላታል። እና፤ በምፈልገው ዓይነትና ውበት ሲስለኝ ይኖራል።......› እያለች ታስባለች። ኤርሚያስ በፍቅሯ ቅጥል ብሎ፤ ያልሆነችውን እያደረገ ሲስላት፤ ሲያስውባት...... የምስሏን ቅጂ ቤቱ ውስጥ ሰቅሎ፤ ከስዕሎቹ ሁሉ በላይ ሲያመልክባት ይታያታል።.......

ዕሁድ ቶሎ ባይደርስ ኖሮ በምኞት ብቻ ፍንድታ ትሞት ነበር።

ከቀጠሮዋ አምስት ደቂቃ አለፍ አድርጋ ኤርሚያስ ቤት ደረሰች። የተነገራትን ምልክት አስታውሳ ልደታ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ከደረሰች በኋላ የኤርሚያስን ቤት ማግኘት ከባድ አልነበረም። እሱም ልጆቹን ታክሲ አሳፍሮ ወደ ሮዛ ቤት ከላካቸው ጀምሮ የውጭው በር ላይ ቆሞ እየጠበቃት ነበር።

«የቤቱን ማግኘት እንዳላስቸገረሽ እርግጠኛ ነኝ።» አላት ሰላምታ ተለዋውጠው ወደ ግቢው ሲያመሩ።

«እንዲያውም!.....ግልፅ ቦታ ነው ያለህው። እድለኛ ነህ። የኔን ቤት ብታየው። ......ጉራንጉር ውስጥ ገብቶ ነው።» አለችው፤ ከፊቷ አስቀድማው ወደ ቤት ውስጥ እየገባች።

የኤርሚያስ አነጋገርም ሆነ አረማመድ ከወትሮው የተለየ ባይሆንም፤ የትውሲት ግን እሷን በማግባቱ የሚርበተበት ሆኖ ታያት። ለአንዳንድ ወንዶች አዲስ ሴት ሆና ስትቀርባቸው፤ ወረታቸውን እስኪጨርሱ ድረስ፤ የሚያአዩትን መርበትበት ታውቃለች። «እንኮኮ ልሽከምሽ» የሚሉ አሉ፤ «በአንቀልባ ልዘልሽ» የሚሉ አሉ «ጥፍሮችሽን ልቁረጥልሽ» የሚሉ አሉ፤.....አንዳዶች ደግሞ ሴቷ አጠገባቸው በምትሆንበት ጊዜ፤ በስሜት ብዛት፤ የሚያደርጉትን አጥተው፤ ፍዝዝ፤ ድንግዝ ብለው ደረቅ ምራቃቸውን እየዋጡ የሚመለከቱ አሉ። ኤርሚያስ ከየትኞቹ ወገኖች እንደሆነ ለማወቅ ጓጓች። ፂሙን ያለመላጨቱ፤ ፀጉሩን ያለማሳጠሩና ልብሱን ያለመቀየሩ እምብዛም አላናደዳትም። ብዙ ወንዶች ለሴት ግድያ ሲዘጋጁ የሚያጠልቁትን ጭምቡል ኤርሚያስ ያለማድረጉ፤ ሙያው በስብዕናው ላይ የፈጠረበት ችግር መሆኑን በመገመት ተፅናናች እንጂ፤ ናቀች ብላ አልተቆጠረችም። ይህም ፀባዩ ቢሆን «ትማስ ወርቋን» ቀምሶ በእሷ ቁጥጥር ስር ከዋለ በኋላ የሚታረም ጉዳይ መሆኑን ተስፋ በማድረግ ተኩራራአች።.....

«ሻይ ላፍላልሽ ወይስ ቡና?......» አላት ኤርሚያስ ከፊት ለፊቷ ቆሞ።

«ውይ!....ደሞ የምታፍላው አንተው ነህ እንዴ? ወንድ ያፈላውን ከምጠጣስ ይቅርብኝ።»

«ሠራተኛዬ ሥራዋን አጠናቃ ሄዳለች።.......ከፈለግሽም ለስላሳ መጠጥ ወይም ቢራ ይኖረኛል።»

«ለስላሳው እንኳ ይሻላል እንጂ!.....ቢራ አጠጥተህ የምታነሳኝ ስዕል ታየኝ እኮ!.......»

«የለ፤ ስራ ከመጀመራችን በፊት ትንሽ ትጫወቺ እንደሆነ ብዬ ነው።» አላት በደረቅ ፈገግታ።

«መጀመሪያ ስራ!.......ቢራና ጨዋታ ከስራ በኋላ ይሻላል።» አለችው፤ ስሜቱን ለማጥናት እንቅስቃሴውን እየተከታተለችና በዝግታ እየሳቀች።

ለስላሳ መጠጥ ከማቀዝቀዣው ውስጥ አውጥቶ ካቀበላት በኋላ ወደ ስዕል ክፍሉ ገብቶ በቀለማት የተዥጎረጎረ ጋዋኑ ለብሶ ወጣ። ትውሲት ለስላሳዋን እየተጎነጨች የሣሎን ዕቃዎች አንድ በአንድ ስትቆጥር ነበር የቆየችው።

«የቤትህን አደረጃጀት ሲያዩት፤ አንድም ነባር ወንደላጤ.......ካለዚያም ፈት መሆንህ ያስታውቃል።» አለችው፤ የሳሎን ዕቃዎች እርጅና ለመጠቆም።

«የመጀመሪያ ልክ ነሽ።» አላት፤ ስሜት በሌለው የአነጋገር ስልት።

«......ግን ለምን አላገባህም?»

«የተጋቡት ሲፋቱ እያየሁ እንዴት ብዬ ላግባ?!......»

«እም!.......እሱስ ልክ ነህ።......» አለችና መናገር የፈለገችውን ሁሉ ለስላሳ መጠጡን ተጎንጭታ አወራረደችው።

«......እንዳልሽው፤ ጨዋታውን በኋላ ብናደርገው ይሻላል መሰለኝ። አሁን ወደ ስዕሉ ክፍሌ እንግባና ስራችንን እንጀምር።»

«በደስታ!» ብላ ከተቀመጠችበት ብድግ አለች።

የኤርሚያስ ስሜት - ዓልባ የሆነ ንግግርና እንቅስቃሴ የትውሲትን ምኞት አልገደለውም። ይልቁንም ከውስጥ የሚቃጠል ስሜቱን አፍኖ ለመደበቅ የሚታገል

መስሏል አዘነችለት። አሁን ከሳለኝ በኋላ «መኝታ ቤቴን ላሳይሽ» ብሎ መቅለስለሱን ሳይቀር......ደርሶ መጀነኑ ያዋጣ መስሎታል!» አለች በልቧ።

ስዕል ክፍሉ ውስጥ ከገቡ በኋላ በሩን ከውስጥ ቆልፎ መቀመጫዋን በእጁ አሳያት። እሷ ግን ክፍሉን በሞሉት ስዕሎች ተመስጣ ግራ፤ ቀኙን በማማተር ላይ ስለ ነበረች ኤርሚያስን አልተከታተለችውም። ደስ ያሰኛት ግልፅ ሆነው የወጡት የሰውና የአራዊት ስዕሎች ናቸው እንጂ፤ እንግዶቹ ረቂቅ ስዕሎች እንዲያው በቀለም ብዛት መጫወት መስለ ታዩዋት።

«ይቺን ሴትዮን ደሞ ምነው ራቁቷን አደረካት?» አለችው፤ ‹ሔዋን 1999› የተሰኘው ጅምር ስዕል አትኩራ እየተመለከተች።

«ልብስ ለመግዛት ገበያ መውጣት አቅቶኝ ነው።» በማለት ደረቅ ቀልድ ቀለደ።

«አሄሄ!.......ጡቷንና ጭኗን እያየህ ስትመረቅን ለመኖር ነው እንጂ!.....»

ትውሲት ማከላላቷን ጀመረች። ኤርሚያስ ግን ሸራውን ወጥሮ፤ በብሩሹ የተለያዩ ቀለማት እያጠቀሰ በመምረጥ ላይ ስለነበር አላስተዋላትም። ጀርባውን ሰጥቷት የምትናገረውን ይሰማል እንጂ አያጤነውም።

«አርዕስቷ ደግሞ የሚገርም ነው። - ‹ሔዋን 1999› ገና ያልተፈጠረች ሴት ነው እንዴ የሳልከው?......»

«እኔ ራሴ ፈጣሪ ነኝ እኮ!.......አልመስልም አንዴ?!»

«ድንቄም!........»

«ይልቅ ቁጭ በይና ስራችንን እንጀምር።......»

የተወጠረውን የስዕል ሸራ ከተንቀሳቃሽ ሰሌዳው ጋር አያይዞ ከትውሲት መቀመጫ በፊት ለፊት ቆመ። ትውሲት የኤርሚያስን ፊትና የስሌዳውን ጀርባ እንድታይ ሆና ተቀመጠች።

«የመህ ነው እንዴ የምትስለኝ?»

«አዎ፤ ቁጭ ብዬ መንጠራራቱማ አይመችም።»

«ውይ! ይሄማ በጣም ያደክምሃል?»

«ግድየለሽም፤ እንዴ ፈጠራ ሰገነት ላይ ከወጣው አይደክመኝም።»

«ለመሆኑ የምትስለኝ ሙሉ ነው ጉርድ?»

«የፈለግሽውን.......»

«እኔማ......አንተን ማስቸገር ባይሆንብኝ፤ ሙሉ ቢሆን እመርጣለሁ።»

«እናደርገዋለና፤ ምናልባት........»

«እንግዲህ ይሄውልህ......እንዲህ ሆኘ ነው መነሳት የምፈልገው።......» እያለች፤ ቀኝ እግሯን ግራ እግሯ ላይ ደርባ፤ ከወገቧ በላይ ያለውን ሰውነቷ ፊት ለፊት፤ ከወገቧ በታች ያለው ሰውነቷ ደግሞ የጎድን እንዲታይ ሆና ተቀመጠች።

እግሯቿን አነባብራ ስትቀመጥ፤ ገና ከጠዋቱ የተዘጋጀችበት አጭር ቀሚስ ዳሌዋ ላይ ቀርቶ፤ ቀኝ ጭኗ እርቃን ወጣ። እሷም የፈገለችው ይህንንኑ ነበር።

ኤርሚያስ ብሩሹን እንደያዘ፤ ድንገት አይኑ ላይ ያፈጠጠበትን ጭንዋን እየተመለከተ፤ ወንድነቱ እየተፈታተነው፤ የደም ስሮቹ እያበጡ ሲሄዱ እየተሰማው፤ ለአፍታ ያህል ፍዝዝ ብሎ ቆየ።

«ምነው ፈዘዝክ?......» አለችው፤ ትውሲት በአይኖቿ አይኖቹን ተከትላ፤ ጭኗን እንደ አዲስ ነገር እያየችና በልቧ እየሳቀች።

ኤርሚያስ መልስ አልሰጣትም። የጭኗ እይታ የፈጠረበትን ስሜት በመታገል ላይ መሆኑን ገመተች።

«ምንድ'ነው እሱ?......ሁሉንም ነገር በኋላ ትደርስበታለህ። አሁን ስራህን ስራ።» አለችው በቀልድ ቅላፄ።

ኤርሚያስ ቀልዷን እንዳልሰማ ሆኖ፤ ስሜቱን ረግጦ፤ ዓይኖቹን ከጭኗ ላይ ከነቀለ በኋላ ስራውን ጀመረ።

«ፈገግታዬ እንዴት ነው?.......»

«ጨልሟል፤ ያንቺ አይመስልም። እንደወትሮሽ ጥርስሽን ገለጥ አድርገሽ ብትስቂ ይሻልሻል።»

ጥርሷን ገልጣ፤ አይኖቿን ወደ ሰዓሊው አፍጥጥጣ ሳትነቃነቅ መቆየቱ አስጨነቃት። በተለይም ጥርሷን ገልጣ የምታሳየውን የግድ ሳቅ የማግጠጥ ያህል ሆኖ ስለ ተሰማት፤ ጆሮዋ የሰዓሊውን አስተያየት እየጠበቀ ነበር።

ሰዓሊው ግን ቀለሙን በብሩዙ እያጠቀሰ ሸራው ላይ ከመነታተብ በቀር ምንም አልተናገረም።

«ሁለት ሰዓት ሙሉ እንደዚህ ሆኘ መቆየቱ ሳያስቸግረኝ አይቀርም።......» አለችው፤ ሰውነቷን ሳታንቀሳቅስ፤ አፏን ብቻ እያነቃነቀች።

«የለም፤ ሁለት ሰዓት አይፈጅብንም። አንዴ ንድፉን ከጨረስኩ በኋላ አንቺን መላልሶ ማየትም አያስፈልገኝም። አሁን የሰውነትሽን ቅርፅና መጠን እየነደፍኩ ነው። ከዚያ በኋላ የማቅለሙንና ውስጣዊ አንቺነትሽን የማውጣቱን ጉዳይ ለኔ ትተይዋለሽ። :.....ስለማውቅሽ አያስቸግረኝም።»

«በል እሺ እንዳልክ.......»

«ደሞ ዘና ብለሽ ተቀመጪ። ራስሽን ድርቅ አድርገሽ አታስጨንቂው። በተቀመጥሽበት ብትንቀሳቀሺም ትሽያለሽ።»

«ስዕሉ እንዳይበላሽብህ ብዬ ነዋ.......»

«ብሩሽ እኮ ነው የያዝኩት። - ካሜራ አይደለም።»

«ዋ! ብቻ.......ታበላሸኝና እንጣላለን........»

ኤርሚያስ ዝም ብሎ መሣሉን ቀጠለ። ልክ ወንበሩ ላይ እንደተቀመጠችው አድርጎ ቅርጿን ካወጣ በኋላ ገጿዋ የእሷን እንዲመስልለት በበቂ ሁኔታ ኳለው። አሳሳቋን እሷ ባሳየችው ዓይነት ሳይሆን፤ እሱ በሚያውቃት ዓይነት አፏን አስከፍቶ በመሳል እንድታከላላ አደረጋት። ግንባሯ ላይ በጥቁት ቀለም አንዳች ምልክት ከሰራ

በኋላ ጭንቅላቷ ላይ ሁለት ቀንዶች ሳለ። የቀንዶቹን ሹል ጫፎች ላይ ቀለም ቀባቸው። የእጆችንም ጥፍሮች በጣም ረዣዥም አድርጎ ጫፎቻቸውን ቀይ ቀለም ነከራቸው።

ይህን ካጠናቀቀ በኋላ ከጀርባዋ የቆመ አንድ ጠና ያለ ሰውና፤ ከፊት ለፊቷ የቆመች አንዲት ህፃን ነደፈ። ከጀርባዋ የቆመው ሰየው ፀጉሩንና ፂሙን አጨብርሮ ሁለት እጆቹን ወደ ሰማይ አንስቷል። ከፊቷ የቆመችው ህፃን ደግሞ ጥርሶቿን ነክሳ ዓይኑና አፍጥጣባታለች።......

«ጨርሻለሁ። መነሳአት ትችያለሽ.......» አላት ኤርሚያስ ስዕሉን ጨርሶ አትኩሮ ሲመለከት ከቆየ በኋላ፤ በረዥሙ ተንፍሶ።

«እፎይ!.......ግልግል።» እያለች ትውሲት ከተቀመጠችበት ተነስታ ስዕሏን በጉጉት ወደ ኤርሚያስ መጣች። ሠሌዳው አጠገብ ደርሳ ሸራው ላይ የተሳለውን ነገር ስትመለከት ግን ፈገግታዋ ሁሉ በአንዳፍታ ጠፋ።

«.......ይህን ያህል ሰዓት ጎልተ'ሽኝ፤ አንተ ስትጫወት ነው እንዴ የቆየ'ሽው?»

«ኧረ ጨዋታ አይደለም።.......»

«ጨዋታ ነው እንጂ!.......ታዲያ ይሄ ሁሉ ዝብርቅርቅ ነገር ምንድ'ነው?.......እኔን የምትስለኝ መስሎኝ እኮ ነው ተጎልቼ የዋልኩት!......»

አድራጎቱን ተመልክታ ኤርሚያስ ጤነኛ ፍጡር መሆኑን ተጠራጠረች። ትንሽ ቀውስ ቢጤ መሰላት። ፊቱን የሞላው ፂሙንና የተንጨባረረ ፀጉሩን ደግሞ አትኩራ ስትመለከተው ቅፅበታዊ ግምቷን አጠናከረላት። ሰው አገኘሁ ብላ «ቀውስ» ቤት በመምጣቷ ዕድሏን ረገመች።

«ምኑ ላይ ነው ጨዋታው?......አሁን ይሄ ስዕል አንቺን አይመስልም?!........እስቲ በደንብ ጠጋ ብለሽ ተመልከቺው። ........አቀማመጥሽ........እግር አስተጣጠፍሽ.......አስተያየትሽ.......የአይኖችሽና የአፍንጫሽ አቀማመጥ.......አሳሳቅሽ.......ከንፈር አገላለጥሽ......»

«እሺ ቆይ........ዓይኖቼና አፍንጫዬ አካባቢ በእርግጥ እኔን እመስላለሁ። የፊቴ ቅርፅም ደህና ተመሳስሎልሃል። የጥርስ አሰካከህም ይሁን ግዴለም።.......አሳሳቁ ግን ፍጹም የዝሙት ሳቅ ነው።......»

ተዋጥቶልኛል በይኛ! አለ ኤርሚያስ በልቡ።

«የአሳሳቁ ባልገረመኝ!.......ይሄ ሌላው፤ ሌላው ደግሞ የምን ቅጥያ ነው?! ይሄ ግንባሬ ላይ የጫርከው ጥቁር ነገር......ጭንቅላቴ ላይ የተተከለው ቀንድ ምንድ'ነው እሱ?.....ጥፍሮቹስ ቢሆን ይህን ያህል ረዣዥሞች ናቸው እንዴ? - የአራዊት ጥፍር ይመስላል!.......ምነው እባክህ! መጫወቻህ.......መሰልኩህ?......ወይንስ አክብሬህ በአንድ ቀን ቀጠሮ ቤትህ ድረስ ስለ መጣሁ መቀለጃ ልታደርገኝ ፈለግክ?!.......»

ለ «ቀውስ» ፊት ማሳየት እንደማያስፈልግ በመገመት ኮስተር ብላ ነበር የምትናገረው። ከዚያም በላይ ንዴቱ ስላለ፤ በማከላላት ፈንታ መወተርተር ጀምራለች።

ኤርሚያስ ግን አንጀሩን ቅቤ እየጠጣ፤ ምንም ዓይነት የገጽታ ለውጥ ሳያሳይና ምንም ሳይመልስላት፤ በዝምታ፤ ፂሙን በጣቶቹ ሲቆፍር ቆየ።

«.......ደሞስ አዲስ ሸራ አጥተህ ነው እንዴ ቀድሞ ሌላ ስዕል በተሳለበት ሸራ ላይ የሳልከኝ!.....ይሄ ጸጉሩን ያጨበረረ ሽማግሌና ይቺ ያፈጠጠች ሕፃን እዚህ ሸራ ላይ ምን ያደርጋሉ?!.........ገና........እንትን ሳንል ይህን ያህል መናናቅን ያሳዝናል።........»

«የለም፤ የተጠቀምኩት እንኳ አዲስ ሸራ ነው። አንጋፋውና ሕፃኑም የተሳሉት አሁን ካንቺው ጋር ነው።» አላት ኤርሚያስ ለመጀመሪያ ጊዜ ድምፁን ሳል - ሳል አድርጎ።

«እሺ እንግዲያው ከየት መጡ?»

«ይሄ እንኳ ጥሩ ጥያቄ ነው። ሁሉንም አንድ ባንድ ላስረዳሽ እችላለሁ። አየሽ፤ የስዕል ጥበብ እንደ ካሜራ አይደለም። የስዕሉ ሚስጥር እንድነግርሽ ከፈለግሽ ራቅ ብለሽ ቁሚ......»

ከኤርሚያስ ንግግር ፍሬ ነገር ይገኝበታል ብላም ባትገምት፤ ሀሳቡ ምን እንደሆነ ለመስማት እየተጀነነች ወደ ኋላዋ ፈንጠር ብላ ቆመች።

ኤርሚያስ ብሩሹን አስቀምጦ፤ የስዕሉን ሸራ ወደ ትውሲት ፊት አዞሮ፤ በመጠቆሚያ እንጨት እየነካካ ገለጻውን ጀመረ። -

«ይህ አንጋፋ ሰውዬና ይህች ቁጡ ሕፃን የኔ ምናባዊ ስዕሎች ናቸው። ሰውየው በሴት አብዶ ጅማ ከተማ ውስጥ ጸጉሩን አንጨብርሮ ይዞራል። ሕጻኗ ደግሞ ልጁ ናት። ነገር ግን አብረው ለመኖር አልታደሉም። ለዚህ ነው፤ እንደ ምትመለከቻት ሕፃኗ ቁጡ የሆነችው። ሰውየው እጁን አንስቶ ከጀርባሽ ሲቀር፤ ሕፃኗ ግን ጥርሷን ነክሳ ከፊት ለፊትሽ ያፈጠጠችበት ምክንያት መዘርዘሩ አስፈላጊ አይመስለኝም።.......»

ንግግሩን አቋርጦ ዘወር ብሎ ተመለከታት። ትውሲት በቆመችበት ቦታ ፍዝዝ፤ ድንዝ ብላ ስዕል መስላለች። ሚዛኗን መጠበቅ ያቃታት ይመስል ዳሌና ዳሌዋን በእጆቿ ደግፋለች። እሷ እየደነዘዘች በሄደች ቁጥር የኤርሚያስ ድምፅ በከፍሉ ውስጥ እየጎላና እየከረረ ይሄድ ጀመር።

«.......እንደምታይው፤ መሐላቸው ተቀምጠሽ የተሳልሽው ደግሞ አንቺው ነሽ። ግንባርሽ ላይ የሳልኩት ጥቁር እንገር ጠባሳ ነው። ግራ እጅሽ ላይ ያለውን ጠባሳ ነው ግንባርሽ ላይ ያመጣሁት። - ሁሉም ሰው ከርቀት ማየት እንዲችል። .......ቀንዱ ባልሽንና ልጅሽን የወጋሽበት ሲሆን፤ ጥፍሮቹ ደግሞ በሌሎች ትዳር ውስጥ ገብተሽ የምትቧጭሪባቸው ናቸው።.........»

የምትለውን ለመስማት ወይም ሁኔታዋን ለማየት እንደገና ፊቱን አዞረ። በቆመችበት ቦታ የጨው አምድ ሆና ቀርታለች። ፊቷ ወዙን ጨርሶ፤ አሸቦ እየነዛበት ሲሄድ ይታያል። ከንፈሮቿ መላቀቅ አቅቷቸው እንደተከደኑ ይንቀጠቀጣሉ። ዓይኖቹ አንድ ቦታ ቡዝዝ እንዳሉ ቀሩ። - ብዙ ዓመት ወደ ኋላ ሄደው ከባሏ ጋር የተጣላችበትን ዕለት እንደ አዲስ እየተመለከቱ ነበር።

በትውሲት ቅብጠትና ንቀት የተብከነከነው ባሏ እጁን ለመሰንዘር አጋጣሚ ነበር የሚጠብቀው። ከቅናቱ ብዛት ገድሏት መሞትን ሁሉ ይመኝ ነበር። እሷ ግን በቅናቱ ተደስታ ታከላላለች እኒ፤ ይህን ያህል ያመርራል የሚል ግምት አልነበራትም።

ከፍቅሩ ይልቅ በቅናቱ ትደሰታለች። ሆነ ብላ እሱን ለማስቀናት የመስሪያ ቤቱና ጎረምሶች መኖሪያ ቤቷ ድረስ እንዲሸኝዋት ታደርጋለች። በቅርብ ከማታውቃቸው ወንዶች ጋር ስታስካካ ትውላለች። በየመንደሩ እየዞረሽ ደግሞ፤ «ይሄ ሽማግሌ እኮ አላስቆም አላስቀምጥ አለኝ። በገባሁበት በወጣሁበት ሁሉ አይኑን ከእኔ ላይ አይነቅም። እንዴት ዓይነት እዳ ውስጥ ነው የገባሁት። እኔ እንዲያው ዕድሌ ሆኖ የሚይዙኝ ወንዶች ይቀኑብኛል። - ይሄንንም ዕድል ብሎት!......መከራ ነው እንጂ!» እያለች ጉራዋን ስትቸረችር ትውላለች። ሰውየው በወሬ በሚስማውም ሆነ በዓይኑ በሚያያቸው ነገሮች ቅናቱ እያደገ ይሄዳል። ስለሚወዳት ጨክኖ ሊፈታት አልቻለም። በዚሁ መሐል አንዲት ሴት ልጅ ትወልዳለች። ሰውየው ቅናቱን እየዋጠ ትንሽ እንደ ኖረ፤ ዓይኑ እያየ ብላዩ ላይ መወሰለት ትጀመራለች።

አንድ ቅዳሜ የት እንደ ሄደች እንኳ ሳትነግረው፤ ውጭ አድራ በማግስቱ ጠዋት ወደ ቤቷ ተመለሰች። ሕጻኗ ከእንቅልፏ አልተነሳችም። ባልየው ሌሊቱን በሙሉ ሲጨስ ነበር ያደረው። ምንም ሳይነጋገሩ፤ የውጭ ልብሱና ቀይራ ጓዳ ገብታ፤ ቢላዋና መክተፊያ ካቀረበች በኋላ ቁርስ ለመስራት፤ ሽንኩርት አውጥታ እየላጠች ትከትፍ ጀመር። ባልየው አንዲትም ቃል ሳይተነፍስ ተከትሏት ጓዳ ገብቶ፤ አጠገቧ ቁጭ አለ። እሷም ‹እንደ ልማዱ ሊጨቀጭቀኝ ነው።› በሚል ንቀት ግንባሯን ቋጥራ ስራዋን ቀጠለች። እሱ ግን አጠገቧ ቁጭ ብሎ ሲያሰላስለው፤ እንዴት እንደሚበቀላት ነእብር ፡

አትኩሮ በዕኩይ መንፈስ ሲመለከታት፤ የምትልጠው ነገር ሽንኩርት ሳይሆን፤ የእሱን ቆዳ መስሎ ታየው። የምትከትፈውና የምትከረትፈውም እየሱኑ ሥጋ መሰለው። - በቅናት ቆዳው ተልጦ፤ ስጋው ተከትፎ አልቋል። ንዴቱ ስላየለበት ረኸም የብቀላ ስልት መንደፍ አልቻለም። ድንገት ግልፍ አለውና፤ ቢላዋ የያዘችበትን ቀኝ እጅዋን ዘልሎ በርግጫ ሲለው፤ ሽንኩርት የያዘችበትን ግራ እጇና ተርትሮ ለቀቀው። ትውሲት ደሟን አያንጠባጠበች፤ እየጮኸች ወጣች። ከዚያ በኋላ ወደ ቤቷ አልተመለሰች። ባሏም አብዶ መንገድ ለመንገድ ይዞር ጀመር። የዚያ ቢላዋ ጠባሳ ግን ህይወቷን ሙሉ አብሮአት ኖረ።

«እንግዲህ የስዕሉ ትንታኔ ይሄው ነው። - ባል ከኋላ ጠባሳና ልጅ ከፊት!......»

ግዳጁን እንደ ተወጣ ጀግና፤ የኤርሚያስ ልብ የደስታ ደም መርጨቱን ጀመረ። ከጫካ ፊቱ ውስጥ የፈገግታ ብርሃን ብልጭ አለ።

የትውሲት ልብ ግን በንዴት ተቃጥሎ እየጨሰ ነበር። ብዙ ተገትራ ከቆየች በኋላ፤ ከደነዘዘችበት ዓለትም ቀስ በቀስ ስትነቃ አይኖቹና ገልጣና ከንፈሮቿን አላቅቃ፤ የርሷ ባልሆነ እንቅልፋዊ ርምጃ ወደ ኤርሚያስ ተጠጋች።

«ኤርሚያስ .......» አለችው፤ በተሸፈነ ድምፅ።

«አቤት.......» አላት እየሳቀ።

«ምን በደልኩህ፤......

«ምንም!......»

«ከአሁን በፊት እኔና አንተ አንተዋወቅም።........»

«አንቺ አታውቂኝም እንጂ እኔ በደንብ አድርጌ አውቄሻለሁ። ሳላውቅሽማ ልስልሽ አልችልም እኮ!.......»

የደከመ ገጽዋን ዓይኑ ስር አስጠግታ እያሳየችው፤ ሁለት እጆቿን ዘርታ ግራና ቀኝ ትከሻውን ላይ አሳረፈች። በአንድ በኩል እግሯ መቆም ስላቃተው እንደድጋፍ እንዲሆናት፤ በሌላ በኩል ደግሞ የኤርሚያስን የፍትወት ስሜት ለመቀስቀስ እንዲያመቻት መሞከሯ ነበር። በእሱ ዓይን ውስጥ ግን ህያውነቷ ጠፍቶ፤ ግዙፍ የወሲብ ዕቃ ሆኖ ነበር የምታየው።

«ኤርሚያስ.....»

«አቤት........»

«ለረዥም ጊዜ የማውቅ የማውቅ ሆኖ ተሰማኝ።»

«ተሳስተሻል ትውሲት።»

ድምጿ እየደከመ ገጿ እየጠወለገ ሲሄድ ፍጹም ሌላ ሴት መሰለች።

«.....ግን፤ ማን ነገረህ ኤርሚያስ?»

«ምኑን?.......»

«የሳልከውን.......»

«ለፈጣሪ አይነግሩትም!.....ጥልቅ ዓይኖች አሉት። ያያል!......»አላት በምፀት ድምፅ። - እንዲሁም ሲያዩሽ እኮ የዕኩይ ምናብ ምንጭ ነሽ፤ ሊላት አሰበና ተወው።

«.....እሺ አንድ ነገር ልለምንህ?......»

«ምንድ'ነው እሱ?.......»

«ተ - ተረትቻለሁ፤ ተንሸንፌአለሁ፤ ከእግርህ በታች ውያለሁ፤ የምትጠይቀኝን ሁሉ ለመፈፀም ፈቃደኛ ነኝ። ግን.....ይህን ስዕል አቃጥለው።»

«አአ! ስዕሉ አይቃጠልም። ለታሪክ ይቀመጣል።»

እሱ የፌዝ ሳቅ የእሳቀ፤ የእሷ አንጀት እያረረ ተፋጥጠው ቆዩ። ከኤርሚያስ ጋር ግብግብ ለመግጠም፤ ሙልጭ አድርጋ ለመሳደብ፤ ተንደርድራ የስዕሉን ሸራ ለመቀዳደድ ልቧ ቢከጅልም፤ ባልጠበቀችው ነገር ድንጋጤ ደንዝዞ የደከመው ሰውነቷ አልፈቀደላትም። እንኳንስ ልትወራጭ ቀርቶ ራሷን ተሸክሞ መቆሙም አቅቷት ነአብር።

«.......እሺ እንግዲያው፤ ከጨንክክ ሸኘኝ። በርህን አስወጣኝ።»

«ጨክኘአለሁ፤ መሔድ ትችያለሽ።»

በደከሙ ዓይኖቿ ያንን ቀንዳም ስዕል የጎድን እየተመለከተች፤ ርምጃዎቿን እየቆጠረች፤ ከክፍሉ ወጣች። ሳሎን አስቀምጣው የነበረውን ቦርሳዋን አንታ ክንዷ ላይ ካንጠለጠለች በኋላ ኤርሚያስን ለመጨረሻ ጊዜ፤ የደከሙ ዓይኖቿን አስለምልማ ተመለከተችው። የልመና፤ የማባበል፤ የመረታት አስተያየት ነበር።

ኤርሚያስ እየሳቀ የሳሎኑን በር ከፍቶ ካስወጣት በኋላ ተከትሏት ሄዶ የውጭውን በር ዘጋው።

እና፤ «ጉሮ ወሸባዬን» እያንጎራጎረ ግቢው ውስጥ ሲንጎራደድ ቆየ።....

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ዳኒና ዘኒ መልዕክታቸውን አድርሰው ሲመለሱ በጉጉት፤

«እንዴት ነው? አገኛችኋት?»

«አዎ፤ አገኘናት። ደብዳቤውንም ሰጠናት። ብስኩትና ሻይም ጋበዘችን።» አሉ ሁለቱ ልጆች እየተቀባበሉና አይኖቻቸውን በደስታ እያቁለጨለጩ።

«በጣም ጥሩ። እኔ ደግሞ......ሠይጣኗን ገደልኳት።» አላቸው

«.......ትውሲትን?»

«አዎ!......ኑ እንግባና ሬሳዋን ላሳያችሁ። ዛሬ ሽጉጤንም አሳያችኋለሁ።»

ሁለቱን ልጆች ግራና ቀኝ ይዞ፤ እሱም እንደነሱ እየቦረቀ፤ ወደ ስዕሉ ክፍሉ ይዟቸው ገባ።

«ይኸውላችሁ ሽጉጤ።.....» አለና፤ የስዕል ብሩሹን አንስቶ አሳያቸው።

ልጆቹ፤ የቀለደባቸው መስሏቸው እርስ በርስ ተሳሳቁ።

«የትውሲት ሬሳ ደግሞ ይሄውላችሁ።......» እያለ አዲሱ ሸራ ላይ የሰራውን የቀንዳም ሴት ስዕል አመለከታቸው።

ዳኒና ዘኒ፤ በመልዕክቱም ባይሆን፤ በስዕሉ ተመስጠው ትኩር ብለው ይመለከቱ ጀመር።.....

«ለገሃር.....ሜክሲኮ........የሞላ!.....

ወያላው ታክሲውን የኋላ በር ከፍቶ ቆሞ ይጮሃል። - በጣም ይጮሃል። የታክሲውን መንቀሳቀሻ ስፍራዎች የሚያስተዋውቅ ሳይሆን፤ ስልት በሌለው ሁኔታ የሚዘፍን ወይም የሚያለቅስ ይመስላል። ሹፌሩ በመንቀሳቀስ ዓይነት ሞተሩን ያስጮሃል - ነገር ግን አይንቀሳቀስም። ወያላው በሩን ኳ! አድርጎ ያስጮኸውና ጥሪውን ይቀጥላል -

«አብዮት.....ለገሃር.......ሜክሲኮ!....መሄዳችን ነው!.....ቶሎ ቶሎ በሉ!.....ለገሃርነው!.....ሜክሲኮ ነው!.....የሞላ......የሞላ ነው.....» መንገደኛውን ሁሉ እንደመጥለፍም ይቃጣዋል....

«......ወዴት ነዎት ጋሼ?!......እትዬ እዚህ ይግቡ.....የሞላ ነው።......»

ሌሊቱን ሙሉ እንቅልፍ አጥታ ያደረችው ትውሲት፤ ታክሲው ውስጥ ተጎልቶ መጠበቁ ደግሞ ሌላ ብስጭት ሆነባት። እንደ ወትሮው ቢሆን በዚህ ሰዓት ታክሲ ለማግኘት ከፍተኛ ትንንቅ ነበር። ነገር ግን ሰኞ ጠዋት በመሆኑ አብዛኛው ሠራተኛ በዕሁዱ ዕረፍት ተዳክሞ ገና ከቤቱ አልወጣም። ትውሲትም ብትሆን ማልዳ ስትነሳ የመጀመሪያ ጊዜዋ ነው። ጭንቅላቷን ሲበጠብጠው ያደረው ጉዳይ ሊያስቀምጣትም፤ ሊያስተኛትም ባለመቻሉ በጠዋት ተነስታ ከቤቷ ወጣች። ቁርስ ለመብላት ወስፋት አልነበራትም። መስተዋት ፊት ቆማ ለመኳኳልና ለመቀባባትም ትዕግስት አለነበራትም። ፀጉሯን ለማበጠር ገና መስታወቱ ፊት ስትቀርብ፤ ምስሏ ኤርሚያስ የሳላትን አስፈሪ፤ ቀንዳም ሴት ሆና እየታያት አዕምሮዋን ሰላም ስለነሳው፤ እንዲሁ በሻሽ ሸብ አድርጋው ወጣች። አለባበሷ ሁሉ እንደ ነገሩ በመሆኑ ወደ ቢሮ የምትሄድ ሴት አትመስልም ነበር።

ትዕግሥቷን አስጨርሶ የተንቀሳቀሰው ታክሲ፤ በየመንገዱም እንዲሁ ሰው ሲያወርድና ሲጭን ቆይቶ፤ ለገሀር አወረዳት። ከዚያ በኋላ መስሪያ ቤቷ ሩቅ አልነበረም።

«ምነው ወይዘሪት ትውሲት?.....በደህና?.....» አሿት የመስሪያ ቤቱ ዘበኛ፤ በጠዋት መምጣቷና የአለባበሷ ግዴለሽነት አስደንግጦአቸው።

«እንደምን አደሩ......ደህና ነኝ። አስቸኳይ ስራ ስላለ ቀደም ብዬ ለመግባት ተቻኩዬ ነው።......» ብላቸው አለፈች።

ቢሮዋ እንደ ገባች ኮመዲናዋን ከፍታ ከአቶ ክብረት የተላከውን የእጅ አምባር አወጣች። ወደ ቢሮአቸው መሄድ ፈልጋ ነበር። ገና እንዳልገቡ በመገመት ትንሽ መቆየቱን መረጠች። ስሜቷ ግን አርፎ ሊቀመጥላት አልቻለም። ዘየገን ደግሞ አስበች። ሌሊቱን ሙሉ አውጥታ አውርዳ ጠላቷ ዘገየ መሆኑን ደርሳበታለች። እሷን ለማብሸቅ የጅማ ጓደኛዋን ተወዳጅቶ በአጠገቧ ይዟት ሲያልፍ፤ የጅማ የሚስጥሯ አደባባይ እንደ ወጣ ጠርጥራለች። ከኤርሚያስ ጋር የቅርብ ሰላምታ እንዳላቸው ካየችበት ቀን ጀምሮ ደግሞ ልቧ ፈርቶ ነበር። የፈራቸው ደረሰ።.....ዘገየም ቢሆን ካሁን በፊት ቢሮው አይገባም።

አንድ ሐሳብ መጣላትና ወደ ፅጌረዳ ለመደወል የስልኩን እጀታ አንስታ ተፈላጊውን ቁጥር አዞረች።

«ሀሎ?.....» አለች፤ ስልኩን የተቀበለችው ሰራተኛ።

«ሄሎ......የአቶ ሀይሉ ቤት ነው?»

«አዎ፤ ማን ልበል?......»

«ፅጌረዳን ፈልጌ ነበር እባክዎ.......ትውሲት እባላለሁ።»

«እትዬ ፅጌረዳ እንኳ ከመኝታቸው አልተነሱም። አስቸኳይ ጉዳይ ከሆነ ላስነሳቸው።......»

«አዎ፤ ያስነሱልኝ እባክዎ።»

ፅጌረዳ ወደ ስልኩ እስክትቀርብላት ድረስ፤ ትውሲት መናገር የፈለገችውን ምላሷ ላይ ስታጣጥም ቆየች። ከፅጌረዳ ጋር የነበራት ወዳጅነት ማክተሚያው መቃረቡን በመገመት ልቧ ከበሮውን ይደልቅ ጀመር። ሆነም፤ ቀረ የመጨረሻ ሙከራ ማድረጉ አይከፋም፤ በሚል መንፈስ ተፅናናች።

«ሀ - ሎ?......»

«ሄሎ፤ ፅጌረዳ እንደምን አደርሽ?......በጠዋት ቀሰቀስኩሽ?......

«ምንም አይደል።......»

«.......የሚያስገርም ነገር ሰምቼ እኮ ነው የደወልኩልሽ።......»

«ምንድ'ነው እሱ?......»

«ያ......የምናውቀው ጉዳይ......»

«የትኛው?.....የ - የ - የ - የ.....»

«አዎ፤ የሮዛ......»

«እ.....ሺ?»

«.......ስድስት ወር ያለውፈው ፅንስ አስወረደች አሉ። - ከወንዳፍራሽ ያረገዘችውን!»

«........አትይኝም?!»

«ሙች እልሻለሁ። እኔም ስሰማ ገርሞኝ ልሞት»

የስልኩን መስመር እንደተቋረጠ ሁሉ፤ ከሁለቱም ወገን ድምፅ ጠፋ። ‹....እንዴት ይሆናል?› እያለች ነገሩን ስታሰላስል፤ ትውሲት ደግሞ ‹.....አምናኝ ይሆን?› በሚል ስጋት ተወጥራ፤ የድምጿን ሁኔታ ለመመርመር፤ የፅጌረዳን ንግግር ስትጠብቅ ቆየች።

ነገሮች ተፍረጥርጠው መውጫቸው መቃረቡን በመገመት ትውሲት የራሷን የማስተባበያ ሽፋን ከወዲሁ ማቅረቧ ነው። ሮዛ ፈፅሞ ከወንዳፍራሽ ያለ ማርገዟን ፅጌረዳ ብትሰማ፤ አሁን ትውሲት ከነገረቻት ጋር አያይዛ ‹ውሸት ነው አርግዛ ነበር፤ አሁን አስወርዳው ነው።› የሚለውን አቋም ትይዝላታለች። የውሸቱን ሽፋን ትውሲት ለፅጌረዳ መንገር የፈልገች ከአቶ ክብረት ጋር ከወጣችላት በኋላ ነበር። ነገር ግን የእነ ኤርሚያስ ጣልቃ መግባትና የፅጌረዳም ፍርሀት ምኞቷን ስላከሸፈባት የአሁኑ ሙከራዋ ፅጌረዳ ውሸቷን አውቃባት እንድትጠላት ብቻ ነው።

ፅጌረዳ ደግሞ እናቷና ኤርሚያስ ስለ ሮዛ ያለ ማርገዝ የነገሯትን አሁን ትውሲት ከምታወራላት ጋር አያይዞ ጥርጣሬ ውስጥ ሰምጣለች። ጥንቱንም ቢሆን የትውሲትን ወሬ ያመነችው፤ አንድም በጭንቋ ሰዓት በመሆኑ፤ እውነትም ‹ያልተፈሳ አይሸትም› በሚል ግምት ነበር እንጂ።.....

«......ግን ስድስት ወር ያለፈውን ፅንስ እንዴት በሰላም ልታስወርድ ቻለች?» አለቻት ቆይታ - ቆይታ በጥርጣሬ ድምፅ፡

«እኔንስ የገረመኝ እሱ አይደል?......ጉድ ነው እኮ!

«አይ ትውሲት!.....» አለቻት፤ ቅሬታ ባዘለ ድምፅ።

ይችህን ሐረግ ስትሰነዝር ድምጿ ልዩ ቅላጼ ነበረው። ለወትሮው ትውሲትን የምታነጋግርበት ድምፅ አይደለም። ቅሬታውን፤ ትዝብትን፤ ተስፋ መቁረጥን

የሚያሳይ ድምፅ ነው። ትውሲት ይህን የተለየ ድምፅ ስትሰማ፤ ዓይኖቿ አርቀው የሚመለከቱት የቀድሞዋን የዋህ ቅድስት ፅጌረዳ ሳይሆን፤ ቂም አርግዛ በትዝብት የምትመለከታትን አዲሷን ፅጌረዳ ነበር።

«ምነው......ፅጌረዳ?!......»

«ምንም አይደል.......እንዲያው የሰው ነገር እያስገረመኝ ነው።» አለቻት፤ እንደገና በቅሬታና በምፀት ድምፅ።

«እንዴት ፅግሽ?!.......አልገባኝም።»

«እህህ!......እንዴት አይገባሽም?!.......» አለችና ስልኩን ጆሮዋ ላይ ዘጋችባት።

ትውሲት ጭንቅላቷን እንደተመታች ሁሉ፤ በድንገት ተጫጭናት፤ የተዘጋውን ስልክ እጀታ እንደያዘች ፍዝዝ ብላ ቀረች። ፅጌረዳ ከእንግዲህ ዘመዷ እንደማትሆን ገባት። - ከንቱ ጨዋታ ነበር የሞከረችው.......

ሠራተኛው ሁሉ በየቢሮው ከገባ በኋላ ከኮመዲኖ ውስጥ ያወጣችውን አምባር በወረቅት ጠቅልላ ይዛ ወጣች። ከአቶ ክብረት ቢሮ ቀድሞ የዘገየ ቢሮ ሰለሚገኝ፤ እግረ መንገዷን ልክ - ልኩን ነግራው ለመሄድ አስባ ጎራ አለች። ንቀቷን ለማሳየት በሩን እንኳ ሳታንኳኳ በርግዳ ነው ዘው ያለችው።

ንግግርም፤ ግንኙነትም አቋርጥው ስለ ከረሙ፤ ዘገየ ‹ደሞ ምን አመጣት?› ብሎ ደነገጠ።

«.......አንተ ግን ወንድ አይደለህም! ወሬኛ ነህ!......ቅሌታም ነህ!......» አለችው፤ ፊት ለፊቱ ቆማ፤ ግራ እጇን ወገቧ ላይ አድርጋ።

ዘገየ የቁጣዋ መንስኤ ስላልገባው ትንሽ ግር አለው። የተመታችበት ጉዳይ መኖሩን ግን ገመተ። ተስፋ የቆረጠ አነጋገሯ ብቻ ሳይሆን፤ የወትሮው ሽቅርቅርነቷ መጥፋቱ ራሱ ለሐዘኗ ምልክት ነበር። ልማድ ሆኖባት እጇን ወገቧ ላይ ብትሰካም፤ እንደ ወትሮዋ መውረግረግና በፌዝን ማከላላት አልቻለችም። መንፈሷ ደክሟል።

ዘገየ በስድቧ ቢናደድም ቅሉ፤ ሽንፈቷን ማየቱ ደስ አሰኝቶት፤ ተረጋግቶ ተቀምቶ፤ የፌዝ ሳቅ እየሳቀ ምላሹን ሰጣት።

«......ወንድነቴን እንኳ አንድ ቀን አሳይቼሻለሁ።.....ረሳሽው እንዴ?» አላት እያሾፈ።

እንዳሁኑ ከመጣላታቸው በፊት ከደጃኔ ሰርቆ፤ አንድ ቀን አውጥቷት ነበር። ያሁኑ አነጋገሩም ያንን ለማስታወስ መሆኑ ገባት።

«......እም! እኔም ነኝ ቅሌታሟ!......ከእንዳንተ አይነት ስራ ቤት - ወሬኛ ጋር.....» አለችና የመጨረሻ ቃላቷን ውጣው ከክፍሉ ወጣች። የዘገየ የመረጋት ምላሽ ራሷን መልሶ የሚያበሽቃት ሆኖ ስላገኘችው፤ አስባበት የመጣችውን ያህል ልትሰድበው አልቻለችም። ይልቁንም፤ ጥላቻዋን ሁሉ መግለጫ መንገድ ያገኘች ይመስል፤ ከክፍሉ ከወጣች በኋላ ፊቷን አስፀይፋ፤ በሩ ላይ ምራቋን ጢቅ አደረገች።

ዘገየ በሁኔታዋ ተመስጦ ተከትሏት ወጣ። እሷ ግን ከተቀመጠበት የተነቃነቀ ስላመሰላት ወደ ኋላዋ ዘወር ብላም አላየችውም። በንዴት እግሮቿን እያወናጨፈች ገልመጥ እንኳ ሳትል ገሰገሰች።

ከኋላዋ ሲመለከታት ሁለመናዋ አሳዘነው። ፈፅሞ ያቺ የሚያውቃት ትውሲት አልመስልህ አለችው። ዳሌዋ የሚያጎላውን ጨርቅ አጥቶ ኩራት ጠፍቷል። በስልት ግራ ቀኝ መርገጡም ቀርቷል። «ደሞ ለሰው» የምችለው አረማማዷ ዛሬ አይታይም። ሰው የሚከበርና የሚፈራ ፍጡር መሆኑን፤ የደረሰባት ድንገተኛ ድንጋጤ ሳያስገነዝባት አልቀረም።

እየተወላከፈችና እየተወናጨፈች የቢሮዋን መንገድ ትታ ወደ አቶ ክብረት ቢሮ ስትሔድ ቢመመልከቱ፤ ዘገየ የወሬ ጉጉት አይሎና ሽንፈቷ ከምን ላይ እንደ ሆነ በልቡ ጠርጥሮ፤ በዘዴ ተከተላት። እሱ ተደብቆ ሊከተላት ደከመ እንጂ፤ እሷ ዘወር ብላ ግራ ቀኙን የምታይበት የተረጋጋ አዕምሮ አልነበራትም።

በፀሐፊዋ በኩል ሳይሆን፤ የግል በራቸውን አንኳኩታ አቶ ክብረት ቢሮ ገባች። ዘገየ ተከትሏት ሊገባ ባለ መቻሉ እየበሸቀ፤ መዝጊያው እንጨት ላይ ተለጥፎ፤ ሁነታቸውን በጆሮው የከታተል ጀመር።

«.......ይኸውልዎ፤ አምባርዎን ልመልስልዎት ነው የመጣሁት። ሴትየዋ ፈቃደኛ አልሆነችም። በጣም አዝናለሁ።»

«ቀስ በይ እንጂ ትውሲት።.....ቀስ......ቀስ......ድምፅሽን ዝቅ አድርጊ።......»

በወረቀት ጠቅልላ ያመጣችውን አምባር ገልጣ በሁለት እጇቿ መለሰችላቸው።

«ም - ምነው?.......» አሉ አቶ ክብረት፤ አምባሩን እየተቀበሏት፤ ግንባራቸውን ኮስኩሰው።

«......አልተሳካማ!......ውስጥ - ውስጡን እየተልከሰከሰ ወሬ በመለቃቀም፤ ጉዳያችን እንዳይሳካ ያደረገው ሰው ማን እንደሆነ የሚያውቁት ይመስለኛል።.......»

«ማን'ነው እሱ?»

«ያውቁታል!......ዘገየ ወርቃለማሁ ነው።»

«አሃ!.......እሱ እንኳ ለነገር እንደማይተኛ አውቃለሁ። ግድ የለም ቆይ!......»

«አዎ፤ እሱ ነው። በከተማው እየዞረ ስማችንን በመከል ስራዬ ብሎ ይዞታል። የግቢያችንን ስዕሎች በኮንትራት ከሰራው ሰዓሊ ጋር ተመሳጥሮ ስማችንን ለማጥፋት ተነስቷል። ከአሁኑ በፊትም፤ ደብቄዎት ነው እንጂ፤ እርስዎ ከእኔ ጋር ሌላ ዐይነት ግንኙነት እንዳለዎት አስመስሎ አሰርቶ ከጓደኛዬ፤ ከደጀኔ፤ ጋር አጣልቶኝ ነበር ለምን እንዲህ ጠምዶ እንደያዘኝ አይገባኝም።.......»

«ሰዓሊው ደሞ እዚህ ጉዳይ ውስጥ ምን ዶለው?»

«ለፅጌረዳና ባሏ ጓደኛቸው ነው። ወሬ አቀባዩ ግን ይሄው ርኩስ ነው። ብዙ ቀን አብርው አይቻቼዋለሁ።»

«የእሱ ግዴለም!......ጊዜውን ይጠብቅ!........» አሉና ጥርሳቸውን እያንቀጫቀጩ በዝምታ ቆዩ።

ዘገየ በሩ ላይ እንደ ተለጠፈ፤ ‹ለመሆኑ ኤርሚያስ መረጃዎቹን ከእኔ ማገኘቱን ማን ነገራት?› ሲል አሰበ። በኋላ ግን ለትውሲት ይህን መጠርጠር እንደማይከብዳት ገመተ። - አንደኛ፤ ከሷ ጋር ተጣልቷል፤ ሁለተኛ ከኤርሚያስ ጋር ትውውቅ እንዳለው

አይታለች፤ ሶስተኛ ነገር የጆማ ጓደኛዋን ሲያወጣት በዓይኗ በብረቱ ተመልክታለች።

.......

«አሁን አንድ ነገር ለምንዎት?......» አለች ትውሲት ትንሽ ስታስብ ቆይታ።

«በደስታ!......ምን ልርዳሽ?»

«ቢሮዬን እንዲያስቀሩልኝ ነው የምለምንዎት። ከአሁን በኋላ ፅጌረዳ ጋር አንድ ቢሮ ውስጥ ተቀምጠን መስራት አንችልም። በዚህ ሳምንት ውስጥ እረፍቷን ጨርሳ ወደ ስራዋ ስለምትመለስ፤ እኔ ወይንም እሷ በቅድሚያ ያንን ቢሮ መልቀቅ አለብን።.....»

«ግዴለም፤ ይሄ ቀላል ነው።.....ያንንም፣ የዕድገቱንም ጉዳይ ቢሆን ቸል አላልኩትም። ኮሚቴው ውስጥ ምቀኞች ተሰግስገው አስቸግረውኝ ነው።»

«ኸረ ይኸኛውን እንዲያፋጥኑልኝ ነው የምለምንዎት......» አለች፤ በዕድገቱ ጉዳይ ላይ ተስፋ በመቁረጥ ዓይነት።

«ሁሉንም ለእኔ ተይው......አይዞሽ።» አሉና፤ በማሰናበት ዓይነት ብድግ ብለው ጨበጧት።

በገባችበት በር ለመውጣት ድንገት ስትከፍት፤ በሩ ላይ ተለጥፎ የቆየው ዘገየ ሊወድቅ ነበር። አንዱን ቋሚ ማዕዘን ተደግፎ ለጥቂት ተረፈ። የቢሮው ምንጣፍ የጫማዋን ድምፅ ስለዋጠው፤ ወደ በሩ መምጣቷን በጆሮው መከታተል አቅቶት ነበር እንደ ተለጠፈ የጠእብቃት።

ትውሲት ደግሞ ያ በሩ ላይ ተለጥፎ የቆየው ሰው ዘገየ መሆኑን ስትመለከት አመዷ ቡን አለ። ምን ሊያደርግ ተከትሏት እንደ መጣ መገመት አላቃታትም።

«......ምነው ብትተወኝ ዘገየ?!.......ምነው ለቀቅ ብታደርገኝ!.......ተወኝ ብዬሃለሁ!......ተወኝ!......ተወኝ!......»

ጩኸቷ አስደንግጧቸው፤ አቶ ክብረትም ከውስጥ ብቅ ሲሉ፤ በራቸው ላይ ዘገየን ተመለከቱት። አንዳች አስፈሪ ወይም አስጠሊ ነገር እንደተመለከቱ ሁሉ ፊታቸው ጥቀርሻ ለበሰ።

ዘገየ ከሁለቱ ጋር ተፋጥጦ መቆም አልቻለም። ከት - ከት ብሎ የፌዝ ሳቅ እየሳቀ ወደ ፊቱ እምጭ አለ። - ጀሮውን ወደ ኋላው ጥሎ!

«ተወን ብለንሃል ኋላ!......ተወን!.....ተወን!.......ተወን!......»

ሮዛና ወንዳፍራሽ ተቀጣጥርው ሲገናኙ ፊታቸው ላይ የሚነበብ የወትሮው የፍቅር ኩርፊያ አልነበረም። ሁለቱም አዝነዋል። አንዳች ከባድ ስሜት ተጫጭኗቸዋል። የተገናኙበትን ጉዳይ ለመነጋገር ፈርተው ሁለቱም በየግላቸው ሲያምጡ ብዙ ቆዩ። ፍላሚንጎ ካፊቴሪያ በር ላይ፤ መኪናቸው ውስጥ ሆነው ቡና እየጠጡ ነበር።

«......ለምን እዚህ ቦታ አመጣኸኝ?» አለች ሮዛ እንባ በተናነቀው ድምፅ።

«ምነው?.......ከጠላሽው ሌላ ቢታ እንሄዳለን?» አላት፤ የእሱም ድምፅ እየተንቀጠቀተ።

«አዎ፤ እንሂድ!......ካፊቴሪያ በር ላይ መቆም አልፈልግም።» አለችው፤ የስሜቷ መቆጣትና መቅበጥበጥ ከጀርባው ያዘለው ችግር መኖሩ ገጽ ላይ እየተነበበ።

ወንዳፍራሽ ራሱ ለምን ወደዚህ ካፊቴሪያ እንዳመጣት አልገባውም። ቦታውን ከተውት ብዙ ጊዜ ሆኖአቸዋል። በእርግጥ ፍቅር የጀመሩ ሰሞን ያዘወትሩት ነበር። ያኔ ሮዛ ወንዳፍራሽን ወደዚህ ስፍራ ይዛው የምትመጣው የቀድሞ ፍቅረኛዋን ልታስቀናበት ነበር። ነገር ግን አጋጣሚውና ቦታው ከወንዳፍራሽ ጋር አፋአሮአት ቀረ። እና፤ ይህን ፍቅር የጀመረችውን ቦታ አሁን በመለያያ ሰዓት መልሳ ማየቷ ሰውነቷን ረበሸው። ገና ከቤቷ ስትወጣ በመለያየት ፍርሃት የተቆጣው ስሜቷ ይበልጥ ተቀበጠበጠ። አልቅሺ - አላት።

ስሜቷ ስለገባው ወንዳፍራሽ ቶሎ ሂሳቡን ከፍሎ፤ የእሱም ልብ በሐዘን እየእተንፈራገጠ፤ መኪናውን አስነስቶ ወደ ሌላ ቦታ ይዟት ከነፈ። ከዚያ የትዝታ አካባቢ ለመሸሽ ካልሆነ በስተቀር ወዴት እንደሚወስዳት አያውቅም ነበር።

«ሌላ ቦታ......አንቺ ምረጫ እንግዲህ።» አላት፤ በቦሌ መንገድ ቀጥታውን ከሄደ በኋላ ፍጥነቱን እየቀነሰ።

«እኔ የትም መግባት አልፈልግም። መዝናኛ ቦታው ሁሉ አስጠልቶኛል።» - ግንባሯን እንደከሰከሰች በምሬት ዓይነት አጆቿን አወናጨፈች።

ወንዳፍራሽ ግን ገብቶት ከዋናው መንገድ ወጣ ብሎ፤ ጨለም ያለ ስፍራ ፈልጎ አቆመ። ከእሱ መኪና በስተቀር በአካባቢው የሚንቀሳቀስ ፍጡር አልነበረውም። የሌለውን ድፍረት ይሰጠው ይመስል፤ ፀጥታውንና ጭለማውን ወደደው። እና፤ መርዶው መኪናው ውስጥ ለመጨረስ ራሱን ያዘጋጅ ጀመር። መናገር የፈለገውን ገና ሲያስበው ልቡ በድንጋጤ እየዘለለ አስቸገረው።

«........ቦሌ ድረስ ያመጣኸኝ ለስንብት ነው?»

ሮዛ በትከሻዋ የመኪናውን መስታወት ተደግፋ፤ ፊቷን ወደ ወንዳፍራሽ አዙራ፤ ተመቻችታ ከተቀመተች በኋላ፤ በምጸት ድምፅ ተነፈሰች። በአለባበሷ ራሷን አልጣለችም። ነገር ግን ልብስ ከስሜት ጋር ሲሆን ነው ውበትን የሚያጎላው። - ሁለመናዋ በዳመነው ገጿ ተውጧል።

«አንቺው ቦታ ምረጪ ብዬሽ ነበር 'ኮ!......» አላት በሚያባብል ድምፅ።

ልቡ ውስጥ የሚጉላላው ብሶት መግለጫ ነው እንጂ፤ ቦታውን ጠልታው ወይም ሌላ ቦታ ለመሄድ አልነበረም። ወንዳፍራሽ የተናገረውንም አላዳመጠችውም።

«.......ጓደኛህ የፃፈልኝ ደብዳቤ ደርሶኛል።» በማለት ድንገት ነገሩን ዘወር አደረገችው።

ወንዳፍራሽ ፈርቶ ሲንቀጠቀጥበት የቆየው አርዕስት በእሷው መጀመሩ ደስ አሰኝቶ፤ «አዎ እንደላከልኝ ነግሮኛል። ቅጂውንም አስነብቦኛል።......» አላትና አቋረጠ።

እንዴት እንደሚቀጥል እያሰበ ነበር። ሮዛ በጥያቄ አስተያየት ከት ብላ ተመለከተችው። ወንዳፍራሽ አይቶባት የሚያውቀው አዲስ ዓይነት አስተያየት ስለሆነበት ዓይኖቿን ሸሽቶ ወደ መኪናው መሪ ይመለከት ጀመር።

ገና በቀን ስልክ ተደዋውለው በዚህ ዓይነት ለመገናኘት ሲቃጠሩ ልብ ለልብ ተዋውቀዋል። ፍቅረኞች ምንጊዜም ሳይነጋገሩ ልብ - ለልብ የተግባቡበትን ነገር ፊት

ለፊት ጥፋተኛ ከመነጋገሩ ላይ ነው። በጉዳዩ በማዘን አንዱ ሌላውን ጥፋተኛ አላደረገም። አጋጣሚ አገናኛቸው፤ ሁኔታው ስላልፈቀደ ደግሞ መለያየት አለባቸው። ይህንን ሀቅ ሁለቱም አምነውበታል። ነገር ግን ባመኑበት ነገር ላይ ለመቁረጥ በግንባር ሲገናኙ የፍቅር ፍርሃት ያዛቸው። «መለያየት» የሚለውን ቃል መተንፈሱ ከበዳቸው።

«የመጨረሻችን እንደዚህ መሆኑ ያሳዝናል።......» አለች ሮዛ በረዥሙ ተንፍሳ።

«ምን ማድረግ ይቻላል?! በዓለም ውስጥ መገናኘትና መለያየት ያለ ነገር ነው፤ ጠንከር ብለን ልንቋቋመው ይገባል። ለዚያውም እንደኔና እንዳንቺ በፍቅር መለያየት መታደል ነው።»

«መታደል አልከው?!......ምን ታደርግ?......»

«......ማለቴ.......»

«እኔ የሚያሳዝነኝ ዕድሌ ነው። ከዚያ ከትዕቢተኛ እጅ ሳመልጥ አንተ እጅ ውስጥ ወደቅኩ። ምናልባትም የምፈልገውን ፍቅርና ከበሬታ ያገኘሁት ካንተ ብቻ ነው። ነገር ግን አንተም የሰው ሆንክ!.......ለፍቅር ነው የተፈጠርኩት። የምፈልገውን ፍቅር ግን እየተነፈግኩ ነው። ከእንግዲህ ከፍቅር ውጭ መኖር መቻል አለብኝ። አዎ! ለፍቅር አንተ የመጨረሻዬ ወንድ ትሆናለህ።......»

እንባዋ ድንገት ርግፍ - ርግፍ አለ። ስሜቷን መቆጣጠር ስላቃታት ስቅስቅ ብላ አለቀሰች።

«እባክሺ እንደዚህ አትሁኝ ሮዛ። ገና ወጣት ነሽ፤ ቆንጆ ነሽ። ምን እንደሚጠብቅሽ አታውቂም። በቀላሉ ይህን ያህል ልትመረሪ አይገባም።.......እኔም ስለይሽ ልቤ እንደ ድንጋይ እየከበደኝ ነው። ነገር ግን ልባችንን አጠንክረን አይናችንን መግለጥ መቻል። ነገር ግን ልባችንን አጠንክረን አይናችንን መግለጥ መቻል አለብን። ......ስሚ ሮዛ፤ እባክሽን ተረብሸሽ አትረብሺኝ።......»

የእሱም ልብ አብሮ አለቀሰ። ስሜቱ በሐዘን ተቈነጠነጠ። መለያየት ሞት ነው! እንዴት አድርጎ እንደሚያፅናና ግራ ገብቶት፤ ፍዝዝ ብሎ ይመለከታት ጀመር።

ከውስጥ ታፍኖ ሲያሰቃያትና ሲያቅበጠብጣት የነበረው ስሜት በእንባዋ ተጠርጎ ወጣላት። ከቦርሳዋ ስሜት በእንባዋ ተጠርጎ ወጣላት። ከቦርሳዋ ውስጥ መሐረብ አውጥታ አይኖቿንና ጉንጮቿን ከጠራረገች በኋላ ምጧን እንደ ተገላለጠች ሴት በረዥሙ ተነፈሰች። እንባ የወረደባቸው ቀይ ጉንጮቿ ይብሱን ቀልተው ቲማቲም መስሉ።ዳመናው የተገፈፈላቸው ዓይኖቿም እንደ ወትሮአቸው እየተንከባለሉ ማሳዘን ጀመሩ።

«ለማንኛውም......ከሚስትህ ለመጣላትህና ልጆችህ ለመበታተናቸው ምክንያት በመሆኔ አዝናለሁ።» አለችው በተረጋጋ አነጋገር።

«እሱ ያንቺ ጥፋት አይደለም።.......ስላለፈው መፀፀቱም ዋጋ የለውም። ከፀፀት ለመዳን ወደ ፊት ብዙ ጊዜ ይኖረናል።» አላት፤ በተራው የእሱ ድምፅ እየሻከረ።

«ልጅህን ደግሞ ደብዳቤውን ሲያመጣልኝ አየሁት። የሚያሳዝን ቆንጆ ልጅ ነው።.......እናቱ ቆንጆ መሆን አለባት።»

አሁንም አነጋገሯ ውስጥ የቅናት ቅላፄ ነበረበት። ግምቷ ትክክል ነው። የዳኒ ቁንጅና በአብዛኛው ከእናቱ ደም የተወሰደ ነው። ሆኖም የሮዛ አነጋገር ጤናማ መስሎ ስላልታየው፤ የወንዳፍራሽ መልስ ለመስጠት ተቆጠበ። በስንት መከራ የጠራው ጉዳይ እንደገና እንዳይፈርስበት መጠንቀቅ ነበረች።

«ዋሽሁ እንዴ?......» ስትል አፋጠጠችው።

«ትክክል ነሽ።» አላት ሲፈራ -ሲቸር።

«ወንዴ - እወድህ ነበር አሁንም እወድሃለሁ። አሁንም አፈቅርሃለሁ። ነገር ግን ለሚስትህና ለልጆችህ ስል እየወደድኩህ እለይሃለሁ። እያፈቀርኩህ ፍቅርህን እሸሸዋለሁ። ፍቅርህን መሸሸ ያመኛል፤ እንገር ግን መድሐኒቱ ከአጠገብህ መሰወር ብቻ ነው። አዎ፤ ከአጠገብህ ርቄ ሳስታውስህ እኖራለሁ። ምን ጊዜም ከልቤ አትጠፋም።.......» አለችው ድምጽዋ በትካዜ ዜማ እየተገበገበ።

ወንዳፍራሽ ተመሳሳይ ስሜት ቢፈነቅለውም፤ የኋሊት እንዳይመለስ ፈርቶ፤ ምላሱን ቆንጥጦ ዋጠው። ልብ አንብቶ ከጨረሰ በኋል የቃላት እንባ ምን ያደርጋል?!

የሚያባብሉና አፍጠው የሚጠይቁ ዓይኖቿን ለመሸሽ፤ አንገቱን ዘወር አድርጎ፤ በመኪናው የፊት - ለፊት መስተዋት ወደ ሩቅ ተመለከተ።

እሷም የሸሿትን ዓይኖች ተከትላ ወደ ውጭ ተመለከተች። ሁለቱም በርቀት ሰማዩን ተመለከቱ።

ጨረቃ ጭለማውን እየገለጠች በመውጣት ላይ ነበረች።......

ኤርሚያስ ዒላማዎቹን መትቶ ከጨረሰ በኋላ፤ ተወጥሮ የቆየው ጭንቅላቱ ተፍታታለች። የዒላማዎቹን ውጤቶች ሲሰማ ልቡ የደስታ ዳንኪራ መርገጡን ጀመረ። የትውሲትና የአቶ ክብረት እኩይ ምኞት መቀጨቱን ዘገየ ነገረው። ከሮዛ ጋር የነበረውን ግንኙነት በሰላም መቁረቱን ደግሞ ወንዳፍራሽ ራሱ መጥቶ አበሰረው። አሁን የቀረው የፅጌረዳን የመጨረሻ ውሳኔ መጠበቅ ብቻ ነበር። ለዚያውም ቢሆን ቅድመ ዝግጅቱን አጠናቋል። - ወንዳፍራሽ የይቅርታ ደብዳቤ ፅፎ በሰብለ እጅ እንዲልክላት አድርጓል። የደብዳቤውን ጥሪ ተቀብላ መምጣት ወይም ንቃ መቅረት የፅጌረዳ ውሳኔ ይሆናል። የዚህ ቁርጥ የሚያውቀው ሐሙስ ማታ ነው።

ሐሙስን በተስፋና በጉጉት እየጠበቀ፤ አዕምሮውን ወደ ስዕል ስራው መለሰ። «ሔዋን 1999» በፈገግታ እየጠራችው ወደ ስዕል ክፍሉ ገባ። ይሁን እንጂ አጠገቧ ሲደርስ ከውጭ የጠራውን ፈገግታዋን ሳይታይ እርቃኗን ከስዕሉ ሸራ ላይ እንደታጋደመች ነበረች።

በይ እንግዲህ ሔዋን፤ ቀሚስ ከመልበስሽ በፊት ፈገግ በይ። ፈገግታሽ ልባዊ ይሁን። እና ደግሞ ልበ - ሙሉነትን አስተዋይነት በራስ መተማመንን ተጎናፀፊ።

በብሩሽ ነጭ ቀለም አጥቅሶ፤ ጥርሷን በመጠኑ ለማስገለጥ ከፊት - ለፊቷ ቆመ። ሆኖም በእሷ እብኩል ተቀባይነት አላገኘም። ፊቷን ሳትፈታ በጥያቄ ገተረችው።

ቆይ እስቲ አዳም፤ መጀመሪያ የምጠይቅህ ነገር አለኝ። በእኔ ላይ የምትፈልገው ልበ ሙሉነት አስተዋየንትና በራስ መተማመን በአንተ ውስጥ አለ ወይ

አለ።......ይኖራል......

በሴቶችም ውስጥ አለ፤ ይኖራል። ሴትም ሆነ ወንድ በአፈጣጠር ደረጃ አንድ ከሆነ ይህ ልዩነት ሊከሰት ይችላል።.....

እንዴት ማለት?

ሴቶችም እንደ ወንዶቹ ሁሉ፤ በወንድ ዘርና በሴቷ እንቁላል ውህደት ተፀንሰው ዘጠኝ ወር ተረግዘው ቆይተው የሚወለዱ ናቸው እንጂ፤ በኦሪት ዘፍጥረት እንደተጠቀሰው ከአዳም ግራ ጎን የሚገኙ (የሚወሰዱ) የአጥንት ቁራጮች አይደሉም።......

እሺ በዚህ እንስማማለን

ይህ ከሆነ፤ የአፈጣጠር ተመሳሳይነት ወይም አንድነት አለ ማለት ነው። በዚህ የአፈጣጠር ተመሳሳይ ሂደት ውስጥ አካላዊ አፈጣጠር ልዩነት ደግሞ አለ። ይህ አካላዊ የአፈጣጠር ልዩነት ተቃራኒ ጾታን ያበቅላል። የተቃራኒ ጾታ መከሰት ደግሞ በህይወተ ዘለዓለማዊ እንቅስቃሴ ውስጥ እጅጉን አስፈላጊ ነው። ሴቷን ሴት - ወንዱን ወንድ ያሰኘውም ይህ አካላዊ የተፈጥሮ ቅርፅ ነው። ያለበለዚያ ሁለቱም በአንድ ስም «ሰው» ናቸው።......

በጣም ጥሩ።.....

የአካላዊ ቅርፅ አበቃቀል በስነ ህይወት ሕግ መሠረት ራሱን የቻለ ባዮሎጂካል ምንጭ አለው። ወንዱ ዘር ሰጪ፤ ሴቷ ደግሞ ማህፀኗን ከፍታ ዘር ተቀባይ እንዲሆን ያደርጋቸው ይህ ባዮሎጂካል ምንጭ ነው። በዚህ መሠረት ተቀብላ በማህፀኗ ውስጥ ያዳበረችውን ፅንስ ተንከባክባ የመውለዱ ሂደትም በሴቷ ላይ ይወድቃል። እዚህ ላይ አንዱ ሌላው ጥገኛ መሆኑ መዘንጋት የለበትም፤ የወንዱ ዘር የሴቷን ማህፀን ካላገኘ ዋጋ የለውም። የብልቃጥም ፍጥረት ቢሆን ህልውና ለማግኘት የሴቷን ዕንቁላልና የወንዱ ዘር መውሰድ አለበት።

ይህ ሁሉ አያጣላም።

መልካም። በአፈጣጠር ደረጃ፤ ቅርጹን ትተን፤ የይዘት አንድነት መኖሩን ከተማመንን፤ ሴቶች የሚወነጅሉባቸው ልዩ ድክመቶች ከየት ተከሰቱ?!......

የኔም ጥያቄ ይሄው ነው። የሴቶች መሽቀርቀር ለጌጥ ሟች መሆን የወንዱ ጥገኛ መሆን ወንዱን መሣሪያ ማድረግ በውበታቸው መደለልን ምን አመጣው?

ጥሩ ጥያቄ ነው። እዚህም ላይ ጥያቄውን በጥያቄ መመለስ ይኖርብናል። ወንዱ ለምን የሴቷ መሣሪያ ይሆናል?....ስለምን በውበቷ ይደለላል?......ስለምን የእሱ ጥገኛ እንድትሆን ይፈቅድላታል?.....

ምናልባት ፍላጎቷን ለማርካት ይሆናል።......

እሺ ይሁን ይህ ፍላጎቷስ ከየት መነጨ? ምን መሠረቱ ይዞ ተነሳ?.....

ተፈጥሮዊ ነዋ!

አይደለም። በአፈጣጠር ደረጃ የአካል ወይም የቅርፅ ልዩነት የሚያስከትለው መጠነኛ የባህሪይ ልዩነት ይኖራል እንጂ፤ ሴቶች በድክመት የሚወነጅሉባቸው ነጥቦች ሁሉ ተፈጥሮአዊ አይደሉም።

ታዲያ ከየት መጡ?

ድክመቶቹ ከአካባቢ የመነጬ ናቸው። ምንጫቸው የወንድ ትምክህት፤ ማን አህሎኝነት አባወራነትና የበላይነት ስሜት ነው።......

እንዴት?.....እንዴት?.......

ወንዱ ለሴቷ መሣሪያ የሚሆናት ለጥገኝነት የሚጋብዛት በግልፅ ሆነ በተዘዋዋሪ የበላይነቱን ሊያሳያት ነው። ሴትና ወንድ በተፈጥሮ እኩል «ሰው» መሆናቸውን የውጭው አዕምሮው ያውቃል። ከመጽሐፍ ቅዱስና በአፈ ታሪክ የወረሰው የበላይነት ስሜት ደግሞ ከአዕምሮው ጀርባ ተደብቆ ሚናውን ይጫወታል። እናም ሴቷን እንደ ወሲብ ዕቃ መቁጠር ያሸሞነሙናታል፤ ያብለጨልጫታል፤ ለውበቷ ይደልላታል። በስተመጨረሻም፤ የድክምቷ ምንጭ እሱ መሆኑን ዘንግቶ፤ ሴቲቱን በድክመት ይወነጅላታል። አሁንስ ተግባባን አዳም?!........

ኤርሚያስ ብሩሹን እንደ ያዘ ከስዕል ሸራው አካባቢ ዘወር ብሎ በክፍሏ ውስጥ ይንጎራደድ ጀመር። የአዕምሮውን የውስጥ ፍልሚያ መሸሹ አልነበረም። ለብዙ ጊዜ ሲታገለው የኖረው የዕምነት ግጭት ነጥሮ መውጣቱ እንዲያውም ደስ

የሰኘቶታል። «ሔዋን 1999» ከአዕምሮው ውጭ ራሷን የምትከስበት ጊዜ መቃረቡንም ገምቷል። ያሁኑ ከስዕል ሽራው ርቆ መንጎራደድ በእርካታ የመዝናናት ምልክት ነው።

በክፍሏ ውስጥ ተጠናቀው የተንጠለጠሉትና የተለጠፉት የወንድ፤ የሴት፤ የአራዊትና የተፈጥሮ ስዕሎች በአንድነት አትኩረው እየተመለከቱት ጥያቄ የሚያቀቡለት መስለው። - ፍጡራን ፈጣሪያቸውን ሊጠይቁት -

የሆነስ ሆነና አንተ ለምን ሚስት አታገባም? እስከ መቼ በብቸኝነት ትዘልቀዋለህ?......

ራሴን ሳላውቅ ሌላ የማላውቃትን ፍጥረት አግብቼ መኖር አልፈልግም። ኋላ ራሳችውን የማያውቁ፤ እርስ በርስም የማይተዋወቁ ደባሎች ዓይነት ኑሮ ይሆንብኛል። እኔነቴን አውቄ ምርጫዬን አወቅኩ የምለው «ሔዋን 1999» ከአዕምሮዬ ውስጥ አንጥሬ ማውጣት ስችል ነው። ያኔ፤ ሚስቴ የኔ ምርጫ፤ እኔም የሚስቴ ምርጫ እንሆናለን። አንድ አካል አንድ አምሳል ማለትም ይሸው ነው።.......

ኤርሚያስ ይህ ጊዜ መቃረቡን ልቡ ገመተ። አንዳች ነገር እንደጠራው ሁሉ በፈጣን ርምጃ ወደ ስዕል ሽራው ተመልሶ እንደ ገና ከ «ሔዋን 1999» ጋር ተፋጠጠ።

እና?......

እና፤ ወንዱ ሴቷን እንደ ወሲብ ዕቃ መቁጠሩ ሲቀር ከአዕምሮው ጀርባ የተደበቀው የበላይነት ስሜት ሲጠራ፤ ከትምህክት ፍጹም ራሱን ሲያፀዳ.....ያኔ ሴቱማ የምትወነጀልባቸው ድክመቶች ይወገዳሉ። ሴቷ ቀሚስ ከመልበሷ በፊት ባህሪዋ እንዲገራ ከተፈለገ ወንዱም ሱሪና ኮት ከማጥለቁ በፊት ባህሪው መገራት አለበት። ልብስ ለኁልቱም ቢሆን የውጭውን አየር መቋቋሚያ እንጂ ውስጣዊ ማንነታቸውን መደበቂያ መሆን የለበትም.........

አሁን ተግባባን።

በዚህ ከተግባባን በመሐላችን እርቅ ወረደ ማለት ነው።

እንደገና በብሩሽ ነጩ ቀለም አጥቅሶ ከንፈሯ አካባቢ መነታተቡን ቀጠለ። «ሔዋን 1999» ቀስ በቀስ ፈገግ እያለች ጥርሷን ገለጠች።

የትውሲት ሁኔታ መለወጥ ደጀኔን ጋራ አጋብቶት ከረመ። ጋራ መጋባት ብቻ ሳይሆን፤ የፍቅሩንና የቅናቱን መጠንም እየቀነሰበት መጣ። ሶት ቀን በተከታታይ ሲመለከታት፤ አንገቷን አቀርቅራ፤ ሻሽ እያሰረች ግንባሯን አኮማትራ በቀጥታ ወደ ቢሮዋ ከመግባት በስተቀር ግራ ቀኝ እንኳ አታማትርም። «ደሞ ለሰው» የምትለው የአረማመድ ስልቷ «ከሁሉም በላይ ሰው!» በሚል የፍራቻና የአክብሮት ዓይነት የተተካ ይመስላል። በአለባበስ መሽቀርቀሯን በቅባትና በጌጥ መብለጭለጩንና ባየችው ወንድ ላይ ማክላላቷን ሁሉ ቸል ብላዋለች። ደጀኔ ደሞ የለመዳት፤ የወደዳት፤ ፍቅሯ ወጥመድ ውስጥ የገባላት በቀድሞ ሁኔታዋ ስለ ነበር ያሁኑ ለውጧ አልመጣውም። እሷም እየቀረቀረች፤ ወንዱም ፊቱን አዞረባት። በዚህ መሐል ደጀኔም ፍቅሩ ውስጥ ቅናት አጣበት።

«......ሰሞኑን ምን ሆነሻል ትውሲት?» ረቡዕ ቀን ለምሳዋ ስትወጣ ጠብቆ።

«ምን የሆንኩ እመስላለሁ?!........» አለችው እሷም፤ በተዘጋ ጉሮሮ።

«እንዲያው ብቻ.....የከፋሽ ትመስያለሽ።»

«መከፋትና መደስት በሰው እጅ ላይ ተፈራራቂ ነገሮች ናቸው።»

«ኧረ እንደመፈላሰፍ ጀምረሻል መሰለኝ.......»

«አይ ደጀኔ።.......»

«እስቲ ለማንኛውም ወደ ማታ ብቅ በይ። ቤቴ ሆኘ እጠብቅሻለሁ።.......» ብሏት ተለያዩ።

ማታ ወደ ደጀኔ ቤት ስትሄድም ያው ነበረች። በቀሚሷ ላይ ነጠላ ቢጤ ደርባ ቤተ ክርስቲያን ወይም ለቅሶ ቤት እንጂ ወደ ፍቅረኛዋ የምትሄድ አትመስልም ነበር። ከደጀኔ ጋር ስትጫወትም የፍርሃትና ወደ ኋላ የማለት ስሜት ገጿ ላይ ይነበባል። ፈገግ ማለት ስትሞክር በፍራቻ የተወጠረው ስሜቷ ከውስጥ አሸንፎ እየወጣ ፈገግታዋን ውበት ያሳጣዋል። ኤርሚያስ ቤት ደርሳ ከተመለሰች ዕለት ጀምሮ ዓለም በሙሉ ሚስጥሯን ያወቀባትና ጉድዋን ገልጦ ያየባት ስለመሰላት ሰው መፍራትና መሸሽ ጀምራለች። ደጀኔንም የፈራችው ወሬውን ሰምቶ እንደሆነ በሚል ግምት ነው።

ነገሩን የሚያውቅ ወይም ያውቁ ጥቂቶች ቢሆኑም፤ ለሷ ግን ሁሉም ሰው ግዷን የሰማና የሚያያት ሁሉ በርቀት በእሷ ላይ እየጠቋቆመ የሚያጥላላት መስሎ ይታያታል። አካላዊ እንቅስቃሴ የውስጥ ስሜት ነፀብራቅ በመሆኑ መላ ሁኔታዋ ላይ የሚነበበው ተስፋ መቁረጥ ሽንፈትና ጥርጣሬ ነበር።

«.......የደበቅሺኝ ነገር ያለ ይመስለኛል። ፊትሽ ሁሉ በጣም ተለዋውጡላ።» አላት ደጀኔ ለተወሰኑ ደቂቃዎች እንደተኮራረፈ ሰው በዝምታ ከቆዩ በኋላ።

«አዎ፤ ሐዘን ላይ ነኝ።........» አለችው እሷም በምፀት ድምፅ።

«ማን ሞተ?.......»

«እኔ ትውሲት»

«ትቀልጃለሽ እንዴ?»

«የምቀልድ እመስላለሁ እንዴ?........ይልቅ የሚጠጣ ነገር እንዳለ አምጣልኝ። ....ወይንስ ልትጋብዘኝም አልፈገግክም?»

የራሱ ሰውነት እየከበደው፤ ፊቱን አቅፍፎ ከተቀመጠበት ተነሳ። በመሐከላቸው መጥፎ አየር የገባ መስሎ ተሰማው። ‹መለያየት ፈልጋ ይሆናል። መብቷ ነው። እስካሁንም ያለ ምርጭዋ አስገድጄአት ነበር ማለት ነው። ያሳዝናል!› በማለት በሀሳብ እየዋተተ ወደ ኮመዲኖው ሄደ።

«መሎቲ ኮኛክ ብቻ ነው ያለኝ።.......ትጠጪያለሽ?» አላት፤ ኮመዲኖውን ከፍቶ ከርቀት እያሳየት።

«ይሁን፤ እጠጣለሁ።»

ጠርሙሱን ከሁለት ቀጫጭን ብርጭቆዎች ጋር አቅርቦ ለሁለቱም መጥኖ ከቀዳ በኋላ ተመልሶ አጠገቧ ተቀመጠ።

ትውሲት የተቀዳላትን መሎቲ ኮኛክ በአንድ ትንፋሽ ቋ! አድርጋ ጠጣችው።

ደጀኔ በልቡ፤ «ይቺ ሴት ጤናም አይደለች እንዴ?» እያለደግሞ ቀዳላት።

«ደጁ፤ የምትወደኝ ከሆነ፤ የመሥሪያ ቤት ሰው ሁሉ የከተማው ሰው ሁሉ ስለ እኔ የሚያወራውን ንገረኝ።» አለችው።

«የምን ወሬ ነው እሱ?......»

«በቃ.......ስለ እኔ የሚወራውን!»

«እኔ ምንም አልሰማሁም።»

«እስቲ ሙች በለኝ!» አለችና እጇን ዘረጋችለት።

«ሙች!» አለና እጅዋን መታት።

«ግን ደጀኔ......ትወደኛለህ?!»

«ሰክረሻል መሰለኝ ትውሲት?!»

«አዎ፤ ነገር አስክሮኛል።.......»

ግራ ተጋብቶ ትክ ብሎ ሲመለከታት ቆየ።

«የምትወደኝ ከሆነ እስቲ ሳመኝ......»

ጉንጯ ላይ ሳምት። ይሄው አመነችው። ስለ እሷ ከማንንም ምንም እንዳልሰማ ተረዳች። ቀድሞውንም ከንቱ ጥርጣሬ ነበር እንጂ ደጀኔ ከማንም ሊሰማ አይችልም። ምናልባት ሊነግረው የሚችለው ዘገየ ነበር። ከእሱም ጋር በእሷው ምክንያት ተኮራርፈዋል። አይነጋገሩም።

«የእኔ በግ!......ምን ላርግህ!.......ምን አልሁልህ?» አለችው ከሳማት በኋላ፤ ንግግሯ ወደ ለቅሶ እያደላ።

ሰው ሁሉ እንተን የነካው እንጨት ካደረጋት በኋላ፤ የአንድ ተስፋዋን የደጀኔን ማወቅ ፈልጋ ነበር። እሱ ያው እንደ ጥንቱ ነው! ትንሽም ቅር ያሰኘው ቀድሞ ያስለመደችውን የማቀናት ውዝዋዜ ስለነፈገችው ነው እንጂ፤ ስለ እሷ ክፉ የሚሰማበት ጆሮ የለውም። ትውሲት ይህን መረዳቷ የበለጠ የህሊና ፀፀት ውስጥ ጨምሯት ለብዙ ጊዜያት ስትቀልድበት መኖሯ ህሊናዋን ለበለባት። እሱ እንደቀድሞዋ እንድትጫወት በክፍሉ ውስጥ እየተውረገረገች እያከላላችና ቀሚሷን እየነሰነሰች የወንዳወንድ

ስሜቱን እንድትቀሰቅስበት ይፈልጋል። እሷ ደግሞ በዚህ የዋህ ፍጡር ፊት እንደቀድሞዋ መሆን አልቻለችም። የአክብሮት የፍቅና የፀፀት ስሜት ጨምድደው ስለያዟት ሐጢያቷን ለማጠብ እንባዋ ርግፍ - ርግፍ ማለቱን ጀመረ።

ለምን እንደምታለቅስ ቢጠይቃትም በቂ መስል ባለማግኘቱ ደጀኔም በበኩሉ አንዴም አብሯት ሲተክዝ አንዴም በብስጭት አኩርፎ ሲጠጣ ቆየ።

መጠጡን ደግጋግሞ፤ ትውሲት ሞቅ ሲላት፤ ድንገት የኮኛኩን ጠርሙስ ብድግ አደእገችና አፏ ላይ ለጎመች። ደጀኔ ደንግጦ ተነስቶ ጠርሙሱን ከአፏ ለመጣል ይታገል ጀመር።

«ተይ እንጂ ትውሲት!......ቀስ!......ኧረ......ኧረ ተይ ቀስ!......አብደሻል መሰል!.......» እያለ ትንሽ እንደተጎነጨ፤ ቀማት።

«እ....ፎ.......ይ!» አለች እሷም የተጎነጨችው ኮኛክ ደረቷን እየሰነጠቀ ሲወርድ እየተሰማት።

«ልክ አይደለሽም ትውሲት......ሁኔታሽ ሁሉ ተለዋውጧል። አንድ የሆንሽው ወይም ያደረግሽው ነገር አለ እንጂ በጤናሽ እንዲህ አትለዋወጭም!......

ደጀኔ ሐዘኔታና ንዴት በተቀላቀለበት ድምፅ ሲለፈልፍ፤ ትውሲት ፈፅሞ አልሰማችውም። አልኮሉ ስራውን እየሰራ፤ በተቀመጠችበት ቦታ፤ ሁሉም ነገር ብዥዥዥ እያለ ታያት፤ እና ደግሞ ጆሮዋ የሌለ ድምፅ ፈጥሮ ይሰማ ጀመር።

«ደጀኔ፤ ተነስ በሩን ክፈት.....በሩ ሲንኳኳ ይሰማኛል።» አለችው በተገማመደ ምላስ።

«ትቃዢያለሽ መሰለኝ። ምንም ድምፅ የለም።» አላት ጆሮውን አስልቶ ወደ ውጭ ሲያዳምጥ ከቆየ በኋላ።

«ለእኔ ይሰማኛል። አሁንም እየተንኳኳ ነው። የኋላውም የፊቱም በር ነው የተንኳኳው። የማውቀው ድምፅም ይሰማኛል። አዎ! የመጡት ሰዎች ባሌና ልጄ ናቸው። ባሌ በኋላ በር፤ ልጄ በፊት መጥተዋል። እያንኩዋኩ ነው። እባክህ ደጀኔ ክፈትላቸው።......»

«የምን ባል፤ የምን ልጅ ነው የምታወሪው?! ሰክረሻል ትውሲት - ሰክረሻል። በቃ፤ አልጋው ላይ ውጪና ተኚ።»

«አልተኛም ደጀኔ። እንቅልፍ አይመጣልኝም። ይልቅ አስገባቸው። ከባሌና ከልጄ ጋር ላስተዋውቅህ።»

«ዱላ አምሮሻል መሰለኝ።.........» አላት፤ ድምጹ የቅናት ቅላፄ እየያዘ። በቅናቱ ውስጥ አነጋገሯን የማመንም ያለማመንም ዓይነት ድብልቅልቅ ስሜት፤ ተሰማው። ካሁን በፊት ባልና ልጅ እንደነበራት ስላልነገረችው እንግዳ ወሬ ሆነባት። ወሬውን በቀልድ መልክ እንዳይወስደው ደግሞ ሁኔታዋ አጠራጠረው።

«ምን ዓይነት ዱላ?......» አለችው፤ ስካሩ ባጨማደደው ፊቷ ላይ ምጻት ጨምራትበት።

«ደሞ ስንት ዓይነት ዱላ አለ?.....ያው የለመድሽውን ነዋ!»

»ይሄ ባካልቾ በጡቻ የሰው ስጋ ማሰቃየት?!.....እሱ ዋጋ የለውም። አሁን እንደሱ ብትመታኝ የሚሰማኝ አይመስለኝም፤ የሚያመኝ አይመስለኝም። ጊዜ ያለፈበት የዱላ ስልት ነው።»

«ኧረ?.......ላሳይሽ እንግዳው!» አለና ደጀኔ፤ የብሽቀቱንም ጭምር ግራ እጇን አዙሮ ጠመዘዛት።»

ምንም ሳትነፍስ ጥርሶቿን ነክሳ ቻለችው። እንደወትሮዋ ቢሆን ኖሮ፤ ‹ውይ.....ውይ! በሞቴ......ነግሬሃለሁ ደጀኔ......ነግሬሀለሁ።......እንዳትነካኝ......ደጁ!......› እያለች የሚያንሰፈስፍ ወሲባዊ ድምፅ ታሰማ ነበር። ደጀኔ ይህንን ድምፅና መሽኮርመም ዛሬ ባለ ማየቱ በሽቆ እጇን ለቀቃት።

«ነገርኩህ እኮ!......ዋጋ የለውም። የሕሊና ዱላ ሞቶ ስጋን ማሰቃየት ምን ይሰራል?!.........ይልቅ አንድ ሚስጥር ላሳይህ.....ይሄውልህ፤ ተመልከተው ይሄንን ጠባሳ......» አለችና ግራ እጇን ዘርግታ አሳየችው።

«ሰካራም!.......ስንት ጊዜ ያየሁትን ነገር እንደ አዲስ ታሳይኛለሽ?!»

«እሺ.....ምን ሆኘ ነው?!»

«በልጅነቴ እሳት ጠብሶችኝ ነው። አላልሽኝም እንዴ?»

«ያቺ ውሸታም ትውሲት ትሆናለች እንዲህ ያለችህ። ይልቅ እኔ እውነቱን ልንገርህ። እጄን በቢላዋ ተርትሮ ጠበሳ ያተረፈልኝ ባሌ ነው።.......»

«እሱን ነገ ጠዋት በጤናማ ምላስ ተነግሪኛለሽ።......» አላት ጥርጣሬው እየጎላ ስሜቱ ከውስጥ እየተቆጣ።

«የኔ በግ!.....ዛሬም ትቀናለህ እንዴ?......የኔ አንበሳ!......እስቲ አሁን ምኔ ያስቀናል? ስማኝ እስቲ ደጄ ዛሬም ትቀናልህ?......እያለች እንደማቀፍ እጆቿን ዘርግታ ተጠጋችው።

«ልቀቂኝ እባክሽ!.......ይልቅ ትንሽ ብትተኚ ስካርሽም ይለቅሻል። ደሞ ይሄን ዛሬ ያመጣሽውን ‹የኔ በግ፤ ምናምን› የሚል ፈሊጥ ብታቆሚ ይሻልሻል።» አላትና በማኩረፍ አይነት መንጭቆአት ከአጠገቧ ርቆ ሄዶ ለብቻው ተቀመጠ።

«ጠላኸኝ እንዴ ደጄ?!......እኔ መውደድ ስጀምር አንተ ጠላኸኝ ማለት ነው?!......እኔ እኮ ዛሬ ነው አንተን መውደድ የጀመርኩት።......በቃ አታገባኝም?!.......ሚስትህ አታረገኝም?!.......አንተም ልትጥለኝ ነው?......ስማኝ ደጄ......» እያለች በርቀት ጮኸች።

ደጀኔ ሁኔታዋ ሁሉ ግራ አጋብቶት፤ አገጩን በመዳፉ ደግፎ ዝም ብሎ ይመለከታት ነበር። ፍጹም የማያውቃት አዲስ ሴት ሆና ታይችው። እንዲህ የረበሻትን ነገር ምንም እንደሆን ለማወቅ ጓጓ። ከእሷ መዘባረቅ ፍንጭ ቢያገኝም፤ በጥርጣሬ ብቻ ባገኘው ፍንጭ አልረካም። ዝርዝር ጉዳዩን የማወቅ ድንገተኛ ጥማት አደረበት። አኳኋኗ የወትሮው ቅናቱን አስውጦ ሐዘኔታ ለተሞላበት ፍቅር ይጋብዘው ጀመር። - አተኩሮ ሲያያት አዘነላት።

ትውሲት የጠጣችው ኮኛክ ልቧን እያቃጠላት ዓይኖቿን ስትከድንና ስትገልጥ ከቆየች በኋላ ህልም ዓለም ውስጥ እንደ ገባች ዓይነት በተቀመጠችበት ወንበር ላይ አንገቷን ወደ ኋላዋ ወጥራ ተጨፍና ቆየችና ድንገት ብድግ አለች። አንዳች ነገር ቆንጥጦ ወይም ገፍትሮ ያስነሳት እንጂ እሷ ራሷ ሰውነቷን ያዘዘችው አትመስልም ነበር።

በርግጥም ገፍትሮ ያስነሳት ዓይናን በጨፈነችበት ቅጽበት አዕምሮዋ ውስጥ ያየችው ስዕል ነበር። ሽሽታው የተነሳችውን ስዕል እንደገና ዓይኖቿን ገልጣ ለማየት እየተንገዳገደች ግድግዳው ላይ ወደተሰቀለው የፊት መስታወት ሄደች።

እና፤ አፍጥጣ ተመለከተች። ከመስታወቱም ውስጥ ግንባሩ ላይ ጠባሳ ያረፈበት ቀንዳም የሴት ምስል ዓይኑን አፈጠጠባት።

«ና ተመልከት ደጀኔ.......ቀንድ!......ቀንድ!........ቀንድ!....ቀንድ!» እያለች ጮኸች።

ድንጋጤዋ አደናግጦት ይሁን አጃጅሎት ለራሱም ሳይገባው፤ ደጀኔ ወደ መስታወቱ ሄደ።

«አታጠጋው ደጀኔ.......እንዳይወጋህ!.......ራቅ በል።.......ራቅ በል........እንዳይወጋህ!......»

«ምንድ'ነው የምታወሪው?!»

«አይታይህም እንዴ?.......ቀንድ!......ቀንድ!.......ጠባሳ!........አይታይህም?!.....»

«ያሁኑስ እብደት ነው እንጂ ስካር ብቻ አይመስለኝም።......»

«......ነገ ፅጌረዳና ባሏ ሊታረቁ ነው። አልሰማህም እንዴ ደጀኔ?!.......የኔ በግ! አልሰማሁም እንዳትለኝ ብቻ!.......ያ ቡዳ፤ ዘገየ፤ ወሬውን መስሪያ ቤት ውስጥ በትኖታል።......ባልና ሚስቱ ሊታረቁ ነው።» አለችው፤ ዓይናን ከመስታወቱ ነቅላ ደጀኔ ፊት ላይ ተከላ።

«የምን መቀባጠር ነው?!......እኔ ምንም አልሰማሁም።»

«እኔ ሰምቻለሁ። ነገ!......ነገ ሊታረቁ ነው። ፅጌረዳ ደግሞ ከሦስት ቀን በኋላ እረፍቷን ጨርሳ ሥራ ትገባለች።»

«የራሳቸው ጉዳይ!......አንቺ ምን አስጨነቀሽ?!.....»

«ጭንቅ ጥበብ ነው እንጂ!......ሽሽት ነው እንጂ!......ብርር ነው እንጂ!» እያለች ዘለባብዳ፤ እንደገና ዓይኖቿን ወደ መስታወቱ መልሳ፤ «....ንቀልልኝ ደጀኔ፤ ቀንዱን ንቀልልኝ!......የምትወደኝ ከሆነ ቀንዱን ንቀልልኝ።» አለችው።

በሐዘን ጭንቅላቱን እየነቀነቀ እጇን ጎትቶ ወስዶ አልጋው ላይ አጋደማት «በቃ አርፈሽ ተኚ፤ ትንሽ እንቅልፍ ያስፈልግሻል። በጣም ደክመሻል።» አላት።

እሷ ግን መጮኋን አላቋረጠችም።

«ውደደኝ ደጀኔ!......ውደደኝ!......ቀንዱን ነቅለህ ሰው አርገኝ!.....የምትወደኝ ከሆነ ቀንዱን ንቀልልኝ!.....

....ጥፍሮቼን ቁረጥልኝ!.....ጠባሳውን አጥፉልኝ!......ደጄ!......ቀንዱን ንቀልልኝ!......»

«ፅጌረዳ እንደ ጥንቱ «ፅግዬ» ለማለት አልደፈርኩም። ቀልድ ይመስልብኛል ብዬ ፈራሁ። አንቺም እንደ ጥንቱ «ወንዴ» ለማለት የሚያስቸግርሽ ይመስለኛል። በሞቀው ፍቅራችንና ትዳራችን ላይ ውሃ አፈሰስንበት፤ የቁልምጫ ስማችንን አሻከርነው፤ የአንድነት ምሰሶአችንን አላላነው። ነገር ግን ዛሬም ‹ወንዴና ፅግዬ› እያሉ የሚያቆላምጡን ልጆች አሉን። ዳኒና ሰብለ የኔና ያንቺን ፍቅር ወደ ነበረበት ለመመለስ የቆሙ ሽማግሌዎች ሆነዋል። ፍቅራችን ወደ ነበረበት ተመልሶ ቁልምጫችንን የምናድስበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን ተስፋ ኧልኝ።

«የደብዳቤዬን ዓላማ መንደርደሪያ ስታነቢ የምትረጂው ይመስለኛል። ......ታውሬ ነበር፤ ዛሬ ዓይኔን ገለጥኩ። በታወርኩበት ሰዓት ከቤት ወጥተሽ ስትሄጂ አልታየኝም ነበር። ዛሬ ዓይኔን ስገልጥ አጣሁሽ!......እና፤ እፈልግሽ ጀመር። ባለማወቅ በድዬሽ ይሆናል፤ ታውሬ ስደናእብር ረግጬሽ ይሆናል፤ ከንጹህ ልብሽ ቀልጄም ይሆናል። ዛሬ ግን በሩን ከፍቼ እየጠበቅኩሽ ነው። ፅጌረዳዊ ይቅርታሽን ለማግኘት ከፊትሽ እቆማለሁ። በንፅህናሽ ኮርተሽ፤ በደሌን ሁሉ ንቀት ይቅር በይኝ!......

«ከእንግዲህ ዝብዝብ ማብዛቱ ምን ፋይዳ አለው? ህይወትን ወደ ፊት ወደ ኋላ አይኖሯትም። ሁለታችንም ወጣቶች ነን። ፍቅራችንን ለማደስና የትዳርን ፍም ለመሞቅ ገና ብዙ ጊዜ ይኖረናል። ለትዝታም ቢሆን ጊዜ አናጣም። ጊዜያዊ

ሁለትነታችንን እርሺውና ለዘለቄታዊ አንድነታችን መንፈስሽን አነሳሺ። ጊዜያዊ ጎርፍ አራርቆ እንዳያስቀረን፤ ድልድይ ሆኖ በመሐከላችን በመቆም ያገናኘን፤ ጓደኛችን ኤርሚያስ የዘላለም ባለውለታችን ነው።

ያንቺው

ወንዳፍራሽ በቀለ።»

ማክሰኞ በምሳ ሰዓት፤ ሰብለ ከትምህርት ቤቷ ስትመለስ «ትዬ ይሔውልሽ ደብዳቤ። ወንዴ ትምህት ቤት ድለስ አምትቶ ሰተኝ። ላንቺ ነው የላከው።......» ብላ የሰጠቻት ደብዳቤ ነበር። ሁለት ቀንና ሌሊት ከእሷው ጋር ውሎ ቢያድርም፤ ከሦስት ጊዜ ያላነሰ ደጋግማ ብታነበውም በዚች የመጨረሻ ደቂቃ ደግሞ ለመጨረሻ ጊዜ የመኝታ ክፍሏን በር ዘግታ አነበበችው። ያው ነው! ምንም አዲስ ነገር አላገኘችበትም።

የልብን ሰርቶ ይቅር በሉኝ!......እያለች በዝግታ በማንጎራጎር ልብሷን መለባበሷን ቀጠለች። የእርቁን ስነ ሥርዓት ሐሙስ ማታ እንዲሆን ያቀናጀው ኤርሚያስ ነበር። የሮዛና ወንዳፍራሽ ግንኙነት መበጠሱን የትውሲትን ተንኮልና ሌሎችም ጉዳዮች ለፅጌረዳ ነግሯት ሊያስምናት ሞክሯል። አሁንም ልጆቹን ወደ ወንዳፍራሽ ቤት ወስዶ ካዘጋጃቸው በኋላ እሱ ፅጌረዳንና እናቷን ለማጓጓዝ ተመልሶ በር ላይ ይጠብቃቸዋል። አባትየው ከሁለት ሳምንታት በኋላም ቁጣቸው ስላልደረበ፤ ገላጋይ ጠፍቶ፤ እዚያው ልኳንዳቸው ውስጥ እንደአኮረፉ ተቀምጠዋል።

«ፅጌረዳ፤ ለብሰሽ አልጨረስሺም እንዴ?.....እየጠበቅን እኮ ነው።» አሏት እናትየዋ የመኝታ ክፍሏን በር አንኳኩተው።

«መጣሁ እማምዬ ጨርሼአለሁ።» አለች እሷም ከውስጥ ሆና ስትንጎዳጎድ ጫማዋ እየተሰማ።

በሙሽራነቷ ዘመን ትለብሳቸው የነበሩትን ልብሶቿን በደመ ነፍስ ከሻንጣዋ ውስጥ መርጣ ከለባበሰች በኋላ ወጣች። እናትየዋ አለባበሷን አላጤኑትም። ኤርሚያስ ግን መኪናው ውስጥ ስትገባ ሁሉ ዓይኖቹን ከልብሷ ላይ አልነቀለም። ከዘጠኝ ዓመት በፊት፤ ሠርጓ አንድ ቀን ሲቀረው፤ ወንዳፍራሽ ገዝቶ፤ ኤርሚያስ

በሚዜነቱ የወሰደላት ቀሚስና ሹራብ ነበር። የቀሚሱ ቀለም መደብዘዝ ቢጀምርም፤ በስፌቱና ጥራቱ አስታወሰው። በዚያን ጊዜ ፋሽን ነበር የተሰፋው።.......

«ብዙ አቆምንህ እንዴ?......ይቅርታ።» አለችው ፅጌረዳ ኤርሚያስን፤ መኪናው ውስጥ ገብተው እናቷ ከፊት እሷ ከኋላ ከተቀመጡ በኋላ።

«ምንም አይደል።» እያለ ኤርሚያስ የመኪናውን ቁልፍ ኮርኩሮ አስነሳ።

«የተባረከ ልጄ፤ ዕድሜህን ያርዝመው።......መቼም ይሄ ሁሉ የሆነው ባንተው ብርታት ነው።» አሉት እናትየዋ መንገድ ከጀመሩ በኋላ።

ኤርሚያስ ለምርቃታቸው እጅ እየነሳ ወደ ፊት ሾፈረ። በጉዞአቸው ላይ የፅጌረዳ እናት አሁንም አሁንም ይተነፍሱ ነበር። የደስታ ሲቃ የያዛቸው ይመስላሉ። ለኤርሚያስ ያላቸውን ፍቅርና አክብሮት መግለጫ ቃላት እንዳጡ ሁሉ፤ ፊታቸውን ወገግ ብሎ፤ አምጠው እየተነፈሱ ዓይን ዓይኑን በዝምታ ይመለከቱ ጀመር።

«ፅግሽ.....ተጫወቺ እንጂ።» አላት ኤርሚያስ፤ የፀጥታውን አየር ስለመስበር።

«እሺ......እየተጫወትኩ ነው።»

«የዓመት ፈቃድሽን አልጨረስሽም እንዴ?»

«ጨርሼአለሁ። ሰኞ ወደ ስራዬ እገባለሁ።»

ስለ ትውሲት ያላትን አመለካከት ሊጠይቃት ፈልጎ ከምላሱ ላይ መለሰው። ምን የሚያጣድፍ ነገር አለ?!.......አንዳንድ ለጊዜ የሚተውና በጊዜያቸው መስል የሚያገኙ ነገሮች አሉ። ከውስጥ ፈንቅሎ ሳይመጣ ኮርኩሮ ማሳቅ አይቻልም። ምናልባት ኮርኩሮ ማስገልፈጥ ይቻል ይሆናል፤ ግን ትርጉም የለውም።

ይልቁንም ሐሳቡ ዘሎ ዘገየ የነገረውን ነገር አስታወሰ። ትውሲት ቅስሟ መሰበሩን ከተመለከተ በኋላ እየሮጠ ቤቱ ድረስ መጥቶ «......ኤርሚያስ አንድ የነገርኩህ ውሸት ነበር። ሕሊናዬን ስለ ከበደኝ ላስተባብልህ ነው የመጣሁት። ፅጌረዳ ከአቶ ክብረት ጋር ስትወጣ በአይኔ አላየሁም። - ጥርጣሬ ነው።» ብሎት ነበር። ዘገየ ይህን የተናገረው የኤርሚያስን ትግልና ጥበብ ከተመለከተ በኋላ ባደረበት አክብሮታዊ ፍራቻ ነበር። ኤርሚያስ ግን የመቀየም ሆነ የፀፀት ምልክት አላሳየውም። መረጃው

ውሸትም ቢሆን ጠቅሞታል። ፅጌረዳን ከአቶ ክብረት እጅ ለማስጣል ጥረት እንዲያደርግ አስነሳስቶታል።

ውሸት ለግንባታ አስከዋል ድረስ፤ አስፈላጊና ጣፋጭ ነው። ውሸት የሚያስጠላው አፍራሽ ሲሆን ነው፤ አለ በልቡ፤ ሀሳቡን እያሰበ።

«.......ጉዞ፤ ወደፊት......ወደኋላ!» በማለት ድንገት ፅጌረዳ ተነፈሰች።

«ምን አልሽ?......» አላት ኤርሚያስ ከሀሳቡ ነቅቶ።

«የለ፤ ወዲህ ነው።.......» አለችው።

የሷም ሀሳብ ውስጥ ነበረች። በዚህ መንገድ ሻንጥዋንና ሰብለን ይዛ፤ ወደ ወላጆቿ ቤት የሸሸችበት ቀን ትዝ አላት። ባለ ታክሲውና ምክሩን አስታወሰች። - የሕይወት ጉዞ!.....ወደ ፊት.......ወደ ኋላ......። ጨረቃ ትወጣለች - ትገባለች። ፀሐይ ትወጣለች፤ - ትጠልቃለች። መሬት ትዞራለች - የሰው ልጅም አብሮአት ይዞራል፤ ይሽከረከራል። ጥላው አንድ ቦታ አይረጋም፤ ይዟዟራል።......የሰው ልጅ ጥላ.....

ፅጌረዳ፤ ከየዋህነት ውጭ፤ በህይወቷ ለመጀመሪያ ጊዜ፤ እንዲህ ዐይነት ረቂቅ ስሜት ተሰማት። በቀሪው የህይወት ዘመንዋ፤ ልበ - ደንዳና ወገብ - ብርቱ ሐሞተ - ኮስታራ መሆን ያስፈልጋት ይሆናል።.....ዓለም ለግለሰብ ደንታ የላትም። ለግለሰብ ብላ እንቅስቃሴዋን ለአፍታ እንኳን አትገታም። እና፤ የዓለምን በረከት ተቀብሎ ለዓለም እየሰጡ፤ የእንቅስቃሴው አካል መሆን የግድ ነው።.......

ከመኖሪያ ግቢዋ ሲደርሱ፤ መኪናዋ ወርደው፤ እናቷና ኤርሚያስ ግራና ቀኝ አጅበዋት፤ ወደ ቤት አመሩ ፡ ሦስቱ ሕጻናቶች እቅፍ አበባ ይዘው መምጫዋን ሰዓት እየተጠባበቁ ነበር። ከበረንዳው ላይ ተንደርድረው እየሮጡ ተጠመጠሙባት። ትንሿ ሰብለ በታዘዘችው መሠረት እቅፍ አበባውን አበረከተችላት። እልፍነሽ በጓሮ በኩል ብቅ ብላ እልልታዋን አቀለጠችው።

ፅጌረዳ አበባውን ተቀብላ የልጆቿን ግንባር ተራ - በተራ ስትስም፤ አንዳች ነገር ጉሮሮዋ ላይ ተናነቃት። ሆኖም የተናነቃትን ስሜት ታግላ ውጣ ወደ ቤት ውስጥ ገባች።

ወንዳፍራሽም ሳሎን ውስጥ ቆሞ እየጠበቃት ነበር። እንደሚፈራሩ አዲስ ፍቅረኞች በርቀት ተጨባብጠው ተቀመጡ።

ዳኒ የዝምታውን አየር የሚሰብር ቃል እስኪተነፍስ ድረስ፤ የፅጌረዳ እናትና ኤርሚያስም እንኳ ብዙ ዓመት በሚያውቁት ቤት ውስጥ እንግዳ ይመስሉ ነበር።

«ወንዴ.......ቤታችን እንደ ገና ገነት ሊሆን ነው።» አለው፤ ወደ አባቱ ተጠግቶ ዓይኖቹን በደስታ እያቁለጨለጨ።

«ወንዴ.....ቤታችን እንደገና ገነት ሊሆን ነው።» አለው፤ ወደ አባቱ ተጠግቶ ዓይኖቹን በደስታ እያቁለጨለጨ።

«ልክ ነህ ዳኒ.......» አለው አባትየውም፤ ስሜት በሌለው ድምፅ። ስሜቱ የፅጌረዳን የገፅታ ለውጥ ተመልክቶ ውስጥ ውስጡን እያለቀሰ ነበር። ለምን እንደሆን በውል ባይገባውም፤ ያቺ የዋህና ቅድስት ሴት ዛሬ ኮስታራና ቁጡ ሆና ታየችው። እና፤ ስሜቱ የፈጠረው እይታ ውስጣዊ ሐዘን ለቀቀበት።

«እኔም እኮ እናትና አባቴ ሲጣሉ ተወልጄ ቢሆን ኖሮ አስታርቃቸው ነበር።» በማለት ዘኒም በበኩሏ እዝን ብላ ወደ ኤርሚያስ ተነፈሰች። ኤርሚያስ ምን እንደሚላት ግራ ገብቶት ሲጨነቅ የሰብለ ጣልቃ መግባት ገላገለው።

«ኤልሚ.......እልፍነሽ እኮ ዶሎ ቤት ወት ሰልታለች።»

«ኧረ፤ አሁን እንበላዋለና።»

«እንግዲህ......ይቅር ለግዜር ተባባሉ እንጂ» አሉ፤ የፅጌረዳ እናት አንዴ ወደልጃቸው፤ አንዴ ወደ ወንዳፍራሽ እየተመለከቱ፤ ውስጥ......ውስጡን ሲያምጡ ቆይተው።

«.......ስለ ጥፋቴ ሁሉ ይቅር በይኝ።» አላት ወንዳፍራሽ፤ ከተቀመጠበት ተነስቶ፤ የፅጌረዳን ዓይኖች በልመና እየተመለከተ።

«የልብን ሰርቶ ‹ይቅር በሉኝ› ምን ዋጋ አለው?!.......ለማንኛውም እኔ ለልጆቼ ስል እኖራለሁ። - ለልጆቻችው ስንል አብረን እንኖራለን።» አለችው እሷም በከረረ ድምፅ አንገቷን አቀርቅራ፤ ጥፍሮቿን በአውራ ጥፍሯ እየከረከመች።

«እንደሱ አይደለም ፅጌረዳ.....ተሳስተሻል! ተሳስተሻል......» ወንዳፍራሽ ሳግ ተናነቀው፤ «ለልጆቻችን ብቻ ስንል አይደለም አብረን የምንኖረው። ለፍቅር ስለ ፍቅር አብረን እንኖራለን። ፍቅራፍን ተዳፍኖ ይሆናል እንጂ አልጠፋም። ከፊታችን በሚጠብቀን ጊዜ ላይ ተስፋ እንጣል።......»

የምትለውን ለመስማት ንግግሩን አቋርጦ በጥያቄ አስተያየት ተመለከታት። በቤቱ ውስጥ የተሰበሰበው ፍጥረት ሁሉ ወደ እሷ እየተመለከተ ነበር። ፅጌረዳ ግን ካቀረቀረችበት ቀና አላለችም። መልስም አልሰጠች። አዕምሮዋ መንገድ ላይ ወጥሮት የቆየውን ረቂቅ ሀሳብ እንደገና እያውጠነጠነ ነበር -

የሕይወት ጉዞ!.......ወደፊት ......ወደ ኋላ......ወደ ፊት!.......ፀሐይ ትወጣለች - ትጠልቃችለች።.......ጨረቃ ትወጣለች - ትጠፋለች።......መሬት ትዞራለች። የሰው ልጅ ጥላም ይዟዟራል።......

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ስለደራሲው በጥቂቱ



አዲስ አበባ በ፲፱፵፮ ዓ.ም. የተወለዱት ሲሳይ ንጉሡ አንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በባልቻ አባነፍሶ፣ የሁለተኛ ደረጃን ደግሞ በአዲስ ከተማ አጠቃላይ ተከታትለዋል፡፡ የከፍተኛ ትምህርታቸውን በአሥመራ ዩኒቨርሲቲ ከ፲፱፷፬-፲፱፷፯ ዓ.ም. ድረስ ተምረዋል።

በዩኒቨርሲቲ ሕይወት ዙሪያና በፍቅር ታሪክ ላይ በሚያተኩረው ሰመመን በሚባለው መጽፈሐፍቸው በብዙዎች ዘንድ የታወቁት ሲሳይ ንጉሡ፣ ጉዞው፣ ግርዶሽ፣ የቅናት ዛር የተባሉ ረጃጅም ልብወለዶች አሏቸው፡፡ ጉዞው የሚለውን ኖቬላ ጨምሮ ሌሎች አጫጭር ልብወለዶችን ጽፈዋል፡፡ ከኢትዮጵያ ሥነ ጥበባትና መገናኛ ብዙኃን ሽልማት በሥነ ጽሑፍ ዘርፍ ተሸላሚም ሆነዋል፡፡ ቀደም ባሉት ጊዜያት የደራሲያን ማኅበር ዋና ጸሐፊ በመሆን አገልግለዋል፡፡

ምንጭ: የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር ለሚሊኒየም ያሳተመው አጀንዳ።

## የደራሲው ሥራዎች

1. ሰመመን (**ልብወለድ**)
2. ግርዶሽ (**ልብወለድ**)
3. ጉዞው (**ልብወለድ**)
4. የቅናት ዛር (**ልብወለድ**)
5. ረቂቅ አሻራ
6. ትንሣኤ

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY